


የእስክንድር ነጋ ቃል 7



“አባይድክ ድክ እኛ ብርክርክ”

አቤ ቶኪቻው

13



አገዛዝና ዓለም-አቀፍ ፖለቲካ የሶርያ ምሳሌ

ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም

3



የተባበሩ ጨኸቶች- ቦአዚዝ፣ መጅሊስ፣ መምህራን... 5

ሰላማዊ ትግል አብቅቶለታል?



2

በእነ አንዷለም አራጌ የክስ መዝገብ የመከላከያ ምስክሮች ተደመጡ 15

የአርሶ አደሮቹ መፈናቀል ቀጥሏል

- ‹‹የዜጎች የመኖር መብት ይከበር ህልውናቸውም ይጠበቅ›› ሰመጉ
- መኢአድ በጽ/ቤቱ ጊቢ ውስጥ 114 ተፈናቃዮችን አስጠልሏል 14

የአይካ አዲስ ፋብሪካ ሠራተኞች ጉዳት ደረሰባቸው 15

ከአርበኞች ግንባር ጋር በተገናኘ በሽብርተኝነት ወንጀል የተከሰሱ በእስራት ተቀጡ 15



ደጅዓዝማች ለኢትዮጵያ ህዝብ

ናትናኤል መኮንን

(ከቃሊቲ ማረሚያ ቤት)

4

ለመብታችን፣ ለጥቅሞቻችን እና ለፍትሐዊነት እኛ መምህራን ባንድነት እንቁም!!

ከመምህር ተፈራ ታደሰ 10



መምህራኑን ሕጋዊ ትግላቸው እንደሚቀጥል አሳወቁ

- ‹‹በአሸባሪነት›› መፈረጃቸውን ተቃውመዋል
- *መምህራንን ለስራ ማሰናበት ተጀምሯል*

በቅርቡ መንግስት የመምህራንን የኑሮ ውድነት ለማሻሻል ያደረገው የእርከን ማስተካከያ ዝቅተኝነትን በመንተራስ የተጀመረው ተቃውሞ አይሎአሌ፤ በተለያዩ ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራኖች ‹‹ሕጋዊ ትግላችን ይቀጥላል›› ሲሉ ለፍትህ ገልፀዋል፡፡

በ14/07/2004 ዓ.ም. የቡልቡላ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት 79 መምህራን ለአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ በፃፉት መግለጫ አቋማቸውን አሳውቀዋል፡፡ በዚህም መሰረት የተደረገው ደመወዝ እርከን ህይወታቸውን ለማሻሻል ባለፈ ኑሯቸውን የማያቃውስ መሆኑን፣ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ለአባላቱ ጥቅም የቆመ ባለመሆኑ እንደማይወክላቸው፣ የእርከን ማስተካከያውን አስመልክቶ መንግስት በመገናኛ ብዙሃን የሰጠው መግለጫ ክብራቸውን የሚነካ አሉታዊ ነገር በመሆኑ ማስተባበያ እንዲሰጥበት በጥብቅ እንጠይቃለን ብለዋል፡፡

እንዲሁም በጉዳዩ ላይ ባደረጉት ውይይት አንዳንድ መምህራን ባነሱት ሃሳብ ብቻ ተመርጠው ወረዳ ድረስ ያለፈቃዳቸው እንዲሄዱ በማድረግ ውይይት እንዲያደርጉ መገደዳቸው የመምህራኑን ክብር እና መብት የሚነካ በመሆኑ የሚመለከታቸው አካላት መምህራኑን ይቅርታ እንዲጠይቁና መብታቸውን ለማስከበር ለሚከተሉት ማንኛውም የጋራ ህጋዊ መንገድ ለሚወሰደው ተናጥላዊ እርምጃ በጋራ በመሆን እስከመጨረሻው እንደሚታገሉ አስታውቀው ነበር፡፡

በመጨረሻም የክልሉ ት/ቢሮ የሚመለከተውን አካል ልኮ ግልፅ መረጃና ለጥያቄያቸው ምላሽ እንዲሰጣቸው እስከ ፊታችን ሰኞ ድረስ እንደሚጠብቁ፣ ይህ ካልሆነ ግን መብታቸውን ለማስከበር በጀመሩት ህጋዊ ትግል እንደሚቀጥሉ አሳወቀዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በ17/07/04 የደጃዝማች በላይ ዘለቀ ቁ.1 የመጀመሪያ 2ኛ ደረጃ የህዝብ ት/ቤት መምህራን የአቋም መግለጫና ዴሞክራሲያዊ የመብት ጥያቄዎችን አንስተዋል፡ ፡ የት/ቤቱ መምህራን ያነሷቸው ሦስት ነጥቦች ከላይ ከተገለፀው ት/ቤት ጋር ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ሆኖም በትምህርት ቤቱ አስተዳደር ሆን ተብሎ አስተዳደራዊ ጫና ተደርጐ በሞራላቸውና በህሊናቸው ተረጋግተው እንዳይሰሩ በተለያዩ ምክንያቶች እየደረሰባቸው ያለውን ኢ-ዴሞክራሲያዊ ድርጊቶችና ማስፈራሪያዎች እንዲስተካከሉ ጠይቀዋል፡፡ በተጨማሪም ለጠየቁት ዴሞክራሲያዊ መብት አግባብነት ያለው መልስ መሰጠት ሲገባው ጭራሽ ‹‹በአሸባሪነት›› መፈረጃቸው ከአላማቸው ውጪ በመሆኑ ጥያቄያቸው በትኩረት ካልታየ በስተቀር የስራ ማቆም አድማው እንደሚቀጥል

ወደ ገፅ 15 ዞሯል

ሰላማዊ ትግል አብቅቶለታል?



ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

በጉጉት ተጀምሮ የከሸፈው የ1997ቱ ሀገራዊ ምርጫ ከ1984 ዓ.ም. ወዲህ የተካሄደው የሰላማዊ ትግል እንቅስቃሴ መጦዣ ተደርጎ ይታሰባል። በደርግ ውድቀት ማግስት የተነቃቃው የሀገሪቱ የዴሞክራሲ ግንባታ ጅማሮ በዚህ ምርጫ ማግስት እንደተደመደመ የሚናገሩ ፀሐፊዎች ቁጥራቸው ይበዛል። በዚህ ምርጫ ማግስት በስፋት የተካሄደው የአፈና እርምጃ እና ተከትሎት የመጣው የፖለቲካ ምህዳር መጥበብ ብዙዎቹ የሀገሪቱን ፖለቲከኞች ወደሌላ የትግል ጫፍ ገፋቸው። በኢትዮጵያ የተቃውሞ ፖለቲካ አረዳድ የሰላማዊ ትግል ብቸኛ መገለጫ ተደርጎ የሚወሰደው የምርጫ ውጪ በሌሎች ህዝባዊ ዕምቢተኝነትን የሚያካትቱ የሰላማዊ ትግል መንገዶችን የተቃውሞ ልሂቃኑ በቂ ሊባል በሚችል መጠን አለመሞከራቸው ልሂቃኑን ሰላማዊ ትግልን ከምርጫ ፖለቲካ ስኬት እና ክስረት አያይዘው እንዲረዱት ዳርጓቸዋል። ከዚህ መንፈስ በመነሳት የምርጫ ፖለቲካ በታላቅ ክስረት ተደምድሞበታል የሚባልለትን የምርጫ 97 ፖለቲካዊ አውድ ከሰላማዊ እና ከአመፅ የትግል መስመሮች ጋር አዛምዶ ማየት ፖለቲካዊ ስርዓታችንን በተመለከተ የተሻለ ዕይታ የሚሰጥ ይመስላል።

የመታገያ ስልቶች መታያ....

ከባለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ የሰላማዊ ትግል አያዋጣም ብለው ያመኑ ፖለቲከኞች የአመፅ መንገድን ጠቀሜታ እና አስፈላጊነት ሲተነትኑ ቆይተዋል። የእኒህ ፖለቲከኞች መከራከሪያዎች ግልፅ ናቸው። አምባገነን ብለው የጠሩትን የኢህአዴግን ስርዓት ለመጣል ሰላማዊ ትግል ተሞክሮ ከሸፈል፣ የፖለቲካዊ ምህዳር ጠቧል፣ ስርዓቱም የሚገባው ጉልበት ነው የሚለው የመጀመሪያው ሲሆን አያይዘው የሚያነሷቸው ሁለት ነጥቦች አሉ። አመጽን የሚመርጡ ቡድኖች ለተነሱበት ፖለቲካዊ ግብ ህይወታቸውን እስከመስጠት መወሰናቸው ለተሳታፊዎቹ ከሚሰጠው ሰዋዊ የክብር ስሜት በተጨማሪ አምባገነኖች የዜጐችን መብቶች መጨፍለቅ ምን ያህል አደገኛ መዘዞች እንዳሉት ይረዳሉ የሚለው የመጀመሪያው ሙግት ነው። ከዚሁ በተቀዳሚ የተነሳውን ደም አፋሳሽ አመፅ ለመግታት መንግስታት በሚያደርጉት ሙከራ ስልጣናቸውን እና ከዚህ ስልጣን የሚነሱ ምቾቶቻቸውን ግድያን በሚያካትተው እንቅስቃሴ ሊያጡት እንደሚችሉ መረዳታቸው የአመፅን መንገድ የተሻለ ያደርገዋል ሲሉ የጉዳዩ አቀንቃኞች ይከራከራሉ።

አመፅን የተሻለ የፖለቲካ ትግል ስልት የማያደርጉት ሁኔታዎች መከሰት ከጀመሩ ከሶስት ዓስርታት በላይ ዘልቋል። የቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት አብዮትን መለያው የሚያደርገው የማርክሲስት ርዕዮተ-ዓለም በአለም የፖለቲካ ገበያ ላይ ገዢ ያጣ ሀሳብ መሆኑ ከአመፅ ይልቅ ለሰላማዊ ትግል አማራጭ የተሻሉ ሁኔታዎችን ፈጥሯል። የፖለቲካል ሊበራሊዝም ርዕዮት በበላይነት መውጣቱ የሰላማዊ ትግል እሴቶችን እና አማራጭ መንገዶችን በመጠቀም ቀዳሚ እንደሆኑ ለሚያምኑ ምዕራባውያን ይህ የትግል መንገድ አምባገነንነትን በሚታገሉ የሶስተኛው ዓለም ሀገራት እንቅስቃሴዎች ላይ ተፅዕኗቸውን እንዲያሳርፉ አስችሏቸዋል። ከዚህ ውጪ ያሉ ዓመፅ ተኮር እንቅስቃሴዎችን ‹‹ሽብርተኝነት›› ሲሉ በጥቅሉ ለመፈረጅ እየደፈሩ መምጣታቸው ዓመፅን ለሚመርጡ ሃይሎች የሚኖራቸውን ድጋፍ እያቀዛቀዙ፣ በግልባጩ ሰላማዊ ትግል እንዲጎለብት እንዲደግፉ አስችሏቸዋል። የሰላማዊ ትግል መንገድ በብቸኛ ጠቅላይ አስተሳሰብነት እንዲወጣ ያደረገው ሌላኛው ምክንያት የሀሳቡ አቀንቃኞች ለአቋማቸው ማጠናከሪያነት የሚጠቅሷቸው ማሳያዎች መሆናቸው ይጠቀሳል። የጋንዲ የህንድ የነፃነት መንገድ፣ የአፓርታይድ ውድቀት አልፎም የምስራቅ አውሮፓ ሶሻሊስት አምባገነን መንግስታት መፈራረስ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሱ መሞገቻዎች ናቸው።

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ክርክሮች መሀከል ሰላማዊ ትግልን በተመለከተ ሁለት የአተረጓጎም ስህተቶች እንዳሉ የሚናገሩት ፕ/ር መሳይ ከበደ እኒህ የአረዳድ አካሄዶች ፅንሰ ሀሳቡን በአግባቡ ካለመገንዘብ የመነጩ እንደሆኑ ይተነትናሉ። የመጀመሪያው የትግል አማራጩን ከድፍረት አልባነት ጋር የሚያስተሳስረው ትርጓሜ ነው። እንደ ፕ/ር ጀን ሻርፕ ባሉ የጉዳዩ ቀዳሚ ተንታኞች ትርክት ሲቪል አለመታዘዛችን፣ የስራ ማቆም አድማ፣ ሰላማዊ ሰልፍን እና ለመንግስት ተቋማት ትብብር መንፈግን የሚያካትተው ይህ የትግል መንገድ መጠኑ ከሌላው የትግል አማራጭ ይነስ እንጂ ሞት እና መሰል አደጋዎች እንዳሉት በመጥቀስ በጥብቅ የሞራል መትከላዊ መስጠት ላይ የሚቆም ከባድ መንገድ እንደሆነ ይናገራሉ። ፕ/ር መሳይ “Which way Ethiopia?” በሚለው ፅሁፋቸው የሚያነሱት ሁለተኛው የሀሳብ ጉድለት በሰላማዊ ትግሉ አራማጆች በኩል ያለው ህግን እና የትግሉን ቅርፅ የሚያስተሳስረው ትርጓሜ ነው።

ለፕ/ር መሳይም ሆነ ለጀን ሻርፕ ሰላማዊ ትግል መደረግ ያለበት የትኞቹንም የሀገሪቱን ህጎች በመጠበቅ ነው የሚለው ሀሳቡን በአግባቡ ያለመረዳት ነው። የትግሉ አቀንቃኞች ኢ-ፍትሃዊ ነው ብለው የሚያስቧቸውን የትኞቹንም የሀገሪቱ ህጎች የትግሉ መንገድ በሚፈቅዳቸው አማራጮች መጣስ አለባቸው ሲሉ ሮዛ ፓርክስን መሰል የትግሉ መለኮቶችን በመጥቀስ ይሟገታሉ። በዚህ ሙግት መሰረት የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ኢ-ፍትሃዊ ናቸው ብለው የሚናገሩባቸውን ህግጋት በአደባባይ ለመጣስ ቢሞክሩ የሰላማዊ ትግል የሀሳብ ድጋፍ እንዳላቸው የሚናገሩት ፕ/ር መሳይ የተቃውሞ ስብስቡ ይህን ማድረግ ባለመቻሉ አጥብቀው ይከሱታል።

የሀገሪቱ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች ከሚከሰሱባቸው ጭብጦች መሀከል ሌላኛው ጎልቶ የሚነሳው ነጥብ ሀሳቡ በዋነኛ አማራጭነት የሚያቀርበውን ህዝባዊ አለመታዘዞችን ለመሞከር አለመቻላቸው ነው። ህዝባዊ አለመታዘዞች ከሚባሉት ዋነኞቹ መንግስታዊ ተቋማትን በተመለከተ የማህበረሰቡ ትብብር መንፈግን ይመለከታል። በእነዚህ ተቋማት ውስጥ ያለው የቢሮክራሲ ስርዓት ህዝባዊ ትብብርን ከተነፈገ በቀላሉ ይፈራርሳል። ከኒህ ተቋማት በተጨማሪ የገነቢው ፓርቲ ጠቀሜታ ላይ አውሏቸዋል የሚባሉ ሌሎች የኢኮኖሚ ተቋማትን ከህዝባዊ ተሳታፊነት ውጪ ለማድረግ መሞከር የስርዓቱን መሰረቶች የማነቃነቅ ከፍተኛ ሃይል አለው። የትግል አማራጩ ወካይ ተደርገው የሚታሰቡት ማህተመ ጋንዲ የአንድን መንግስት ህልውና ከዚሁ የዜጎች ትብብር መኖር አለመኖር ጋር ያስተሳስሩታል። እንደርሳቸው ክርክር ማንኛውም መንግስት የመንግስት ሰራተኞችን፣ ወታደራዊ ክፍሉን እና ሌሎችን የሀገሪቱን ዜጐች ያቀፈ ነው። እነዚህ አካላት የራሳቸው ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፍላጐቶች አሏቸው። በተቃውሞ ልሂቃኑ የሚቀሰቀሰው የህዝባዊ ትብብር ንፍገት እንቅስቃሴ እኒህን አካላት በበቂ ቁጥር ሊያቅፍ ከቻለ የዚያ መንግስት ህልውና ያከትማል ሲሉ ሀሳቡን የሚያብራሩት ጋንዲ፣ መንግስት ምንም ያህል ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ አቅም ቢኖረው ሰፋ ያለ ቁጥር ከሚይዘው ወጥ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ጋር በአንድ ላይ መጋጨት ስለሚያስቸግረው መንግስታዊ ህልውናው ያከትማል ሲሉ ያወሳሉ።

ትርፍና ኪሳራው

የዓመፅ ትግል የሚያመጣቸውን ጉዳቶች በተመለከተ ኮሊየር እና ሆፍሌርት የማህበረ-ኢኮኖሚን እና ህግ ተኮር ጉዳቶችን አያይዘው ይተነትናሉ። ሁለቱ ፀሐፊዎች “On the incidence of civil war in Africa” በሚለው ጥብቁት ባለው ጥናታቸው ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ውድመቶችን በቀዳሚነት ያነሳሉ። አመፁ በሚቀሰቀስው የእርስ በርስ ጦርነት መሰረተ ልማቶች ይፈራርሳሉ። ከነዚህ መሰረተ ልማቶች ውስጥ የመንገዶች እና የተለያዩ አካባቢዎችን የሚያገናኙ ድልድዮች መፈራረስ በተለያዩ የኢኮኖሚ ክፍሎች መሀከል የሚኖሩትን ግንኙነቶች ያዛባል። ሁኔታው እንደኢትዮጵያ ባሉ የኢኮኖሚ መሰረታቸውን በእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ላይ በመሰረቱ ሀገራት ሲከሰት የምርቶችን ሰንሰለታዊ የገበያ ትስስርሽ ይበጥሳል። በዚህ የተነሳም ብዙዎቹ ቁሶች በተለይም ምግብ ነክ ምርቶች ወደ ተጠቃሚው በቀላሉ መድረስ ባለመቻላቸው ዋጋቸው እጅግ እየናረ ይሄዳል። በርስ በርስ ጦርነቱ ማህበራዊ ተቋማት አገልግሎት መስጠት እንዲያቆሙ መገደዳቸው ማህበራዊ ቀውሱን ያባብሳል። የትምህርት ተቋማት መዘጋት አልያም የትምህርት ሂደቱ መስተጓጎል ወጣቶችን ወደ የርስ በርስ ጦርነቱ ከዋኝ ቡድኖች እንዲሳቡ ያደርጋል። ‹‹እንዲህ ዓይነት የፖለቲካ ቀውሶች የወጣቶች ቁጥር በበዛበት ማህበረሰብ ውስጥ ከተካሄደ መዘዙ የከፋ ይሆናል›› ይላሉ የአክስፎርዱ ፕ/ር ኮሊየር “Wars, Guns and votes” በሚለው መጽሐፋቸው። የእርስ በእርስ ጦርነቱ ኢኮኖሚያዊ ዕዳን በተመለከተ የሀገራዊ የኢንቨስትመንት መቀዛቀዝ፣ የዜጐች የማጠራቀም ፍላጐትም ሆነ አቅም ማጣት እንዲሁም የዜጐች የጥሪት ፍልሰት በማሳያነት ይጠቀሳሉ። በእርስ በእርስ ጦርነቱ ወቅት ብዙዎቹ የንግድ ተቋማቶች መስራት አይቻላቸውም። መንግስታዊ ስርዓቱም ወታደራዊ አቅሙን ለማሳደግ የሚሊተሪ ባጀቱን ከፍ ለማድረግ ሲወስን የሌሎቹን የማህበረ-ኢኮኖሚያዊ መንግስታዊ ወጪጮች ይቀንሳል። ይህም የህዝባዊ ግልጋሎቶችን /Public goods/ የጥራትና የብዛት ማሽቆልቆሎችን ያመጣል። ከምርቶች እጥረት የተነሳ ዜጐች ለሚጠቀሙባቸው ግልጋሎቶችና ምርቶች ከፍተኛ ዋጋ ያወጣሉ። ከዚህ በተጨማሪ ባለው ፖለቲካዊ ያለመረጋጋት ፍርሃት ስለሚያድርባቸው ቁጠባቸውን ይቀንሳሉ። ይህ ሀገራዊ ያለመረጋጋት የሌሎች ሀገራት ኢንቨስተሮችን ስጋት ውስጥ ስለሚከታቸው የንግድ ተቋሞቻቸውን በመዘጋት ከሀገር ለመውጣት ይገደዳሉ። እነዚህ ተያያዥ ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶች ሀገራዊ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ምርት ላይ አሉታዊ አስተዋፅኦ ማድረጋቸው በሀገሪቱ ውስጥ የነበረውን የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ ያባብሰዋል፡ ፡ እነ ፕ/ር ኮሊየር እንደሚከራከሩት ከእርስ በርስ ጦርነቱ በኋላ የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ከነበረው ቢያንስ በ15% ወደኋላ ይንሸራተታል። በጦርነቱ የህዝባዊ የጤና ማዕከላት መጎዳታቸው ጦርነቱ ከሚያስከትላቸው የዜጐች ሞት በተጨማሪ ነዋሪዎች ከአንድ አካባቢ ወደ ሌለ አካባቢ በብዛት መንቀሳቀሳቸው ተላላፊ በሽታዎችን በከፍተኛ መጠን እንዲሰራጩ ያደርጋል። ጦርነቱ የሚያስከትላቸው አጠቃላይ የማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች በቀላሉ ወደ ጎረቤት ሀገራት ይዳረሳሉ። ‹‹ለዚህም ነው ከጎረቤት ሀገር መንግስት ጋር ስር የሰደደ ፖለቲካዊ ግጭቶች ከሌሉባቸው በስተቀር አሁን ባለው አለም አቀፍ የፖለቲካ ስርዓት ሀገራት ዓማሚ ሀይሎችን ለመደገፍ የሚያንገራግሩት›› ይላሉ እን ፖል ኮሊየር ከላይ በተጠቀሰው ፅሁፋቸው።

የብሔር ፖለቲካው ስጋቶች

የዓመፅን አማራጭ አደገኛ የሚያደርገው ቀዳሚው ኢትዮጵያዊ ሁነት አሁን በአደባባይ የነገሰው የብሔር ፖለቲካ መሆኑን የሚናገሩ ተንታኞችም አሉ። ህወሓት መሩ ኢህአዴግ በቀዳሚነት የብሔር ጥያቄ መፈታት አለበት ከሚል መነሻ የብሔር ፖለቲካ የሚስፋፋባቸውን ሁኔታዎች በበቂ አመቻችቷል። በሌላ ጠርዝ የስርዓቱ ተቺዎች የብሔር ፖለቲካው የደረሰበት የጡዘት ደረጃ በሀገሪቱ ዘውጎች መሀከል መቃቃሮችን እና ጥላቻዎችን እያሰረፀ እንደመጣ ይናገራሉ። ከዚህ መሰል የፖለቲካ ስርዓት ብሔርተኛ ልሂቃን እንወክለዋለን ብለው የሚያስቡትን ብሔር የፖለቲካ ጥያቄዎች ብቻ ይዞው ወደ አደባባይ ከመምጣታቸው ሁነት ጋር በተያያዘ የዓመፅ መንገድን መምረጥ የሀገሪቱን ህልውና አደጋ ላይ ሊጥል እንደሚችል ፕ/ር ቴሬንስ ሌዮንስ ‹‹Ethiopia; Domestic and regional challenges›› በሚለው ጥናታዊ ፅሁፋቸው ይተነትናሉ። ዓመፅ እየተስፋፋ ከሄደ እያንዳንዱ የብሄርተኛ ልሂቃን ስብስብ የእኔ የሚለውን ብሔር ‹‹ነፃ ለማውጣት›› ሲሞክር ከሌሎቹ አቻ የብሔር ፓርቲዎች ጋር ደም ወደሚያፋስስ ትግል ውስጥ ሊገባ ይችላል። ይህ ትንቅንቅ በውጤቱ ኢህአዴግ አንግሶታል ተብሎ የሚተችበትን በብሄሮች መካከል ያሉ መቃቃሮችን ወደ ጠርዝ ይወስዳቸዋል። ፓልከለየር እና አንኪ ሆፍለርት በበኩላቸው ዓመፅን የሚመርጡ ብሔር ተኮር ፓርቲዎች እንዴት የብሔር ጥላቻን ሊያባብሱ እንደሚችሉ ይተነትናሉ። ኢትዮጵያን በመሰሉ ህብረ-ብሔር ሀገራት የብሔር ፓርቲዎች ዓመፅን ሲመርጡ ለድጋፋቸው መጠናከር ያላቸው ብቸኛ ምርጫ የእንቅስቃሴያቸውን አባላት ከራሳቸው ብሔር አባላት ብቻ መሙላት ይሆናል። የብሔር አባላቱን በፓርቲያቸው ስር ለማሰባሰብ ዓይነተኛው ምርጫ ‹‹ነፃ ልናወጣው ነው›› የሚሉትን ብሔር ቅሬታዎች ጥብቅ ፖለቲካዊ ልባስ መስጠት ይሆናል፡ ፡ “On Economic causes of civil war” በሚለው ጥናታዊ ስራቸው ሁለቱ ኢኮኖሚስቶች እንደሚሉት ይህ ሌሎችን ብሔሮች ማፅዳል ያደረገ የመገፋት ትንታኔ በብሔሮች መሀከል ስር የሰደደ ጥላቻን ይፈጥራል። የእንቅስቃሴው ውጤትም ማህበረሰቡን በጠርዘኛ ፖለቲካዊ ዓመለካከቶች እንዲበከል ያደርገዋል። ጥልቅ የኢኮኖሚክስ ሞዴሎችን በመጠቀም ሁለቱ ፀሐፊዎች እንደሚሚገቱት ይህን መሰል ብሔር ተኮር የዓመፅ ንቅናቄዎች አንድ ቦታ ላይ ቢያቆሙም በፅንፍ ፖለቲካዊ አቋሞ የተወጠረ ማህበረሰብ የእርስ በርስ ጦርነትን ለማድርግ ከሌሎች ማህበረሰቦች የባሰ እድል ይኖረዋል። በዚህ ትንታኔ መሰረት የብዙ ብሔር ፍላጐቶች በአንድ ባልተማከሉበት የፖለቲካ ስርዓት የሚቀሰቀስ ዓመፅ ሀገሪቱን ወደ ሌሎች የዓመፅ አዙሪቶች ውስጥ ይከታታል። በኢትዮጵያ ሁኔታ ይህንን ሊያባብስ የሚችለው አንደኛው ተለዋጭ ገዢው ፓርቲ ከግራ-ዘመም አስተምህሮው አንፃር ማንኛውም የብሔር ቅራኔ በጉልበት መፈታት አለበት የሚለው እምነቱ እንደሆነ የጉዳዩ ተከታታዮች ይጠቅሳሉ።

የዲያስፖራው ሚና

የኢትዮጵያውያን ዲያስፖራን የሚያጠኑ ፀሐፊዎች በሀገሪቱ ፖለቲካ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እየፈጠረ ያለውን ስብስብ ‹‹አጅግ ፅንፈኛ›› ሲሉ ይጠሩታል። እንደ ፕ/ር ቴሬንሴ ሊዮንስ ያሉ ፀሐፊዎች ይህን የዲያስፖራ ክፍል ‹‹ግጭት የወለደው›› የሚል ስያሜ ሰጥተውታል። ይህ የፅንፈኝነት ባህሪ ስብስቡ ከሀገር ከወጣበት ባህሪይ ጋር እንደሚያያዝ የሚናገሩት እነ ቴሬንሴ ይህ የዲያስፖራ ክፍል ስለትውልድ ሀገሩ ያለው ምልከታ ጥለዋት የሄዷትን ሀገር ታሳቅነት በሚያቀነቅን፣ ቶሎ ወደ ሀገር ከመመለስ ናፍቆት እና ከመጡበት መንገድ ጋር ካለ ህመም /Trauma/ ጋር ይተሳሰራል፡ ፡ ስለሀገራቸው ሲያስቡ ሀገራችንን ይወክላል ብለው በሚያስቧቸው ትዕምርታዊ መለዮዎችን ከሀገራቸው ጋር ያላቸው ትስስር እጅግ ስሜታዊ እንዲሆን እንዳደረገው ፕ/ር ቴሬንሴ “Engaging diasporas to promote conflict resolution” በሚለው ፅሁፋቸው ይጠቅሳሉ። ይህ ሁኔታም ራሳቸውን ለማያመቻመች ፖለቲካ እንዳጋለጣቸው ይከራከራሉ። ከዚህ በተጨማሪ ብዙዎቹ ንቁ የዲያስፖራ የፖለቲካ ተሳታፊዎች ከገዢው ፓርቲ ጋር ተፃራሪ የሆነ የታሪክ ትንታኔ አልፎም ኢትዮጵያ እንዴት መዋቀር አለባት በሚለው ጭብጥ ላይ ጠርዘኛ አቋም ያላቸው መሆኑ በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን የተቃውሞ ፖለቲካ ከሰላማዊ ትግል በማንሸራተት ዓመፅን ለመረጡት የፖለቲካ ስብሰቦች በአንፃራዊነት የተሻለ ድጋፍ እንዲያደርጉ ገፍቷቸዋል ይላሉ በጉዳዩ ላይ የሚፅፉ ተንታኞች። በዚሁ ላይ የፃፉት ፕ/ር ኮሊየር ልክበ1983 በኢትዮጵያ እንዳበቃው በአንድ የርስ በርስ ጦርነት ሀገራቸውን የለቀቁ ዜጎች ጦርነቱ ሲያበቃ ሌላ ጦርነት ሊቀሰቀስበት የሚችልበትን እድል ይፈጥራሉ ሲሉ ይከሳሉ። በሀገሪቱ ውስጥ ካሉት ዜጐች የተሻለ የኢኮኖሚ ገቢ የሚኖራቸው እኒህ ስደተኞች፤ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት በኋላ ለተፈጠረው የዐመፅ እንቅስቃሴ መቀዝቀዝ ዐማሚ ሃይሉን በገንዘብ የሚደግፉ መንግስታት ቁጥር መቀነስ ከመሆኑ እውነት በመነሳት እነዚህ ‹‹ፅንፈኞ›› የዲያስፖራው ክፍሎች አመፅን ለመረጡ ሀይሎች የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ መቻላቸው አንዱ ወሳኝ የእርስ በእርስ ጦርነት አባባሽ ምክንያት እንደሆነ ፕ/ር ኮሎየር “The Bottom Billion” በሚለው የመጀመሪያ መጽሐፋቸው ይሞግታሉ። በአፍሪካ ቀንድ ከተካሄዱት ስኬታማ የጉሬላ ጦርነቶች መሀከል የሚጠቀሱት የህወሓት እና የሻዕቢያ ‹‹የነፃነት›› ትግሎች በሰሜን አሜሪካ ያሉ ደጋፊዎቻቸው ወሳኝ እንደነበሩ ይጠቀሳል። ኮሊየር የስሎቮኪያ ክቼኮዝላቪኪያ የመገንጠልን እንቅስቃሴ የጠነሰሱት በሰሜን አሜሪካ ነዋሪ የሆኑ የስሎቫኪያ ስደተኞች መሆናቸውን በመጥቀስ የመገንጠልን ጥያቄ የሚያነሱ የትጥቅ ትግል አራማጆ ከሌሎቹ በላቀ በዲያስፖራ ተፅዕኖ ስር እንደሚያርፉ ይከራከራሉ።

የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ድምዳሜዎች

የሰላማዊ ትግል ሙከራዎችንም ሆነ የምርጫ ፖለቲካ ማብቃትን በተመለከተ በተቃውሞ ልሂቃኑም ሆነ በለዘብተኛ ምሁራን ዘንድ በምክንያትነት የሚቀርበው የገዢው ፓርቲ የርዕዮተ-ዓለም ትንታኔ ነው። የምርጫ ፖለቲካን ተግባራዊነትን እና የፓርቲውን ርዕዮተ-ዓለም አያይዘው የፃፉ መምህራን ጥቂት ቢሆኑም የእነርሱ መላምቶች እና ፓርቲው ርዕዮተ-ዓለሙን በተመለከተ ያሳተማቸው ድርሳናት ተደጋጋፊ ድምዳሜ ላይ ያርፋሉ። የነገረ-ሀብት ባለሙያው ፕ/ር ብርሃኑ አበጋዝ አብዮታዊ ዴሞክራሲ እንደ ፖለቲካዊ ማህበረሰብ የሚመለከታቸውን የማህበረሰብ ክፍሎችን በተመለከተ ሲፅፉ ፓርቲው ማህበረሰቡን በሁለት ከፍሎ እንደሚመለከተው ይናገራሉ። በዘመናዊት ኢትዮጵያ ምስረታ ወቅት በገዢ መደቦች እንደተጨቆኑ የሚታመኑትን ‹‹ተጨቋኝ ብሔሮች›› ዋነኛው የድጋፍ ምንጩ አድርጎ ይቀጥራቸዋል። ፕ/ር ብርሃኑ “The 2005 Ethiopian election: Millstone or mile stone?” በሚለው ጥናታዊ ፅሁፋቸው እንደሚሉት ፓርቲው እነዚህን ዘውጎች ከምንም በላይ እና በፊት ባህላዊ ማንነታቸውን ለማስጠበቅ እንደሚፈልጉ ስብስቦች አድርጎ መመልከቱ መራጮችን የስልጣን ማደላደያው መሳሪያ /Means/ አድርጎ ይፈርጃቸዋል። አነስተኛ ቁጥር ያለውን መካከለኛ መደብ ከግራ-ዘመም ዕይታው አንፃር ሊመታ እንደሚገባው ‹‹የንዑስ ክበርቴ›› ስብስብ ሲቆጥረው፤ በዘመናዊ ትምህርት የገፉ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችን አሸንፈዋለሁ ብሎ የሚያስበውን ‹‹የአማራ የበላይነት›› ወካዮች እንደሆኑ ያምናሉ። እንደ ፕ/ር ብርሃኑ ይህ የፓርቲው ርዕዮተ-ዓለማዊ አተናተን አይደግፉኝም ብሎ የሚያምናቸውን እኒህን ሁለት የማህበረሰብ ክፍሎች በተለያየ መንገድ በምርጫ ፖለቲካ ላይ የሚኖራቸውን ተፅዕኖ ለመቀነስ ይጥራል። ሌላኛው የጉዳዩ ተንታኝ ፕ/ር ኪጅቱል ቶርኖቬል የምርጫ ፖለቲካውን መክሸፍ አብዮታዊ ዴሞክራሲ መታገስ ከማይችለው የሀሳብ ብዙህነት ጋር ያስተሳስሩታል። እንደእርሳቸው ሙግት ፓርቲው በአባላቱ መሀከል ክርክሮች እንዲደረጉ መለስተኛ ፍቃድ ቢኖረውም ፓርቲው ወደ ውሳኔ ከደረሰ በኋላ ማንኛውም አባል ለማይስማማበት ውሳኔ መገዛት እንዳለበት ያምናል፡ ፕ/ር ቶርኖቬል “Non-electoral politics in Ethiopian democratization” በሚለው ፅሁፋቸው የርዕተ-ዓለሙ ዋነኛ አርቃቂ ህወሓት በትጥቅ ትግሉ ወቅት ያደረጋቸውን የመሬት ማሻሻያዎች በመጥቀስ ከላይ ካነሱት ነጥብ ጋር አያይዘው ፖለቲካዊ አንድምታ ሊሰጡት ይሞክራሉ። ህወሓት በትግሉ ዘመን ነፃ ባወጣቸው የትግራይ አካባቢዎች ያደረጋቸው የመሬት ማሻሻያዎች በክልሉ ያሉ ነዋሪዎችን ወደ አንድ ወጥ ስብስብነት ለመቀየር ሞክሯል። እኒህ ሁለት ሁነቶችን በማያያዝ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ተዋስኦ ሌሎች ሀሳቦችንም ሆነ የፖለቲካ ፍላጎቶችን መቀበል እንደሚችገር የሚናገሩት ኖርዊጂያዊው ፀሐፊ ፓርቲው በምርጫ ፖለቲካ ወደ አደባባይ የሚመጡትን አማራጭ ሀሳቦች ለመጨፍለቅ መታተሩ አስገራሚ እንዳልሆነ ይከራከራሉ። ሌሎች የፖለቲካው ታዛቢዎች ይህ የፕ/ሩ ቶርኖቬል ክርክር በአቶ መለስ በራሳቸው እንደሚቀነቀን ይናገራሉ፡ ፡ እኒዚህ አስተያየት ሰጪዎች ለዚህ ሀሳባቸው

ወደ ገፅ 6 ዞሯል

አገዛዝና ዓለም-አቀፍ ፖለቲካ የሶርያ ምሳሌ



ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም

በአረብ አገሮች የተካሄደውና በመካሄድ ላይ ያለው ሕዝባዊ አብዮት ማስተዋልና መማር ለሚችሉ ሁሉ ጠቃሚ ትምህርት እያሳየ ነው። መጀመሪያ በአገዛዝና በሕዝብ መሀከል ያለውን ገደል ገልጦ ያሳያል። ከሕዝብ ቁጥር ጋር ሲነጻጸር በጣም ጥቂት በሆኑ የተቀለቡ የሰላማዊና መለዮ-ለባሽ ሎሌዎች በቃሬዛ ታዝሎ ልዩ ዓለም ውስጥ የሚኖር መሆኑ በቱኒዚያም፣ በሊብያም፣ በግብጽም፣ በየመንም ታየ። ገና አልለየም እንጂ በሶርያም እየታየ ነው። በተጠቀሱት የአረብ አገሮች ሁሉ የይስሙላ ምርጫ ሲደረግ ኖሮአል። ሕዝቦቹም የዓርባ ቀን ዕድላችን ብለው ወደእግዚአብሔር ሲያመለክቱ ቆይተዋል። እግዚአብሔር ልቦናቸውን አሳያቸውና የጋረዳቸውን ጥቁር መጋረጃ ቀድደው ጸሐይ ሲወጣ አዩ። የአእምሮአቸው ዓይን ተከፈተ። ብርሃንን ያየ ወደጨለማ መመለስ አይችልም።

በሕዝቦቹ በኩል አስደናቂው ነገር በመሸጦነት ከተያዙት በቀር ወንድ፣ ሴት፣ አሮጊት፣ ሽማግሌ ሕፃናት ሳይቀሩ አገዛዙን ለመጣል በቆራጥነትና በአንድነት ተነስተው ለብዙ ወራት ለአገዛዙና ለሎሌዎቹ ፋታ ሳይሰጡ ትግላቸውን ለድል ማብቃታቸው ነው። የሴቶቹ ተሳትፎ የሚያስደንቅ ነበር። ከአገዛዙ ሎሌዎችም ቢሆን ከህዝብ ጋር ቅራኔ ውስጥ ላለመግባት የፈለጉ ብዙዎች ሎሌነት በቃን እያሉ ከህዝባዊው ትግል ጋር ተቀላቅለዋል።

የአምባ-ገነኖቹ መልስም በጣም የተለያየ ነበረ። የቱኒዚያው አምባ-ገነን ገና በመጀመሪያው ላይ ሳይባባስ ሚስቱን ይዞ ሹልክ አለና ሳኡዲ ገብቶ የሙጢኝ አለ። የግብፁ ደግሞ ትንሽ ከተግደረደረ በኋላ ሥልጣኑን ለምክትሉ አስረክቦ ወጣና በሕዝባዊው ኃይል ቁጥጥር ስር ገባ። ታምሜአለሁ ቢልም በቃሬዛ እየተያዘ ፍርድ ቤት እየቀረበ ነው። የሊቢያው ጋዳፊ ከነልጆቹ ፎከረ፣ ሸለለና በመጨረሻ ስንት ሺህ ሰዎች አጫርሶ የጎርፍ መውረጃ ቦይ ውስጥ ተወሽቆ ተያዘና ጭካኔ ባስተማራቸው ሰዎች አጉል አሟሟት ሞተ። የሱ ቢጤው የየመኑ አምባ-ገነን ከወንበሩ ጋር ተጣብቆ እምቢኝ ብሎ በተጣለበት ቦምብ ቆስሎ ለህክምና ሳኡዲ ሄዶ ቆየ። ተሽሎት ከተመለሰም በኋላ ሥልጣን አልለቅም በማለት ቀጥሎ ብዙ ሰዎችን ከአስጨረሰ በኋላ በድርድር ለቀቀ። ለህክምና ብሎ ወደአሜሪካ ሄደ። ምናልባት እዚያ ለመኖር የማይፈቀድለት በመሆኑ በኢትዮጵያ በኩል ወደአገሩ ገባ። በኢትዮጵያ በጥገኝነት ለመኖር እየተዘጋጀ ነው ይባላል። እጅ እየነሡ ቹክ ሲቀበሉ የነበሩት ሁሉ ለጋዳፊ ለቅሶ አልተቀመጡም። ፈረንሳይ ለቱኒዚያኑ ቤን አሊ ለቅሶ አልተቀመጠም። አሜሪካ መባረክን በርታ አላለም።

እነዚህ አምባ-ገነኖች በሥልጣን ላይ የቆዩባቸው ዓመታት ብዙ ናቸው። ጋዳፊ ዓርባ ሦስት ዓመት፣ መባረክ ሠላሳ፣ ቤን አሊ ሃያ ሦስት፣ ሳላህ ሃያ ሁለት፣ ገና በትግል ላይ ያለው ሀኪሙ አምባ-ገነን ዶር. አሳድ አሥራ ሁለት ዓመታት ገዝተዋል። አእምሮአቸው በትዕቢት ባይደፈን ለትምህርትና ለንስሐ በቂ ጊዜ ነበራቸው። መማርና ንስሐ መግባት ተስኖአቸው ራሳቸውንም አገሮቻቸውንም አጠፉ። በአንጻሩ ሥልጣን አልጠግብ ብሎ ሕገ መንግሥቱን በመጣስ ለሦስተኛ ጊዜ ለምርጫ የገባው የሴኔጋሉ የሰማንያ አምስት ዓመት ሽማግሌ መሸነፉን ሲረዳ ለአሸናፊው ስልክ ደውሎ ‹‹እንኳን ቀናህ!›› ብሎ ሥልጣኑን ለማስረከብ ቆርጦአል። የአፍሪካ መሪዎች ሰማንያ እስኪሞላቸው አይበስሉም እንዳይባል የዚንባብዌው ሙጋቤ አሉ።

ዛሬ የዓለምን ሁሉ ትኩረት የሳበው የአረብ አምባ-ገነን የሶርያው አሳድ ነው። የግብጹና የየመኑ አምባ-ገነኖች በአሜሪካ ስር የነበሩትን ያህል የሶርያው በሩስያ ስር ነው። ከዚያም በላይ ለእስራኤል፣ ለቱርክና ለኢራቅ ጎረቤት ነው። የሶርያ ደቡባዊ ጎረቤት ዮርዳኖስ ነው። ዮርዳኖስ የዙፋን አገዛዝ ሆኖ የምዕራባውያን ምሽግ ነው። ለሶርያ ፋርስም ሩቅ አይደለም። የሶሪያ ጦስ ጦሰኛውን አካባቢ ይበልጥ እንዳይመርዘው ሁሉም ይፈራል። የሶርያው አምባ-ገነን ይህንን እንደጥንካሬ ቆጥሮታል። ስለዚህም የሚቀጣጠለውን እሳት ፈርተው አይነኩኝም በማለት ከሕዝቡ ጋር ሙሉ ጦርነት እያካሄደ ነው። በመድፍና በታንክ ሳይቀር ሕዝቡን እየደበደበ ነው። እስካሁን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ አሥራ ሁለት ሺህ የሚጠጉ ሰዎች ሞተዋል። ቆም ብለን ራሳችንን አንድ ጥያቄ ጠይቀን ከየራሳችን ጋር እንነጋገር። የሶርያው አምባ-ገነን ከሕዝቡ ሲገነጠልና በሕዝቡ ላይ ሲነሣ በርከት ያሉ የጦር ኃይሉ አባላት ከሕዝቡ ጋር ተሰለፉ። ብዙዎች ግን ሎሌነት በልጦባቸው ሕዝቡን እየጨፈጨፉት ነው። አገርንና ሕዝብን አጥፍቶ የሚገኘው ጥቅም ምንድን ነው?

በሶርያ ጉዳይ ለተባበሩት መንግሥታት በምዕራባውያን ኃይሎችም በአረቦች ማኅበርም የቀረቡትን የውሳኔ ረቂቆች ሩስያና ቻይና እየተቃወሙ ለሶርያ ህዝብ ማንም ሳይደርስለት አሳድ በሩን ጥርቅም አድርጎ ዘግቶ ሕዝቡን በጭካኔ እየደበደበ ነው። ሩስያና ቻይና ከዓለም መንግሥታት ተገንጥለው አሳድን የሚደግፉበት ምክንያት ምንድን ነው? ጥቅም ነው። አሳድ የጦር መሣሪያውን የሚገዛው ከነዚህ አገሮች ነው። ከገንዘብ ጥቅምም ሌላ የሶሪያ አቀማመጥ ለሩስያ ወታደራዊ ፋይዳ አለው። ለዚህ ነው አሜሪካ የሶርያን መዳከም የሚፈልገውን ያህል ሩስያ የሶርያን ጥንካሬ የሚሻው። የምዕራባውያንን በጥቅም ላይ የተመሠረተ አመራር አሜሪካ አሁን ለማለ ወታደሮች በሰጠው የእርዳታ መንፈግ ማስጠንቀቂያም ይረጋገጣል።

በሦስተኛው ዓለም የሚገኙ ደሀ ሕዝቦች ቢጨራረሱ ምዕራባውያንም ሆኑ ሩስያና ቻይና ከይስሙላ በላይ ግድ የላቸውም። ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ ባለዕዳ አይቀበለውም እንደሚባለው ነው። የሦስተኛው ዓለም አገዛዞች የሕዝቦቻቸውን ሕይወት እንዲጨነቁላቸው መመኘት ከንቱ ነው። አንድ ጊዜ ተማሪዎች ለሰላማዊ ሰልፍ ሲወጡ ተገድለው ስለሞቱት ሳዝን አንድ ጎረምሳ ዲፕሎማት (አገሩን መጥቀሱ አስፈላጊ አይመስለኝም) ‹‹እዚህ አገር ሰዎች በችጋር ያልቁ የለም እንዴ እነዚህ ተማሪዎች በጥይት መሞታቸው ምን ያስደንቃል!›› አለኝ። ሁኔታን መካድ አልቻልኩም። በወገን ጥይት መሞትና በችጋር መሞት ውጤቱ አንድ ነው። ግን ሁለቱንም አሚሚቶች ማኅበረሰባዊ ኃላፊነት የሚመለከታቸው ቢሆንም መንፈሳዊ ቁም-ነገር የጨበጠ ሰው በችጋር የሚሞተውን በጥይት ከሚገደለው ጋር አያመሳስለውም። ለጎረምሳው ዲፕሎማት የሰጠሁትም መልስ ይኸው ነበር።

የሦስተኛው ዓለም አገዛዝና የምዕራባውያን ዓለም-አቀፋዊ ፖለቲካ በጥብቅ የተቆራኘ ነው። አሁን ግን ለምዕራባውያን ኃይሎች የአምባ-ገነኖች ጠቀሜታና አገልግሎት በጥያቄ ውስጥ ገብቶአል። ከአሁን በኋላ ሕዝብን ችላ ብለው በአምባ-ገነኖች ላይ መተማመኑ የማያዋልቅ ለመሆኑ የአረብ አገሮች አብዮት ትምህርት እየሰጣቸው ነው። አምባ-ገነኖች ግን በዚያው ልክ ለመማር ይችላሉ ለማለት የሚቻል አይመስለኝም።

የሁለት ሥልጡን-ህዝቦች ወግ

ዓለማየሁ ገላጋይ

ኢትዮጵያና ጃፓን ከአንድ የጊዜ ማህፀን የተወለደ መንትያ ታሪክ አላቸው። ያቺ የመንታ ታሪኮች እናት የሆነችው ዘመን 1860 ዓ.ም ናት። ኢትዮጵያ በአፄ ቴዎድሮስ፣ ጃፓን በአፄ ሙትሱሒቶ (Mutsuhito) ከመሣፍንት አገዛዝ ነፃ ወጡ። ሁለቱም ወጣት ንጉሠ-ነገሥቶች ‹‹ሥልጣኔን›› በተመሳሳይ ሥሜት የሚመኙ ሆኑ። አፄ ቴዎድሮስ እና አፄ ሙትሱሒቶ የአውሮፓውያን ስልጣኔ ወደ አገራቸው የሚገባበትን መንገድ እኩል አዉጠነጠኑ። ሁለቱም አፄዎች ስለስልጣኔ ህልማቸው የአገር ውስጥ ተቃውሞ ገጠማቸው። አፄ ቴዎድሮስ ከቤተክህነት ነባር ስርዓትና ወግ ጋር ፊት-ለፊት ተላተሙ። አፄ ሙትሱሒቶም ‹‹ቡሺዶ›› (Bushido) እየተባለ ከሚጠራው ከኮንፊሺየስ መንፈሳዊ ነባር ሥርዓትና ወግ ጋር ግጭት ውስጥ ገቡ። አፄ ቴዎድሮስ ተጠለፉ፣ አፄ ሙትሱሒቶ አለፉ...

...ኢትዮጵያና ጃፓን ከአንድ የጊዜ ማህፀን የተወለደ ተመሳስሏቸው ይሄ ብቻ አይደለም። ሁለቱም አገሮች ተዘግተውና ተቆልፈው ከውጭው ዓለም ጋር የተረሳሱበትን ረጅም ዘመን አሳልፈዋል። ጃፓን ከ1630 እስከ 1850 ዓ.ም. ድረስ ከሁሉም የአለም አገራት ጋር የተቆራረጠች ሆና ነበር። JAMES CLAVELL በጃፓን ታሪክ ላይ ተመስርቶ በተፃፈው “SHOGUN” በተባለ መጽሐፉ መሳፍንቶቹ (Shogunate) የተሳሳቱበትን ውሳኔ ለማስረዳት ይጥራል። የፖርቹጋሎችን በሃይማኖት ስም የመንሰራፋትና አገር የመቀማት ዘዴ በመፍራት ሁሉንም ባዕዳን አስወጥተው በራቸውን የጠረቀመ አዋጅ አወጡ። የዜጐች መውጣት፣ የባዕዳን መግባት በሞት እንዲያስቀጣ ተደነገገ። እስከ ሁለት መቶ ሃያ አመት ድረስ ጃፓን ፀጥ ም፣ ፍቅሯም፣ ንግዷም... እርስ በእርስ ተወሰነ። በወግና በስርዓት ተቀበተተች። ጥቂትም ከፖላንዶች ጋር (እጅግ የሩቅ የሚባል) የንግድ ልውውጥ ከማካሄድ ውጭ ጃፓን ለተቀረው አለም የተጠረቀመች በር ሆና ቆየች።

በ1853 ዓ.ም ነበር። አሜሪካ የጃፓን በር በተለይ ለንግድ መክርቸሙ እየከነከናት ሄደ። በመሆኑም አንድ የባህር ኃይል ቡድኗ የጃፓንን ወደብ ለንግድ ክፍት እንዲያደርግ ግዳጅ ሰጥታ ላከች። ግዳጁን የተቀበለው መኮንን Matthew C. Perry ይሰኛል። በመንፈሳዊና በአስተዳደራዊ የገዛ ጉዳይዋ ብቻ ተጠምዳ የኖረችው ጃፓን በአሜሪካ ባህር-ኃይል ጥቃት ተደናገጠች። መሳፍንቶቹ ገዢዎች ከአቅማቸው በላይ ስለሆነ ሺሞዳ እና ሐኮዳቴ ወደቦች ለአሜሪካ ንግድ ክፍት እንዲሆኑ የግዳቸውን ተስማሙ። ጃፓኖች ለራሳቸው ያላቸው ክብር ጥያቄ ውስጥ ገባ። የማንነት ቀውስ አንገበገባቸው። መንፈሳዊ ስልጣኔያቸው ከቁሳዊ ስልጣኔ ሥር እንዲወድቁ እንዳስገደዳቸው ተረዱ-ቁጭት። አፄ ሙትሱሒቶ የዚህ ቁጭት ውጤት ነው። የተውሸለሸሉትን መሳፍንት ገዢዎች ሁሉ ድል አድርጐ የጃፓንን አንድነት እውን አደረገ።

ኢትዮጵያም ተመሳሳይ ዕጣ-ገጥሟታል፡ በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከመካከለኛው ምስራቅ የተነሳው የእስልምና እንቅስቃሴ የኢትዮጵያን የባህር በር ዘግቶ ነበር። ኢትዮጵያ ከዚያ በፊት የነበራት ዓለማቀፍ የዲፕሎማሲ ግንኙነትና የንግድ ልውውጥ ሙሉ በሙሉ ተቋረጠ። ኤድዋርድ ጊበን “History of the Decline and foll of the Roman Empire” የተሰኘ መጽሐፉ ላይ እንዳለው ሆነ ‹‹ኢትዮጵያና የቀረው ዓለም ተረሳሱ›› እንደ ጃፓን ሁሉ ኢትዮጵያም ፀጪ፣ ፍቅሯ፣ ንግዷ... እርስ በእርስ ተወሰነ። በወግና በሥርዓት ተቀበተተች። አንድ ያደረጋት አፄ ቴዎድሮስ እስኪመጣ በዘመነ መሳፍንት ኃይሏ ተባጣጥሶ እና ተዳክማ ቆየች፡ አውሮፓዊ ሥልጣኔን ለመጀመሪያ ጊዜ በአፄ ቴዎድሮስ ብትማትርም የከሸፈ መማተር ሆነባት።

ጃፓን ግን ሥልጣኔ መማተሯ ስላላት-እንዴት?

አፄ ሙትሱሒቶ የጃፓንን መሳፍንታዊ አገዛዝ (Shogunate) አስወግደው ሙሉ ስልጣን እጃቸው እንዳስገቡ አዲሱን ስርዓትና እራሳቸውን ‹‹ሚጂ›› (Meiji) ሲሉ ሰየሙ። ቀጥታም ወደ ባህል አብዮት አመሩ። የጃፓንን ልምድ በዘመናዊው አውሮፓዊ አስተሳሰብ ለመተካት ኃይል ተጠቀሙ። ከአውሮፓ ባስመጧቸው ከባባድ ጦር መሣሪያዎች በጉራዴና በቀስት የተደገፈውን ባህላዊ ሰራዊት (Samurai) ገጥመው ድል መቱት። ይሁንና የባህላዊው ጦር አስተሳሰብ ከጃፓናዊው ልብ ውስጥ እንዳልተነቀለና እንዳልተመታ ተረዱ፡ ስለዚህ ለማስወገድ ከመሞከር ይልቅ የጃፓንን መንፈስ ከአውሮፓዊ መንፈስ ጋር የማዋሃድ ሥራ ሰሩ። ጥንታዊው የጃፓን ትውፊታዊ መሠረት ላይ አዲሱን ሠራዊትና ኢንዱስትሪያዊ ፍላጐት ተከሉ። “The cultural Library” የተሰኘው መጽሐፍ በ10ኛ ቅፁ ገፅ 373 ላይ “There forces combined to create in Japan an irresistible drive toward imperialism the conquest of foreign lands and peoples.” ይላል። (ጃፓን ወደ ኢምፔሪያሊዝም የምታደርገውን ጉዞ የማይገታ ለማድረግና የአካባቢውን አገሮች እንዲሁም ህዝቦች ድል ለመምታት እነዚህ ኃይሎች ህብረት ፈጠሩ) እናም በአርባ አመታት እድሜ ውስጥ ጃፓን ኃያል ከተሰኙት የአለም አገራት አንዷ ሆነች።

የአፄ ቴዎድሮስ የለውጥ ፍላጐት ብቻ ሳይሆን አተገባበራቸውም ጭምር የአፄ ሙትሲሒቶን መንገድ የተከተለ ነበር። ዓፄ ትእዛዘቸው አለቃ ዘነብ አፄው ዘመናዊ ሰራዊት እንዲደራጅ ጥረት አድርገው እንደነበር ይናገራል፡ የባህበሬው ቤት እየተሰራ በመዝረፍ የሚኖረውን ባህላዊ ወታደር ወደዘመናዊ ሰራዊትነት ለማሸጋገር በቅድሚያ የወሰዱት እርምጃ የጉልበት ሥርዓትን በማጥፋት የመንግስት ግምጃ ቤትን ማዳበር ነበር፡ ከዚያ ለሰራዊቱ ቀለቡን ከመንግስት እየሰፈሩ ደሃውን ከማስቃየት እንዲተቃብ ማድረግ። ለዚህም በ1856 ዓ.ም አቡኑና ዋና-ዋና የቤተክህነት ሰዎች በተገኙበት አንድ ጉባኤ አካሄዱ። ጉባኤው የግብር አሰባሰብን የተመለከተ ነበር። አልተሳካም እንጂ።

ስለዚህ ያልተሳካ የአፄው ትልም የእንግሊዙ ቆንስል ፕላውደን በቁጭት ይናገራል። የቴዎድሮስ መሪነት ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን እድገት የሚጠቅም መሆኑን በመረዳቱም ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ለማቀራረብ ተዘጋጅቶ ነበር። ምን ይሆናል፤ ፕላውደን እቅዱን ሳይተገብር በጋረድ ተገደለ።

አፄ ቴዎድሮስ ጉልትን አስቀርተው ግብር በቀጥታ መንግሥት እንዲሰበሰብ የማድረግ እቅዳቸው ተሳክቶ ቢሆን ኖሮ ጃፓን ወደ ኢምፔሪያሊዝም ያደረገችው ጉዞ በኢትዮጵያም በተደገመ ነበር። ይህን የምንለው የአፄው የስልጣኔ ፍላጐት በአውሮፓውያን መንፈስ ስር ብቻ የወደቀ እንዳልነበር በመገንዘብ ነው። የአፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያዊ መንፈስ ከፍተኛ እንደነበር የምናውቀው ነው። እንደ አፄ ሙትሲሒቶ ሁሉ ‹‹ኢትዮጵያዊውን ሥልጣኔ›› ከአውሮፓዊ ሥልጣኔ ጋር አዋህደው አንድ የማይገታ ጉዞ መፍጠራቸው አይቀርም ነበር፡ ለመሆኑ በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ‹‹ኢትዮጵያዊ ሥልጣኔ›› የሚባል ነገር ነበር? ኢትዮጵያዊውስ ሥልጡን ህዝብ ሊባል ይችል ነበር?

ኢትዮጵያ እና ጃፓን በሥልጣኔ ረገድም መንትዮች ነበሩ ማለት ይቻላል። የሁለቱም ነባር ስልጣኔ ከአውሮፓው ስልጣኔ የተለየና መንፈሳዊነት ላይ የተመሰረተ ነው። “Theocentric” ይሉታል። እንደአውሮፓውያኑ ስልጣኔ በቁስ ላይ የተመሰረተና የሰውን ልጅ ማዕከል ያደረገ “Anthropocentric” አይደለም። ኢትዮጵያዊው ሥልጣኔ እንደ አውሮፓዊው ሥልጣኔ የሰው ሕሊና በገዛ ሕግጋቱ እየተመራ በመጣር ያገኘው እንዳልሆነ ዶ/ር እንለ ገብረዮሐንስ ‹‹የክፍተኛ ትምህርት ዘይቤ›› የተሰኘ መፅሐፋቸው ላይ ይገልፃሉ። ኢትዮጵያዊው ሥልጣኔ ‹‹በራዕይ፣ በሕልም፣ በአቡቀለምሲስ... ከአምላክ ወይም ከመላዕክት የተገለፀ የህይወትና የአለም ዘይቤ ወይም ትርጓሜ›› ነው ይሉታል።

ጥንታዊዎቹ ኢትዮጵያውያን ‹‹የነገሮችን ሁሉ ባህርይ ማያ፣ መመልከቻ መነፅሩን እግዚአብሔርን በማድረግ ብዙ እውቀቶች ስለአለምና ስለህይወት›› አግኝተዋል። በእነዚህ እውቀቶች ፋናነት የታሪክ ጉዳናቸውን ቀደው ተጉዘዋል የሚሉት ዶ/ር እንለ ከመቅድማዊ ሁኔታ ከአረማዊነት ወደ ከፍተኛ የሥልጣኔ ደረጃ መድረሳቸውን፣ እውነትን፣ ትክክለኛነትን፣ ፍርድን በመትከል የአናብስት መፈንጫ ምድረበዳ የነበረውን ቤተመቅደስ፣ ቤተ መንግስት፣ ሐውልት፣ እልፍኝ ከአዳራሽ እየሰሩ ከትመዋል። በዙሪያቸው የነበረውን እንደ እሳት ያለውን የሥነ ፍጥረት ተቃራኒነት አስገዝበው ለፈቃዳቸው አስገብረውታል። የኢትዮጵያና የጃፓን ነባር ስልጣኔ ይሄ ነው።

አፄ ቴዎድሮስ አውሮፓዊ ስልጣኔ እንዲገባ ከመፈለጋቸው ጋር ጐን ለጐን ነባሩ ስልጣኔያቸን እንዳይጠፋ ይጣጣሩ ነበር። እውነት፣ ትክክለኛነት ፍርድ የነባሩ ሥልጣኔ አውዶች እንደሆኑ ተገንዝበው በአርአያነት ያከናወኗቸው ነበር። እውነትን የሚያጠፉ፣ ትክክለኛነትን የሚበርዙና ፍርድን የሚያዛቡ ካጋጠማቸው መቀጣጫ ከማድረግ ወደኋላ አይሉም ነበር።

በአፄ ቴዎድሮስ ተጀምሮ የነበረው በነባር ሥልጣኔ ላይ አዲሱን ሥልጣኔ የመገንባት ፍላጐት ከአንድ ተኩል ክፍለ ዘመን በኋላም አልተሳካም። ዶ/ር እንለ ይሄን ተመልክተው እንዲህ ብለው ነበር ‹‹ሁለቱን ስልጣኔዎች የኢትዮጵያንና የአውሮፓን በገዛ መንፈሳችን ድልድይነት ማገናኘት በጥረታችን ግለትና ሙቀት እንዲዋሐዱ ለፍሬም እንዲበቁ ማድረግ። ዋናው ሥራ ይህ ነው። መጀመሪያ የገዛ ራሳችንን ደህና አድርገን ማላመጥ መዋጥ፣ ቀጥሎም ከውጭ የመጣውን በዚሁ መንገድ አግልፎ መደባለቅ ማዋሐድ። ያን ጊዜ ከሁለቱ የሰረፀ በገዛ ወዛችን የተጥለቀለቀ አዲስ የመንፈስ ህይወት ይታያል። በሁለቱ ስልጣኔዎች መዋሃድ መንፈስ ከፍራሉማነቱ፣ ከወላድነቱ እንደገና ይመለሳል።››

በአዲሱ ዘመን... በአዲሱ ትውልድ... በአዲሱ መንግስት ይሄ አልሆነም። ‹‹ነባሩን ኢትዮጵያዊ ስልጣኔ ጥሎ፣ ቻይናዊ እድገትን አንጠልጥሎ›› ሆነናል። እውነት፣ ትክክለኛነትና ፍርድ ሆን ተብሎ ተገስሰዋል። ‹‹እስካልተያዙ ድረስ ሌብነትም ሥራ ነው›› ተብሎ በመሪዎች ተለፍፏል። የልማት እሳቤ ከሰው አልፎ ከመሬት ላይ እንዲውል ተደርጓል። ኢትዮጵያዊ ኩራት፣ በኢትዮጵያዊ ኃፍረት፣ ኢትዮጵያዊ ጀግንነት በኢትዮጵያዊ ፍርሃት፣ ኢትዮጵያዊ እምነት በኢትዮጵያ ሥጋት... ተተክተዋል። ጃፓን ስፈጣን እድገቷ መሰረት ያደረገችውን ነባር ስልጣኔ እኛ ፈነቃቅለን ጨርሰናል። የማንነት ምድረ-በዳ ላይ ቆመናል። ከዚያስ??

የመምህራኑን ጥያቄ ይታሰብበት!

አንድ ሀገር እንደሀገር ለመቆም ከሚያስፈልጋት በርካታ ምሶሶዎች መካከል የተማረው ማህበረሰብ አንዱና ወሳኙ ክፍል ነው። ይሄን ወሳኝ ማህበረሰብ ለማፍራት ትልቅ ሙያዊ ሀላፊነት የተጣለበት ደግሞ መምህሩ እና መምህርቷ ናቸው።

የመማር ማስተማር ሂደት ስሙር መሆን ህዝብ ለሚቋምጥለት የሀገር እድገት ዋና ጎዳና ነው፤ በትምህርት ራሱን የቻለ የተሻለ ገቢ እና ርእይ ያለው ትውልድ በመፍጠር ነገን በተሻለ አበጅቶ ለተተኪ ሀገር ተረካቢ ትውልድ ለማስረከብ ሀላፊነት የሚሰማው ትውልድ ለመፍጠር ትምህርት መተኪያ የማይገኝለት እንደሆነ ግልፅ ነው።

ለዚህ ሀገራዊ ግብ መሳካት ደግሞ የመምህራን የስራ ድባብ፣ አካዳሚክ ነጻነት እና ኑሮውን እንዲያሸንፍ የሚያስችለው ወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታውን እና ትክክለኛ ሁኔትን መሰረት ያደረገ የኑሮ መሻሻልን ሊፈጥር የሚችል የስራ ሂደት የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መልኩ ሊፈጠርለት ይገባል።

ይህ ሲሆን ለስራቸው ትጋትን በመጨመር በመማር ማስተማር ሂደቱ የእውቀት ማስተላለፍ መንገዱን ብሩህና ነፃ ያደርገዋል።

የዛሬ የጋዜጣችን አቋም መነሻ ጉዳይ ሰሞኑን መምህራን ከ16 አመታት ጀምሮ ሲጠይቁ የነበረው የደመወዝ ጭማሪና የእርከን ማሻሻያን ተከትሎ በመንግስት በኩል ተሰጠ ስለተባለው ምላሽ ነው። ከዚህም ጋር ተያይዞ በመምህራኑ በኩል እየታየ ያለው የስራ ማቆምና እስካሁን ተገቢውን ምላሽ አለማግኘት በፍትህ ጋዜጣ አይን አሳሳቢ ሀገራዊ ጉዳይ መሆኑን ለማሳየት ነው።

በውጪው አለም የተማሩ ዜጐች የኑሮ ደረጃቸውን ለማሻሻልና የብቃታቸውን ያህል ክብር ለማግኘት ሲሉ ሀገራቸውን፣ ትውልዳቸውንና እምቅ አቅማቸውን አባክነው ከሀገር እንዳይሰደዱ ለመከላከል ከፍተኛ ጥንቃቄና እንክብካቤ ይደረግላቸዋል። መምህራንም ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሙያዊ ነፃነት ለሰጣቸው ህዝብና መንግስት የምላሽ ክፍያቸው በማድረግ ሀሳብና እውቀታቸውን ያለመሰሰት ለትውልድ ሲሰጡ ይስተዋላል። እነዚህ አገራት የእውቀት አባት የሆነውን መምህር በማክበርና የተሻለ የስራ ድባብ በመፍጠር የማይናወጥ መሰረት ያለው ትውልድና ሀገርም ፈጥረዋል።

በሀገራችንም እንደዚህ ያለ ማህበረሰብና ሀገር ለመፍጠር የሚደረገው ሀገራዊ እንቅስቃሴ ከመምህራን ልባዊ ተሳትፎ ውጪ ሊሳካ እንደማይችል ፍትህ በፅኑ ታምናለች።

ከሰሞኑ የመምህራኑ ሰዋዊ እና ሙያዊ ጥያቄ ጋር ተያይዞ ጥቂት የመማር- ማስተማር ቀናት ባክነዋል፣ ይህ መንግስትን ቆም ብሎ እንዲያስብ ሊያደርገው ይገባል፤ የመምህራኑን የስራ ሁኔታ፣ የገቢ መጠን፣ እና እየኖሩት ያሉትን ህይወት ታሳቢ ያደረገ እውነተኛ ምላሽ ሊሰጣቸው ይገባል ስትል ፍትህ ትጠቁማለች።

ነገር ግን አሁን በመንግስት በኩል ሊደረግ የሚስተዋለው የተወሰኑ መምህራንን ነጥሎ እርምጃዎችን በመውሰድ ብዛት ያላቸው መምህራን ከስራ ገበታቸው ሊባረሩ እንደሚችሉ ስጋት እንዲገባቸው ማስፈራሪያን ጨምሮ የተለያዩ ጫናዎች እየደረሰባቸው እንደሆነ ተሰምቷል።

በትምህርት ሚንስትር በኩልም የጉዳዩን ባለቤት አቅርቦ በማነጋገር እውነተኛ መፍትሄ ከመሻት ይልቅ ችልተኝነትና ዳተኝነት ታይቶበታል፤ የመምህራን ማህበሩ ደግሞ የሙያ ማህበር ሳይሆን የመንግስትን ስራ የሚሰራ ተቀጥላ ጽ/ቤት መምሰሉን በተደጋጋሚ ከአባላቱ ስሞታዎች በመቅረብ ላይ ይገኛሉ።

በፍትህ እምነት ለዚህ የአንድ ትልቅ ማህበረሰብ ጥያቄ በቂ ምላሽ ሳይሰጡ ማለፍ እየተከሰተ ያለውን የትውልድ ክስረትና የአእምሮ ፍልሰት /Brain drain/ ማባባስ ነው የሚሆነው።

መንግስት ከዚህ ቀደም በአካዳሚክ ብቃታቸው የተመሰከረላቸውን 40 የዩኒቨርስቲ መምህራንና በርካታ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን በፖለቲካዊ ግምገማ ብቻ በማባረሩ የከፍተኛ ትምህርት ሂደቱን ምን ያህል እንዳስተጓጎለውና እንደጎዳው ዛሬ ዛሬ አሉታዊ ውጤቱ በትውልድ ላይ ወለል ብሎ ሲታይ መንግስትም ሳይወድ በግዱ እያመነበት መጥቷል።

በመሆኑም መምህራኑን ያለበቂ ነፃነት በግዴታ ወደ ስራ ገበታቸው ማሰማራት፣ ለጥያቄዎቻቸው ምላሽ መንፈግ፣ ችግሮቻቸውን በሩቁ መመልከትና ስራ ማቆማቸውንም እንደ ፖለቲካዊ አመፅ መቁጠር ውሎ ሲያድር ጠልፎ የሚጥል ሀገራዊ በሽታ በመሆኑ በልዩ ትኩረት ይታይ ዘንድ ፍትህ ማስገንዘብ ትወዳለች።

በመምህራኑ ላይ የተስተዋለው ችግር በሀገሪቱ ለተከሰቱትና ለሚከሰቱት ጥያቄዎች ማሳያ ነውና ፍትህ በአግባቡ ይታሰብበት በማለት መልዕክቷን በጽኑ ታስተላልፋለች።

አስተያየት

ደርዱስ ለክቡር ፍ/ቤት፤ ደርዱስ ለኢትዮጵያ ህዝብ



ናትናኤል መኮንን
(ከቃሊቲ ማረሚያ ቤት)

ክቡር ፍ/ቤት ከመታሰሬ በፊት በሰላማዊ መንገድ የሚታገሉ ድርጅቶች አባሎችን ማሰር የአቶ መለስ የ20 ዓመታት አገዛዝ የባህሪ መገለጫ በመሆኑ በማናቸውም ጊዜ ልታሰር እንደምችል የጠበቅኩ ቢሆንም እንደዚህ ዓይን ባወጣ ሁኔታ ከሽብር ጋር በተያያዘ እከሰሳለሁ ብዬ በህልሜም በውኔም አልጠበቅኩም ነበር። ምክንያቱም ትግሉ ውስጥ በነበርኩበት ወቅት በድርጅቱ የውስጥ ስብሰባዎችም ሆነ ድርጅቱ ከህዝብ ጋር በሚያደርጋቸው ስብሰባዎች ወይም ደግሞ በግል ከግለሰቦች ጋር በነበሩኝ ውይይቶች ሁሉ በምሰነዝራቸው ሀሳቦችም ሆነ በምይዛቸው አቋሞች አገዛዙን በሰላማዊ መንገድ ታግሎ መለወጥ አማራጭ ብቻ ሳይሆን እምነታችንም መሆን እንዳለበት በተደጋጋሚ እገልፅ ስለነበርና በተግባራዊ እንቅስቃሴዬም ከዚህ የተለዬ ተግባር ስላልነበረኝ ነው።

ክቡር ፍ/ቤት በእኔ እምነት ሰላማዊ ትግል ሳትገድል የምትሞትበት ወንጀል ሳትሰራ በተደጋጋሚ የምትከሰስበትና ወደ ወህኒ የምትወርድበት እየተበደልክ ይቅር የምትልበት፣ በአጠቃላይ የሰውን መብት ለመንጠቅ ሳይሆን የራስን መብት አሳልፎ ላለመስጠት በፅናትና በታላቅ ዲስፕሊን የሚደረግ ሰላማዊ ተጋድሎ ነው። መጨረሻውም ቂምና በቀል ሳይሆን ፍቅርና እርቅ ነው።

ክቡር ፍ/ቤት ከላይ የዘረዘርኳቸው የሰላማዊ ትግል መርሆዎች በመርህ ደረጃ ብቻ የማራምዳቸው ሳይሆኑ በዕለት ከእለት የትግል እንቅስቃሴዬ ውስጥም የተግባር መመሪያዎች ነበሩ። ስለሆነም በሽብር ተጠርጥረሃል ስባል የራሴን ማንነት ሳይሆን የተጠራጠርኩት አገዛዙ ምን ያህል ሰላማዊ ትግል የሚያካሂዱ ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ከፖለቲካ መድረኩ ጠራርጐ ለማጥፋት እንደተዘጋጀና የህዝቡን ህገ-መንግስታዊ የነፃነትና የዴሞክራሲ ትግል ለማዳፈን ምን ያህል እንደቆረጠ የሚያሳይ ነው።

ክቡር ፍ/ቤት፡- እኔ እንኳን ሰውን ያህል ክቡር ፍጡር ስለመግደል ላሴርና የህዝብ ሀብት፣ የሆኑትን መሰረተ ልማቶች ስለማውደም ላቅድ ቀርቶ አፈናን፣ ጭቆናንና ግፍን በሰላማዊ መንገድ ከመታገልና ከመቃወም ውጭ የገዥውን ፓርቲ አባላትና አመራሮች እንኳን በጥላቻ ዓይን ተመልክቼ አላውቅም። ወደፊትም አልመለከታቸውም። ነገር ግን በዕናት አምርሬ እታገላቸዋለሁ። አፈናቸውን እንዲያቆሙ ከቁልቁለት ጉዟቸው እንዲመለሱ፤

ክቡር ፍ/ቤት፡- ሽብር የእኔ መገለጫ አይደለም። ሽብር የፓርቲዬ የአንድነት መገለጫ አይደለም። ሽብር የኢትዮጵያ ወጣት መገለጫ አይደለም። በአጠቃይ ሽብር የኢትዮጵያ ህዝብ መገለጫ አይደለም። እኔ የምለው አቶ መለስ የሽብር ሀጉን በዓለም ምርጥ ተሞክሮ ካላቸው ሀገሮች ኮማ እንኳ ሳይቀር ቀድተው እንዳመጡት ነግረውናል፡ ፡ ነገር ግን አይደለም የሚፈነዳ ቦንብና ተተኳሽ ጥይት ሊይዙ ቀርቶ ስለሽብር የሚያወራ ወረቀት እንኳ ይዘው ያልተገኙ ሰላማዊ ፖለቲከኞችን አሸባሪ ብሎ ማሰርን ከየትኛው ሀገር ምርጥ ተሞክሮ ነው የቀዱት? መቼም የፖለቲካ ተቀናቃኝን በሽብር የመክሰስ ሴራ ከአሜሪካና ከአውሮፓ ወይም የሽብር ሀጉን በቀጥታ ከቀዱባቸው ሀገሮች እንዳልሆነ እርግጠኛ ነኝ። በዓለም ላይ ከአቶ መለስ አገዛዝ በስተቀር በፖለቲካ የሚቀናቀኑትን ሰላማዊ ታጋዮች ሽብርተኛ ብሎ የከሰሰም ሆነ የፈረጀ ሀገር የለም።

ክቡር ፍ/ቤት፡- አገዛዙ እንዳለው እኔ ባለስልጣናትን ለመግደልና የህዝብ ሀብት የሆኑትን መሰረተ ልማቶች ለማውደም ያሴርኩ፣ ያቀድኩና በሽብር የተፈረጀ ድርጅት አባል ያልሆንኩና ከኢትዮጵያ ጋር በጦርነት ሁኔታ ላይ ካለው የሻዕቢያ መንግስት ጋርም የተባበርኩ ሳልሆን በሰላማዊ መንገድ የሚታገለው የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ መስራችና የም/ቤት አባል ለአንድነት አላማዎች ተፈፃሚነት በቁርጠኝነት የምታገል፣ እንኳን ከሻዕቢያ ጋር ልተባበር፡- ከሻዕቢያ ጋር በመተባበር ሀገሬን የባህር በር ያሳጣትን አቶ መለስን ጭምር የምታገል ለሀገር አንድነትና ክብር የምታገል፣ ሀገር ወዳድ ዜጋ ነኝ።

ክቡር ፍ/ቤት የድርጅቴም ዓላማ ሁላችንም በእኩልነትና በነፃነት የምንኖርባት ሀገር መፍጠር፣ ነፃነታቸውና ገለልተኝነታቸው የተረጋገጠ የፍትህ ስርዓት፣ የፀጥታ ኃይልና ሚዲያ መፍጠር፣ የህዝብን እኩል ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ተቋማዊ ሙስናን ማስወገድ፣ ህዝብ የሚፈራቸው ሳይሆን ህዝብን የሚያከብርና ተጠያቂነት ያለው መንግስት መመስረት፣ ዘረኝነትና አድሏዊነትን መዋጋትና ብሔራዊ መንግስትና ብሔራዊ እርቅ እንዲፈጠር መታገል ናቸው።

ክቡር ፍ/ቤት፡- በእኔም ሆነ በድርጅቴ በአንድነት እምነት አሁን በስልጣን ላይ ያለው ሥርዓት ከሻዕቢያ ጋር በመተባበር ደርግን ከስልጣን አስወገደ እንጂ ዴሞክራሲን አላመጣልንም። ጭቆናን አላስወገደልንም። እነ አሞራው ሞቱለት የተባለው የ17 ዓመታት የእኩልነትና የዴሞክራሲ ትግል እነሱ የታሰሩበት የምርመራ ክፍል እንኳን ሳይቀር እኔን ጨምሮ ሰላማዊ የዴሞክራሲና የነፃነት ታጋሮች በግርፋት ቁም ስቅላቸውን አይተውበታል፡ ፡ አሁንም ያዩበታል። በእኔ እምነት በአስር ሺዎች መስዋዕትነት የተከፈለበት የዚያ ትውልድ የነፃነት፣ የዴሞክራሲና የእኩልነት ጥያቄ ትግል ጨንግፏል፡ ፡ በዚያ ጊዜ የነበረው አፈና፣ ግድያና እስር አሁንም መልኩን ቀይሮ ቀጥሏል። ልዩነቱ አሁን አፈናውን፣ ግድያውንና እስሩን የሚያካሂደው የአቶ መለስ አገዛዝ ሲሆን በዚያ ጊዜ ደግሞ መንግስቱ ኃ/ማርያምና ደርግ መሆናቸው ብቻ ነው።

ክቡር ፍ/ቤት የእኔም ሆነ የድርጅቴ የአንድነት ትግል ወቅታዊ ትኩረት አቶ ‹‹ሀ››ን ከስልጣን በማውረድ አቶ ‹‹ለ››ን ወደ ስልጣን ማምጣት አይደለም። ትግሉ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ መስፈን እንቅፋት የሆኑትን ሀይሎች ሁሉ መለወጥ ነው። ትግሉ ለብሔራዊ መግባባትና እርቅ በር የዘጋውን አምባገነን ስርዓት ለሰላም፣ ለውይይትና ለእርቅ በሩን እንዲከፍት ማድረግ ነው። ትግሉ የመንግስትንና የገዥውን ፓርቲ ሥራና ተግባር በመደባለቅ በህዝብ ቢሮክራትና በህዝብ ገንዘብ ፓርቲ እያደራጀ ያለውን ተቋማዊ ሙሰኛ ማስወገድ ነው። ትግሉ ህዝብ የፈለገውን የፖለቲካ ፓርቲ የመደገፍ ህገ-መንግስታዊ መብትን በመፃረር የተቃዋሚ ድርጅት ጽ/ቤት በሮች ላይ ተቀምጠው የሚወጣውንና የሚገባውን ሰው ሁሉ የሚያስፈራሩ፣ በህዝብ ሀብት እየተዳደሩ ህዝብን የሚያስፈራሩ የመንግስት ደህንነቶችን አትችሉም በቃ ማለት ነው። በአጠቃላይ ወቅታዊ የትግሉ ትኩረት ህዝብን ከፍርሃት ቆፈን ነፃ በማውጣት የነፃነትና የዴሞክራሲ ትግሉ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግና የዴሞክራሲ ተቋማትን ነፃነት በማረጋገጥ የፖለቲካ ምህዳሩን ማስፋት ነው።

ክቡር ፍ/ቤት፡- እኔም ሆንኩ የኢትዮጵያ ወጣት በአጠቃላይም የኢትዮጵያ ህዝብ የግንቦት ሰባት አባል መሆን ሳያስፈልገን የሻዕቢያም ተላላኪዎች ሳንሆን ለነፃነታችን መታገል እንችላለን፡ ፡ ህዝብን እየጨቆኑ የሚመጣ ልማትም ሆነ እድገት ባርነት ነው ማለት እንችላለን። የካድሬ ልጅ ጠግቦ ኬክ ኬክ እያገላ የብዙሃኑን ኢትዮጵያዊ ልጅ ዳቦ መመገብ ያልቻለ ልማትም ሆነ እድገት በአፍንጫችን ይውጣ ማለት እንችላለን። በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ተላላኪ ወይም ደግሞ አሸባሪ ሳይሆን ነፃ አውጭም ሳያስፈልገው ለመብቶቹ መታገልና ግፍን ማስወገድ፣ ከጭቆናም ነፃ መውጣት ይችላል። ራሱን ችሎ በሰላማዊ ትግል አበይት ለውጥ ማምጣት እንዲችል ጭቆና በቃኝ ዘረኝነት አንገሽግሾኝ፣ አቶ መለስ ከጫንቃዬ ይውረዱ ማለት ይችላል። ይህን

ወደ ገፅ 12 ዞሯል

ፍትህ ጋዜጣ

በማስተዋል ህትመት ማስታወቂያ ስራድርጅት በየሳምንቱ የሚታተም

የአሳታሚው አድራሻ
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 11/12
የቤት ቁጥር አዲስ
ፒያሳ ራስ መኮንን ድልድይ አጠገብ

ሥራ አስኪያጅ
ማስተዋል ብርሃኑ

ዋና አዘጋጅ
ተመስገን ደሳለኝ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ ጀሞ ሳይት የቤ.ቁ. 012

አዘጋጆች
ሙሉነህ አያሌው
ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

ከፍተኛ ሪፖርተሮች
መሐመድ ነስሩ
ኤልያስ ገብሩ

ሪፖርተር
ሰውዓለም ታዬ

አምደኞች
ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም
አለማየሁ ገላጋይ
ጌታቸው ታምራት
ዳንኤል ተፈራ
ቅጣው እጅጉ
ታዲዮስ ታንቱ

ግራፊክስ ዲዛይን
ሀብታሙ ታደሰ
ቤቴልሄም አመነሸዋ

የሽያጭ ሰራተኞች
ደለለኝ ሙሉጌታ
ታመነ ደገፋ

0911 928401
0911 712361
011 8951856
✉ 110744

E-mail:
fetih_gazeta@yahoo.com

www.fetehe.com

አታሚ
ብርሃንና ሰላም
ማተሚያ ድርጅት
ክ/ከተማ፡- አራዳ
ቀበሌ፡- 17
የቤት፡- 984

የተባበሩ ጩኸቶች- ቦአዚዝ፣ መጅሊስ፣ መምህራን...



ተመስገን ደሳለኝ

ጆርመናዊው ካርል ማርክስ ‹‹አለምን ለሁለት የከፈለ›› የሚል ቅጽል ለማግኘቱ በምክንያትነት የሚነሱት የራሱን ሶስት የዳስ ካፒታል ቅፆች፣ ኮሚኒስት ማኒፌስቶ እና የ1844ቱ ማንስክሪፕትን ጨምሮ ሌሎቹ ስራዎች እስኪመጡ ድረስ የምድራቱ የማህበረ-ኢኮኖሚ መዋቅር በካፒታሊዝም ላይ ይደመደማል የሚል ትንተና ሰለነበር ነው። ካርል ማርክስ በተጠቀሱት ስራዎቹ የማህበረሰብን የእድገት ደረጃዎች ጋርዮሻዊ፣ የባሪያ አሳዳሪ፣ ፊውዳሊዝም እና ካፒታሊዝምን በመሰሉ አራት ተከታታይ ስርዓቶች ውስጥ እንደሚያልፍ፣ በመጨረሻም ካፒታሊዝም በሚያጋጥመው ውስጣዊ ተቃርኖ ሶሻሊዝም እንደሚወለድ ተነበዮአል።

እናም ድንገት የተከሰተው ካርል ማርክስ ‹‹Equal wealth of distribution (እኩል የሀብት ክፍፍል ወይም እኩልነት ይስፈን)›› የሚል አስተሳሰብ አመጣና አለምን አስደነገጠ። በሂደትም እነ ፊዴሬክ ኤንግልስ፣ ቭላድሚሪ ሌሊች ኡሊያኖቭ ሌኒን... አዳብረውት ‹‹ሶሻሊዝም›› በሚል የዳቦ ስም ገበያ ላይ ዋለ። ይህንን ተከትሎም አለም ለሁለት ተከፈለ ‹‹በሶሻሊዝም እና በካፒታሊዝም›› (ምስራቅ እና ምዕራብ) በሚል ርዕዮተ-አለም ይሉሃል የፖለቲካ ተንታኞች።

መቼም ካርል ማርክስ ሚስትና ልጆቹን እያስራበ እነዚህን ሁሉ ሲፅፍ ‹‹አለምን ለሁለት ከፍዬ ታሪክ እሰራለሁ›› ብሎ አይደለም። (ህይወቱ ባለፈ ጊዜ እንኳ በቀብር ስነ-ስርአቱ ላይ የተገኙት ስምንት ሰዎች ብቻ ናቸው)፤ ሌሎች ባለታሪኮችም ‹‹ታሪክ ልስራ›› ብለው ተነስተው አይደለም ታሪክ የሰሩት። ሆኖም ኢ-ፍትሃዊነትን፣ ጭቆናን፣ መገፋትን፣ አድሎን፣ በደልን፣ ደህንነትን፣ ረሃብን... አንቀበልም ሲሉ የፈጠሩት ‹‹እምቢተኝነት›› ነው ሄዶ ሄዶ አዲስ ታሪክ የሰራው። በዚህም ባቡር ተሳፍረው ያለፉ በርካታ ባለታሪኮች አሉ። ከሀገራችንም እንደምሳሌ ማንሳት ካስፈለገ ጥቂቶቹ የህወሓት መስራቾች የሰሩትን ገድል ማየት ትችላለህ። ምንድር ነው የሰሩት? ብለህ ጠይቅ፣ የምታገኘው ግልፅ ነው። አዎ! ‹‹ተበደልን›› ወይም ‹‹የትውልድ አካባቢያችን ተበደለ›› ሲሉ አመፁ፡ ይህ አመጻቸውም መነሻ ምክንያት ስለነበረው ብዙዎች ተቀላቀሏቸው። ከ17 ዓመት ውጣ ውረድ በኋላም ‹‹አልፍ›› ሆኑ። ‹‹አልፍ ሆነናል›› ሲሉም እየዘመሩ መንግስት መሰረቱ። ይህ ትልቅ ታሪክ ነው። ለአላማ የመፅናታቸውን ተሞክሮ በሚገባ ከተከተለከውና በልቦናህ ካሰረፀከውም እመነኝ ተጠቃሚ ልትሆን የምትችልባቸው የፅድል ቁጥሮች ጥቂት አይደሉም።

ከሀገር ውጭ ደግሞ አንድ እንጨምር። ታሪኩ የቅርብ ነው። ቦታውም ሰሜን አፍሪካ ነው። የታሪኩ ባለቤት መሀመድ ቦአዚዝ የተባለ ቱኒዝያዊ ወጣት ነው። ይህ ወጣት በሀገሩ ቱኒዚያ ለዕለት እንጀራው የሚሆን ስራ አጣና ብዙ ተንከራተተ። ሌላው ቀርቶ በአነስተኛና ጥቃቅን እንኳን ሳይቀር የሚያደራጀው አጣ። ችግሩም ሲበረታበት አትክልት በጋሪ እያዞረ መሸጥ ጀመረ። ይህም ሆኖ እንቅፋት ገጠመው። በእርግጥ እንቅፋቱ የገበያ እጦት አልነበረም። ለዚህማ ‹‹ኢንሽ አላህ›› ከተማ ለከተማ በጋሪ የሚያዞረውን ፍራፍሬና አትክልት የሚገዛው አላጣም። እንቅፋቱ ከመንግስት ነው። ይኸውም የከተማው ደንብ አስከባሪዎች ጎዳና ላይ አትሸጥም ብለው ንብረቱን ነጠቁት። ይህን ጊዜም ቦአዚዝ ወሰነ፡ በህይወቱ የመጨረሻውን-አደገኛ የሆነ ውሳኔ። የውሳኔውም መንፈስ ሲጨመቅ እንዲህ የሚል ነው ‹‹ህግጋቱ የስርዓቱ ደጋፊና ወገን ላልሆነ ቱኒዝያዊ ኢ-ፍትሃዊ ነው። እናም ዛሬ እኔ ይህንን አሰራር ብቻዬን መለወጥ ባልችልም ድርጊቱን ለመቃወም ግን ራሴን ማጥፋት እችላለሁ››

ወስኖም ሲያበቃ ጎዳጅ ገዛ። የገዛውን ጎዳጅ እንደያዘ ወደ ከተማው አስተዳደር ቢሮ አመራ። ከቢሮው ፊት ለፊት ሲደርስ ቆመ። በጎዳጅ የተሞላውን ኮዳም ክዳን አነሳ። ጎዳጁንም በላዩ ላይ አርከፈከፈ። ገላው በጎዳጅ ራሰ። ይህን ጊዜ የልብ ምቱ ጨመረ። የፍርሃት ግን አልነበረም። ኢ-ፍትሃዊነትን በመቃወም ራሱን ቤዛ ከማድረግ በወሰነው ቁርጠኛ ውሳኔ እንጂ። በእርግጥም የመጨረሻው ጊዜ እንደደረሰ ገብቶታል። ሆኖም አንድ ነገር እንደሚቀረው ያውቃል። ‹‹አላሃ-ጀነትን›› ያወርሰው ዘንድ የህሊና ፀሎት ማድረግና ከአምላኩ ጋር መታረቅ። እናም በለሆሳስ ፀሎቱን አደረሰ። ከአምላኩ ጋርም እንደታረቀ ባሰበ ጊዜ በእጁ የያዛትን ማቀጣጠያ ክብሪት ለኮሰ። ሰውነቱም እንደ ጧፍ ይነድ ጀመረ። በድንገትም አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት...እያሉ የተሰባሰቡ የአካባቢው ነዋሪዎች እሳቱን ለማጥፋት የአቅማቸውን ያህል ተረባረቡ፡ ማጥፋትም ቻሉ። እሳቱ ግን መጀመሪያውኑ ከቦኢዝዝ ገላ ላይ የቻለውን ያህል በልቶ ስለነበረ ሆስፒታል በደረሰ በሶስተኛው ቀን ህይወቱ አለፈ።

ይህንን ተከትሎም በርካታ ቱኒዚያውያን በመንግስታቸው ላይ ‹‹የተቃውሞ ሀብረ ድምፅ›› አሰሙ። ጩኸታቸውም በረከተ፣ የቤን አሊም መንግስት በአፍሪካ እና በአረብ ሀገራት በ‹‹ጩኸት የፈረሰ›› የመጀመሪያው መንግስት ሆነ። ቱኒዚያም ከአምባገነን ስርዓት ነፃ ወጣች። የቦአዚዝ መንፈስ ግን መጮኹን አላቋረጠም። ድንበር ተሻግሮም ፈርኦኖቹ ጋ ደረሰ፤ አምባገነኑ ሆስኒ መባረክም በ18 ቀናት ጩኸት ተንኮታኮተ። ይህንንም ተከትሎ በአለማችን በየትኛውም ጫፍ ያሉ ‹‹ጉልቤ›› መንግስታቶች በዚህ የነፃነት መንፈስ መብረክረክ ያዙ። ከተብረክራኪዎቹም አንደኛው የሞሮኮው ፈላጭ ቆራጭ ንጉስ ነገስት አገዛዝ ነው። ይህ አገዛዝም ተደነባብሮ “ህገ-መንግስታዊ ዘውዳዊውን ስራአት (Constitutional Monarchy)” ሊያሻሽል ቃል ገብቶ የ‹‹እፎይታ ጊዜ›› ተሰጠው (በእኛ ሀገር የእፎይታ ጊዜ የሚሰጠው የኮንድምንየም ቤት ለገዛ ብቻ ነው)

የሆነ ሆኖ የቦአዚዝ መንፈስ ጉዞውን ቀጠለ፤ ‹‹ሆ ብሎ ተነሳ›› እያለም ሊቢያ ገባ። ሊቢያውያኖችም ዳር እስከዳር ተነቃነቁ። ጋዳፊም በቦአዚዝ መንፈስ ተገፍተው የወጡ ‹‹ቁጡ›› ሊቢያውያኖችን በሀይል ለማፈን ያደረገው መከራ ሀገራቱን በአንድ ጀንበር የጦር ቀጣና አስመስላት፡ : አመፁም በረታ። የለውጥ ናፋቂዎቹ ጩኸትም ከቤንጋዚ እስከ ትሪፖሊ አስተጋባ። ከታሪክ እንደተማረነው ህዝብ ተሸንፎ አያውቅምና ከብዙ ትንቅንቅ በኋላ ትግሉ በህዝብ አሸናፊነት ሲርጥ ላይ ተደመደመ። ጋዳፊም ከአርባ አመት በላይ የቆየበትን ወንበር ከ‹‹ታላቅ-ውርደት›› ጋር አጣ። ጋዳፊ ከወንበር ማጣትም አልፎ በአሰቃቂ ሁኔታ ተሰቃይቶ ተገሎ-ተቀበረ። አሁንም የቡአዚዝ መንፈስ አላረፈም። ሱዳን፣ ጅቡቲ፣ የመን፣ ሶሪያ እያለ... ዛሬም እንደቀጠለ ነው። በእርግጥ የየመናዊያን ድምፅ ፍሬ አፍርቷል። የሶሪያውም እነሆ በደጅ ቆሟል።

ከዚህም ባሻገር ይህ የነፃነት መንፈስ ብዙ ሀገራትን እንቅልፍ ነስቷል። አንዳንዶቹ በየቀኑ ፖሊሲ በማውጣት እና ለህዝባቸው በየቀኑ ቀቢፅ-ተስፋ በመስጠት ስራ ላይ ተጠምደዋል። አረ ከዚያም አልፈው አንዳንድ ተሰሚነት ያላቸው ግለሰቦች ላይ ወንጀል እየፈበረኩ እስር ቤት ማስገባት ሁሉ የጀመሩ አሉ።

...ለዚህም ነው ቦአዚዝ አለምን ከለወጡ ሰዎች ተርታ ተሰልፏል የምልህ። ካርል ማርክስ ‹‹የአለም ሰራተኞች ተባበሩ›› ብሎ ባመጣው አዲስ ርዕዮተ-አለም፣ አለምን ለሁለት እንደከፈለው ሁሉ የቦአዚዝ መንፈስም አለምን እየቀየረ ነው፡ : የራሱ የካርል ማርክስንንም ሆነ የምዕራብዊያን የርዕዮተ-አለም መሀንዲሶችን ‹‹ድምዳሜ›› ሳይቀር አፋልሶታል። ለምሳሌ ምዕራቡም፣ ምስራቁም የአረብ ሀገራትን ህዝብ ‹‹ለለውጥ የማይመቹ፣ ለአብዮት የማይነሱ...›› ወዘተ እያሉ ብዙ ጽፈዋል፡ : ይህ ደግሞ የመነጨው እስልምናን በቅጡ ሳይረዱ ‹‹እስልምና ለዲሞክራሲ፣ ለሰብአዊ መብት፣ ለሰው ልጅ እኩልነት፣ ለህግ የበላይነት... አይመችም›› የሚል ጨለምተኛ አስተሳሰባቸውን በሙሁራኖቻቸው በኩል ከ‹‹ባህል ወሳኝነት (Cultural Detriminzim)›› ጎልዮት ጋር እያያዙ እስከመተንተን በመደረሳቸው ነው። የነፃነቱ መንፈስ ግን እነዚህን ሁሉ የለወጠ ሆነ። ቱኒዚያ፣ ግብፅ፣ ሊቢያ፣ የመን... ብዙ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የሚኖሩባቸው ሀገራት ናቸው። ነገር ግን ዛሬ የዴሞክራሲ አብዮት አካሄደው ወደ ሌላ የታሪክ ምዕራፍ እየተሸጋገሩ ነው። ሶሪያውያንም እያካሄዱ ያለው አብዮት፣ የፖለቲካ እንጂ የሃይማኖት አይደለም።

ሁላችንም እንደምናውቀው እስከ ቦአዚዝ መስዋእትነት ድረስ ‹‹አብዮት›› የሚተነትነውም ሆነ፣ የሚብራራው ከካርል ማርክስ የመደብ ጥያቄ አንፃር ብቻ ነበር። ከዚህ በተጨማሪም የማርክሲስቶቹ አብዮት በደም የሚመጣ ነው። ዛሬ ግን ይህ ተቀይሮአል። አብዮት እንዲነሳ ጥልቅ የመደብ ቅራኔዎች መኖር እንደማያስፈልገው ሁሉ፣ ደም አልባ አብዮትም ማካሄድ እንደሚቻል የቡአዚዝ መንፈስ ከነስኬቶቹ ጮኾ ይናገራል። እነዚህ ሁኔታዎች ናቸው የቦአዚዝን ተፅዕኖ ከካርል ማርክስ ተፅዕኖ ጋር የሚያመሳስሉት። ደግሞም መስዋዕትነቱ በሚሊዮን ሳይሆን በቢሊዮን በሚቆጠሩ የአለማችን ሰዎች፣ ሰተገፉ፣ ሰተበደሉ ዜጐች ተስፋ መሆኑን አትዘንጋ። ዘመኑም ካርል ማርክስ የጭቁኖች ነፃ አውጭ ተደርጎ እንደ‹‹መሲህ›› ይታየበት የነበረው አይነት ዘመን ላይ ነው ያለው-ሰላማዊ አብዮቱ... ይህ ታሪክ ከተሰራ ከአንድ አመት ብዙም የዘለለ አይደለም።

...በኢትዮጵያ ከህወሓት በተጨማሪ በርካታ ያልተሳኩ የ‹‹ፀረ-ጭቆና›› ድምፆች ተደምጠዋል። በትግራይ የቀዳማይ ወያኔ አመፅ፣ በጎጃም፣ በባሌ፣ በሲዳማ.. ተከታታይ የገበሬው የአመፅ ጩኸት በምድሪቱ ናኝቷል። እነዚህ ምንም እንኳ የከሸፉ ጩኸቶች ቢሆኖም ለሌላ አዲስ ጩኸት ግን መነሻ መሆናቸው አይካድም።

ይህ ማለት ግን በኢትዮጵያ የተሳኩ ጩቶች አልተከሰቱም ማለት አይደለም፤ ተከስተዋልና። ለምሳሌ የያ ትውልድ የ‹‹መሬት ላራሹ›› ጩኸት የአፄውን መንበር እስኪገፈተር ድረስ የተጓዘ ‹‹ውጤታማ ጩኸት›› ነው። የህወሓትም ጩኸት እንዲሁ የአምባገኑን ወታደራዊ መንግስት ግብአተ-መሬት ያስፈፀመ ታላቅ ጩኸት ለመሆን የበቃ ነው።

ዛሬ ደግሞ ከፀረ-መጅሊስ እስከ መምህራን በርካታ ጩኸቶች እየተሰሙ ነው። መጅሊስ ይውረድ፣ ገዳሙ ስኳር ፋብሪካ አይሆንም፣ ዝቋላ ሲቃጠል አየር ኃይሉ አልተባበረንም፣ የደሞዝ ጭማሪው ሙያችንን ዝቅ ያደረገ እኛንም ያወረደ ነው.... ብቻ እነዚህ ሁሉ ከጣሪያ በላይ የሆኑ ጩኸቶች ሆነዋል። በተለይም በየጁማው ‹‹አላህ ወክበር›› በሚል የምስጋና ድምፅ ታጅቦ ‹‹መጅሊሱ አይወክለንም›› የሚለው ጩኸት እየበረታ ነው።

‹‹የመምህራን ማህበር›› አይወክለንም የሚለው የመምህሩ ጩኸትም እንዲሁ አጋዥ የሚሻ ብርቱ ጩኸት ነው። እዚህ ጋ አንድ ገጠመኝ ልንገርህ። (የት መጽሐፍ ላይ እንዳነበብኩት አላስታውስም) ሆኖም ታሪኩ እንዲህ ነው። ጊዜው በሁለተኛው የአለም ጦርነት ወቅት ነው። አንድ በእግዚአብሔር የማያምን /ኢ-አማን/ ጀርመናዊ ሂትለር ብዙዎችን ከጨፈጨፈ በኋላ እርሱ ጋር እንዴት እንደደረሰ የተረከው ነው። የጀርመናዊው ትርክት ይህ ነው፡-

‹‹የናዚ ወታደሮች መጀመሪያ ‹ጂብሲ›ዎችን ወሰዷቸው። እኔም ጂብሲ ስላልሆንኩኝ ዝም አልኩ። ቀጥለውም አይሁዶችን ወሰዱ። አይሁድ ስላልሆንኩኝም ‹አያገባኝም› ብዬ ቁጭ አልኩ። ከዛም ካቶሊኮች ጋር መጡ፣ አሁንም ካቶሊክ ስላልሆንኩ አያገባኝም አልኩ። ቀጥለውም ናዚን የማይደግፉ ፕሮቴስታኖች ጋር መጡ፡ : ፕሮቴስታንት ስላልሆንኩ ‹ምን አገባኝ› ብዬ ተቀመጥኩ። ሆኖም በመጨረሻ እኔ ጋር መጡ፡ : ነገር ግን ማንም የቀረ ስላልነበረ የሚጮኽልኝ አጣሁ›› ...ድንቅ ምሳሌ።

ጥቂት ስለመምህራን..

ቡደሃ፣ ዛራቱስትራ፣ ኢየሱስ፣ ነብዩ መሀመድ... የመምህር ‹‹አናት››፣ የዕውቀት የመዐዘን ድንጋዮች እንደማለት ናቸው። ወይም ትጉህ እረኞች። መቼም መምህር ሲባል ቀድሞ ትዝ የሚሉን እነዚህ ናቸው። ደግሞም መምህር የሚመዘነው በእነርሱ የስብና መነፅር ነው። በሀገራችንም ቢሆን ሙያው እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የተከበረ ነበር፤ በማህበረሰቡም የሚሰጠው ቦታ ከፍ ያለ ነበር። ለዚህም ይመስልኛል በሰርግ ላይ ሁሉ ሳይቀር የሚዘፈነው ዘፈን እንዲህ የሚል የነበረው፡

-

የእኛ ሙሽሪት ኩሪ፣ ኩሪ
አገባች/ ወሰዳት/ አስተማሪ

እነሆም አስተማሪ ማግባት ክብርና ኩራት የሆነበት ያ ደጉ ዘመን እንደዋዛ ተረት ሆኖ አልፏል። እንዲህ ‹‹...ነበር›› እያልን የምንተርከው ሆኗአል ማለቱ ነው።

እውነትም እኮ የመምህር ደግ ዘመን ታሪክ ሆኖአል። ሌላው ቀርቶ በማህበረሰቡ ዘንድ፣ ለአስታራቂነትም ሆነ ለሽምግልና በግንባር ቀደምትነት የሚፈለገው መምህር ነበር። የዛሬን አያድርገውና። ተማሪ መምህሩ የሚገባበት ምግብ ቤት እንኳ ደፍሮ አይገባም። (ይህ ምንም እንኳ የተጋነነ ቢሆንም ተማሪ ለመምህሩ የነበረውን የአክብሮት ደረጃ ያሳያል። ወይም የመምህር እና የአስተማሪ ግንኙነት ምን ይመስል እንደነበረ ምስክር ሊሆን ይችላል።)

ዛሬ ያለውን የመምህርና የተማሪ ግንኙነት ብናይ በእጅጉ እናዝናለን። ‹‹ተማሪው መምህሩን ደበደበ›› የሚል ወሬ መስማት ተራ ነገር ሆኗአል። ስርአቱ ደግሞ ለዚህ አይነትቱ ‹‹የሞራል ውድቀት›› መዳለድሱን አመቻችቷል። ለምሳሌ የኢህአዴግ አባል የሆነ አንድ ተማሪ መምህሩ እያስተማረ፣ ተማሪዎችም በተመስጦ እያደመጡ ሳለ ከፈለገ ያለመምህሩ ፍቃድ ትምህርቱን አቋርጦ ይወጣል። ምን አልባት ተማሪው ትንሽ በሰል ያለ ከሆነ ግንለመምህሩ በጨዋነት እንዲህ ብሎት ይወጣል ‹‹ስብሰባ አለብኝ››

በንፋስ ስልክ የቲቪቲ ኮሌጅ በ2002ዓ.ም የትምህርት ዘመን ‹‹ቢዝነስ ኢኮኖሚክስ›› ያስተምር የነበረ አንድ መምህር የገጠመውን እንዲህ ሲል አጫውቶኛል፡-

‹‹የማስተምረው ቢዝነስ ኢኮኖሚክስ ነው፡ : እናም ስለሀገሪቱ አጠቃላይ አመታዊ ገቢ (GDP) ሳስተምር ‹ሀገሪቱ ደሃ ነች› ማለቴን በክፍል ውስጥ የነበሩ የኢህአዴግ ወጣት ሊግ አባላት ተማሪዎች ለኮሌጁ ዲን ይነግሩታል። ዲኑም ከምክትል አካዳሚክ ዲኗ ጋር በመሆን ቢሮአቸው አስጠሩኝ፡ : ምክትል ዲኗ ቃል በቃልም ‹ሀገሪቱን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ጋር ለማሰለፍ ኢህአዴግ እቅድ አለው። ስለዚህም ተማሪዎቹን ኢትዮጵያ ደሃ ነች እያልክ መናገር የለብህም› ሲሉ ከገሰፁኝ በኋላ የቃል ማስጠንቀቂያ ሰጡኝ።››

ይህ ሁኔታ መምህሩ በመማር ማስተማር እንቅስቃሴ ውስጥ ለሚጠቀማቸው እያንዳንዱ ቃላት ምን ያህል እንደሚጨነቅ ያሳያል። ወይም መምህሩ ተማሪውን ምን ያህል እንደሚፈራው ያመላክታል። ይሰልለኛል ብሎ ይጠረጥረዋል። እራሱንም በፍርሃት ውስጥ ይከታል። እናም ቀስ በቀስ መታፈንን እየለመደው ይሄዳል። አፈናን አምኖ የተቀበለ መምህር ደግሞ ምን አይነት ተማሪ ‹‹ሊያወጣ›› እንደሚችል መገመት ይቻላል፡ : ለዚህም ነው መምህራኖች ስለሀገሪቱ ችግር በግልፅ የማይናገሩት። ምንአልባትም የሰሞኑ የመምህራን ጥያቄ በተቀናጀ መልኩ ሊቀርብ ያልቻለው የእነዚህ የእነዚህ ተፅኖዎች ድምር

ወደ ገፅ 11 ዞሯል

ስብሐት ገ/እግዚአብሔር ሕይወትና ክህሎት


መጽሐፍ ድጋሚ ታትሞ ገበያ ላይ ዋለ!

‹‹ይህ የዓለማየሁ ገላጋይ መጽሐፍ... የስብሐትን ማንነት (በሰብዓዊነቱ፣ በተፈጥሮው፣ በአመለካከቱ፣ በአስተሳሰቡ) በመውደድና በማክበር ረገድ ጥሩ ትሕትና የተላበሰ መጽሐፍ ነው። እውነት ለመናገር እንደ ቀደሞ ሥነ-ጽሑፍ መምህርነቴ በአፌ ሙሉ ላድንቅ ብል ዓለማየሁ ገላጋይን ጥሩ አማርኛ አዋቂና ከቃላት አመራረጡ ጀምሮ እስከ ንድፈ ሀሳብ አደራደሩ... የመሰጠኝ መሆኑን መግለፅ እፈልጋለሁ።። . .በምርመራውና አዲስ የአመለካከት ፈር በመቅደዱ ዓለማየሁን አሁንም የደራሲነት ጥረትና ቋንቋውን አደንቅለታለሁ።።››

መስፍን ኃ/ማርያም

‹‹ድንቅ ሰራ ነው።። ይህ የዓለማየሁ ገላጋይ መጽሐፍ የሥነ-ጽሑፍና ሃያሲያንን ትኩረት እንደሚስብ አያጠራጥርም። ጋዜጠኛ ዓለማየሁ ለብዙ መሰረታዊ ሂደቶች የሚሆን ጥናት አቅርቧል ማለት እችላለሁ።።››

አዮብ ካሣ



‹‹በዚህ በዓለማየሁ ገላጋይ መጽሐፍ ላይ....መጠነ ሰፊ ውይይትና ክርክር የተደረገበት አጋጣሚ ተከስቷል። ዓለማየሁ ገላጋይ በዚህ መጽሐፍ... ያልተደፈሩ ርዕሶችን በማንሳት ችሎታው ያለውን የተለየ ነገር ከመግለፁም በላይ... ስለስብሐት ህይወትም ሆነ ስለሥራዎቹ በርካታ አዳዲስ ነገሮች ነግሮናል። በሚያምር የቋንቋ አገላለፅ ስለስብሐት የተለየ ህይወትና ክህሎት ከማናውቀው አቅጣጫ ተነስቶ በተጋፋጭነት አቋም ይተርካል። ተወደደም ተጠላም ለደረሰባቸው አዳዲስ ድምዳሜዎች ምክንያቱን አቅርቧል። በዚህ መጽሐፍ የተነሱትን ጉዳዮች ወደ ጉን በመግፋት የምናደንቃቸው ታላላቅ ሰዎች ሲነኩ ብቻ ‹‹ዘራፍ!›› ማለት ከታሪክ ተጠያቂነት አያስተርፍም።››

ሰለሞን ጉሹ

ይህን በታዋቂ ሰዎች ዘንድ እንዲህ ምስክርነት የተሰጠለት አነጋጋሪና ድንቅ መጽሐፍ በአነስተኛ ቅጂዎች የታተመ ስለሆነ ሳያመልጥዎ ዛሬውኑ ፈጥነው የግልዎ ያድርጉት በሁሉም መጽሐፍት መደብሮች ያገኙታል።

ዋና አከፋፋይ አምባሳደር መጽሐፍት መደብር ስ.ቁ. 0911 67 64 57

እውቀትና አስተያየት ምንና ምን ናቸው?



ውድ ዶ/ር አድሰር

እውቀት የሚባል ነገር አለ፣ ወይስ ሁሉም ነገር የአስተያየት ጉዳይ ነው? ባለፉት ሃምሳ አመታት ውስጥ ስለዓለም ሁኔታና ስለህይወት አቅጣጫችን ያለን ግንዛቤ ተለውጧል። በዚህም ስለአብዛኞቹ ጉዳዮቹ የተወሰነ እውቀት መጨበጥ መቻላችን በራሱ አስደማሚ ይሆንብኛል። ያም ሆኖም እስከዛሬ ያከማቸናቸው አብዛኞቹ እውቀቶቻችን አስተያየቶች አይደሉም?

ኤፍ.ኤስ

አብዛኞቻችን አስተያየት የሚባለውን ነገር ጠንቅቀን እናውቀዋለን። አስተያየታችን ሁሉም ሰው ሊስማማበት እንደማይገባም ጭምር እንረዳለን። ከኛ ጋር በሐሳብ የሚይስማሙ ሰዎች ‹‹መልካም እንግዲህ፣ ያ-የአንተ አስተያየት ብቻ ነው›› እያሉ ነገሩን እንድንለምደው አስገድደውናል። ሌላው ቀርቶ በጥሩ መረጃ ላይ ተመስርተን የምንሰጠው አስተያየት ላይ እንኳን የተሟላ እምነት ሳይኖረን ቀርቶ በጥርጣሬ እንናጣለን። ‹‹እርግጠኛ የሆንኩበት ምክንያት አለኝ›› እንላለን ‹‹ነገር ግን ነገሩን በመሐላ ማስደገፍ አልችልም።››

በመሆኑም ሦስት አይነት የአስተያየት ባህሪያት እነዚህ ናቸው፦

1. ከእርግጠኝነት ይልቅ በመሆን እድላቸው መስፋት ላይ ተመስርተው ይገልፃሉ።
2. የጥርጣሬ ጥገኞች ናቸው
3. ምክንያታዊነት ያላቸው ናቸው

የሚጋጩ አስተያየቶች በማቅረብ ቢለያዩ እንኳ እንደ ጤናማ ነገር ይወሰዳል። ሁሉም ነገር የአስተያየት ጉዳይ ነው ብለን ከተነሳን የረጅም ጊዜ ተጠራጣሪነት እንደሰፈነ የሚቆየው ሁሉም ነገር የአስተያየት ጉዳይ ነው ብለን ከደመደምን ነው። የሂሳብና የሳይንስ አስተያየቶችንም ዘንድ የቀነሰ ቢሆንም ቅጥያው ጥርጣሬ እንዳለ ነው። ለምሳሌ በጂኦሜትሪን ዘዴ አንዳች ልኬት ለመጠቆም የሚፈልግ ሰው ባወጣ ያውጣው ግምት መጠቀሙ የግድ ነው። ሌሎችን የግምት አሰራሮች ተግባር ላይ ባዋልን ቁጥር የጂኦሜትሪው ዘዴ እየበለፀገ ይመጣል። ምርምርነክ ሳይንስ መሰረት የሚያደርገው እርግጠኝነትን ሳይሆን ተጠራጣሪነትን፣ ከፍተኛ የግምት አሰራርንና ማጠቃለልን ነው።

የጥንቶቹ የግሪክ ፈላስፎች ከ‹‹ጠርጣሪነት›› (Skepticism) አመለካከት ጋር የሚለይ የራሳቸው አመለካከት አላቸው። ፕሌቶና አርስቶትል የሰው ልጅ እውነተኛ እውቀት የሚያገኝባቸው የተወሰኑ ርዕሰ ጉዳዮች አሉት ሲሉ ያስባሉ። በነገሮች ተፈጥሮ ውስጥ አንዳንድ ነገሮች የግድ አስፈላጊ የሚሆኑ አሉ፡ ፡ ለምሳሌ ድፍን በተፈጥሮው ካየነው ከራሱ ቁራሽ ጋር በንፅፅር እኩል አይሆንም። ድፍኑ ከራሱ ቁራሽ መብለጥ እንዳለበት ማወቅ አስፈላጊ ነገር ነው። ይሄ ደግሞ ስለእርግጠኝነት የምናውቀው ነገር እንዳለ ይጠቁማል። በሌላ በኩል ደግሞ የተከበሩ ሰዎች በተፈጥሯቸው ወርቃማ ፀጉር ያላቸውን ሴቶች ይመርጣሉ ብሎ ማሰብ ላይ እርግጠኝነት የለምና የአስተያየት ጉዳይ ይሆናል።

በእውቀትና በአስተያየት መካከል ያለው ልዩነት በስነ-ልቦናው ዘርፍም ውስጥ አለ። ለምሳሌ ‹‹የተከበሩ ሰዎች ወርቃማ ፀጉር ያላቸውን ሴቶች ይመርጣሉ?›› ወይም ‹‹በሚመጣው ምርጫ ሪፐብሊካን ያሸንፋል?›› ተብለን በተጠየቅን ጊዜ አእምሯችውን የምናዘጋጀው ‹‹አዎ›› እና ‹‹አይ›› ብለን ለመመለስ ነው። ጥያቄውም የዚሁ የአማራጭ ምላሽ ጉአ ዳይ ነው። ነገር ግን ድፍን ከራሱ ቁራሽ መብለጡን በተጠየቅን ጊዜ አማራጭ ምላሽ የለንም፡ ፡ አእምሯችንን በድፍንና በቁራሽ መካከል ያለው ግንኙነት ላይ እናሳርፋለን። ይሄንኑ ግንኙነት ከአንድ አቅጣጫ ብቻ መመልከት እንችላለን።

ከላይ የተመለከትነው እውቀት እና አስተያየት መካከል ያለውን ግልፅ መስፈርት ለመለየት ያስቸለናል። እርግጠኛ በሆነ አግባብ የምናስበው ነገር ከእውቀት የሚመደብ ጭብጥነት አለው። ሀሳባችንም በግል አስተያየት ላይ አይመሰረትም። ይሁንና የምናስብበት አግባብ ያልተቀደና በአማራጭ የተሞላ ሲሆን እያሰብን ያለነው ነገር አስተያየት ነው ማለት ይቻላል። በነፃ ፍላጐት ብቻ ተነስተን የምናውጠነጥነው የግል አስተያየታችን ነው። እዚህ ላይ ምክንያታዊ ሰዎች እንኳን ቢሆኑ ከኛ የተለየ አስተያየት ሊኖራቸው እንደሚችል ልብ ማለት ይገባል።

በዚህ ግንዛቤ መሰረት የእውቀትና የአስተያየት ልዩነት ግልፅ ነው። እርግጠኝነት የሌላቸው ነገሮች አስተያየት ብቻ መሆናቸውን አምነን መቀበል ይኖርብናል። ይሁንና እዚህ ላይ አስተያየቶች ሁሉ ባላቸው የእርግጠኝነት ጥልቀትና ስፋት ሊለያዩ እንደሚችሉ ማወቅ ይኖርብናል። አንዳንዶቹ አስተያየቶች ባልተጠቃለለ እንጥልጥል መረጃና ምክንያት ላይ በመመስረት ሊሆን የሚችሉ በመምሰል ያጭበረብሩሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ በእውነታ ላይ ያልተመሰረቱ እርግጠኝነት የሌላቸው ይሆናሉ፡ ፡ ይሁንና የጭፍን ፍረጃችን ላይ ተመስርተው ይቀርቡልናል።

መስፈርቱ በታሪክ ሆነ በሒሳብ፣ በምርምራዊ ሳይንስ ሆነ በግምታዊ ፍልስፍና ውስጥ ተከስቶ የእውቀትና የአስተያየት አማራጭ ይቀርብልናል። ከላይ ለመመልከት እንደሞከርነው ጥብቅ ተጠራጣሪነት ካለ ሁሉም ነገር አስተያየት ጉዳይ እንደሆነና እርግጠኝነት የሚሰማን ቢሆን እንኳን የግል አስተያየትና የጭፍን ፍረጃ ውጤት መሆኑን ልንናገር እንችላለን። የዚህ ተቃራኒ አመለካከት፣ ማለትም እኔም የምደግፈው ደግሞ በሒሳብና በፍልስፍናው ዘርፍ እውቀት ልናገኝ የምንችልበት አግባብ ሲኖር የምርምር ሳይንስና የታሪክ ዘርፍ ደግሞ ከፍተኛ የመሆን እድል ያለው አስተያየት እንደሚኖር ነው።

ሰላማዊ ትግል ... ከገፅ 2 የዞረ

በማሳያነት የሚጠቅሱት በ1993ቱ የህወሓት መፈረክስ ወቅት ‹‹የዴሞክራሲ መሰረታዊ ጥያቄዎች በኢትዮጵያ›› በሚል ርዕስ ባዘጋጁት ድርሳን ርዕዮተ-ዓለሙ በሁለት መንገዶች ብቸኛው ገዢ ሀሳብ መሆን እንዳለበት መከራከራቸውን ነው። እንደ አቶ መለስ የፓርቲውን አባላት በተከታታይ ስብሰባዎች ማጥመቅ /indoctrination/ ቀዳሚው መንገድ ሲሆን ሌሎቹን የማህበረሰብ ክፍሎች በተመለከተ የህግን እና ተቋማትን በመጠቀም የድጋፉ መሰረት ማሳጣት ርዕዮተ-ዓለሙን የማስፈፀሚያ መንገዶች ናቸው።

አቶ መለስ በተጠቀሰው ድርሳናቸው ‹‹የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ የበላይነትን ማረጋገጥ ማለት በጣም የሚበዛውን የህብረተሰብ ክፍል ስለማንኛውም ዓይነት ጥያቄ ብቻውን ሆኖ በነፃነት ሲያስብ በውስጡ ያሉት መሰረታዊ እምነቶች የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ሆኖ ዞሮ ዞሮ ወደ አብዮታዊ ዴሞክራሲ አቋም መድረስ የሚችልበት ሁኔታ መፈጠር ነው። በአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ በሁሉም ማዕዘናት ሰርፆ በመግባት እያንዳንዱ ሰው ሲያስብ ከዚህ ውጪ ማሰብ የማይችልበት ደረጃ መድረስ ማለት ነው›› ሲሉ የሀሳቡን ውስጣዊ ግብ ያብራራሉ።

ለምርጫ ፖለቲካዊ ዴሞክራሲያዊነት የነፃ ተቋማት አስፈላጊነት የበዛ እንደሆነ የጉዳዩ ምሁራን ይናገራሉ። ከነዚህ ተቋማት መሀከል እንደምርጫ ቦርድ ሁሉ መንግስታዊ ስርዓቱን እንዲያገለግል የሚጠብቀው የፖሊስ እና የመከላከያ ሰራዊት ፖለቲካዊ ገለልተኝነት እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የሽግግር ማህበረሰቦች ዓይነተኛ ሚና አለው። ዴሞክራሲያዊ ተቋማት በሚፈለገው መጠን ያለመጠናከራቸው አልፎም ለምርጫ ፖለቲካ ተሳላጭነት አስፈላጊ ነው የሚባለው ዴሞክራሲያዊ ባህል ገዢውን ፓርቲ ጨምሮ በተቀናጀ የፖለቲካ ሃይሎች ባግባቡ አለመስተዋሉ ለምርጫ ተኮሪ ግጭቶች መከሰት እድል ይከፍታል። የሚሊተሪ ስርዓቱ በዚህ መሰል የፖለቲካ አውድ ውስጥ የሚኖረው ጠቀሜታ ግልፅ ቢሆንም ኢህአዴግ የዚህን ህዝባዊ ተቋም ነፃነትም አይቀበልም የሚል ትችት ይሰነዝርበታል። በ1985 ዓ.ም. በታተመው ‹‹አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግቦች እና ቀጣይ እርምጃዎች›› በሚለው የፓርቲው ዶክመንት ይህን ጉዳይ በተመለከተ ‹‹የኢትዮጵያ ሰራዊት ራሳችንን ከምዕራባውያን ቁጣ ለማዳን ገለልተኛ እንዲመስል መደረግ እንዳለበት ቢገለፅም የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስፈፃሚ መሆኑ ግን የግድ ነው›› ሲል አቋሙን በግልፅ አስቀምጧል።

ከ97 በፊት

ኢህአዴግ ወደ 1997ቱ ምርጫ ሲገባ ‹‹የተሰላ ቁማር›› ለመጫወት ወስኖ እንደነበር የፓርቲው መሪዎች በተከታዮቹ ዓመታት ተናግረዋል። ከዚህ የፓርቲው የስሌት አካሄድ ውጪ ያሉትን የፓርቲውን እና የመንግስታዊ ስርዓቱን ባህሪይ ያጠኑት ፕ/ር ክርስቶፈር ክላፍም ገዢው ፓርቲ ወደ ምርጫው ሲገባ የነበሩትን መንግስታዊ እና ፖለቲካዊ ጉድለቶች “Comments on the Ethiopian crisis” በሚለው ፅሁፋቸው ይተነትናሉ። የመጀመሪያው የአቶ መለስን ለተከታታይ አስራ አራት ዓመታት በስልጣን ላይ መቆየትን ይመለከታል። ራሱን ዴሞክራሲያዊ መሪ አድርጎ ለሚያስብ እና ቢያንስ እስከ ወቅቱ ድረስ የምዕራባውያንን የተራማጅ መሪነት ምስል ለሚናፍቅ መሪ ዓመታቱ ረዥም የሚባሉ ናቸው። የመለስ የስልጣን ቆይታ ከፕ/ት ኢሳያስ፣ ሙጋቤ፣ አልበሽርና ሙሴቬኒ ጋር የተቀራረበ መሆኑ በወቅቱ የነበረውን የአቶ መለስ የዴሞክራሲያዊ መሪነት ስዕል እንዲደበዝዝ አድርጓል። ከዚህ ውጪያዊ ተስዋጭ በዘለለ ይህ የዘመን ርዝመት የፓርቲውን አባላትም ሆኑ ደጋፊዎች በስልቹነት እንዲዋጡ አድርጓል፡ ፡ ሁለተኛው ነጥብ ኢህአዴግ ራሱን እንደ የብሄር ፓርቲዎች ቅንጅት አድርጎ ቢያቀርብም የፓርቲው ወሳኝ አካል ሆኖ የወጣው ህወሓት በአንፃራዊነት በትግራይ ውስጥ ካለው ድጋፍ በስተቀር በሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች ጠንካራ የድጋፍ መሰረት አልነበረውም። ህወሓት እንዳደራጃቸው የሚጠቀሱት ሌሎቹ የኢህአዴግ አባላት እንወክለዋለን በሚሉት ብሔር አካባቢ የነበራቸው የቀዘቀዘ ድጋፍ በወቅቱ ፓርቲውን በጠባብ የድጋፍ መሰረት ላይ እንዲቆም አድርጎታል። ከህወሓት ውጪ የሌሎቹ ፓርቲ አመራሮች በፍጥነት መቀያየር ኢህአዴግን ጠንካራ ፓርቲ ሊያደርገው እንዳልቻለ ፕ/ር ክላፍም ይከራከራሉ። ወደ 97ቱ ምርጫም ሲገባ ይህን ድክመቱን ተሸክሞ እንደነበረም ይጠቅሳሉ።

ገዢው ፓርቲ ካስተዋወቀው ቋንቋ-ተኮር ፌደራሊዝም በተገናኘ የፌደራል ስርዓቱን ተሳላጭነት በሚያደናቅፍ መልኩ ወደ አሃዳዊነት ማዘንበሉ በሁለት አጣብቂኞች ውስጥ እንዳስገባው የሚናገሩት ፕ/ር ክላፍም ይኸም የ97ቱን የምርጫ ሂደት የወሰነ ሶስተኛ ፖለቲካዊ ሁነት እንደሆነ ያወሳሉ። የፌዴራሊዝሙን ቅርፅ ከቀድሞዋ ሶቪየት ህብረት የተኮረጀ አድርገው ያሰቡ ልሂቃን በስርዓቱ ላይ ከፍተኛ ትችት ይሰነዝሩበት የነበረበት ወቅት ነው። በሌላ ጫፍ ፌደራሊዝሙ በአግባቡ አልተተገበረም ብለው የሚያምኑ ብሔርተኞች መብዛት ኢህአዴግን ብቸኛ የፌደራሊዝሙ ተከላካይ እንዲሆን አስገድዶታል። እነዚህ ሁለት የፖለቲካ ስብስቦች በገዢው ፓርቲ የድጋፍ መሰረት መሳሳት ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል። የካምብሪጅ ዩኒቨርስቲው መምህር እንደሚገቱት ፓርቲው ከሚያምንበት ማርክሲስት አስተምህሮ አንፃር ገጠርን ወደ ማልማት ብቻ ማተኮሩ ከተሞችን እንዲዘነጋ አድርጎታል። ይህ አካሄዱም ድህነት በከተሞች እንዲስፋፋ አስተዋጽኦ አድርጓል። ይኸም የከተማ ነዋሪዎች በገዢው ፓርቲ ላይ የነበራቸው ቅሬታ እንዲስፋፋ አግዟል። ከነዚህ የቅድመ 97 ፖለቲካዊ አውዶች በተጨማሪ የ1993ቱ የህወሓት መክፈል በተቃዋሚዎች፣ በደጋፊዎቻቸው እና በራሱ በኢህአዴግ አባላት አተያይ ፓርቲው የሚመራው መንግስት እየደከመ እንደሆነ እንዲያስቡ ገፍቷቸዋል፡ ፡ ከሌሎቹ አባል ፓርቲዎች ይልቅ ጠንካራ ድጋፍ እንደነበረው የሚታሰበው ህወሓት ከክፍፍሉ በኋላ በተከተሉት ዓመታት ትግራይ ተኮሩ የድጋፍ መሰረቱ መበጣጠሱ ለዚህ መንግስታዊ መዋቅሩ ደክሟል ለሚለው አተያይ የመደጋፊያ ጭብጥ ሆኗል።

ከ97 ወዲህ

ከ1997ቱ አስደንጋጭ ሽንፈት በኋላ ኢህአዴግ ሁለት የሀገሪቱን ቀጣይ የፖለቲካ ስርዓት የወሰኑ እርምጃዎችን ወስዷል። የመጀመሪያው የፓርቲው አካሄድ የአባላቱን ቁጥር ማስፋፋት ነበር፡ ፡ በ1997 ዓ.ም. ከነበረው 760,000 የአባላት ቁጥር በ2001 ዓ.ም. እስከተካሄደው የአካባቢ ምርጫ ድረስ ወደ 5 ሚሊዮን አሳድጓል። ገዢው ፓርቲ አባላቱን ለማብዛት የወሰዳቸውን እርምጃዎች ‹‹ካሮት እና ስቲክ›› ብለው የሚጠሩት ፕ/ር ኪጅቴል ቶርኖቭል እና ዶ/ር ሎቪስ አለን በ97ቱ ምርጫ በዋናነት የከተሜ ወጣቶችን ድምፅ ማጣቱን ተከትሎ ወጣቶችን በአነስተኛ እና ጥቃቅን የፓርቲው ማዕቀፍ ስር እንዲደራጁ አድርጓል ሲሉ ይከራከራሉ። በወቅቱ አቶ በረከት ‹‹ከ1997ቱ ምርጫ በኋላ ወጣቱን ማግለል እንደማንችል ተረድተናል›› ማለታቸው የሁለቱ ፀሐፊዎችን ክስ እውነትነት ያስረግጣል። እነ ፕ/ር ቶርኖቭል “The 2008 Ethiopian elections: the return of electoral authoritarianism” በሚለው ፅሁፋቸው ገዢው ፓርቲ ከዚህ ወጣቶችን በስፋት በፓርቲው ስር ከማደራጀት በተጨማሪ የመንግስት ተቋማት ሰራተኞችን በተመለከተ ተቀራራቢ እርምጃ እንደወሰደ ይተነትናሉ። እንደ ፀሐፊዎቹ ፓርቲው እነዚህ ዜጐች የፓርቲውን አባልነት የማይቀበሉ ከሆነ የትምህርት እና የተሻሉ የስራ እድሎችን ከመንፈግ በተጨማሪ ስራ ማጣትን ያካተተ አማራጭ ብቻ እንዳላቸው ለማሳመን መሞከሩ የአባልነት ቁጥሩን ለማስፋት እንደጠቀመው ይከራከራሉ።

ሁለተኛው የፓርቲው አካሄድ የነበርው የአባላት ቁጥሩን ከላይ በተጠቀሰው መልክ ከማብዛቱ ጋር የሚያያዝ ነው። ይኸም በዋናነት የከተማ ቀበሌዎችን መዋቅራዊ ስርዓት በማስፋፋት የሚያስፈልጋቸውን የሰራተኛ ኃይል መጨመር ነበር። ሁለቱ ኖርዊጂያውያን ፀሐፊዎች “The end of democracy” በሚለው ሌላው ጥናታዊ ስራቸው እንደሚሉት በእነዚህ ህዝባዊ ተቋማት ውስጥ ፖለቲካዊ ስራ የሚሰሩትን ዜጐች ቁጥር ከ15 ወደ 300 አሳድጓል። በዚህ ስሌት ፓርቲው ለተከተሉት የአካባቢ እና ብሄራዊ ምርጫዎች እስከ 4 ሚሊዮን እጩዎችን ለማቅረብ አስችሎታል፡ ፡ ተቃዋሚዎች ካሉባቸው ውስጣዊ ድክመቶችና ውጪያዊ ተግዳሮቶች አንፃር ከገዢው ፓርቲ ጋር የሚመጣጠን የአባላትም ሆነ እጩ የማቅረብ እድል ስለማይኖራቸው ኢህአዴግ ብቻውን ህዝባዊ ተቋማቱን መቆጣጠር ችሏል። ከ1997ቱ የተከተለውን እና እነ ዶ/ር ሎቪስ ‹‹በሚገባ ተጭበርብሯል›› ካሉት የአካባቢ ምርጫ በተጨማሪ የ2002ቱን ብሔራዊ ምርጫ ኢህአዴግ በ99.6% አሸናፊነት አጠናቀቀ። ‹‹ቀይ ሽብርን በሚያስታውስ መልኩ ከተካሄደው የድህረ-97ቱ ግድያ እና አፋኝ ህግጋት በኋላ ፓርቲው ሀገሪቱን ወደ አምባገነናዊ ስርዓት እንዲቀይር የሚያችለውን ውጤት ማግኘቱ አያስገርመኝም›› የሚሉት ፕ/ር ቶርኖቬል፣ ገዢው ፓርቲ ከ2002ቱ አሸናፊነት በኋላ እየሄደበት ያለው መንገድ ከሰላማዊ ትግል ውጪ ሌላ የትግል ስልት ለመጠቀም ለወሰኑት የፖለቲካ ቡድኖች በተሻለ አቅም ሊሰጣቸው እንደሚችል “The Ethiopian 2010 elections: re-establishing the one party system” በሚለው ስራቸው አስጠንቅቀዋል።

ፕ/ር ቶርኖቬልን በዚህ መሰል ፀለምተኝነት እንዲዋጡ ያደረጋቸው ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ ኢህአዴግ የወሰዳቸው ሁለት ህግን የታከኩ እርምጃዎች ናቸው። የመጀመሪያው ለሰላማዊ ትግል መሳካትም ሆነ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ወሳኝ እንደሆኑ በሚነገርላቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ላይ የወጣው ‹‹አፋኝ›› ተብሎ የሚወገዘው ህግ ነው። ፓርቲው ገቢያቸውን ከውጪ ያደረጉ ማህበረሰቡን ስለመብቶች እና ዴሞክራሲያዊ እሴቶች በማስተማር የተሰማሩ መያዶችን ‹‹ኪራይ ሰብሳቢዎች ናቸው›› ሲል ‹‹ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ለመገንባት የሚደረግ ትግል›› በሚል ርዕስ በ1999 ዓ.ም. ባወጣው ፅሁፉ ይከሳቸዋል። የኢትዮጵያ ፖለቲካ ዋነኛ ተከታታይ ከሆኑት አንዱ ፕ/ር ቴድሮ ቬስታል የመያዶቹ መፈራረስን ፓርቲው ከሚያቅደው ጠቅላይነት ጋር ያስተሳስሩታል። ‹‹በህገ-መንግስቱ ላይ ምንም ዓይነት ብዙሀነትን የሚቀበሉ አንቀፆች ቢኖሩም የፓርቲው ህልም ሀገሪቱን በብቸኝነት መግዛት ነው›› የሚሉት ፕ/ር ቬስታል “Ethiopia in broader perspective” በሚለው ስራቸው ኢህአዴግ መያዶችን የፖለቲካው ምህዳር እንዲሰፋ በማገዝ የሰላማዊ ትግሉን ሊያነሳሱ እንደሚችሉ ተቋማት እንደሚመለከታቸው ይናገራሉ፡ ፡ የተለያዩ የፓርቲውን ድርሳናት የመረመሩት ፕ/ር ቬስታል ‹‹የተለያዩ ማህበራዊ ተቋማት በነፃነት የሚንቀሳቀሱበትን መድረክ ማመቻቸት ማለት ተፅዕኗችንን አናሳርፍም፤ አባሎቻቸውንም አንመለምልም ማለት አይደለም›› የሚል ሀረግ በ1985 የፓርቲው አንድ እትም ላይ መኖሩን በማስታወስ ኢህአዴግ ለምንም ዓይነት ህጋዊ ነፃ ተቋማትም ሆነ የሰላማዊ ትግል እንቅስቃሴ ትዕግስት እንደሌለው ይከራከራሉ።

ሁለተኛው የነ ቶርኖቬል የስጋት ምንጭ የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጁ እና አተገባበሩ ነው። ይህ አዋጅ በሰላማዊ ትግል ምርጫቸው የሚታወቁትን ፖለቲከኞች እና ነፃ ጋዜጠኞችን ለማሰር መንግስት እያዋለው ነው በሚል ከተለያዩ ተቋማት ትችት ይሰነዘርበታል። በአዋጁ መነሻነት የትግሉ አቀንቃኞች እና ጋዜጠኞች ዕስር አሁን በአደባባዩ ላይ በቀሩት አቻዎቻቸው ላይ እየፈጠረ ያለው አሉታዊ ጫና የሰላማዊ ትግል አማራጭን እያጠበበው እንደመጣ ተንታኞች ይናገራሉ። ብዙዎቹ የአዋጁ ተቺዎች በማሳያነት የሚጠቀሱት ሰላማዊ ሰልፉን በተመለከተ አዋጁ ያስቀመጣቸው የቅጣት ማዕቀፎች ናቸው። የሰላማዊ ትግል አቀንቃኞች እንደሚሉት ህዝባዊ እምቢተኝነት እና የትራፊክ ፍሰትን የመሰሉ ሰላማዊ እንቅስቃሴዎች የትግሉ ዋነኛ አዕማዶች ናቸው። የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጁ እኒህን መሰል እንቅስቃሴዎች አዋጁ እስከ 15 ዓመት የሚያስቀጡ የሽብር እንቅስቃሴዎች አድርጎ ይቆጥራቸዋል።

መውጫ መንገድ አለ?

አሁን ያለው የተቃውሞ ፖለቲካ የትኞቹንም የትግል አማራጮች በመጠቀም እና ባለመጠቀም መሀከል የሚዋልል ይመስላል። አንደኛውን የትግልመንገድ የመረጡት የሌላኛውን አማራጭ ተከታዮች ነባራዊውን የሀገሪቱ የፖለቲካ ባለመረዳት ይከሷቸዋል። ምፀታዊ በሆነ መንገድ የገዢው ፓርቲ ጥብቅ አካሄድ እየፈጠራቸው ያሉት ክስተቶች አንደኛውን መስመር ለመረጡት ፖለቲከኞች የመከራከሪያ እና የማሳመኛ መነሾች እየሆኑ ነው። ዶ/ር መዓምር መናሰማይ በበኩላቸው ገዢው ፓርቲ ሰላማዊ እና ሰላማዊ ያልሆኑ ብሎ የትግል መንገዶችን ለመክፈል መነሻ የሚያደርገው ፓርቲውን ከስልጣን ለማውረድ ከሚኖራቸው የስኬታማነት እድል አንፃር እነደሆነ ይጠቅሳሉ። ዶ/ር መዓምር በፓርቲው እና በተቃውሞ ፖለቲከኞች መሀከል ባንዳ እና ኪንግ ከገዢዎቻቸው ጋር እንደነበራቸው የግራ የሞራል እሴቶች አለመኖር፣ የከተሞች እድገት እና ተያይዘው የሚመጡት ፖለቲካዊ ንቃቶች አለመኖር እና የመሳሰሉት ሁነቶች ሰላማዊ ትግልን እንደ ብቸኛ አማራጭ ለመመልከት አስቸጋሪ እንደሆነ “Ethiopia: whither the democratic opposition?” በሚለው ፅሁፋቸው ይሞግታሉ። ከእርሳቸው ሙግት ጋር በተቀራረበ ኢህአዴግ በ2002 ዓ.ም. የመጋቢት-ሚያዝያ የአዲስ ራዕይ ዕትም ‹‹በዴሞክራሲያዊ ምርጫ መንግስትን ለመመስረት በሚቻልበት አገር በሲቪል ማፈንገጥ (Civil disobedience) የትግል ስልት ተጠቅሞ ስልጣን ለመያዝ የሚደረግ ትግል ዴሞክራሲያዊ አይደለም ከሚለው የፓርቲው መንፈስ በመነሳት ኢህአዴግ ሀገሪቱን አደገኛ ቅርቃር ውስጥ እየከተታትእንደሆነ ይናገራሉ።እኒህ መሰል የስጋት መንፈሶችን የሰላማዊ ትግል ስኬታማ ተግባር የሚባለው የማርቲን ሉተር ኪንግ “Those who make peaceful change impossible, make violent change inevitable” የሚለው ሀይለ-ቃል ሳይወክል አይቀርም።

የእስክንድር ነጋ ቃል



የተከበረው ፍ/ቤት ጥር 15 2004 እኔን 7ኛ ተከሳሽ እስክንድር ነጋን አስመልክቶ የሰጠው ብይን በ3 ይከፈላል፡፡ እነዚህም፡-

1ኛ. የአመፅ ተግባርን ለመፈፀም ከሚንቀሳቀሱ የሀገር ውስጥ ፓርቲ አመራሮች ጋር ስለጉዳዩ ተደጋጋሚ ስብሰባ ያደረግኩ መሆኔን፤

2ኛ. የተከበረው ፍ/ቤት የግንቦት 7 ልሳን ነው ብሎ ለጠረጠረው የኢትዮጵያ ሣተላይት ቴሌቪዥን የተለያዩ መረጃዎች የሰጠኹ መሆኔን፤

3ኛ. ሁከትን የሚቀሰቅሱ ፅሁፎችን የፃፍኩና ያሰራጨኹ መሆኔን የሚያስረዱ መረጃዎች እንደቀረቡብኝ የተከበረው ፍ/ቤት በይኗል፡፡

<u>‹‹የአመፅ ተግባርን ለመፈፀም ከሚንቀሳቀሱ የሀገር ውስጥ ፓርቲ አመራሮች ጋር ስለጉዳዩ ተደጋጋሚ ስብሰባ አድርጓል›› ከተባልኹት ልጀምር</u>

ስብሰባዎቹን ከመቃኘቴ በፊት ግን፣ ስብሰባዎቹ ሲደረጉ አጥሎ ስለነበረው ድባብ ለተከበረው ፍ/ቤት ግንዛቤ ማስጨበጥ የግድ ይላል፡፡ ድባቡ በስብሰባዎቹ ይዘት፣ ዓላማና ግብ ላይ ቀጥተኛ አንድምታና ተፅዕኖ ነበረውና፡፡

ምንም እንኳን እንደ አንድ ለነፃነቱ ትልቅ ዋጋ እንደሚሰጥ ጋዜጠኛ ከመንግሥት ጋር ያለኝ ተቃርኖ ብዙ ዓመታትን ያስቆጠረ ቢሆንም፤ በየካቲት 2003 ዓ.ም. በግብፅ እንደድንገት ስኬት ለመሆን በበቃው ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ህዝባዊ ለውጥ የተደናገጠው የኢትዮጵያ መንግስት ‹‹እርምጃ እንወስድብሃለን›› ብሎ እንዲዝትብኝም ምክንያት ሆነ፡፡ ቀደም ባሉት 4 ሳምንታት፣ ማለትም በወረሃ-ጥር ዓለምን አስደምሞ ስለነበረውና በግብፅ ለተቀጣጠለው ህዝባዊ ተቃውሞ አርአያ የነበረው የቱኒዚያ ዴሞክራሲያዊ ለውጥ በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን አስተያየት ስሰጥና ስተነትን፣ በጋዜጦችና በኢንተርኔት ደግሞ ፅሁፎች ሳቀርብ ሰነባብቼ ነበር፡፡

እውነቱን ለመናገር፣ በአረብ ሀገራት እንዳየነው ዓይነት ፈጣን፣ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሂደት በሀገሬም ማየት እንደምሻ በቀጥታ አልናገር እንጂ፣ ልቤም አእምሮዬም በአዲሱ ክስተት ተሸንፎና ተማርኮ እንደነበር መደበቅ አልሻም፡፡ ከሚያውቀኝ ህዝብና መንግሥትም የተሰወረ አልነበረም፡፡ ማስጠንቀቂያ ያስጠኝም ይህ እውነታ ነበር፡፡ ‹‹ኢትዮጵያ ሰላማዊ የሆነ የዴሞክራሲ ሽግግርና ለውጥ ያስፈልጋታል›› ብዬ ያኔም ሆነ ዛሬ ከልብ አምናለኹ፡፡ ሂደቱን ጠብቆ ለተከበረው ፍርድ ቤት እንደማስረዳውም ይህ እምነት የእኔ ብቻ ሳይሆን የብዙሃኑ ኢትዮጵያዊያንም እንደሆነ በሰላማዊና በህጋዊ መንገድ በተግባር ለማሳየት የጀመርኹት እንቅስቃሴ፣ ውሎ አድሮ ‹‹የማይቀረጠም ባቂላ›› እንዳይሆን በኢህአዴግ በእንጭጩ ተቀጭቶ፣ የህሊና እስረኛ ለመሆን አብቅቶኛል፡፡

ለማንኛውም፣ በወረሃ-የካቲት 2003 ዓ.ም. ፒያሳ ከሚገኝ አንድ የኢንተርኔት ቤት በር ላይ በፌደራል ፖሊስ አባላት ተይዤ በመንግሥት የተሰጠኝን ማስጠንቀቂያ በሚመለከት፣ በወቅቱ ለንባብ አብቅቼው ከነበረው ባለ2 ክፍል መጣጥፍ የመጀመሪያውን ክፍል አቃቤ ህግ ለፍርድ ቤቱ አቅርቦታል፤ ምን እንደሚያስረዳለት ለእኔ ግልፅ ባይሆንም፡፡ ለፍርድ ቤቱም ያስረዳው ነገር የለም፡፡ በእኔ በኩል ግን፣ አሁን ከሳሼ ሆኖ የቆመው መንግሥት ሲዝትብኝና ሲያስፈራራኝ እንደነበር ያረጋግጥልኛል፡፡ ይህን ነው በዚህ ክስ ላይ ያጠላው ድባብ የምለው፡፡ የተመሰረተብኝ ክስ ግልፅ የሆነ መነሻ አለው፡፡

መቋጫው እዚህ ፍ/ቤት አድርሶኛል፡፡ የመጣጥፉ ርዕስ ‹‹ጄኔራል ጻድቃን፣ ኢህአዴግና የሰሜን አፍሪቃ አብዮት›› የሚል ነው፡፡ የተከበረው ፍ/ቤት በአፅንኦት እንዲያነበው አሳስባለኹ፡፡

የተመሰረተብኝ ክስ በሐሰት የተቀነባበረና የበቀል ግብ እንዳለው ግልፅ ቢሆንም፣ የተከበረው ፍ/ቤት ከሀገር ውስጥ ፓርቲ አመራሮች ጋር ስላደረግኳቸው ስብሰባዎች እናድከላከል ባዘዘው መሰረት በክሱ ውስጥ የተካተቱትን 3 ስብሰባዎች በአጭር በአጭሩ እቃኛቸዋለኹ፡፡

<u>1ኛ. በአንድነት ጽ/ቤት ስለተካሄደው ስብሰባ</u>

ነሐሴ 29 2003 ዓ.ም. በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ጽ/ቤት ተደርጎ የነበረውን ህዝባዊ ስብሰባ አቃቤ ህግ ለተከበረው ፍ/ቤት በማስረጃነት አቅርቦታል፡፡ እንደ አቃቤ ሕግ አቀራረብ ከሆነ፣ ስብሰባው በህብዑ የተደረገ፣ የአመፅ ቅስቀሳ የተጧጧፈበትና ተሰብሳቢዎቹ ህገ-ወጥ ተግባር ለመፈፀም ያሴሩበትና የተስማሙበት መድረክ ነበር፡፡

በዚህ ክስ ሂደት አስደማሚ ከነበሩት ክስተቶች መካከል ይህን ህዝባዊ ስብሰባ ‹‹ህብዑ ነበር›› በማለት አቃቤ ህግ የተከራከረው ነው፡፡ እንዳልነበር ግን አሳምሮ ያውቃል፡፡ ምርመራውን ያጣራው ፌደራል ፖሊስ የሚያውቀውን ሐቅ አቃቤ ሕግ አያውቅም ተብሎ ሊጠረጠር አይችልም፡፡

ይጠርጠር ከተባለም የአቃቤ ህግን ሙያዊ ብቃት ጥያቄ ውስጥ የሚከት ከመሆን አያልፍም፡፡ ችግሩ ግን የአቃቤ ህግ ሙያዊ ብቃት አይደለም፡፡ ፖለቲካው ጣልቃ እየገባ ወደማይፈልጉት አቅጣጫ ባይመራቸው ኖሮ፣ አቃቤ ህጋን ማህበረሰባቸውንም ሆነ ሀገራቸውን በብቃት ማገልገል የሚችሉ ናቸው፡፡ ሆኖም፣ በባዶ እጅ ክስ እንዲመሰርቱ ሲገደዱ የሌለን ያለ አስመስለው ከማቅረብ ውጭ አማራጭ የላቸውም፡፡ ይህንን ነው በዚህ ክስ ውስጥ በድግግሞሽ የምንታዘበው፡፡

ለማንኛቸውም፣ ህዝባዊ ስብሰባው ህጋዊ እንደነበር፣ በህብዑ ሳይሆን በሚዲያ ጥሪ ተደርጐ የተከናወነ እንደነበርና ምንም ዓይነት የአመፅ ቅስቀሳ እንዳልተደረገበት በማያሻማ ሁኔታ የሚያስረዱ የፅሁፍና የቪዲዮ ማስረጃዎች ለተከበረው ፍ/ቤት አቅርበናል፡፡ በዚህ ብቻ ግን አላበቃንም፡፡ ከሚያስፈልገው በላይ ቢሆንም፣ ዛሬና ነገ ደግሞ በሰው ማስረጃዎች ይበልጥ እናጠናክራቸዋለን፡፡

የተከበረው ፍ/ቤት ጠንቅቆ እንደሚረዳው፣ መሰብሰብ ህገ-መንግስታዊ መብት ነው፡፡ ከዚያም አልፎ በህገ መንግስታዊ ድንጋጌ እውቅና አገኘም አላገኘም ተፈጥሯዊ መብትም ነው፡፡ እነዚህ እውነታዎች ግን ከምርጫ 97 በኋላ በአብዛኛው ተጥሰው ይገኛሉ፡፡ ኢትዮጵያም የመሰብሰብ መብት በወረቀት ላይ እንጂ በተግባር የማይከበርባት ሀገር ሆናለች፡፡ አንድነት ፓርቲ ባዘጋጀው ስብሰባ ላይ ፅሁፍ እንዳቀርብ ስጋበዝ ምንም ሳላቅማማ የተቀበልኹት፣ ይህ መብት ምንም ሳይሸራረፍ ሊከበር ይገባዋል ብዬ ስለማምን ነው፡፡ ባለኝ አቅም ህዝብ ተሰባስቦ በሰላማዊ መንገድ ስለሀገሩ ጉዳይ እንዲመክር ለማበረታት አስቤ ያደረግኹት ነበር፡፡ ይህ መብት እንዲከበር መታገል ሁሉም ዜጐች ላይ የተጣለ ኃላፊነት ነው፤ ይህንን የተከበረ ፍ/ቤት ጨምሮ፡፡ በዚህም መሰረት የተከበረው ፍ/ቤት በዚህ ስብሰባ ዙሪያ የቀረበውን ፍሬከርሲ ክስ ሁሉ ውድቅ በማድረግ ለዜጐች ተፈጥሯዊና ህገ-መንግስታዊ መብት መከበር የፍርድ ቤቶችን ከለላና ጥበቃ የመስጠት አደራና ኃላፊነት አለበት፡፡ ብይኑን ታሪክና ህዝብ በጉጉት ይጠብቁታል፡፡

<u>2ኛ. ከመኢዴፓ አመራር አባላት ጋር ስላደረግኳቸው ስብሰባዎች</u>

የተመሰረተብኝ ክስ አስቂኝና አዝናኝ ምዕራፍ ደግሞ በአንድ በኩል እኔ፣ በሌላ በኩል መኢዴፓ፣ በሌላው ጫፍ ደግሞ ግንቦት 7 የተሳሰርንበት ልብ-ወለድ ትረካ ነው፡፡ በዚህ ልብ-ወለድ ትረካ ግንቦት 7 በዋና ተዋናይነት መመሪያ አውራጃ ሆኖ ቀርቧል፡፡ ድጋፍ ሰጪ ተዋናያንና መመሪያ ተቀባዮች ደግሞ እኔና መኢዴፓ ሆነን ተስለናል፡፡ አስቂኙ ተግባር፣ ድርሰት ፀሃፊዎቹ ወደ ዝርዝር ትረካቸው ገና ከመግባታቸው መነሻ ሃሳባቸውን አፈራርሰውት ማረፋቸው ነው፡፡

እንደልብ-ወለዱ ትርክት ከሆነ እኔና መኢዴፓ በግንቦት 7 የተሰጠንን ተልዕኮ ለማሳካት መጀመሪያ በአንድነት ጽ/ቤት በተደረገው ህዝባዊ ስብሰባ፣ በቀጣይነት ደግሞ በጣይቱ ሆቴል እየተገናኘን እንመክርና እናሴር ነበር፡፡ ዛሬ በቪዲዮ ማስረጃ ለተከበረው ፍ/ቤት እንደምናሳየው፣ ትራጂ-ኮሜዲው የሚጀምረው አንድነት ጽ/ቤት በተደረገው ህዝባዊ ስብሰባ ላይ ነው፡፡ የግንቦት 7 ወኪልና የመኢዴፓ አመራር አባል ነው የተባለው አበበ ቀስቶ፣ በመስከረም ወር በመስቀል አደባባይ እንዲደረግ በታቀደ ህጋዊ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ተሰብሳቢ እንዲካፈል ጥሪ ያቀርባል፡፡ የስብሰባው ተካፋይ የሆንኹት ሌላኛው የግንቦት 7 ወኪል የተባልኹት እኔ ደግሞ፣ ሰላማዊ ሰልፍ መደረግ የለበትም ብዬ ተቃውሞ በማቅረብ የተሰብሳቢውን ልብ እከፍላለኹ፡፡ አስቂኝም-አዝናኝም ነው፡፡ ወይ ግንቦት ሰባቶች በአስቂኝና አዝናኝ ደረጃ ዝርክርኮች ናቸው፣ ወይ ደግሞ ልብ-ወለድ ትረካው በጀማሪዎች ተቀናብሯል ማለት ነው፡፡

ትራጂ-ኮሜዲው በጣይቱ ሆቴልም ይቀጥላል፡፡ የአቃቤ ህግ ምስክርና የመኢዴፓ መሪ የሆኑት አቶ ዘመኑ ሞላ በዚህ ፍ/ቤት ተገኝተው እንደመሰከሩት፣ በጣይቱ ሆቴል ባደረግነው ውይይት ‹‹ከኢትዮጵያ ውጭ የሚላክ ገንዘብ አትቀበሉ›› ብዬ ምክር ሰጥቻለሁ፡፡ በልብ-ወለዱ ግን ግንቦት 7 ገንዘብ ላኪ ወይም ፋይናንስ ሆኖ ቀርቧል፡፡ እዚያው ጣይቱ ሆቴል መኢዴፓዎች ‹‹ሰልፍ እናደርጋለን›› ሲሉ፣ እኔ ‹‹ተው›› እላላኹ፡፡ በዚህ አስቂኝ ትረካ፣ ግንቦት 7 በአንድ እጁ የሚገነባውን በሌላኛው እጁ ያፈርሳል፡፡ በእንደዚህ ዓይነት አስቂኝ ድራማ የተጠመደ ድርጅት የልጆች እንጂ ፊፅሞ የአዋቂዎች ስብስብ ሊሆን አይችልም፡፡ በፀረ-ሽብርተኝነትም ለመከሰስ ብቃት የለውም፡፡ ይሄ ጉድ ተይዞ ነው የተከበረው ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ እንዲያስተላልፍብኝ የሚጠብቀው፡፡

<u>3ኛ. በመቋቋም ላይ የነበረው የሲቪክ ተቋም</u>

ብዙሃኑ ኢትዮጵያዊያን ሰላማዊ ለውጥ እንደሚፈልጉ በተግባር መታየት አለበት ብለን የምናምን 7 ኢትዮጵያዊያን ተሰባስበን ኮሚቴ አቋቁመን ነበር፡፡ ህቡዕ ድርጅት የተቋቋመ በማስመሰል የዚህን ኮሚቴ አንድ ቃል-ጉባዔ አቃቤ ህግ በማስረጃነት አቅርቦታል፡፡ ይህ ኮሚቴ በሰላማዊና በህጋዊ መንገድ ብቻ የሚንቀሳቀስ እንዲሆን በመስማማት ቃል-ጉባኤ ይዘን በመፈራረም ይፋዊ እንቅስቃሴ ለመጀመር ተዘጋጅተን ነበር፡፡ ይህን የሚገልፀው ቃል-ጉባዔ ለፍርድ ቤቱ አይቅረብ እንጂ፣ መኖሪያ ቤቴ ውስጥ በፍተሻ ተገኝቶ በኤግዚብትነት ተመዝግቦ በፖሊስ እጅ ይገኛል፡፡ ቃል-ጉባዔው በሁለት ኦርጅናሎች ተዘጋጅቶ የተቀመጠ በመሆኑም፣ ሁለተኛውን ኮፒ ለተከበረው ፍ/ቤት በፅሁፍ ማስረጃነት አቅርበናል፡፡ ኮሚቴው ፍፁም ህጋዊና ሰላማዊ መሆኑን መንግሥት በመተማመኑም ከእኔ ውጭ ያሉት አባላት ለእስር አልተዳደረጉም፡፡ ከስድስቱ መካከል 2ቱ ዛሬ በሰው ማስረጃነት ቀርበው የነበረውን ሂደት ለተከበረው ፍርድ ቤት ያስረዳሉ፡፡

እዚህ ላይ ቢሆንም፣ አቃቤ ህግ የሌለን ነገር ያለ አስመስሎ ለማቅረብ የተገደደው፣ ‹‹የተቸገረ እርጉዝ ያገባል›› እንዳሉት፣ በእጁ ላይ ምንም ተጨባጭ ማስረጃ ስለሌለ መሆኑን ፍ/ቤቱ ልብ ሊለው ይገባል፡፡

<u>4ኛ. ከኢትዮጵያ ሣተላይት ቴሌቪዥን ጋር አለህ ስለተባልኹት ግንኙነት</u>

የተከበረው ፍርድ ቤት በሰጠው ብይን፣ የግንቦት 7 ልሣን ነው ብሎ ለጠረጠረው ኢሣት የተለያዩ መረጃዎችን መስጠቴን በአቃቤ ህግ ማስረጃ መረጋገጡን አትቷል፡፡ አቃቤ ህግ ባቀረባቸው ማስረጃዎች ውስጥ ግን አንድም ቦታ ላይ እኔና ኢሣት ቴሌቪዥንን የሚያገናኝ ማስረጃ ማቅረቡን አልገለፀም፡፡ በሌላ በኩል ግን፣ ከኢሣት ሬዲዮ ጋር ቃል-ምልልስ አድርጓል በሚል ከአበበ በለው ጋር ያደረግሁት ቃለምልልስ በማስረጃነት ቀርቧል፡፡ የተከበረው ፍ/ቤት ለኢሣት ቴሌቪዥን የተለያዩ መረጃዎች እንደሰጠሁ አድርጐ የተረዳው፣ የኢሣት የቦርድ አባል ከሆነው አበባ በለው ጋር ያደረግሁትን የተለያዩ ቃል-ምልልሶች አጣቅሶ ነው ብዬ እገምታለሁ፡፡

ኢሣት በቀጥታ የግንቦት 7 ልሣን ነው ተብሎ መገመቱ ስህተት ነው ብዬ አምናለኹ፡፡ ይህንን ስል፣ የግንቦት 7 አባላት በኢሣት ዝግጅት ክፍልም ሆነ በቦርድ አባላት የሉም ብዬ መከራከሬ አይደለም፤ እንዳሉ አውቃለሁ፡፡ ብዙሃኑ የኢሣት ዝግጅት ክፍልና ቦርድ አባላት ግን የግንቦት 7 አባላት እንዳልሆኑ ጠንካራ እምነት አለኝ፡፡ ለምሳሌ ከቦርድ አባላቱ መካከል በግል የማውቃቸውና የማከብራቸው ወዳጆቼ ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማርያም፣ ታማኝ በየነ፣ አበበ ገላው፣ አበበ በለው፣ ሉሊት መስፍንና ለጊዜው የማላስታውሳቸው ሌሎችም የግንቦት 7 አባላት እንዳልሆኑ አውቃለሁ፣ እመሰክራለኹም፡፡ ከሙህራዊ ብቃታቸውና Integrity አኳያም ግንቦት ሰባትም ሆነ ሌላ ማንኛቸውም ድርጅት ከኋላ ሆኖ በዘፈቀደ የሚያሽከረክራቸውና የሚጠመዝዛቸው ሰዎች አይደሉም፡፡

ግንቦት 7 የተባለው ድርጅት ‹‹የግንቦት 7 ድምጽ›› የሚባል ልሣን አለው፡፡ በኢንተርኔት የሚሠራጭ ጋዜጣ ነው፡፡ ‹‹የግንቦት 7 ድምፅ›› የሚባልም ሬዲዮ ጣቢያ አለው፡፡ ከሬዲዮና ከጋዜጣው ባሻገር ቴሌቪዥን ካለውም ‹‹የግንቦት 7 ድምፅ›› ብሎ የማይሰይምበት ምክንያት አይታየኝም፡፡ እንዲያውም፣ ነገሮቹ የፖለቲካ ድርጅቶች ባላደረጉት ደረጃ አዲስ የተቋቋመው ግንቦት 7 የቴሌቪዥን ጣቢያ ባለቤት ለመሆን ከበቃ፣ ግርማ ሞገሱንም ሆነ ተሰሚነቱን የሚያጐላለት በመሆኑ እንዲታወቅለት እንጂ እንዳይታወቅበት የሚፈልግበት ምክንያት ግልፅ አይደለም፡፡

ለማንኛቸውም፣ ለተከበረው ፍ/ቤት ግንዛቤ የኢሣትን ቻርተር በፅሁፍ ማስረጃነት አያይዘነዋል፡፡ ቻርተሩ እንደሚገልፀው ከሆነ፣ ቴሌቪዥን ጣቢያው ከማንኛቸውም የፖለቲካ ድርጅት ጋር ያልወገነ ነፃ ተቋም ነው፡፡

በዚህ ክስ ውስጥ እስከተገለፀበት ጊዜ ድረስ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ኢሣት የግንቦት 7 ልሣን መሆኑን አንድም ጊዜ ተናግሮ አያውቅም፡፡ በዚህም ሳቢያ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ በህጋዊና በሰላማዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች፣ ጋዜጠኞችና ሙህራን ከኢሣት ጋር ተደጋጋሚ ቃለ-ምልልሶች እንዳደረጉ ሀገር የሚያውቀው ሐቅ በመሆኑ፣ ማስረጃ ማቅረብ የሚያስፈልገኝ አይመስለኝም፡፡ የተከበረው ፍ/ቤት በjudicial notice ግምት ውስጥ ሊያስገባው ይችላል፡፡ ፍሬ ነገሩ፣ ከኢሣት ቴሌቪዥን ጋር ቃለ-መጠይቅ ማድረግ ከግንቦት 7 ጋር መወገን ወይም ማሴር ነበር ብሎ መደምደም የሚቻልበት Context አልነበረም፡፡ ይህን ስል ግን፣ በኢሣት ውስጥ ያሉት የፖለቲካ ድርጅት አባላት ሚና ሊያሳስበን አይገባም ማለት አይደለም፡፡ ኢሣት ነፃ ተቋም ነኝ እስካለ ድረስ፣ ሊያነጋግረንም ሊያሳስበንም ይገባል፡፡ የውይይት መድረኩ ግን ከቶ ፍርድ ቤቶች ሊሆኑ አይገባም፡፡

በመጨረሻም፣ ከአበበ በለው ጋር ስላለኝ ግንኙነት ልናገር፡፡ ሰሞኑን በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ቐሺ ገብሩ በሚል ርዕስ የተላለፈ ዶክመንተሪ ፊልም ነበር፡፡ ዋና ማጠንጠኛ የሆነችው ታጋይ በደርግ እጅ ወድቃ ቃለ-ምልልስ ሲደረግላት፣ ‹‹የመንግሥትን ሬዲዮ እንዳናምን ያደረገን የትግራይ ገበሬ በሕወሓት እየተገደደ ለጦርነት ይማገዳል የምትሉት ነው›› ብላ ነበር፡፡ መላ የትግሬ ገበሬ እውነት አለመሆኑን ያውቅ ነበርና፡፡ በተመሳሳይ መንገድም፣ በዚህ ክስ አበበ በለው፣ አበበ ገላው፣ አባንግ ሜቶን የመሳሰሉ ታዋቂ ግለሰቦች የግቦት 7 አመራር አባላት ናቸው ተብለው መፈረጃቸው በዲያስፖራውና በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ክሱን፣ ሂደቱንና በአጠቃላይ የኢትዮጵያን ፍትህ ሥርዓት ተአማኒነት የሚያሳጣ ነው፡፡ እንዳልሆኑ ቢያንስ ቢያንስ መላው ዲያስፖራ ያውቃልና፡፡ ከአበበ በለው ጋር ያደረግኳቸው ቃለ-ምልልሶች ሙሉ ዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ ባለ የኤፍ ኤም (በእነሱ ኤ.ኤም) ሬዲዮ ጣቢያ ላይ የተላለፈ ነው፡፡ በሬዲዮ ጣቢያው የሚተላለፈው የአማርኛ ቋንቋ ፕሮግራም ግንቦት ሰባትም ሆነ ኢሣት ከመቋቋማቸው በፊት የነበረ ነው፡፡ መንግስትም ጠንቅቆ የሚያውቀው ጉዳይ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱን ሆን ተብሎ ለማሳሳት እየተሞከረ የሚገኘው፣ ለቀረበብኝ የፈጠራ ክስ ተጨባጭ ማስረጃ ማቅረብ ስለማይቻል ብቻ መሆኑን ለተከበረው ፍ/ቤትም ሆነ ለማንኛውም ገለልተኛ ተመልካች ሊሰወር አይችልም፡፡

5ኛ. ሁከትን የሚቀሰቅሱ ጽሁፎችን የፃፈና ያሰራጨ ስለተባልኹት

አቃቤ ህግ ያቀረበብኝ የፅሁፍ ማስረጃዎች ሲቃኙ፣ በጋዜጣና በኢንተርኔት የወጡ 6 መጣጥፎች፣ በሀገር ውስጥ ከሚታተሙ ጋዜጦች ጋር ያደረግኳቸው 2 ቃለ-ምልልሶች፣ በአሜሪካ፣ በካናዳና በስዊድን ሀገራት ካሉ ሬዲዮ ጣቢያዎችና ፓልቶኮች ጋር ያደረግኳቸው ቃለ-ምልልሶች ተካተዋል፡፡ በተጨማሪም እንዴት እንደሚመለከተኝ ግልፅ ባይሆንልኝም፣ ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ በስዊድን ሀገር ያደረጉት ንግግርና ይልማ በቀለ የተባሉ ኢትዮጵያዊ ምሁር ያወጡት አንድ መጣጥፍም በማስረጃነት ተቆጥረውብኛል፡፡

እነዚህን ሁሉ በዝርዝር መቃኘት አስፈላጊ ነው የሚል እምነት የለኝም፡፡ ሆኖም፣ For the record በስሜ የወጡት መጣጥፎችና የሰጠኋቸው ቃለ-ምልልሶች የእኔ የሆኑና እስካሁን ድረስ ያለምንም ማሻሻያና መሸራረፍ ሙሉ ለሙሉ የማምንባቸው ናቸው፡፡ ዓላማቸው ብጥብጥ ማስነሳት አልነበረም፡፡ በሀገራችን የህልውና ጉዳይ የሆነውን ሰላማዊ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር እንዲኖር የሚመክሩ፣ የሚማፀኑ፣ የሚገስፁ፣ የሚለምኑና መንገዱን የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ የአውራ ፓርቲ ግንባታ ሙከራ በሀገሪቷ አንድነት ቁማር መጫወት ነው፡፡ እንደአንድ ለሀገሩና ለህዝቡ የሚቆረቆር ዜጋና ጋዜጠኛ ድምፄን የማሰማት ኃላፊነት ነበረብኝ፤ ኃላፊነቴንም ተወጥቻለኹ፡፡ ከዚህ በኋላ ከእኔ የሚጠበቀው የምከፍለው ዋጋ ካለ በፀጋ መቀበል ብቻ ነው፡፡

ሰላም፣ ዴሞክራሲ፣ አንድነትና ፍቅር ለሀገሬና ለህዝቧ እመኛለሁ፡፡

አመሰግናለሁ፡፡

ኢትዮጵያ፡- አንድ እግሯ ሱዳን፣ አንድ እግሯ ሶማሊያ



በሙሉነህ አያሌው
muleayalew@yahoo.com

በዘንድሮው ግማሽ አመት አጠቃላይ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በተለይም የሚንስትሮች መስሪያ ቤት የስራ አፈፃፀም ዳሰሳ እናድርግ ቢባል እስከአሁን ባለው የውጭ ጉዳይ ሚንስቴርን መ የሚስተካከለው አናገኝም። ከሚንስቴር መስሪያ ቤቱ ዋና ኃላፊ ጀምሮ በሚንስትር ዴኤታ ማዕረግ ያሉት ግለሰቦች ስማቸው ለመገናኛ ብዙሃን ቅርብ እንደነበር መጥቀስ ይቻላል። የውጭ ጉዳይ ሚንስትሩን አቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝን ጨምሮ አቶ ዲና መፍቲና፣ አቶ ብርሃነ ገ/ክርስቶስ ጉልህ ድርሻ ነበራቸው። በተለይ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ይህ መስሪያ ቤት በምስራቅ አፍሪካ ባሉ አገራት ላይ እየተወጣ ያለው ወሳኝ ሚና ቀላል የሚባል አይደለም።

በታሪክም ይሁን በፖለቲካ መስተጋብር ኢትዮጵያ በምስራቅ አፍሪካ አገራት ላይ ያላት የበላይነት የዛሬ አይደለም። የነበረ የፖሊሲ መመሪያ ነው።ይህ እውነታ ግን ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ለውጭ አገራት ሰላምና መረጋጋት የምንሰጠው ትኩረት በመጨመሩ ምክንያት የውስጥ ችግሮቻችንን ወደ መዘንጋቱ እንድናዘነብል አድርጐናል። ለዚህም ማሳያ የሚሆነን በግማሽ አመት ውስጥ ስለሁለቱ መስሪያ ቤቶች የስራ ሪፖርት (የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚንስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚንስትር) እንቅስቃሴ በንፅፅር ብናይ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚንስቴር የሚባል ሁሉ ያለ እስከማይመስለን ድረስ የምናገኘው ውጤት የትየለሌ ነው።

የቀጠናው አለመረጋጋት

የምስራቅ አፍሪካ በተለይም የአፍሪካ ቀንድ እየተባለ የሚጠራው አካባቢ በአለማችን ከሚገኙ ክልሎች ያልተረጋጋ እና ሰላም የራቀው እየተባለ የሚጠራ ሲሆን በተለይም ረሀብ፣ ሽብር፣ የእርስ በርስ ጦርነት፣ ስደት፣አክራሪነት... አይነተኛ መገለጫው ናቸው።

በተለይ ቀጠናውን አደጋ ውስጥ ይከተዋል እየተባለ የሚሰጋው እና በተደጋጋሚም ላለመረጋጋቱ ምክንያት የሆነው የቀጠናው አገራት የተረጋጋ መንግስት አልባነት የፈጠራቸው የሽብርተኝነት አደጋዎች እና ይህንንም ተከትሎ የተፈጠሩት ፅንፈኛ ቡድኖች የሚያደርሱት የጥፋት ተልዕኮ ስጋት ወደተቀሩት የጎረቤት አገራት መዛመዳቸው ተጠቃሽ ነው። ይህን ችግር ከስሩ ለማወቅ በዋናነት በአካባቢው የሚገኙ አገራትን ባህሪ ማየት ተገቢ ነው። በዚህ ረገድ ፖለቲካ ተንታኞች አገራቱን በሁለት ከፍለን ልናያቸው እንደምንችል ያትታሉ።

የመጀመሪያው ረድፍ ላይ የሚቀመጡት በምስራቅ አፍሪካ የሚገኙ አንዳንድ አገራት ሆን ብለው ታጣቂ ቡድኖችን የሚደግፉ፣ መረጃ የሚሰጡ፣ የተለያዩ ማቴሪያሎችን የሚያቀብሉ፣ የአገራቸውን መሬት ሁሉ ለልምምድ በመፍቀድ እገዛ የሚያደርጉ ናቸው። እነዚህ አገራት ለሽብርተኛ ሀጋዊ እውቅና እና ፍቃድ የሚሰጡ (Enabler state) ሲሆኑ በዚህ ረገድ ሱዳን እና ኤርትራ ተጠቃሽ ናቸው። እንደዚህ አይነት አገራት ከሚያከናውኗቸው ድርጊቶች ይታቀቡ ዘንድ በተደጋጋሚ የዲፕሎማሲያዊ ጫና የተደረገባቸው ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም የወታደራዊ እርምጃ በሁለተኛ አማራጭነት ይቀመጥላቸዋል።

በሁለተኛው ረድፍ ላይ የሚቀመጡ የምስራቅ አፍሪካ አገራት ችልተኛ አገር እየተባሉ የሚጠሩ ሲሆን በተለይ አገራቱ በውስጥ ባሏቸው የላሉ ህግጋት ወይም አነስተኛ የማስፈፀም አቅም ምክንያት ሽብርተኛ ቡድኖቹ /አልያም ታጣቂ ቡድኖቹ አገሪቱ ውስጥ በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ፣ የጦር-መሳሪያ እንዲያዘዋውሩ፣ ልምምድ እንዲያደርጉ ከማስቻሉም በላይ አንዳችም የህግ ክልከላ ስለማይጣልባቸው ከመጀመሪያው በበለጠ እንዲጠነክሩ እና አደገኝነታቸው ጐልቶ እንዲወጣ ያደርገዋል።

ስለዚህ በአለም አቀፍ ሰላምና ደህንነት (Peace and security) መርህ መሰረት እንደዚህ አይነት አደጋዎችን ለመከላከል ብሎም ለማስቀረት ከጐረቤት የሚመረጡ አገራት፤ በወታደራዊ ይሁን በተለያዩ መስፈርቶች ጠንካራ ናቸው ተብሎ የሚታመንባቸው አገራት ናቸው። አሁን ካለው የቀጠናው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር እንደነ ሱዳን፣ ኤርትራ እና ሶማሊያ ባሉ አገራት መነሻቸውን አድርገው አካባቢውን ያውካሉ ለተባሉ አገራት መፍትሄ ናት የምትባለው ኢትዮጵያ ነች።

ለምን ኢትዮጵያ?

ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ያለመረጋጋት ምክንያት ናቸው የሚያስብሉትን መስፈርቶች ከወሰድን የአፍሪካ ቀንድ አስቸጋሪ የሚባል አይነት የፖለቲካ ማዕቀፍ ውስጥ የሚገኝ ክልል ነው። እነዚህ ሁሉ ችግሮች የሁሉም የቀጣናው አገራት የጋራ መታወቂያቸው ቢሆንም አሁን ካለው ወቅታዊ የፖለቲካ አጀንዳ አንፃር ‹‹ሽብርተኝነት›› ልዩ ትኩረትን በመሳቡ የኢትዮጵያ ሚና ከሌሎቹ ጐልቶ እንዲወጣ አስችሎታል።

ኢትዮጵያ ይህንን ከባቢያዊ አደጋ መታደግ ትችላለች ከሚለው ተጠቃሽ ከሆኑት ምክንያቶች መካከል ጥቂቶች የሚከተሉት ናቸው

ድንበር መጋራት፡- ኢትዮጵያ በምስራቅ አፍሪካ ከሚገኙ አገራት ጋር ከሁሉም ማለት ይቻላል በድንበር ትዋሰናለች። ኬንያ፣ኤርትራ፣ ሱዳን፣ ጅቡቲ፣ ሶማሊያ፣ ደቡብ ሱዳን፣ ሶማሊላንድ፣ ለዚህ ማሳያ ናቸው። ስለዚህ ኢትዮጵያ ከእነዚህ ሁሉ አገራት ጋር ድንበር የመዋሰኗ ምክንያት፣ በየአገራቱ በሚፈጠሩ ማናቸውም ግጭቶች ትኩሳቱ ይደርሳታል። ስለዚህ የእነዚህ አገራት መረጋጋት በተዘዋዋሪም የኢትዮጵያ መረጋጋት ስለሚሆን ኃላፊነቱን ከመረከብ የውዴታ ግዴታ ይሆንበታል፡

የህዝቦች መጋራት፡- ኢትዮጵያ ከላይ ከጠቀስኳቸው አገራት ጋር በመሬት ድንበር ብቻም ሳይሆን በህዝቦችም የጋራ አንድነት ትጋራቸዋለች፡ ፡ በዚህ አካባቢ በሚገኙ አገራት ውስጥ በሚኖሩ ማህበረሰቦች አንድም በኢትዮጵያ የድንበር ከተሞች አካባቢ መገኘታቸው ጥምረቱን ያጠነክረዋል። ለምሳሌ ያህል አፋሮችን (በኢትዮጵያ፣ በኤርትራ፣ በሶማሊያ፣ በጅቡቲ)፣ ኑዌር እና አኙዋክቾን (በኢትዮጵያና በደቡብ ሱዳን)፣ በደቡብ ኦሞ የሚገኙ ህዝቦችን (በኢትዮጵያ እና ኬንያ)፣ ትግርኛ ተናጋሪዎችን (በኢትዮጵያ እና ኤርትራ) አጣምሬ በመያዟ የችግሩ ተያያዥነትን ያጐላዋል። የውዴታ ግዴታው የሚመነጨው ከዚህ በመነሳት ነው።

የተፈጥሮ ኃብት፡- በአሁኑ ጊዜ አለም በታዳሽ የኃይል ምንጭ ላይ እያደረገው ያለው ሰፊ ትኩረት (ከአካባቢያዊ ጥበቃ አንፃር እና ዋጋ አንፃር) ለቀድሞው የኃይል ምንጭ ነዳጅ (አሁንም በጣም ወሳኝ ቢሆንም) እየተሰጠ ያለው ትኩረት እየቀነሰ መጥቷል። ከዚህ አንፃር በቀጣዮቹ ጊዜያት ኢትዮጵያ በውስጧ ባዘለቻቸው የተለያዩ የውሃ ምንጮች ምክንያት እና ከዚህ ጋር አያይዛ የምታጐለብታቸው የኃይል አቅርቦቶች በጐረቤት አገራት ዘንድ ተጠባቂ እንድትሆን አድርጓታል፡ ፡ ከዚህ አንፃር የሃይድሮ ኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ የቀጠናውን አገራት የኃይል ሚዛን ወደ ኢትዮጵያ እንዲያዘነብል ረድቶታል።

ከዚህ በተጨማሪም በህዝብ ብዛት ቀዳሚነት፣ የቆዳ ስፋት፣ ወታደራዊ ኃይል የበላይነት፣ የተረጋጋ ፖለቲካ ስርዓት (አንፃራዊ ቢሆንም) የመሳሰሉት ሁነቶች ኢትዮጵያን በቀጠናው የኃይል ሚዛን ላይ ሰፊውን ድርሻ እንድትይዝ አስችሏታል። ለዚህም ነው አገራችን በተ.መ.ድ፣ በአፍሪካ ህብረትና በኢጋድ የሚወሰኑ የተለያዩ የሰላም ማስከበር ተልዕኮዎች ኃላፊነቱን እንድትወጣ ቅድሚያ እየተሰጣት ያለው።

ኢትዮጵያ ለቀጠናው ወሳይ አገር ተደርጋ መቀመጧ ከተለያዩ መለኪያዎች አንፃር ተጠቃሚ እንድትሆን እንዳደረጋት ቢታመንም ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር የውጭው የተጠናከረ የፖሊሲ ተልዕኮ የውስጡን ፖለቲካ በእጅጉ በመዘንጋቱ እና ሁለቱን ተመጋጋቢ በሆነ መልኩ መመጣጠን አለመቻሉ አደጋ ነው።

እነዚህ የሰላም ተልዕኮዎች ለአገራችን የገንዘብ ድጋፍ ማስገኘት፣ ተሰሚነት መጨመር፣ የኃይል ሚዛንን መድፋት፣ በተዘዋዋሪ የውስጥ ደህንነት ከማስጠበቅ ፖሊሲ አንፃር የምናገኛቸው ትሩፋቶች መሆናቸውን መካድ አንችልም። ከዚህ በተቃራኒ የነዚህ ሰላም ማስከበር ተሳትፎዎች ጐትተው ይዘዋቸው የሚመጧቸው የተለያዩ መዘዞች መኖራቸውንም አስቀምጠን ልንፈትሽ ይገባል። አገራችን ባልተረጋጋው ማህበረሰብ እና ፖለቲካ ከባቢ የምታካሂዳቸው ጣልቃ ገብነቶች አንድም በዚህ ረገድ በአገራቱ ከሚገኙ ማህበረሰቦች ከሚደርስባት የጥላቻ መንፈሶች የሚወለዱ የበቀል እርምጃዎች፣ በሌላም በኩል የሌሎች ታጣቂ ቡድኖች መገልገያ መሳሪያ በመሆን የሚያደርሱት የሽብር ጥቃት በአሉታዊ ጐናቸው ሊታዩ የሚገቧቸው እውነታዎች ናቸው።

የተልዕኮዎቹ ይዘት

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከተቋቋመ ጊዜ አንስቶ ኢትዮጵያ በተለያዩ የአለም አገራት ወደ አስር በሚጠጉ የሰላም ማስከበር ተልዕኮዎች ላይ ተሳትፋለች፣ እየተሳተፈችም ትገኛለች።

በ1940ዎቹ እና በ1950ዎቹ አካባቢ በኮሪያ እና በኮንጎ የተጀመረው የሰላም ማስከበር ሂደት ቀጥሎ በቅርቡም በሩዋንዳ፣ በላይቤሪያ፣ በብሩንዲ፣ በዳርፉር ያደረገቻቸው ተልዕኮዎች እና ያስመዘገበቸው ውጤት በሁሉም ዘንድ ተአማኒነትን እንድታተርፍ አስችሏታል። በአሁኑ ወቅትም የኢትዮጵያ ጦር ሰራዊት ለሁለት የተለያዩ ተልዕኮዎች በሱዳን እና በሶማሊያ ውስጥ ይገኛል፡ ፡ ተልዕኮውንም በአግባቡ እየተወጣ እንደሚገኝ በቦታው ሆነው የዘገቡ የተለያዩ የሚዲያ ተቋማትን በዋቢነት መጥቀስ እንችላለን።

አሁን ባለው መረጃ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ውሳኔ ኢትዮጵያ ከ7000 በላይ የሚሆነው የጦር ኃይሏ በተለያዩ አገራት የሰላም ማስከበር ተልዕኮዎች ላይ ተሳትፎ እያደረገ ይገኛል። ይህ ማለት ኢትዮጵያ በአለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ የጦር ኃይል ከሚያዋጡ አምስት አገራት አንዷ እንድትሆን አስችሏታል።

እነዚህን እንደ ተጨባጭ እውነታዎች ወስደን በጥቅሉ የኢትዮጵያ መንግስት ወታደሮች በጐረቤት አገራት ላይ እየወሰዳቸው ያለውን ወታደራዊ ተልዕኮ በሁለት ከፍለን ልናየቸው እንችላለን። የመጀመሪያው በሱዳን እየተደረገ ያለውን ተልእኮ በመጥቀስ ቀጥሎም የሶማሊያን ተሞክሮ በማንሳት።

የኢትዮጵያ መንግስት ወታደሮች በደቡብ እና ሰሜን ሱዳን መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት እልባት ለመስጠት ከሚያስችሉ የውሳኔ ሀሳቦች መካከል የኢትዮጵያ ጦር አንገብጋቢ ወደተባለችው የአቢዬ ግዛት ዘልቆ መግባት እና የውሳኔ ሀሳብ እስኪሰጥ ድረስ አካባቢውን ከጦርነት ስጋት ማላቀቅ የሚለው ሲሆን ይህ የሰላም ማስከበር ተልዕኮ የሁሉንም ወገኖች ይሁኝታ ያገኘ እርምጃ ብለን ልንፈርጀው እንችላለን።

ከዚህ ሌላ የኢትዮጵያ መንግስት በሶማሊያ እያደረገ ያለውን ተሳትፎ በሌላኛው ደርዝ መመልከት ያስችለናል። አንደኛ ጦሩ በሶማሊያ እየተንቀሳቀሰ የሚገኙትን የተለያዩ ታጣቂ ቡድኖች ይሁኝታ ያገኘ አለመሆኑ እና ወደ ቀጠናውም ዘልቆ የገባው የአንዱን ወገን ፍላጐት ለማሟላት የሚለውን ትርጉም ብቻ ይይዛል። ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያ ጦር በሶማሊያ የሚያደርገው ተልእኮ ልክ ከጦርነት ምዕራፍ የተላቀቀች አገርን የመርዳት ያህል ሳይሆን ቀጥተኛ ጦርነት ውስጥ የገባበት በመሆኑ ሂደቱን ከሱዳን ለየት ያደርገዋል። ይህንን ተልዕኮ የፖለቲካ ተንታኞቹ ‹‹ጣልቃ ገብነት›› ይሉታል።

ከላይ በንዕዕር ባቀረብኳቸው ሁለቱ የተልዕኮ ልዩነቶች በኢትዮጵያ ጦር ላይ የሚደርሰውንም የአደጋ ስጋት ልዩነት እንደሚኖረው መታዘብ እንችላለን። አሁን ካለው እና በቀጣይ ከሚኖረው ስጋት አንፃር የኢትዮጵያ ወታደር በአገራቱ እያከናወነው ያለው ሂደት በንዕረት እንመልከት

Meles-Mbeki factor

የአፍሪካ ህብረት በተደጋጋሚ በሚወስዳቸው የውሳኔ ኃሳቦች ላይ ተንታኞች በአመዛኙ ወደ አንድ ጥልቅ ነጥብ መምጣት እንችላለን ይላሉ። በህብረቱ ትልቅ ተሰሚነትን እያገኙ ካሉት ግለሰቦች መካከል የቀድሞው የደቡብ አፍሪካው ፕሬዘዳንት ምቤኪ እና ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ ሁለቱ ግለሰቦች በሚያራምዷቸው ተቀራራቢ የውሳኔ አቋም ምክንያት በሚወሰኑ ውሳኔዎች ላይ በጋራ የመደጋገፍ ባህሪ ይታይባቸዋል። ይህንንም ሂደት የ‹መለስ-ምቤኪ› ጥምረት ይሉታል።

ለዚህ በዋቢነት የሚጠቀሰው የቀድሞው የሊቢያ ፕሬዘዳንት ሞአመር ጋዳፊ ላይ ሊወሰድ የነበረውን እርምጃ የተከላከሉበትን መንገድ በመጥቀስ ነው። በጊዜው አብዛኛው የአፍሪካ ህብረት ልዑካን ከውጭ በሚደረስባቸው ጫና እና ጋዳፊ በህዝቡ ላይ እየወሰደ ከሚገኘው ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት አንፃር መመታት አለበት የሚለው አቋም ቢደግፉም፣ የእነዚህ ሁለቱ ግለሰቦች ይሁኝታ ማግኘት ባለመቻሉ ሳይሳካ ቀርቷል ይላሉ። የሁለቱ ጥምረት እና መናበብ ዳግም የደቡብ ሱዳን እና የሰሜን ሱዳን መንግስታትን ለማስማማት የተደረሰው ስምምነት ላይ እናገኛቸዋለን።

ጉዞ ወደ አቢዬ

ካለፈው አመት ጀምሮ በሱዳን እና በደቡብ ሱዳን መካከል በተለያዩ ወቅቶች አካባቢውን ወደለየለት የጦር አውድማ ሊከቱ የሚችሉ የተለያዩ ግጭቶችን አስተናግዷል። በተለይ በአካባቢው በነዳጅ በልፅገዋል በሚባሉት በሁለቱ ግዛቶች በአቢዬ እና ደቡብ ኮርዶፋን ለዚህ ግጭት መባባስ እንደምክንያትነት ከሚጠቀሱ በርካታ ነገሮች መካከል የሰሜኑ ሱዳን መንግስት በአብዬ ግዛት ላይ በተደጋጋሚ እየወሰዳቸው ያሉ ወረራዎች እና ጥቃቶች ናቸው። ለዚህም ባለፈው አመት እ.ኤ.አ በግንቦት 2011 የደረሰውን ወረራ መጥቀስ ይቻላል፡ ፡

ይህን ግጭት በተከናወነ ባወሩ በቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንት ታቦ ምቤኪ አደራዳሪነት ሁለቱ መንግስታት እዚሁ አዲስ አበባ ላይ በአብዬ ግዛት ዙሪያ ሰላም የሚሰፍንባቸውን መንገዶች አንስተው ተወያይተዋል። ስምምነት ላይም ለመድረስ ችለዋል። በአዲስ አበባው የሰላም ስምምነት መሰረት የአቢዬ የግዛት ማካለል ውሳኔ እስኪተላለፍ ድረስ ግዛቲቱ ከሁለቱም አገራት ጦር ሰራዊነት ነፃ ቀጠና (Demilitarized Zone) ሆና እንድትቀመጥ ይደነግጋል።

ከዚህ በተጨማሪም የድንበር ማካለሉ ውሳኔ ተግባራዊ እስኪሆን ድረስ የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ቡድን ላልተወሰነ ጊዜ አካባቢውን በኃላፊነት ተረክቦ እንዲያስተዳድር መግባባት ላይ ሊደርስ ችሏል። ይህንን ተከትሎም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት በውሳኔ ቁጥር 1990 መሰረት የኢትዮጵያ ሰራዊት በኃላፊነት እንዲረከብ በሙሉ ድምፅ ወሰነ።

የዚህን የውሳኔ ሀሳብ ተከትሎ የኢትዮጵያ መንግስት ወደ 4250 የሚጠጉ ወታደራዊ እና ሲቪሎችን የያዘ የልዑካን ቡድን ወደ ስፍራው ለመላክ ችሏል። ይህ የልዑካን ቡድን እስከዛሬ በአለማችን ከተሰማሩት የሰላም አስከባሪ ቡድኖች በብዙ መልኩ የተለየ ተብሎለታል። ከነዚህም መካከል

- ወደ ስፍራው ካቀኑት 4250 መካከል ሁሉም ኢትዮጵያውያን ብቻ ከመሆናቸው በተጨማሪም የልዑካን ቡድኑን በኃላፊነት እንዲወጡ የተመረጡት ሌፍተነንት ጀኔራል ታደሰ ወረደ ኢትዮጵያዊ መሆናቸው

- የልዑካን ቡድኑ እንደከዚህ ቀደሙ ወታደራዊ ቡድን ብቻ ሳይሆን ሲቪል ሰራተኞችንም በጥምረት ያቀፈ መሆኑ

-እስከዛሬ በተመድ ተልዕኮ ከተሰጣቸው አገራት መካከል ሰፊ ቦታን በኃላፊነት እንዲያስተዳድር እድል የተሰጠው ከመሆኑም በተጨማሪ በስሌት በ1 የኢትዮጵያ ወታደር ክበብ ውስጥ 2.3 ኪ.ሜ ያህል እንዲሸፍን መደረጉ።

የውስጥ እና የውጭ ፖሊሲ

የሶማሊያን ጉዳይ በተደጋጋሚ ማቅረቡ ተገቢ መስሎ አልታየኝም። ከዚህ ይልቅ ውጤቱ ላይ ማተኮሩን መርጫለሁ። የኢትዮጵያ መንግስት በሁለቱ አገራት ላይ እየወሰዳቸው ያሉት ተሳትፎዎች ሁሉንም ወገን ያስደሰተ አልያም ያስማማ ነው ለማለት አያስደፍርም። አንዳንዶቹ እርምጃውን ከሉዓላዊነት መጣስ ጋር አቆራኝተው የሚመለከቱት ሲሆን ሌሎቹ በተለይ እንደ ሶማሊያ ባሉ ማህበረሰቦች ድርጊቱን ከታሪካዊ ጠላትነታቸው ጋር ያያይዙታል። በተለይ ሶማሊያውያን የቅኝ ግዛት ወረራም አድርገው ይጠሩታል። እንደዚህ በጥላቻ የተሞሉ ቡድኖች እድሉን ካገኙ በአገራቸው በሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ላይ የበቀል ጥቃት ከመፈፀም ወደ ኋላ አይሉም። ከዚህ በተጨማሪም ኢትዮጵያን በክፉ አይን ከሚያዩት እንደ ኤርትራ ባሉ አገራት በሚደረግላቸው ድጋፍ ስደተኞች መስለው የተለያዩ ጥቃቶችን ለመፈፀም የሚዳዱ አይጠፉም።

የሰውን አገር ሰላም ለማስከበር ደፋ ቀና በምንልበት በአሁኑ ወቅት መሰረታዊው የዜጎቻችን ፍላጐት በእጅጉ የተዘነጋ ከመሆኑም በተጨማሪም ከዚህ ሰላም ማስከበር እያገናኛቸው ያሉ ኢኮኖሚ ድጋፎች ምን እንደሆኑ እንኳን እስከዛሬ ማወቅ አልቻሉም። ስለሆነም የውጭ ጉዳይ ፖሊሲው ለውስጥ ጉዳይ ፖሊሲ መጋቢ መሆን ካልቻለ ለምን አላስፈላጊ መስዋዕትነት እንከፍላለን?

የመምህሩ ደብዳቤ



አናኒያ ሶሪ
የአውራምባ ታየምስ ጋዜጣ አዘጋጅ

የተወደድሽው ወላጅ እናቴ አገርነሽ ለሁሉ ለጤናሽ እንደምን አለሽልኝ? እታለምስ እንዴት ናት? ትበረታላችሁ? ኑሮ እንዴት ይሏችኋል እምዬ? በዓይነ-ስጋ ከተያየን እነሆ 4 ዓመት ሊደፍን 3 ወር ብቻ ቀረው። አይ-ጊዜ! ልጓም የለው መቼም ስበው አያስቀሩት! ይኸው እንዳለያየን ቀረ። ይሁና-መቼም ህይወት እንዳሰቡት አይተም። ብቻ ሁልጊዜ ደብዳቤሽ ሲደርሰኝ፦ እምዬ አንቺን እናቴን ያገኘሁ እየመሰለኝ ባልፅናና ኖሮ ሰውም አልሆን ነበር። ከ783 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ሆነሽ የኔን የልጅሽን ማዘንና መንከላወስ የምታውቂበት ምን አንጀት ቢያድልሽ ነው ግን እምዬ?

ያንቺን ደብዳቤ ባገኘሁ ጊዜ ሁሉ እንደው የፈጣሪ ስራ ግርም ይለኛል። አፅናኝ ወዳጅ እንኳ በሌለበት፤ ሁሉ ሰው ‹ለኔ ለኔ› እያለ በሚከንፍበት የከተማ ግርግር መሃል ልብ-የሚለኝ ጠፍቶ ባይተዋርነት ሲሰማኝ ያንቺ የእምዬ መልእክት ከተፍ እያለ የልቤን ባያዋየኝ ኖሮ እስካሁንም በእስትንፋሴ ባልተገኘሁ ነበር። አዎ እምዬ-ሰው ባጣሁ ጊዜ፣ ልቤ ተሰብሮ ሀዘን በዋጠኝ ወራት፣ እንዳው ክፍት ብሎኛ አልቅስ አልቅስ በሚለኝ ሰሞን፣ ያንቺ የእናቴ ምክር እና ማፅናናት ባይደርስልኝማ ያየሁት ግፍና መከራ ብዛት ይገድለኝ አልነበር?

ግን ምኗ ብርቱ ነሽ እምይዬ? እኔ አፍላው እንኳ ትዳር ቤተሰብ ይሉት ጣጣ ሳይመጣብኝ ያልቻልኩትን የህይወት ቀንበር በምን ጫንቃሽ ቻልሸው እናት ዓለም? ሊያውም በዛ ስልጣኔ ዝር-ባላለበት የገጠር መንደራችን በሴት አቅምሽ ያለአጋር ብቻሽን እንደእናትም እንደ አባትም ሆነሽ ለዚህ አብቅተሽናል። አሁን በዓይነ-ህሊናዬ መለስ ብዬ ያለፈውን ሁሉ ስቃኘው የተዓምር ያህል ድንቅ ይለኛል። በእውነት የእኔ እናት ጀግና ሴት ነሽ።

ታዲያ ልጆቼ ደርሰውልኝ ከድካሜ ያሳርፉኛል፣ ወልደው ክብደው የልጅ-ልጅ ያሳዩኛል፣ በስተርጅናዬ ይንከባከቡኛል፣ ይጦሩኛል ብለሽ በልብሽ ያዘልሽውን ተስፋ እውን ለማድረግ እንደዋተትኩ ሀሳብሽን ሳልሞላ በመቅረቴ ታላቅ ሃፍረት ይሰማኛል። አንቺ ብቸኛዋ እናቴ በደካማ አቅምሽ ያደረግሽልኝን እሩቡን እንኳ ላደርግልሽ አለመቻሌ ዘወትር ያሰቅቀኛል፡ ፡ አንቺ እኔንና እታለምን ለማሳደግ ያየሽውን መከራ እና መስዋዕትነት ሳስብ ህሊናዬ በፀፀት አለንጋ ይገረፋል። ምን ያለሁት ጨካኝ ነኝ እያልሁ ብቻዬን እንሰቀስቃለሁ። የልጅ አንጀት ደንዳና ኖሯል እምይዬ? እንባዬ አንዳች ላይበጅሽ እጄ ባጠረብሽ ጊዜ ሁሉ ስላንቺ ይፈላል። እምዬ-ምነው እንባዬ በጦረሽ? ምነው ፍቅሬ ብቻውን ከድካም ባሳረፈሽ? ምነው ናፍቆቴ የልጅ ልጅ በሆነልሽ?

እማ-ገና በቅጡ ሰላምታዬንና ናፍቆቴን እንኳ ሳልገልፅልሽ ከሩቅ የመጣ ዘመዱን እንዳየ ለቀስተኛ ሰው ልክ እንዳገኘሁሽ ያህል እዬዬዬን ያቀለጥኩት ወድጄ አይደለም። እስካሁን ለማንም ትንፍሽ ያላልኩት ውስጥ-ውስጡን ሲብላላ የነበረ እና ያዳፈንኩት የህይወቴ ረመጥ እሳተ-ገሞራ ሆኖ ፈንቅሎኝ ነው። እማይዬ! ዛሬስ ሁሉንም ገመናዬን ግልጥልጥ አድርጌ ልንገርሽ። ከእንግዲህም እውነቱን እወቂው። እውነቱ ያማል አውቃለሁ፤ ግን ደግሞ ለሚወዱት ካላካፈሉት እንደክፉ ቅኝት ያስጨንቃል፡ ፡ ካንቺ ከዘጠኝ ወር ቤቴስ እንዴት እደብቃለሁ? እናት-ዓለም፦ ችግሬን ሰምተሽ መላ ባትዘይጂልኝም የልቤን ተካፍለሽ ግን ሀዘኔን ታቃይዋለሽ። ስለሆነም፦ ሀይወቴን አንድ ባንድ ምንም ሳላስቀር እነግርሻለሁ!

እማ-መቼም እንደምታውቂው የዛሬ ሶስት ዓመት ገደማ ወደስራ ዓለም እንደገባሁ በተስፋ ተሞልቼ አያሌ ቃልኪዳኖች ገብቼልሽ ነበር። ምንም እንኳ ሁሉንም እንደቃሌ ባልጠብቅ ዋኖቹን ግን እንደምንም ብዬ ፈፅሜያቸዋለሁ። በጀማሪ መምህርነት በ1571 ብር ስቀጠር 500 ያህል ጥሬ ብር እና የሀገር ባህል ልብስ ገዝቼ ልኬልሽ ነበር፡ ፡ ለእናትነትሽ ዋጋ እንኳን ይቺ ሌላም ብዙ ነገር ባይመጥንሽም እንደው እኔን ደስ እንዲለኝ ብዬ ያደረኳት ትንሿ ነገር ምን ያህል ሀሴት በነብሴ ሞልታ እንደነበር እኔ ነኝ የማውቀው። ውለታሽን መክፈል ጀመርኩ ብዬም ኩራት ተሰምቶኝ ነበር። በቃ ከዚህ በኋላ እናቴ እፎይ ብላ ትኖራለች፤ እኔ ልጇ ደርሼላታለሁ እያልኩ ሳስብ የህይወት ጠመዝማዛ መንገድ የኑሮ አቀበቱን አምጥቶ ፊቴ ላይ ደቀነው፡ ፡ በፊት ከደሞዜ ላይ ቆጥቤና አብቃቅቼ እልክልሽ የነበረው ብር ቀስ-በቀስ መመናመን ያዘ። በተሰይ ደግሞ የውዴታ-ግዴታ የሆነብኝን የድርጅት መዋጮ ማዋጣት ከጀመርኩ ወዲህ ለጋዜጣ፣ ለመጽሐት፣ ለምን ስንተኛ ዓመት በዓል አከባበር እየተባለ የደሞዜ ነገር እጅጉን አሳሳቢ ሆነ። በዚህ ሁሉ ላይ ደግሞ ለልማት መዋጮ በሚል ከመምህር ደሞዛችን ላይ በየወሩ የሚቀነስብን ብር ህልውናችንን በአያሌው ተፈታተነው።

ይሁን ግዴለም! ምናልባት የወደፊቶቹ የነእታለም ትውልዶች ብሩህ ቀን ይወጣላቸው ይሆናል በማለት አንጀታችንን አጥፊን ሁሉንም ለመቻል ስንል ቁርሳችንን መተው መረጥን። እማይዬ-እናንተስ እኛን እዚህ ለማድረስ በብዙ ተጋድላችሁ አይደል? ነገር ግን ይህም እንዳሰብነው አልሆነም። ዕለት በዕለት የሚንረው የምግቦች ዋጋ፣ የቤት ኪራይ መጨመር፣ የትራንስፖርት እጥረትና ዋጋ መጨመር ኑሯችንን ከእጅ ወደ አፍ አደረገው። ከዚህ ሁሉ የከፋው ግን ከምናስተምራቸው ታዳጊ ተማሪዎች ውስጥ ገሚሶቹ በረሃብ ምክንያት እዛው በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ ተዝለፍልፈው ሲወድቁ ማየት ለኛ ለመምህራን በፍፁም ልንቋቋመው ያልቻልነው የአእምሮ ሰቀቃ ነበር። በዚህም ምክንያት አንዳንዶቻችን 4 የነበረውን የትምህርት ክፍለ ጊዜ ወደ 2 ቀንሰን ስናስተምር ይህ እንደጥፋተኛ አስቆጥሮን ‹ኪራይ ሰብሳቢ መምህራን› አስባለን። ነገ ቀን ይወጣላቸው ይሆናል ብለን ተስፋ ያደረግንላቸው ታዳጊ ተማሪዎቻችን ዛሬያቸውም ጭምር ተስፋ-አጣ። ለካስ እኛም ተማሪዎቻችንም እየራበን ነው! ታዲያ ማን ለማን መስዋዕትነት እየከፈለ ይሆን?

እማይዬ! የምወደውን የመምህርነት ሙያ በሙሉ ልብ አንገቴን ቀና አድርጌ እንዳልሰራ ከውስጥ ሆዴን እየራበው፣ ከላይ የለበስኩት እዚህ-ግባ የማይባል ልብስ እያሳቀቀኝ፣ ከስር የተጫማሁት ጫማ በቅያሪ እጦት ሳልቆ እየቆረቆረኝ ይኸው እስካሁን እንደምንም ዘለቅሁ። በዛ ላይ ባለፈው እንደገለፅኩልሽ የእግሬ ህመም ከቀን ወደቀን እየባሰ በመሄዱ ለህክምና የጤና ዋስትና እንኳ ባልሰጠኝ ሙያዬ ላይ እጅግ እያማረርኩ ሳለ በአንድ የቀን ክፉ አጋጣሚ ለቅርብ ወዳጄ አጫወትኩትና ይኸው ብሶቴ በሌላ ተተርጉሞ በበላይ አለቆቼ ለመጠየቅና ለመገምገም አበቃኝ። ድሮውንም ቢሆን አንተ በመንግስት የትምህርት ፖሊሲ አታምንም፣ በዛ ላይ ባለፈው ስብሰባችን የቤተ-መጽሐፍት ቁሳቁሶች እና መማሪያ መጻህፍት አልተሟሉም እያልክ ድርጅቱን ክፉኛ ታሳጣለህ፣ ባጠቃላይ የአመለካከት ችግር አለብህ ተባልኩኝ። ለሙያዬ በተሟገትኩ እና ለተማሪዎቼ በተከራከርኩ ይህ እንደነውር ተቆጠረብኝ። እኔ ግን እቺን ታህልም ለመኖር ስል ሁሉን ችዬ ቀጠልኩ። በመሆኑም ላለፉት ተከታታይ 6 ወራት አልፎ አልፎም እልክልሽ የነበረውን ብር ሳልወድ በግድ ለማቋረጥ በቃሁ። እንጂማ ባንቺ በእምዬ የሚያስጨክን አንጀት እንደሌለኝ አንቺም ታውቂዋለሽ። እንደምንም ታግዬ ረሃቤን እየቻልኩ መኖሬን እንዳልቀጥል ግን ኑሮው በእጅጉ እየተወደደ የኔ ህይወት ግን በአያሌው እየረከሰ መጣ። ዳቦ መብላት ፈተና ሆነ።

እናም እማ! እኔ ልጅሽ ስራ ይገፍ የሚርበኝ ተምሬም ድሃ የሆንኩ የሰራተኛ ረሃብተኛ የተማርኩ ደሃ ሆኛለሁ። በመሆኑም፦ እኔና መሰል መምህራን ባልደረቦቼ አሁንስ በቃን! ከዚህ በላይ መታገስ አቅቶናል! መንግስት አንዳች መፍትሄ ያብጅልን! ስንል በመምህራን ማህበሩ በኩል ጥያቄያችንን ማሰማት ጀመርን። ይህን ተከትሎም በቅርቡ የሙያችንን ክብር ያዋረደና ህሊናችንን ያደማ የደሞዝ-ማሻሻያ ተብዬ ተደርጉላችኋል! እልል በሉ መምህራን ከእንግዲህ በተድላ ልትኖሩ ነው! ብለው የምፀት ቀልድ ቀለዱብን። በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት ዓይነት ብሒል በየቴሌቪዥኖቻቸውና በሬዲዮው እየቀረቡ የኛን ችግር ለፖለቲካቸው ፍጆታነት በማዋል እንዴት የልግስና እና የቸርታ ስራ እንደሰሩልን ማወጅ ጀመሩ። የነሱን ምኞት የኛ ምኞት አስመስለው በማውራት የመምህራኖችን ህይወት የሚቀይር ጭማሪ ሰጠናቸው ሲሉ ተዘባበቱብን።

እነሱ በሚያካሂዱት እርባና-የለሽ ስብሰባዎች ላይ ለመብልና መጠጥ ብሎም ለዳንኪራ የሚያወጡትን ወጪ እንኳ የማይስተካከል ጉርሻ ወርውረውልን ከዚህም የፖለቲካ ትርፍ ለማካበት ሻቱ። ከዚህ በላይ እንዲፈዝብን ስላልፈቀድንም በጨዋ ደንብ ቅሬታችንን ገልፀን የሆነው ሁሉ እንዲታረም አለበለዚያ የስራ ማቆም አድርገን ብሶታችንን ለሁሉም እንደምናሳይ ተናገርን። ወትሮውንም ቢሆን ተናጋሪ ምላስ እንጂ ሰሚ ጆሮ ያልፈጠረባቸው አካላት እንደበፊቱ ሊደልሉን እና እኛም ሆድ-ሲያውቅ በሚል ፊሊጥ እንድንታለል ፈለጉ። በአቋማችን በመፅናታችንም በደህንነቶቻቸው ሊያስፈራሩን ቃጡ።

እናት-ዓለም፦ ራበኝ ማለት ከፖለቲካ ተቆጥሮብኝ እየራበኝ ዝም-እንድል ተፈለገ። እማ በትንሽነቴ ሲርበኝ አንቺው ላይ አለቅስ ነበር። ዛሬ ግን ርቦኝ ማልቀሻ አጣሁ። ከረሃቤም በላይ እንባዬን ጠሉት። እሺ እኔስ ማን አለኝ? ርቦኝ እያስተማርኩ እስክወድቅ ነው የምጠበቀው?

እማምዬ-ብቻ ብዙ ብዙ ነገር እንዳይሆን እንዳይሆን ሆኗል። የጨካኙ አገዛዝም ሆነ ግራ-የተጋባው ትውልድ የአረኝነት ሸክም በኛው በመምህራን ጫንቃ ላይ አርፏል። ይህን የኑሯዜ ያህል የከበደ ደብዳቤ እንድፅፍልሽ ያስገደደኝም ይህ ከላይ የዘረዘርኩልሽ መከራ ነው እንግዲህ እናት-ዓለም።

መቼም የማያልፍ የለምና ይሄም ያልፋል። አንድ ቀን እኔም ሰው ሆኜ ሰው አረግሽ ይሆናል። በኔም በሙያዬም የምትኮሪበት ቀንም ሩቅ አይሆንም፡ ፡ ብቻ አንቺ በጤናና በህይወት ቆይልኝ። አደራ-እናት ዓለም ፅኚልኝ። እታለምንም ምከሪያት። ለሷ እና ለመሰሎቿ ታናናሾቻችን ቀን እንዲወጣላቸው እንታገላለን። ወትሮም እንደሻማ በርቶ ማለፍ የሙያችን ቃል-ኪዳን መሆኑን አትዘንጊ-እማምዬ!

ያንቺው ተወዳጅ ልጅሽ
21/7/2004 ዓ.ም የማይነበብ ፊርማ

የትናንት ወጣት፤ የዛሬ ወጣትና መጪው ጊዜ

ዳንኤል ተፈራ

ይሄ የሁለት ትውልዶች ወግ ነው። አሁን ያሉ ወጣቶችና የአባቶቻቸው ወግ ልንለውም እንችላለን። በፖለቲካ ትኩሳት የነደደውና፣ በሀገር ፍቅር ያበደው፤ በአንድነትና በዘውጌነት ጦራ ተሟድኖ፣ በማርክስና ኤንግልስ ፍልስፍና ተራቅቆ መሰብሰቢያው የቸገረው... ያ ትውልድ የትናንት ትውልድ ነው። የትናንት ወጣት ነው። የዛሬው ወጣት ደግሞ የትናንትናው ወጣት ልጅ ነው፡ ፡ የመጪው ትውልድ ደግሞ አባት። ለዛሬም ምን ተቀበልን? ምንስ እናስረክብ? የሚለውን የሁለት ትውልዶች ወግ እያሰናሰልን እንመልከት።

በቅድሚያ የትናንት ወጣቶች ብለን እንጀምር፡ ፡ በተለምዶ የ60ዎቹ ትውልድ የምንላቸው ናቸው፡ ፡ ለዛሬ ወጣቶች አባቶቻችን። አሁንም ሌላ ጥያቄ ልሰንዝር ለእኛ። የትናንት ወጣቶች የሀገር ፍቅር ከዛሬ ወጣቶች የሀገር ፍቅር ጋር እንዴት ይመዘናል? እየተሸረሸረ፣ እየተቦዳደሰ የመጣውን የሀገር ፍቅር፣ ለፖለቲካ ፍጆታ ሲባል ተቀንጥቦ ያለቀውን ወኔ፣ ተሸራርፎ ያለቀውን ኢኮኖሚ፣ ከዓረብ ሀገር እስከ ስልጡኗ አሜሪካ፣ ከደቡብ አፍሪካ እስከ ካረቢያንና ቻይና እንደ ርካሽ የተቆጠረውን ኢትዮጵያዊነት፣ አስፓልት ለአስፓልት የሚጐተተውን ኢትዮጵያዊነት፣ እንደማይረባ ቀራቅንቦ ከፎቅ ላይ የሚጣለውን ኢትዮጵያዊነት፤ ሀገሬ ከምትመልሱኝ እዚያው ግደሉኝ የሚባለውን ኢትዮጵያዊነት፤ ከሱዳንና ኬንያ ጀምሮ እስከ አውሮፓና እስያ የሚገኙ የመጠለያ ካምፖችን የሞቀ ቤት አድርጐ በኪሎ ምግብ እየተተመነለት የተስፋ ህይወት የሚገፋውን ኢትዮጵያዊነት... ከማን ተቀበልነው? ለማንስ እንዴት አድርገን ልናስረክበው ነው?

እነዚህ አስጨናቂ ጥያቄዎች ወደ አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት ላይ የሚላከኩ አይደሉም። ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም ዋነኛ የሆነ ጠቅላይ ገላጭ ቃል የፈጠሩለት ‹‹የቁልቁለት ጉዞ›› ወይም ‹‹ዳገት ላይ ሰው መጥፋቱ››፤ ክቡር የሆነው ኢትዮጵያዊነት ጥያቄ ምልክት ውስጥ መግባት፤ ብርቱ ባህላችን በብልጭልጭና መጪ ምናምንቴዎች መተካቱ ከራት ለፊታችን ያለውን ጋራ የሚያክል ፈተና የሚያሳይ ነው።

የትናንት ወጣቶች በማርክሲዝምና ሌኒኒዝም ፍልስፍና ተውጠው፣ መደማመጥ የሚሉት ቃል ከአጠገባቸው ጠፍቶባቸው፣ አንዱ ገዳይ ሌላው ደግሞ ተገዳይ፣ አንዱ ሰጭ ሌላው ምንደኛ፣ አንደኛው ሀገር ወዳድ ሌላው የሀገር ጠላት፣ አናርኪስትና አስገንጣይ... እየተባባሉ የተላለቁበትን ታሪክ ከራሳቸው ከባለታሪኮቹ የሰማንባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው።

ለ17 ዓመታት ሀገሪቱን በፋከራና በመሳሪያ ጋጋታ፣ እንዲሁም ደረቅ መፈክርና ምንም አይነት የመቅደም እንቅስቃሴ ሳይደረግ ‹‹ኢትዮጵያ ትቅደም!›› የሚል መመሪያ ከፊት ለፊት አስቀድመው ግን ደግሞ ራሳቸው ቀድመው ሀገሪቱን የመሩት ኮለኔል ኀድ መንግስቱ ኃ/ማርያምና በተለመደው መሳሪያ መንግስቱን አስወግደው ሀገሪቱን ለባለፉት 20 ዓመታትና በቀጣይም የመምራት ህልም (ቅዠት) ያላቸው አቶ መለስ ዜናዊ የአንድ ትውልድ ሰዎች ናቸው። የትናንት ወጣቶች ናቸው። ኀድ መንግስቱ ‹‹ኢትዮጵያ ትቅደምን›› በማስቀደም የራሳቸውን ቀዳሚነትና ትልቅነት፣ ቆራጥነትና ጀግንነት እንዳስቀደሙ ሁሉ አቶ መለስ ዜናዊም ‹‹ልማት!›› የሚለውን መፈክር በማስቀደም የሳቸውን ትልቅነት፣ ከሳቸው ወዲያ ሰው ያለመኖሩን፣ ፓርቲያቸው ከሌለ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር እንደማትኖር ይነግሩናል፡ ፡ አንድ ጊዜ እዚሁ ፍትሕ ጋዜጣ ላይ ይሄኛው ትውልድ ከዚያኛው ትውልድ ሊወስዳቸው የማይገቡ ጥቂት ነጥቦች ብዬ ፅፌ ነበር። ይህን ያልኩት አባቶቼን ከመጥላት ወይም ምንም አልሰሩም ከሚል ጭፍንነት ተነስቼ አይደለም። እንደዚያም ሊሆን አይችልም። በሀገር ፍቅር መንደድ፣ መንደድ ብቻ ሳይሆን በአደባባይ ጧ ብሎ መሞት እስከመምረጥ የደረሰ ፍቅር እድለኛ ካልሆኑ በቀር ከየት ይገኛል?

ጥያቄው ከሞቱለት ዓላማ ጀርባ ስኬት አለ ወይ? የሚለው ነው። ለልጆቻቸው የሚያወርሱት ውጤት አለ ወይ? የሚለው ነው። አለበለዚያ ህይወት እያባከኑ ጨዋታ ይመስለኛል። ክፍተቱን በጥናት አስደግፎ ያሳየን ባይኖርም በትውልድ መካከል የማይገናኝ ትልቅ ስንጥቅ እንዳለ በርካታ ሰዎች ሲናገሩ እናደምጣለን። የዛሬው ትውልድ ውጤቱን ይመዝንና አባቶች እርስ በርስ የሞቱለትን አላማ እንደ ምንም መቁጠር የክፍተቱ አካል ነው፡ ፡ ለዚህ ነው የሚቆጨን። ኢህአዴግ ‹‹ሰማዕታት›› የሚላቸው ታጋዮች ሞት በቁጭት የሚያንገበግበን የምር ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ሰፍኖ ሳናይ ስንቀር ነው። በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ብርቱ አቋም የነበረው ኢህአፓና የተሰዉ ኢትዮጵያውያን የሚቆጨን ትግሉ በመበተን ሲቋጭ ስናይ ነው። እና የተበታተነው የወኔ ትግል ለዛሬው ወጣት የሚያበረክተው አጣና በማህበራዊ ድረ-ገፅ ፍቅርና በእግር ኳስ ልክፍት ያበደ ሆነ። አብዛኛው የሀገር ፍቅርንና ፖለቲካን የሚጠየፍ ‹‹ፖለቲካንና ኮረንቲን በሩቁ!›› የሚል ሆነ የዚያ ትውልድ ልጅ የዛሬው ወጣት።

የሚገርመው ‹‹በምንትስ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ›› እንደሚባለው የትናንት ወጣት የነበሩት እነ አቶ መለስና አስተዳደራቸው የዛሬው ወጣት ፖለቲካ ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግ አለመፈለጋቸው ነው፡ ፡ በርካቶች ይሄንን ፍላጐታቸውን ‹‹ከስልጣን ሱስነት የመጣና ትውልድ አድርቅ›› እያሉ ቢያብጠለጥሉትም የ‹‹ፌስ ቡክ›› ትውልድ ምቾት ሰጥቷቸዋል። እናም ‹‹ፖለቲካና ኮረንቲን በሩቁ›› የሚለውን ጥቅስ ተገቢና ሰላም ወዳድነት እንደሆነ ይሰብኩታል። መቃወም እግር እንደሚያስቆርጥ ይነግሩታል፤ አንዳንድ ይሄን ሴራ ሰብረው የወጡ ወጣቶች ላይ ሽብርተኛ፣ ነውጠኛ፣ ምንትሴ... በማለትም ዙሩን ያከሩታል። መቀጣጫም በማሳየት ያስበረግጉታል።

እናም መብትህን ጠይቅ ሲባል ብትት የሚል ትውልድ መፍጠር የተቻላቸው ይመስለኛል። በድፍረት ለመናገር ደግሞ የፖለቲካ ንቃተ ህሊናው የተንኮለሸና መብቱንና ነፃነቱን አሳልፎ የሚሰጥ፣ በአቋራጭ ለመበልፀግ አሊያም ሀገር ጥሎ ለመሰደድ የተሰናዳ ትውልድ፣ የዛሬው ወጣት ነው።

እውነት እውነቱን እንነጋገር ከተባለ የትናንትናው ወጣት ሀገር ጥሎ የተሰደደው ወደና ፈቅዶ አይደለም። ከሚያሯሩጠው ሞት አምልጦ ነው፣ ተገፍቶ ነው። ዛሬም ድረስ በህይወት ያሉና በማያውቁት ጥበብ ከሞት አምልጠው አሜሪካና አውሮፓ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በሚዕፂቸው መፅሐፍ ስደትን ሲረግሙ እንጅ ሲመርቁ አላየንም፡ ፡

ዛሬስ? እስቲ ወደ አውሮፓና አሜሪካ መሐዴድ ተፈቀደ ቢባል ስንት ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ ይቀራል? ስንት ወጣት አልሄድም ይላል? ያፈጠጠ ሞት ያለበት አረብ ሀገራት ለመሄድ የሚሳለውና የሚሰለፈው ስንቱ ነው? ይሄን ነው የትውልድ ክፍተት የምላችሁ።

የትናንት ወጣቶች ከሀገር ቤት ሞት አሯሩጦ አስወጣቸው፤ የዛሬ ወጣቶች ደግሞ ሞት ወዳለበት ሀገር ይሄዳሉ። በእርግጥ ሀገር ውስጥ አልሞላ ያለ ህይወት፣ አልስተካከል ያለ ኢኮኖሚ እንደሚያስወጣቸው እውነት ነው። ለዚህ ግን ተጠያቂው ማነው? ሀገር ጥሎ ለመውጣት የተሰናዳው የዛሬ ወጣትስ የማን ውጤት ነው? ለመጪው ትውልድስ?... እነዚህ እንደ ሀገር ለመቆየት፣ ትቢያ ላይ የወደቀውን ኢትዮጵያዊነት ለማንሳት ባስቸኳይ ሊመለሱ የሚገባቸው ጥያቄዎች ናቸው። ሁሉንም ኢትዮጵያዊ የሚመለከቱ አንገብጋቢ ጥያቄዎች።

የትናንቱ ወጣት አብዮቱ አካሂዶ ነበር። በነበር ቀረ እንጂ! አብዮቱ በኢትዮጵያ ወርድና ቁመት ልክ የተሰራ ሳይሆን ከነ ቀይ ሪባኑ በውስት የመጣ ነበር። ስለዚህ ጨነገፈ። ደርግ፣ ኢህአፓ፣ ማሌሪድ፣ መኢሶን፣ ኢጭአት.... አብዮቱ የፈጠራቸው የትናንቱ ወጣት ቡድኖች ነበሩ። የዛሬ ወጣትም ቡድን አለው። ማንችስተር፣ አርሴናል፣ ቼልሲ፣ ማድሪድ፣ ባርሳ... የሚባል። የሁለቱ ትውልዶች ወግም ይሄው ነው።

ለምን ወጣቱ የፖለቲካ ቡድን አላቋቋመም የሚል አመለካከት የለኝም። ነገር ግን የዛሬው ወጣት ለምን ከሀገሩ ጉዳይ ላይ ሸሸ? ማንስ ሊረከብ ነው? እያልን ስለተተኪው ትውልድ፣ ትውልዱ ሊፈጥራት ስለሚል ኢትዮጵያ ስናስብ ስለሚያስጨንቅ ነው፡ ፡ የትናንትናው ወጣትና የዛሬው ወጣት በተለያዩ ጫፎች የቆሙም ይመስላል። የዛሬ ባለስልጣናትና የትናንት ወጣቶች ደግሞ ይሄ ምኞት የሰጠቸው ይመስላል።

በእርግጥ የትናንት አብዮተኛ ወጣቶች በየዩኒቨርስቲያቸው ስለለውጥ ዘምረዋል፣ ላመኑበት አላማም ወደ አደባባይና ወደ በረሃ ወርደዋል። የዚያ ትውልድ አካል የሆኑት አቶ መለስ እንኳ አሁን ያለን ወጣቶች አብዮተኛ እንድንሆን አይፈልጉም እንጅ እሳቸውና ጓደኞቻቸው ቅልጥ ያሉ አብዮተኞች ናቸው። ያውም ጫካ የወረዱ አብዮተኞች። ወጣት ሆነህ አብዮተኛ ካልሆንክ፤ ወጣት ሆነህ ለውጥ የማያምርህ ከሆነ ምን ዋጋ አለው? ይሄ ማለት ግን አደባባይ ወጥተን ድንጋይ እንወርውር እያልኩ አይደለም። ግን ሞጋቾች መሆን አለብን። ልክ እንደ አባቶቻችን ማለት ነው።

ዩኒቨርስቲዎቻችን ሞገደኛ ወጣቶች የሚያፈሩ ማህፀናቸው የደረቀ ይመስላል። ወጣት ሞገደኛ መሆን ይገባዋል። ሞገደኛ ስንሆን ልንሳሳት እንችላለን። በጣም ጥሩ። ከተሳሳትን ተማርን ማለት ነው። ድሮ ዩኒቨርስቲዎች ርዕዮተ-ዓለም የሚተነተንባቸው፤ የፖለቲካ ክርክር የሚጧጧፍባቸው፤ በማህበረሰብ ላይ የደረሰ ችግር ለምን ተብሎ የሚጠየቅባቸው ነበሩ። የትናንቱ ወጣት ይሄን አድርጓል። የዛሬው ወጣት ደግሞ የ‹‹ደይ ፓርቲ›› የሙዚቃና የፋሽን ትንታኔዎችን ዩኒቨርስቲ ውስጥ ይቀምራል። ሌላው የሁለቱ ትውልዶች ወግም ይሄው ነው።

እንግዲህ ላሳርግ። ትውልድ የመክሰስ አባዜ አልተጠናወተኝም፡፡ነገር ግን የ‹‹ቁልቁለት ጉዞአችን›› አስፈሪ ነው። በየትውልዱ መካከል የሚከሰተው ልዩነትም ስፋቱ የትየለሌ ነው። መልካም ነገሮችን እየያዝንና አይረቤዎችን እየጣልን መሄዱም የተሳካልን አይመስልም። የትውልድ ሰንሰለቱ በመያያዝ ፈንታ ተበጥሶ ሁሉም በራሱ ዓለምና፣ በራሱ ክብ መስመር መንኮዱን ቀጥሏል። ይሄው ‹‹ክሰንሰለት ውጭ›› የሆነ ጉዞም ዋጋ እያስከፈለን ነው። የምንከፍለው ዋጋ ደግሞ ፈፅሞ በምንም አይነት ገንዘብ የምንመልሰው አይሆንም ምክንያቱም የምናጣው ክቡር የሆነውን ኢትዮጵያዊነትን ነውና!

የፍትህ ዓምድ

በዚህ ዓምድ የአገራችንን ህጎች ፣ ዓለም አቀፍ ህግጋት ፣ በሀገራት መካከል የተደረጉ ስምምነቶችን እንዲሁም ለንፅፅር እና ለማገናዘቢያ ይረዳን ዘንድ ሌሎች ሀገሮችን ህጎች መሰረት በማድረግ ከማንኛውም አይነት የፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ በሆነ መልኩ ትንታኔ ይሰጣል፡፡

‹ሰው› ማለት?

በ1952 ዓ.ም. በተለየ እትም የወጣው ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 1 የፍትሐ ብሔር ህግ በመባል ይታወቃል፡፡ የዚህ ሕግ የመጀመሪያ አንቀጽ (አንቀጽ 1) ደግሞ እንዲህ ተዕፏል፡፡ ‹‹ሰው ከተወለደበት ቀን አንስቶ እስከ ሞተበት ቀን ድረስ የሕግ መብት አለው፡ ፡›› ለመሆኑ ሰው ማለት በህጉ ዕይታ ምን ማለት ነው? የሰውነትን ጉዳይ በሕግ በተገለጠ ግልፅ እና ለአፈፃፀም በሚመች መልኩ ማስቀመጥ በተያያዥነት ለሚነሱ ህግ ነክ ጉዳዮች መሰረት እንደሆነ በየትኛውም ደረጃ ያሉ የህግ ሊቃውንትን ያስማማል፡፡ ለዚህም ይመስላል የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ህግ የሰውነትን ጉዳይ በመጀመሪያው ረድፍ ላይ ያስቀመጠው፡፡ ከላይ ለተቀመጠው ሰው ማለት ምን ማለት ነው? ለሚለው ጥያቄ አንዳንድ ምሁራን በግርድፍ ሃሳቡን በሁለት በመክፈል የህብረተሰብ አካል አድርገው ይገልፁታል፡፡ በዚሁ ትርጓሜ መሰረት ሰው ማለት በህግ የተቀመጠ መብት እና ግዴታዎች ያሉት አካል ነው፡፡ ይህን ትርጓሜ መሰረት አድርገው ሰውነትን በሁለት መክፈል ይቻላል የተፈጥሮ ሰዎች እና አርተፊሻል ሰዎች በማለት፡፡ የተፈጥሮ ሰውነት የህግ ሽፋን የተሰጠው የሰው ልጅ ሲሆን በሁለተኛው ክፍል የተፈጥሮ ያልሆነ ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው ደግሞ ልክ እንደ ሰው ልጅ መብት እና ግዴታ ያላቸውን ተቋማት ያጠቃልላል፡፡ በዛሬው ፅሁፌ ለሰው ልጅ ህጋዊ ሰውነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ እናያለን፡፡

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ1969 በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ህግ በተለይም በህጋዊ ሰውነት (ለሰው ልጅ) ላይ ጥናት ያደረጉት ጃክስ ቫንደር ሊደን ሰውነት የሚጀምረው ከውልደት ቀን ጀምሮ ነው ይላሉ፡፡ በጃክስ ትንታኔ መሰረት በህይወት ወደ ዚህች ምድር መምጣት እና ህጋዊ ሰውነት ማግኘት ሁለቱም በአንዱ ይከሰታሉ፡፡ የሰው ልጅ በማናቸውም መልኩ የዘር፣ የሃይማኖት፣ የቀለም፣ የስራ ሁኔታ፣ ወይም ሌላ ዓይነት ልዩነት ሳይደረግበት ከውልደቱ ቀን ጀምሮ ህጋዊ ሰውነት ይሰጠዋል የፍትሐ ብሔር ህጉ አንቀጽ አንድ ይህን ሁኔታ ይገልጻል፡፡ ይህን አንቀጽ መነሻ አድርገን የሀገራችንን ሕግ ስንቃኝ ውልደት ብቻ ለአንድ ሰው ህጋዊ ሰውነት ያሰጠዋል፡፡ በቀድሞ የሮማውያን ህግ እና ጥንት በሀገራችን በነበረው ስርዓት መሰረት ለአሳዳሪዎቻቸው እነዚህ ግለሰቦች በውልደት ብቻ የሚገኘውን ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኙ ይደረጉ ነበር፡ ፡ ነገር ግን አሰቃቂ የሆነው የጨቋኝ /Slavery/ ስርዓት ከጠፋ በኋላ ግን በየትኛውም የዓለም ክፍል በውልደት መነሻነት የሚሰጠው ህጋዊ ሰውነት በምንም መንገድ ሊገሰስ እንደማይችል ሀገራት በህገ-ቻቸው አካተውት ይገኛሉ፡፡

ምንም እንኳ የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ህግ ሰው ከተወለደበት ቀን አንስቶ እስከ ሞተበት ቀን ድረስ የሕግ መብት አለው ቢልም የሰው ልጅ ተወለደ የሚባለው መቼ እንደሆነ በበቂ ሁኔታ አላስቀመጠም፡፡ ቀድሞ በተለያዩ ሀገራት ይሰራበት በነበረው የመወለድ ፅንሰ ሀሳብ መሰረት አንድ የሰው ልጅ ተወለደ የሚባለው በተፈጥሮውም ሆነ በሰው ሰራሽ መንገድ ከእናቱ ማህፀን ሲነጠል ነበር፡፡ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የሚታዩት የቅራኔ ሀሳቦች ደግሞ አንድ ልጅ ተወለደ የሚባለው ካለ እናቱ እርዳታ በነፃነት የሚያስፈልጉትን የተፈጥሮ ርዳታዎች በራሱ አማካኝነት ሲያከናውን እንደሆነ ይገልጻሉ፡ ፡ ይህም ማለት በራሱ አማካኝነት ሲተነፍስ፣ የደም ዝውውርም ሆነ ሌሎች የሰውነቱ አካላት በራሳቸው ስራቸውን መስራት ሲጀምሩ ይህ ሰው ራሱን ችሎ ተወልዷል ማለት የሚቻለው በማለት የእንግዴው ልጅ መቆረጥን የመውለድ ማሳያ አድርገው ይከራከራሉ፡ ፡ በእርግጥ ከእናት ማህፀን መነጠል እና የእንግዴ ልጅ መቆረጥ መካከል ያለው ልዩነት ከምናባዊነት ባለፈ በተግባር ሊታይ የሚችል በሕግ አፈፃፀም ላይ ሊያመጣ የሚችለው ችግር በተቃርኖ ከተቀመጡት ቡድኖች በበቂ ሁኔታ ሲገለፅ አይታይም፡፡

በአገራችን የፍትሐ ብሔር ህግ መሰረት መወለድ ብቻ ህጋዊ ሰውነት ያሰጣል በሕጉ አንቀጽ 1 ላይ እንደተቀመጠው፡፡ ይሁንና በሌሎች የሲቪል ህግን በሚከተሉ ሀገራት ሕግጋት መሰረት አንድ ለተዋለደ ህፃን ከመወለድ ሌላ አንድ ወይም ሁለት መስፈርቶች ህጋዊ ሰውነት ለማግኘት የግድ ይላሉ፡ ፡ በአንዳንድ ሀገራት የተወለደው ህፃን በህይወት ያለ መሆኑ /born a live/ እንደ ተጨማሪ መስፈርት የተቀመጠ ሲሆን በሌሎች ሀገራት ህጐች ደግሞ በህይወት መወለድ እና ለተወሰነ ጊዜ በህይወት መኖር አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው የተወለደው ህፃን በህይወት ከሌለ ለህፃኑ የሚሰጠው መብትም ሆነ በሂደት እንዲወጣው የሚጠበቀው ግዴታ ምክንያታዊ አይደለም፡፡ ስለዚህ ህፃኑ ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኝ በህይወት መኖሩ አስፈላጊ ነው በማለት ይከራከራሉ፡፡ ሌሎች የህግ ሊቃውንት ደግሞ በህይወት መወለድ ብቻ ሳይሆን ለተወሰነ ጊዜ በህይወት መኖር ይገባዋል የሚለውን ሀሳብ አጥብቀው ይከራከሩበታል፡፡ የነዚህኛዎቹ ምሁራን መከራከሪያ አንድ ህፃን በህይወት ተወልዶ ወዲያው ከደቂቃዎች በኋላ ቢሞት በህይወት ተወለደ ከማለት ውጭ እንደተወለደ ከሞተ ህፃን ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ በመሆኑም በህይወት ለሌለ ህፃን መብትን መስጠትም ሆነ የግዴታ ሁኔታዎችን ማስቀመጥ በሌለ ነገር ላይ ክርክር እንደ ማድረግ ዓይነት ነው በማለት የህፃኑ ለተወሰነ ጊዜ በህይወት የመኖር ሁኔታ በህጐች ውስጥ መካተት አለበት በማለት ይሞግታሉ፡፡ ከሦስቱ የመከራከሪያ ነጥቦች እንደምንረዳው በሀገራችን ፍትሐ ብሔር ህግ አንቀጽ 1 የተቀመጠው በመወለድ ብቻ ሊገኝ የሚያስችለው ህጋዊ ሰውነት በአንዳንድ ነባራዊ ሁኔታዎች ሲታይ ትርጉም እንዲያጣ ያደርገዋል፡፡ ይኸውም ህፃኑ በህይወት ባይወለድና በህይወት ተወልዶ በአጭር ጊዜ ውስጥ ቢሞት የሚለውን ጉዳይ ሲያጋጥም፡ ፡ ስለዚህ እነኚህ ሁለት ሁኔታዎች እንደ መርህ በአንቀፅ 1 ውስጥ ቢከተቱ ሀጉን ይበልጥ ወደነባራዊ እውነታ የተጠጋ ያደርገው ነበር፡፡

ይሁንና የፍትሐ ብሔር አንቀፅ 2 የተፀነሱ ልጆች መቼ ህጋዊ ሰውነት እንደሚያገኙ ይገልጻል፡፡ አንቀፅ 2 እንዲህ ይላል ‹‹የተፀነሰ ልጅ በህይወት ከተወለደና የሚኖር ከሆነ የራሱ ጥቅም በሚያሻበት ጊዜ ሁሉ እንደተወለደ ይገመታል ይላል፡፡›› አንቀፅ ሦስት ንዑስ አንቀጽ (1) ደግሞ ‹‹የልጅ መፀነስ ጊዜ የሚቆጠረው ልጅ ከተወለደበት በፊት ካለው ከሶስት መቶኛው ቀን ወዲህ ነው፡፡ ›› ይላል፡፡ እንግዲህ አንድ ህፃን ከተወለደበት ቀን በፊት በሶስት መቶኛው ቀን በፊት ተቆጥሮ በዚያ ጊዜ ውስጥ የተፀነሰ እንደተፀነሰ የሚቆጠር ሲሆን ይህ ፅንስ በህይወት የተወለደና የሚኖር ከሆነ እንደተወለደ ይቆጠርና በአንቀጽ አንድ መሰረት ህጋዊ ሰውነት ያገኛል ማለት ነው፡፡ ነገር ግን በአንቀጽ ሁለት የተቀመጠው በህይወት የመወለድ እና የመኖር ጉዳይ በተለይ በህይወት የመኖር ጉዳይ ግልፅ በሆነ ሁኔታ በጊዜ ገደብ በዚሁ አንቀጽ ውስጥ አለመቀመጡ በማንኛውም ጊዜ በህይወት የተወለደ ህፃን ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኝ ያደርገዋል የሚል ክርክር ያስነሳል፡፡ አንቀጽ 4 ግን ለዚህ መልስ አለኝ ይላል፡፡ አንቀጽ 4 የሚኖር ወይም የማይኖር ልጅ በሚለው ርዕስ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር ‹‹ይህን ተቃዋሚ የሚሆን ማናቸውም ማስረጃ ቢቀርብም እንኳ አንድ ልጅ ተወልዶ 48 ሰዓት በህይወት ከቆየ በህይወት እንደኖረ ይቆጠራል፡፡›› አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2 ደግሞ አንድ ልጅ ተወልዶ በህይወት የቆየው ከ48 ሰዓት ያነሰ ጊዜ የሆነ እንደሆነ በህይወት እንዳልኖረ ሆኖ ይቆጠራል፡፡›› የ48 ሰዓት የጊዜ ገደብ በምን መስኪያ እንደተቀመጠ ግልፅ የሆነ መረጃ ባይኖርም በአብዛኛው ሁለት ቀን እና ከዚያ በላይ ከወለድ በኋላ የሚኖሩ ህፃናት በተፈጥሮ በተለይም ከወሊድ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ችግሮችን ይቋቋማሉ ተብሎ ስለሚገመት ነፃ ሆነው መኖር ጀምረዋል በሚል በህይወት እንዲኖሩ /viable/ ይቆጠራል፡፡

ከላይ ከዘረዘርናቸው ሁኔታዎች መገንዘብ እንደሚቻለው በሀገራችን ህግ መሰረት ህጋዊ ሰውነት /የተፈጥሮ ሰውነት/ ለማግኘት በአንቀጽ 1 ውስጥ የተጠቀሰው የመውለድ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን አብረውን ሊሄድ የሚችሉት በአንቀጽ 2 እና 3 የተቀመጠው የተወሰኑ ልጆች፣ የተፀነሱበት ጊዜ እንዲሁም በአንቀጽ 4 የተቀመጠው የሚኖር ወይም የማይኖር ልጅ የሚሉት ሁኔታዎች በህብረት መታየት ይገባቸዋል፡፡ ቸር እንሰንብት፡፡



ከመምህር ተፈራ ታደሰ

ለመብታችን፣ ለጥቅሞቻችን እና ለፍትሐዊነት እኛ መምህራን ባንድነት እንቁም!!

በኢትዮጵያ ታሪክ ከ1942 ዓ.ም. ጀምሮ መምህራን በየስርዓቱ የተለያዩ ተግዳሮቶችና ፈተናዎች ገጥሟቸዋል፤ እየገጠመንም ነው፡፡ ለወደፊትም ብዙ እንቅፋቶችና መሰናክሎች ከፊታችን የሚጠብቁን ለመሆኑ ጠንቋይ መሆን አያስፈልግም፡ ፡ የአካዳሚክ ነፃነት፣ የደመወዝ ዝቅተኛነት፣ ጥቅማጥቅም ያለመሟላት፣ የፖለቲካ ጫና እና የስራ አካባቢ ደህንነት ከሚፈታተኑን አንኳር ጉዳዮች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

ህገ-መንግስቱ የሰጠንን መብቶች፡- የመጠየቅ፣ የመቃወም፣ የማንም ፖለቲካ ድርጅት አባል ያለመሆን/የመሆን፣ የመደራጀት እና ሌሎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻችን እየተጨፈለቁና እየተሸረፉ የመኖር ህልውናችን ጥያቄ ውስጥ ከገባ ሰነባበተ፡፡ ሌሎችን ሁሉ ለጊዜው ትተን ዛሬ አንዱንና ዋነኛው የመኖር ዋስትና የሆነውን ወቅታዊና አንገብጋቢ የደመወዝ ጉዳይን በጨረፍታ ለመዳሰስ እሞክራለሁ፡፡

በተለያዩ ጊዜያት በብዙሃን መገናኛ እና በመምህራን ውይይቶች ላይ ቱባ ቱባ የሆኑ (የነበሩ) የመንግስት ባለስልጣናት ከ‹ዋልጌ መምህራን› እስከ ሌሎች ሸንቋጭና አሸማቃቂ ቃላትን በመቀም በይፋ ሲሰድቡንና ሲያሸማቅቁን ቆይተዋል፡፡ ዛሬ ዛሬ ስድቦቹን እና ማንጓጠጡን የመንግስት አካላት ስልታዊ በሆነ መንገድ ተያይዘውታል፡፡ በ1998 ዓ.ም. በደመወዝ ማስተካከያ ወቅት የተወራውና የተደረገው ለዚህ አንዱና የመጀመሪያው ማሳያ ነው፡ ፡ በጥር 2003 ዓ.ም ዳግመኛ በተደረገው የደመወዝ ማስተካከያ ጊዜ በብዙሃን መገናኛዎች ‹‹ለመምህራን የተደረገላቸው ልዩ ጭማሪ ነው›› በማለት መምህራኑንና ህብረተሰቡን ያሳሳተበት እና ምን ያህል የስነ-ልቦና ቀውስ ውስጥ እንድንገባ ማድረጉ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡ በየደረጃው የነበረው ጭማሪ ግን ከ35 ፐርሰንት እስከ 39 ፐርሰንት ብቻ ነበር ፤ ጭማሪው እንኳን ከሌሎች ሊበልጥ እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ ዛሬ ለሦስተኛ ጊዜ ‹‹ሲጠና ሲፈተሽ ቆይቶ›› በሚል መግለጫ ከመጋቢት 1/2004 ዓ.ም ጀምሮ ‹‹መምህራኑን ከሌሎች በተሻለ የደመወዝ ማስተካከያ ተደርጓል፡፡›› ያሉትና የተደረገው ለየቅል መሆኑን ለመምህሩ መንገር ‹ለቀባሪው ማርዳት› ነው፡፡ ሌሎች አካላት እንዲያውቁት ለማንዛቤ ያህል ማስተካከያዎቹን ለጀማሪ መምህራን በየትምህርት ደረጃዎች እንደሚከተለው አስቀምጣለው፡፡ ለጀማሪ ዲፕሎማ ከብር 1171 ወደ 1233 (62 ብር ጭማሪ)፣ ለጀማሪ ዲግሪ ከብር 1571 ወደ ብር 1644 (73 ብር ጭማሪ)፣ የዲፕሎማ ጣሪያ ብር 2807፣ የዲግሪ ጣሪያ ብር 3665 እና የማስተር ዲግሪ መነሻ 2151፤ በማስተር ዲግሪ ከፍተኛ መምህር የደረሰ የሚያገኘው ብር 3208 ናቸው፡፡ ‹‹መምህሩ ቀና ብሎ፣ ደረቱን ነፍቶ እንዲሄድ የሚያደርግ ማሻሻያ ነው፤ የሚያተጋ ነው›› የሚሉ መግለጫዎች በየቤታችን በትንንሿ መስኮት እና በንፋስ የደረሰን፡፡ ነገሩ ሲታይ ‹ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ› ነው የሆነብን፡፡ ሁሉ ነገር ቀርቶ ለምን እውነት አይነገርም? ለምን መንግስት በጠራራ ፀሐይ እና በአደባባይ ይዋሸናል? ይህን ነው እንግዲህ መንግስት ስልታዊ በሆነ ዘዴ ማሸማቀቅ ማሳፈር የተያያዘው ያልኩት፡፡

ዛሬ በየትኛውም ሲቪል ሰርቪስ መ/ቤት የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው በስምንት ዓመት የስራ ልምድ (ለማስተርስ 6 ዓመት) ደመወዙ 3348 ብር ነው፡፡ እውነቱ ይህ ነው፤ በት/ት ሚ/ር ስር ላለ ለመሪ መምህር (የመጨረሻው ደረጃ) የደመወዝ ጣሪያው እስከ የካቲት 30/2004 ዓ.ም. ድረስ ብር 3066 ብቻ ነው፡፡ ይህን የደመወዝ መጠን ለመድረስ አንድ ዲግሪ ያለው መምህር ያለምንም እንከን ሳይወድቅ ሁሉን ደረጃዎች (6ቱን) እያለፈ ቢመጣ 16 ዓመታት ይፈጅበታል፡፡ እንግዲህ ይህን የመምህሩ ጣሪያ የነበረው ከሌላ መስሪያ ቤት ሰራተኛ በተመሳሳይ የት/ት ደረጃ በስምንት ዓመት የስራ ልምድ ጋር ማወዳደርና ሃቁን ማየት፡፡ ብዙ ማለት ይቻላል፤ ከአሁኑ ከላይ ያስቀመጥኩት መረጃ ተገንዝቦ እያንዳንዱ የራሱን የህሊና ፍርድ ይስጥ፤ ልብ ያለውም ልብ ይበል፡፡ ለሲቪል ኮሚሽን፣ ለት/ሚኒስቴር እና ለመምህራን ማህበር ባለስልጣናት ‹ደባ ድግሱን፣ ስስት ራሱን› የሚለውን ምሳሌያዊ አባባል ባስቀምጥላቸው በአግባቡ ይገልፁቸዋል፡፡ ታዲያ በአንድ አገር ውስጥ (በሲቪል ሰርቪ. ስር) እንዲህ ያለ የደመወዝ እርከን ልዩነትን ማሳየትና ይስተካከል ብሎ መጠየቅ ነው ሀጢያት የሚሆነው? ከኛ ከመምህራን ወዲያ ማን ስለኛ ይጨክ፣ ይጠይቅ፣ ይናገር? መምህራን ማህበርም ሆነ ሌሎች የሚመለከታቸው የሰብዓዊና እንባ ጠባቂ ተቋማት ሁሉ በሆዳቸው ተሰንገዋል፤ አፋቸው ተለጉሟል፡፡ እኔ፣ አንተ፣ አንቺ፡ እርሶ፣ ሁላችንም ነን መጮኽ ያለብን፤ ህብረተሰቡም መንግስትም ሆኑ ሌሎች አለም አቀፍ ማህበረሰብ እንዲያውቁት ማድረግ ያለብን፡፡ ይህ የህልውና፣ የመኖር፣ የመብላት እና የእኩልነትና ፍትሐዊ ጥያቄ ነው፤ ሌላ ምንም ድብቅ አጀንዳ የለውም፡፡

ባለቅኔ ብላቴን ጌታ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን በዓለም መምህራን ማህበር ዓለም አቀፍ በዓል ላይ ተጋብዘው እንዲህ ብለው ነበር፡- ‹‹ጨለማንና ሞትን ከቶም አልቀበላቸውም፤ ፊደልንና ትምህርትን ግን አመልካቸዋለሁ፡፡ ድንቁርናንና ጨለማን ያጠፋሉ፡፡ ትምህርት ብርሃን ነው፡፡ ጭፍን ሃይል ግን ብቻውን ያው ጨለማ ነው፡፡ መምህር ብርሃንን ያሰርፃል፤ የፖለቲካ ስልጣን የሚሉት ኃይለ ፖለቲካ ግን ጨለማን ያጐዳኛል...›› (የተሰመረበት ይሄ)፡፡ ይህን ንግግር ያገኘሁት የመምህራን ድምፅ መጽሔት የ1999 ዓ.ምእትም ላይ ነው፡፡ ዋናው ቁም ነገር ለመምህሩ መብትና ጥቅም ካንተ፣ ካንቺ፣ ከኔ፣ ከእርሶ ከመምህሩ ውጭ ማን ይጠይቅ? ወኪላችን መምህራን ማህበር እንደሆነ የመንግስት ድምፅና መሳሪያ ከሆነ ቆየ፡፡ ካየነውና ከሰማነው አካያ ‹‹ሁሉም በሆዱ ተሰንጓል›› የሚለውን አባባል ከፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም ተውሼ ለአድርባይ መምህራን ማህበር ስራአስፈፃሚ ከመሰረታዊ ማህበር እስከ ኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ድረስ ያሉትን አብዛኞቹን ይገልፃል ብዬ አምናለሁ፡፡ ማህበሩ ‹ከቁም እስር ቤት› እስኪፈታ ድረስ ለኢኮኖሚያዊ መብቶቻችን የኢህአዴግ አባላት መምህራንን ጭምር መጠየቅ አለብን፡፡ እዚህ ጋር ‹‹የተከፋፈለ ህዝብ ጉልበቱን ያባክናል፡፡›› የሚለውን አባባል ከታላቁ አፍሪካዊ፣ ዴሞክራሲያዊ መሪ ኩሲየስ ኔሬሬ ላይ ወስዶ መጥቀስ ተገቢ ነው፡፡ የተከፋፈለ መምህርም ጉልበቱን ያባክናል እና ይህ መልእክት ለመምህራን እድገት፣ ህብረትና አንድ ዓላማ በጋራ መቆም የተደረገ ጥሪ ነው፡፡ ህዝብ የመረጠው መንግስት ለመረጠው ህዝብ ተጠያቂነት አለበት፣ እኛ መምህራንም የህዝብ አካል በመሆናችን መንግስት ለምንጠይቀው ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ መስጠት አለበት፡፡ እኛ መምህራን ዓይናችን እያየ በሰቆቃ ለመኖር ለምን ፈቀድን? መልሱ የተከፋፈልን የሚል ነው፡፡ እያንዳንዱ መምህር በራሱ ቅርፊት ውስጥ ይገላበጣል እንጂ የአንዱ ጉዳይ የሁሉም አልፎም የሀገር ጉዳይ ሆኖ አይታየውም፡ ፡ መምህር መሆንና በመምህራን ማህበር መታቀፍ ብቻ ‹አንድ ሆነናል› ብሎ ለመማማል አያስችልም፡ ፡ በኢህአዴግ አባላት መምህራን እና አባል ባልሆንን መምህራን መካከል ያለክፍፍል ለጋራ ጥያቄ አንድ መሆን አለብን፡፡ ተበጣጥቀን የጋራ ራዕይ፣ የጋራ ሕልም፣ የጋራ ጥያቄ የለንም፡፡ ይህ አካሄድ የትም አያደርስም፡፡

ሰው ሰራሽ ክፍፍሉን አጥብበን፣ የጀሮ ጠቢን ስጋት ተቋቁመን በዚህ ጉዳይ (የደመወዝ እርከን) ላይ ተቀራርበን እንነጋገር፣ እንወያይ፣ እንከራከር፣ በአንድ ላይ እንጨክ፡፡ ከእውነትና ከአንጀታችን ከሆነ ሕገ-መንግስታዊ መብታችን መከበሩ የማይቀር ሃቅ ነው፡፡ ህገ-መንግስቱ ያስቀመጠልንን መብቶች ተጠቅመን በሰላማዊና በሰለጠነ መንገድ ስለጥቅማችን የዘርን፣ የሃይማኖትን እና የፖለቲካ ልዩነቶቻችንን አቻችለን አንድ በሚያደርገን የህልውና ጥያቄ በአንድ ድምፅ መጮኽ አለብን፡፡

በየትምህርት ቤቱ ብዙ መሰናክሎች እንዳሉ ይታወቃል፤ በግል ማስፈራራት፣ ድምፅህን እንዳታሰማ ‹ጓደኛ መሳይ መካሪ› ፍርሃትን የሚነዛብህ ካንተው ጉያ ስላለ እሱን እየመከርክና እያስተማርክ መሄድ የግድ ነው፡፡ ከኢህአዴግ ስትራቴጂዎች ውስጥ ማደየት እና ማስፈራራት ዋናዎች እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ ማደየቱ በኛ ላይ በደንብ ተሰርቷል፤ ግን ፍርሃትን ሰፍሮ እና ለክቶ ስለማይሰጠን ፍርሃትን ማሸነፍ ያለብን አሁን ነው፡፡ ፍርሃት የሰውን የማሰብ ኃይል፣ እምቅ ችሎታ እና ስነ-ልቦናዊ ጥንካሬን የሚጎዳ፤ ይባስ ሲል የሚገድል አደገኛ መርዝ (ነቀርሳ) ነው፤ ድምፃችን ከሰለለ፣ አፋችን ከተለጎመ ፍርሃት ውስጥ ነን ማለት ነው፡ ፡ ‹‹የማይፈራውን እየፈራን፣ ፍርሃትን በራሳችን ላይ የመጫንን በሽታ ምን ጣለብን? መፍራት እኮ የሸንፈት ምልክት ነው፤ መፍራት እኮ ራስን የማዋረድ ፈቃደኝነት ነው፤ መፍራት እኮ ለራስ ከፈጣሪ የተሰጠንን የሰውነት ክበሬታ ማጣት ነው፤ ስንፈራ ይበልጥ እየተደፈርን፣ የባሰ እየተናቅን፣ ጭርሱን ከሌለን ላይ ተበድረን እንድንፈራና የበታችነት አድሮብን አንገተ-ሰባራ እንድንሆን የሚያደርገን ነው፡ ፡›› (ደበበ እሸቱ (2002)፡- የእምነቱ ፈተና፤ ከምርጫ 97 ቃሊቲ እስራት... ገጽ 83፤ የተሰመረበት የኔ)፡፡ መጀመሪያ ፍርሃታችንን አሸንፈን ነው መብታችንና ጥቅማችንን የምናስከብረው፡፡ የተባበረ ድምፅ ይሰማል፤ የብዙሃን ጥያቄ ምላሽ ያገኛል፡፡

እውነትን ይዘን በሰላማዊና በሰለጠነ መልክ በአንድነት እና በህብረት ‹በአንድ ልብ› እስከቆምን ድረስ ጥያቄዎቻችን ይመለሳሉ፤ አሸናፊ እኛ ጭቁን መምህራን ነንም፣ እንሆናለንም፤ የሞራል እና የስነ ልቦና የበላይነትም ከኛ ጋር ነው፡፡

የዩኒቨርስቲ ህይወት እና የሱስ ወጥመድ

የድባብ ድባብ

መጋቢት 17/2004ዓም ሰኞ ማለዳ 4:30 ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ስድስት ኪሎ ጊቢ ፊት ለፊት ከሚገኘው ድባብ መናፈሻ ተገኘሁ፡፡ መናፈሻው ውስጥ 25 ሰዎች ተቀምጠዋል፡፡ ሁሉም ወጣት ፊት ያላቸው ናቸው፡፡ ከ25ቱ ወጣቶች አስራ ሶስቱ እያጨሱ ነው፡፡ ገሚሶቹ ባንድ እጃቸው ደብተር ወይም ሀንድአውት ይዘው፣ በሌላኛው እጃቸው ጣቶች መሀል ሲጋራ ሽጉጠዋል፡፡ ሌሎቹ ደብተር ላይ ተቀምጠው ሲጋራውን እየማጉት ነው፡፡ እዚህም እዚያም የሲጋራ ጭስ ቡልቅ ቡልቅ ይላል፡፡ እንደጠንቋይ ቤት መናፈሻው በጭስ ታፍኗል፡፡ ጭስ ማውጫው እንደተሰበረበት መኪና ከወጣቶቹ አፍንጫ ጭስ ይንቦለቦላል፡፡ ድባብ የማጨሻ ፓርክ የሆነ ይመስላል፡፡ መናፈሻው የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች ማረፊያ ፌርማታ ነው፡፡ ወጣት ሱሰኞች መልህቃቸውን እዚህ ይጥላሉ፡፡

ቸርነት በቀለ የዩኒቨርስቲው ተማሪ ነው፡፡ እያጨሰ አናገርኩት፡፡ እንደሚቅም ነገረኝ፡፡ በዩኒቨርስቲ ህይወት መቃምና ማጨስን የመሳሰሉ ሱሶች የመበራከታቸው ምክንያት ከቤተሰብ መራቅ እንደሆነ ይናገራል፡፡ ‹‹የቁጥጥር አለመኖር እንደልብ ለመሆን በር ይከፍታል›› ይላል፡፡ እሱ ቀደም ሲል አልፎ አልፎ ይቅም የነበረ ቢሆንም ዩኒቨርስቲ መግባቱ ነፃነት ስለሰጠው ማጨስም እንደጀመረ ይገልፃል፡፡ ቸርነት ቋሚ ቃሚ ከሚባሉት ውስጥ የሚመደብ ሲሆን መጠጡንም /እሱ ‹ጨብሲ› ይለዋል/ እንደሚሞክር ይናገራል፡፡

ሱራፌል (ስሙ የተቀየረ) ቀላ ያለ ወጣት ነው፡፡ ሲጋራውን በእጁ ይዞ ጫትና ሲጋራ ብቻ ሳይሆን ሀሽሽም በዩኒቨርስቲው ተማሪዎች እንደሚጨስ አረዳኝ፡፡

‹‹ከዓመታት በፊት እዚሁ ድባብ መናፈሻ ከጀርባው ሀሽሽ የሚያጨሱበት ቦታ ነበር፡፡›› አለኝ፡፡ ሱራፌል ራሱም ቢሆን ሀሽሹን መሞከሩን አልደበቀኝም፡፡ ጥቂት ሴቶች ሲገቡ አያለሁ፡፡ ሲጋራ እያጨሱ ወጥተው ይሄዳሉ፡፡ ጠየም ያለች ወጣት ገባች፡፡ ፈራ ተባ እያልኩ አናገርኳት፡፡

ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ በ2002 ተመርቃለች፡፡ ሲጋራዋን እያቦነነች መቃምና ማጨስ በሴቶችም ዘንድ አዲስ ወይም ብርቅ እንዳልሆነ ነገረችኝ፡፡

‹‹እንደወንዶቹ ባይሆንም ዶርም ውስጥ በደምብ ይቃማል፣ ይጨሳልም፡፡›› አለች፡፡

የድባብን ድባብ ስታዘብ ለረጅም ሰዓት ቆይቼ 7:00 ሰዓት ላይ ወጣሁ፡፡

ሰባት ሰዓት ላይ መናፈሻው ውስጥ የነበሩ ሰዎች (ተማሪዎች) ቁጥር 43 የነበረ ሲሆን አስሩ እያጨሱ ነበር፡፡

የጠወለጉ አበቦች፣ የመከኑ ፍሬዎች

አንዱ ዓለም ወደ ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ሲገባ በጭምትነቱ የሚታወቅ ሰው ነበር፡፡ ፍፁም ሰላማዊና ተስፋ የሚነበብበት ተማሪ፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የጠበቀ ወዳጅነት በመመስረቱ ‹‹ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚተኛው ልጅ›› ተብሎ የመጠቀስን ማዕረግ አግኝቶ ነበር፡፡

ነገር ግን ነገሮች እንደነበሩ አልቀጠሉም፡፡ አንዱአለምም አንዱአለምን እንደሆነ አልዘለቀም፡፡ በቀድሞ ባህሪያቱ ፈንታ ሌላ ባህሪያትን ወርሶ ሌላ አንዱዓለም ሆነ፡፡ መቃም ጀመረ፡፡ ማጨስ ጀመረ፡፡ መጠጣትን በላዩ ላይ ጨመረ፡፡ አንዱዓለም የሱስ እስረኛ፣ የሱ ምርኮኛ ሆነ፡፡ በጊቢው ማህበረሰብ ዘንድ ‹‹በጀዝባነቱ›› እውቅናን አተረፈ፡፡ በመጀመሪያው ዓመት የመጀመሪያ ሴሚስተር ሶስት ነጥብ ስምንት ያመጣው ጉበዙ፣ በጊቢው አጠራር፣ ‹‹ሰቃዩ›› ተማሪ ቁልቁል ተንሸራተተ፡፡

በዚህ ቢያበቃ መልካም ነበር፡፡ ነገር ግን ይህም በቂ ሆኖ አልተገኘም፡፡ የአንዱዓለም ጤንነት መቃወስ ጀመረ፡፡ የአእምሮ መታወክ ደርሶበት ትምህርቱን ለማቋረጥና በወላጆቹ ለመወሰድ ተገደደ፡፡

የአንዱዓለም ዓይነት ታሪኮችና ተመሳሳይ የዩኒቨርስቲ ህይወት ትርክቶች ጥቂት አይደሉም፡፡ ዩኒቨርስቲ ሲገቡ ብዙዎች ለሱስ ችግር ይጋለጣሉ፡፡ ቀድሞውኑ ሱስ ጀምረው የነበሩ የሚብስባቸው ሲሆን፣ ከዛ ቀደም ምንም ተሞክሮ ወይም ልምድ የሌላቸውም ከሱስ ጋር በሰፊው ይተዋወቃሉ፡፡

ከሀዋሳ ዩኒቨርስቲ በህግ የመጀመሪያ ዲግሪውን ያገኘው አንተነህ አለባቸው በዩኒቨርስቲው በሱሰኝነቱ ከዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ በንዑስ ማህበረሰብነት ይጠቀስ የነበረ ቡድን እንደነበረ ያስታውሳል፡፡ በምህፃረ ቃል መጀንግ ተብሎ ይጠራል፡፡ ሲተነተን ‹‹መላ ጀዝባ ንቅናቄ ግንባር›› ማለት ሲሆን ይህ ቡድን የሚታወቀው ሱሶችን በማዘወተር ነው፡፡ ‹‹ጫት ይቅማሉ፤ ሲጋራ ያጨሳሉ፤ መጠጥ ይጠጣሉ፤ ሀሽሽም የሚወስዱ አሉ፡፡›› ሲል ያብራራል፡፡

አንተነህ እነዚህን ተማሪዎች ሲገልፅ ‹‹ከጊቢው ማህበረሰብ ባብዛኛው ራሳቸውን ያገለሉ፣ ማህበራዊ ግንኙነታቸው የቀዘቀዘ፣ ራሳቸውን የጣሉ፣ የማህበረሰቡ ህግና ደንብ ግድ የማይላቸውና በራሳቸው ዓለም የሚኖሩ ናቸው፡፡›› ይላል፡፡

ጊቢ ከገቡ በኋላ አብዛኞቹ ጥሩ ማህበራዊ ግንኙነት የነበራቸውና መልካም ባህሪ የነበራቸው ቢሆንም ሱሰኝነት ሲመጣ እነዚህ ነገሮች እንደሚቀየሩ ይናገራል፡፡ የሚያውቃቸውን ‹‹የጠወለጉ አበቦች›› ሲያስታውስም ሀዘን ይሰማዋል፡፡

ይህን ለማብራራትም በቅርብ የሚያውቀውን የዮናስን ታሪክ ያወጋል፡፡ ዮናስ ዩኒቨርስቲ ከመግባቱ በፊት ሱስ የሚባል ነገር አያውቅም ነበር፡፡በመጀመሪያው ሰሞን የዩኒቨርስቲ ቆይታው ተግባቢና ጥሩ ተማሪ ነበር፣ በኋላ ግን መለወጥ ጀመረ፡፡ መቃም፣ ማጨስ አዘወተረ፡፡ የ3 ዓመት የManagement ትምህርቱን ለማጠናቀቅም ድፍን ሰባት ዓመት ፈጀበት፡፡

የምርቃቱ ዕለት የሆነውንም እንዲህ ይገልፃል ‹‹ወንድምየው ሊያስመርቀው መጥቶ እሱ በቦታው አልነበረም፡፡ ጠፋ፡፡ ወንድምየው ፈልጎና አስፈልጎት በመጨረሻ ጫት ቤት ተገኘ፡፡››

አሁን ያለበትን ሁኔታ ሲናገርም፤

‹‹ጫት ነጋዴ ሆኗል፡፡›› በማለት ነው፡፡

የሱሱ ክትያዎች

ሱስ ሱስን ይወልዳል፡፡ ሱሰኞቹ ብዙ ጊዜ በአንድ ሱስ አይቆሙም፡፡ የብዙ ተማሪዎች ተሞክሮ እንደሚነግረን ከአንዱ ሱስ በኋላ ሌላ ሱስ ይከተላል፡፡ ጫት ከተጀመረ በኋላ ጫቱ ከሰውነት ጋር እየተላመደ ሲመጣ ለምርቃና ጥሩ ነው በሚል ሲጋራው ይጀመራል፡፡ የጫቱን ተፅዕኖ ወደማታ ላይ ለማጥፋት ሲባል ደግሞ ‹ጨብሲ› ይወሰዳል፡፡

‹‹አብዛኞቹ መጠጥ የሚጀምሩት በቢራ ሲሆን በኋላ ግን ገንዘብ ስለሚያጥራቸው ወደ አረቄ ጠጪነት ይመጣሉ፡፡›› ይላል በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በስነ-ጽሑፍ ሁለተኛ ዲግሪውን የሰራው ሙሉቀን በላቸው፡፡

ተማሪዎቹ ሱሰኛ ከሆኑ በኋላ ራሳቸውን የሚጥሉና ለአለባበሳቸው የማይጨነቁ የሚሆኑ ሲሆን ተጨማሪ አመሎችም የሚያበቅሉ አሉ፡፡ መቃሚያና መጠጫ ሲያጡ ወደ ስርቆት ይሰማራሉ፡፡ ወደዩኒቨርስቲ ሲገባ ጨዋ የነበረ በኋላ ግን በሱሰኝነቱ ምክንያት ለሱሱ ማርኪያ በሌብነት የታወቀ ልጅ ታሪክ ያወራል ሙሉቀን፡፡ ከተማሪ ልብስና ጫማዎች እስከ ካፌ ዕቃዎችና ዳቦ አውጥቶ ይሸጥ እንደነበር ይናገራል፡፡

ሱሰኞቹ ተማሪዎች ከሌሎቹ ተማሪዎች ጋር ለመቀራረብና ለመግባባት የማይደፍሩና ራሳቸውን ያገለሉ በመሆናቸው ከሴቶችም ጋር ቅርርብ የላቸውምና ዓይናቸውን የሚጥሉት ወደውጪ ነው፡፡ ሙሉቀን ‹‹ከሴተኛ አዳሪዎች ጋር ግንኙነት ይፈጥራሉ›› ይላል፡፡ ይህም ኤችአይቪ ጨምሮ ለሌሎች ተዛማች በሽታዎች ተጋላጭ ያደርጋቸዋል፡፡

ጀዝቦች ከዩኒቨርስቲ በኋላ

ጀዝባዎች ተመርቀው ሲወጡ ሱሳቸውን ትተው መደበኛ ሰው የሚሆኑ ባይጠፉም አብዛኞቹ ግን ከተጣባቸው ሱስ ጋር በቀላሉ የሚላቀቁ አይደሉም፡፡ ከነሱሳቸው ወደ ስራው ዓለም ይገባሉ፡፡ ይህም ስራቸው ላይ ተፅዕኖ ሲያሳድር ይታያል፡፡ በጊዜ ቢሮ የማይገቡ ሰራተኞችና ክፍል የሚቀጡ መምህራን ስለመብዛታቸው አሌ የሚባል አይደለም፡፡

ሙሉቀን መደወላቡ ዩኒቨርስቲ ስለተመደበና ትምህርቱን ስለጨረሰ አንድ የሚያውቀው ተማሪ ሲናገር

‹‹ስራ ጀምሮም እንደዛ ነው.. የራሱን ስልክ በየጊዜው ይሸጣል ብር አይበቃውም፡፡›› ይላል፡፡ ስለልጁ ሲጠየቅ አድራሻውን የሚናገረውም በእርግጠኝነት ነው፡፡ ‹‹ፒያሳ አካባቢ ካሉ ጫት ቤቶች በአንዱ አታጣውም›› በማለት፡፡

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በጂኦግራፊ የተመረቀው አህመድ አብዱራህማን ዩኒቨርስቲ እያለ ይቅምና ሀሽሽ ይጠቀም የነበረ ጓደኛው አሁንም እንደዛው እንደሆነ ይናገራል፡፡ ‹‹እንደውም ብሶበታል!›› ይላል ኮስተር ብሎ፡፡

ወደሱስ የሚገፋው ምንድን ነው?

ለሱሰኝነት የሚዳርጉ ምክንያቶች የተለያዩ ሆነው ይጠቀሳሉ፡፡ በህብረተሰብ ጤና ሁለተኛ ዲግሪያቸውን የሰሩት እና በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ መምህር የሆኑት አቶ ቴዎድሮስ ጌታቸው በዋናነት የሚጠቅሱት አራት ነገሮችን ነው፡፡ የትምህርት ጫና፣ የአቻ ግፊት፣ አዲስ ነገር የመሞከር የወጣትነት ባህርይ እና ዩኒቨርስቲዎቹ ያሉበት ሁኔታ፡፡

የትምህርት ጫና ውጥረታቸውን ለማርገብ ወደ ሱሶች እንዲሄዱ ሊያደርግ የሚችል ሲሆን ወጣትነት በራሱም አዲስ ነገር ለመሞከር በጀብደኝነት ስሜት እንዲነሳሱ ሊያደርግ ይችላል፡፡ የአቻ ግፊት ደግሞ ለምሳሌ ከዶርም አባላት ወይም ከጓደኞች ላለመለየት ሲባል ወደሱሱ እንዲገባ ሊያደርግ ይችላል፡፡ የዶርም አባላት ወይም ጓደኞች የሚቅሙ ከሆነ ጫትን ለመጀመር ግፊት ይኖራል፡፡

መምህሩ የዩኒቨርስቲዎቹ ሁኔታም አስተዋጽኦ ሊያበረክት እንደሚችል ይገልጻሉ፤ የመዝናኛዎችን እጥረት በመጥቀስ፡፡ ዩኒቨርስቲዎች በመዋኛ ገንዳዎች፣ ፑል መጫወቻዎችና የተለያዩ ስፖርታዊ ክንውኖችን መከወኛ ቦታዎችና እድሎች ሊፈጥሩ እንደሚገባም ይናገራሉ፡፡

ይግዛው ከበደ “Cigarette smoking and Khat chewing among college students in north west Ethiopia” በሚለው ጥናታቸው ከሚቅሙ ተማሪዎች 40.5 ከመቶዎቹ በንባብ ጊዜ ንቁ ለመሆን የሚቅሙ ሲሆን፣ 33 በመቶዎቹ የሚቅሙት ከጓደኞች ጋር ለመዝናናት ነው ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ 6.1 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ከጫና ለመገላገል፡፡ እንዲሁም 13.9 በመቶዎቹ በአቻ ግፊት ምክንያት የሚቅሙ ናቸው፡፡

የአጫሾቹ ሁኔታም በተመሳሳይ መልኩ በቁጥር የተቀመጠ ሲሆን 24.8 በመቶዎቹ ከጫና ለመገላገል፣ 6.9 በመቶዎቹ በንባብ ጊዜ ንቁ ለመሆን፣ 43.4 በመቶዎቹ ከጓደኞች ጋር ለመዝናናትና 20 በመቶዎቹ በአቻ ግፊት ምክንያት ያጨሳሉ፡፡

ጥሩ ውጤት ለማምጣት በሚል ሰበብ ለጥናት ሲሉ የሚቅሙ ያሉ ቢሆንም አያና እና መኮንን በተባሉ አጥኚዎች “Khat (catha edulis forsk) chewing, social demographic description and its effect on academic performance, Jimma university students 2002.” በሚል ርዕስ የተጠናው ጥናት ፉርሽ አድርጎታል፡፡ ጥናቱ በተማሪዎች ጠቅላላ ውጤት እና ጫት በመቃም ወይም ባለመቃም መካከል ልዩነት አለ ይላል፡፡ አያናና መኮንን በጥናታቸው ‹‹ይህ ጫት መቃም የትምህርት አቋምን ለማሻሻል የማይረዳ መሆኑን ሊያሳይ ይችላል፡፡›› በማለት ይገልፃሉ፡፡

ቸልታው ይቅር

ለዩኒቨርስቲ ህይወት የሱስ ወጥመድነት በሚመለከታቸው አካላት ዘንድ የሚታየው ቸልታ ተጠቃሽ ነው፡፡ የተጠናከረ ጥበቃና ቁጥጥር በየዩኒቨርስቲዎቹ እንደማይደረግ ይነገራል፡፡ አቶ ቴዎድሮስ የጠበቀ ቁጥጥር አለመኖሩን እንደችግር ያነሳሉ፡፡ ድባብ እያጨሰች ያገኘኋት የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ምሩቅዋ አስቴር በጊቢያቸው ቁጥጥሩ በጣም የላላ እንደነበር ትናገራለች፡፡ ሴቶች ምንም ስለማይፈተሹ ጫቱ በሴቶች በኩል ወደጊቢ ይገባ እንደነበር ትጠቅሳለች፡፡ ወንዶቹም ላይ ቢሆን ግን ይህን ያህልም ፍትሻ እንዳልነበረ ነው የምትናገረው፡፡

‹‹ምናልባት ከተገኘብህም›› ትላለች ‹‹አሪፍ ከሆነ ዘበኞቹ ለራሳቸው ያደርጉታል፣ ይቅሙታል፤ ካልሆነ ግን ይበተናል፡፡ የተቀጣ ግን አይቼ አላውቅም፡፡›› ስትል የኖረችውንና ያየችውን ትተርካለች፡፡

በዩኒቨርስቲ ጊቢዎች ዙሪያ በሱቅ ፈንታ በርካታ ጫት ቤቶች ተከፍተው ይታያሉ፡፡ በዚህ ረገድም ክትትል የሚያደርግ አካል የለም፡፡ ስለዚህ ተማሪዎቹ ተጋላጭነታቸው ይጨምራል፡፡

በሀገሪቱ ካሉ ዩኒቨርስቲዎች ካንዱ የተመረቀችው ሰላም ክፍሌ (ስሟ የተቀየረ) በዩንቨርስቲው ጊቢ ውስጥ ሀሽሽ የተከሉ ተማሪዎች እንደነበሩ ትናገራለች፡፡ ‹‹ይህን ያክል ዩኒቨርስቲው የት ሄዶ ነው?›› ስትል ትጠይቃለች፤ በአስተዳደርና በጥበቃ በኩል የነበረውን ችግር ስትገልፅ፡፡ ለጉዳዩ ከወዲሁ ትኩረት ካልተሰጠ የሚጠወልጉ አበቦች እየበረከቱ የሚሄዱና ችግሩም የሚባባስ ይመስላል፡፡

የተባበሩ ጩኸቶች… ከገፅ 5 የዞረ

ውጤት ገፍቶት ሊሆን ይችላል፡፡

የመምህር ፖለቲካ

በኢትዮጵያ የፖለቲካ አውድ ላይ መምህር የአንበሳውን ድርሻ ይይዛል፡፡ ለምሳሌ ለታላቁ የየካቲት አቢዮት ፍንዳታ የመጨረሻው ‹‹ካምሱር›› የኢትዮጵያ መምህራን የካቲት 11 ቀን 1966 ዓ.ም. ‹‹ሴክተር ሪቪዩ›› በሚል ተዘጋጅቶ የነበረውን አዲስ የትምህርት ስርዓት በመቃወም የተቃውሞ ሰልፍ ማድረጋቸው ነው፡፡ በወቅቱ የነበረው መምህራን ማህበር ነፃ፣ በራሱ የሚተማመን፣ ተለጣፊ ያልሆነ ነበረ፡፡ ለዚህም አስረጅ የሚሆነው አብዮቱ ተቀጣጥሎ ደርግ ከተመሰረተ በኋላም ‹‹ደርግ በጥቅማ ጥቅም ተታሎ አብዮቱን ትቶ ወደካምፑ ሊመለስ ይችላል›› የሚል ስጋት ተፈጠረ፡፡ ይህን ጊዜም የመምህራን ማህበር ለደርግ እንዲህ የሚል ግልፅና አጭር ማስጠንቀቂያ ፃፈ፡-‹‹…በያዝከው ብትቀጥል አለንልህ፣ ብታፈገፍግ ግን አለንብህ››፤ እንዲሁም ደርግ ስልጣን ከያዘ በኋላ አምባገን አካሄዱን በመቃወም የተለያዩ መግለጫዎችን አውጥተዋል፤ወታደራዊው መንግስትም የመምህራን ማህበር ጽህፈት ቤትን ከቦ የማባዣ ማሽኖችን ለመውሰድ ሞከረ፡፡ ሆኖም አልተሳካለትም፡፡ ሙሉ ታሪኩንም ከክፍሉ ታደሰ ‹‹ ያ ትውልድ›› ቅፅ 1 መፅሀፍ ላውርድልህ፡-

‹‹ወታደራዊ መንግስቱ ምን እርምጃ ሊወስድ እንደሚችል መምህራኑ ቀድመው ተገንዝበው ኑሮ፣ ውሳኔዎቹን ያዘለው ጽሑፍ ሌላ ቦታ እንዲታተም አድርገው፣ ‹እኛም አውቀናል ጉድጓድ ምሰናል› በማለት ጽሑፍ አወጡ፡፡ የጽሑፉ አርእስት ስለአይጧና ድመቷ ከተጻፈው አጭር ታሪክ የተወሰደ ሲሆን፣ አይጧ ከጉድጓዷ እስክትወጣ ድረስ ድመቷ አድፍጣ ትጠብቅ ኑሮ፣ አይጢት ብቅ ስትል ድመት ልትከመርባት ፈጥና ተንቀሳቀሰች፡፡ ሌላ መሸሸጊያ አዘጋጅታ ትጠብቅ የነበረችው አይጢት፣ ከሌላኛው ጉድጓድ አፋፍ ላይ ቆማ ‹እኛም አውቀናል ጉድጓድ ምሰናል› በማለት አላገጠች፡፡››

ይህ ነው የአንድ ማህበር የጥንካሬ መገለጫ፡፡ የደርግ ውድቀት ማግስት አካባቢም የነበረው የማምህራን ማህበር ጠንካራ ሊባል ይችል የነበረ ነው፡፡ መሪዎቹም እንደ ዶ/ር ታዬ ወልደሰማያት ያሉ መንፈሰ ፅኑና አቋም ያላቸው ምሁራኖች እንደነበሩ የትላንት ትዝታ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት ያለውን የመምህራን ማህበር ማንሳት አልፈልግም፡፡ ይህ ማህበር የሚተነፍሰው በ‹‹ፖለቲካ ሳምባ›› ነውና፡፡ ለዚህ ማህበርም ትልቁ የስራ ድርሻ ከመምህሩ ላይ ወርሃዊ መዋጮ መሰብሰብ ነው፡፡ የመምህሩ እና የማህበሩ ግንኙነትም እዚህ ድረስ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ በተረፈ የመምህሩ መብት ተናደ፣ተገነደሰ፤ መምህሩ የፓርቲ አባል አልሆንም ስላለ ከስራ ተባረረ ወይም የተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊ ተብሎ ታገደ… ሲባል ማህበሩ ትንፍሽ ሲል አይሰማም፡፡

መቼም ከዚህ በኋላ ማህበሩ እና መምህሩ በአንድ መስመር ይሰለፋሉ ማለቱ ከባድ ነው፡፡ የደሞዝ ጭማሪውን አስመልክቶም በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራኖች የያዙት አቋም የተቀናጃ ባይሆንም በሂደት ለውጥ ማምጣቱ አይቀርም፡፡

የሰባ ሶስት ብር ጭማሪው ከ‹‹ቀልዳዊ አስተዳደር›› የመነጨ መታበይ ነው፡፡ በተቀረ ለቀልድ ለቀልዱማ በመምህሩ ገቢ ላይ ብዙ ቀልዶች አሉ፡፡ ለምሳሌ ያህልም እንጥቀስ፡፡ ቀልዱ የተሰማው ‹‹ትምህርት በሬዲዮ›› የሚባለውን የማስተማር ፕሮግራም ተንተርሶ ነው፡፡ እናም በሬዲዮኑ የሚያስተምረው መምህር ስለ‹‹ኢትዮጵያ የብር ኖቶች›› ክፍልፋይ እያስተማረ ነው፡፡ ትምህርቱንም በማስረጃ ለማስደገፍ ‹‹እባክዎ መምህር ለተማሪዎቹ የአንድ ብር ኖት ያሳዩአቸው›› አለ፤ መምህሩም እንደተባሉት አደረጉ፡፡ ቀጥሎም የሬዲዮኑ መምህር አምስት እና አስር ብሮችን በየተራ እንዲያሳዩአቸው መምህሩን ጠየቀ፤ መምህሩም አሳዩአቸው፡፡ በመጨረሻም ‹‹እባክዎ መምህር ለተማሪዎቹ የሀምሳ ብር ኖት እና የመቶ ብር ኖቶችን በየተራ ያሳዩአቸው?›› አላቸው፡፡ መምህሩም ከተማሪዎቹ ፊት ለፊት እንደቆመ፣ በተሰበረ ድምፅ ‹‹ተማሪዎች አሁን የተጠሩትን የብር ኖቶች የደሞዝ ዕለት አሳየችኋላሁ›› ሲል መለሰላቸው የሚል መራር ቀልድ አለ፡፡ እንግዲህ እያወራን ያለነው በደሞዝ ማግስት ሃምሳ ብር በኪሱ ስለማይኖረው መምህር ነው፡፡

መቼም መንግስት በእንዲህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ላለ መምህር ሰላሳ አንድ ብር እና ሰባ ሶስት ብር ጨምሬአለሁ ማለቱ ያው የተለመደ ቧልተኝነቱ ማሳያ ነው፡፡ ነገሩን አሰፋሪ የሚያደረገው ግን ከመምህሩ ችግር፣ ከመምህሩ ኑሮ፣ ከመምህሩ ትዳር…በተቀነሰ ገንዘብ የሚተዳደረው የመምህራን ማህበር ‹‹መምህሩ በጭማሪው ደስተኛ ነው›› ሲል በኢቲቪ ‹‹እርችት›› መተኮስ ነው፡፡

የሆነ ሆኖ በተወሰኑ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራኖች እያቀረቡት ያለው ጥያቄ ህጋዊ ሲሆን፤ ጥያቄያቸው ይፈፀም ዘንድ እየተጓዙበት ያለውም መንገድ እንዲሁ ህጋዊ እና ሰላማዊ ነው፡፡ ከወራት በፊት በዳውሮ ዞን ‹‹ፍትህና ልማት›› የለም ሲል ራሱን ያቃጠለው የኔሰው ገብሬ መምህር መሆኑንም መዘንጋት የለብህም፡፡ ለእኔ መምህር ማለት የኔሰውና ሰሞኑን ድምፃቸውን በድፍረት እያሰሙን ያሉት መምህራኖች ናቸው፡፡

ትውልድ የሚቀርፀው መምህር ነው፤ ሀገር የሚቀይረው መምህር ነው፡፡ በሀገራችን ከየትኛውም የስራ ዘርፍ ይልቅ በርካታ ዜጎች የተሰማሩበት የስራ ዘርፍም የመምህር ሙያ ነው፡፡ እናም መምህራኖቹ ይህንን የ‹‹ሰው ሀይል ካፒታል›› ይዘው ነው ጥያቄአቸውን በሰላማዊ መንገድ እያቀረቡ ያሉት፡፡ በእርግጥ ለጊዜው የመምህሩ ድምፅ ጎልቶ እንዳይወጣ ያደረገው ራሱ መምህሩ ለአመታት ‹‹ሎሌ›› ሆኖ የመቆየቱ ልማድ ነው፡፡ ዛሬ ግን ‹‹መምህር ሎሌ አይደለም!›› ያሉ ጥቂት መምህራኖች ወደ አደባባይ እየወጡ ነው፡፡ በእርግጥ በአደባባዩ ሌላም የለውጥ ድምፅ አለ፤ የፀረ-መጅሊስ ድምፅ፡፡ ይህ ብርቱ ድምፅ ነው፡፡ ማን ያውቃል? ነገ ደግሞ የፀረ-ሲኖዶስ ድምፅ ሊሰማ ይችል ይሆናል፡፡ ፓትርያርኩ ከሲኖዶሱም ሆነ ከምዕመናኑ የተግባቡበት ሁኔታ የለም፡፡ መቼም ካለጠፋ ቦታ ገዳምን ያህል፣ ያውም ዋልድባን ስኳር ፋብሪካ ለማድረግ መንቀሳቀስ…

ዘመኑ የለውጥ ዘመን ነው፡፡ ይህ የኮከብ ትንበያ አይደለም፡፡ በመሬት ያለ የፀረ ጭቆና፣ የፀረ-ድህነት… ድምፅ ነው፡፡ እናም ከጀርመናዊ ኢ-አማኒ መማሩ አይከፋም፡፡ ‹‹…በመጨረሻም እኔ ጋ መጡ ማንም የቀረ ስላልነበረ የሚተባበረኝ አጣሁ!›› ካለው ማለቱ ነው፡፡ ሌላም ማጠናከሪያ ተመሳሳይ ታሪክ አለ፤ የጅቦች እና የበሬዎች፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡-

በአንድ መስክ ላይ ወደተሰማሩ ሶስት በሬዎች ሁለት ጅቦች ይሄዳሉ፡፡ ሶስቱ በሬዎች ነጭ፣ ቀይ እና ጥቁር ቀለም ያላቸው ናቸው፡፡ ሁለቱ ጅቦችም ከበሬዎቹ ትንሽ እራቅ ብለው ጥቁሩን እና ቀዩን በሬ ይጠሩና ‹‹እኛ ከእናንተ ጋ ፀብ የለንም፣ ፀባችን ከነጩ በሬ ጋ ስለሆነ እናንተን አያገባችሁም›› ይሏቸዋል፡፡ በሬዎቹም ‹‹እኛን ካልነካችሁን አያገባንም›› ሲሉ ይመልሱላቸዋል፡፡ ይህን ጊዜ ጅቦቹ ነጩን በሬ ለሁለት ተጋግዘው በማጋደም ዘነጣጥለው በሉት፡፡ ጅቦቹ እንደገና ከጥቂት ቀናት በኃላ ወደእዛች መስክ ተመልሰው ይሄዱና ጥቁሩን በሬ ለብቻ ጠርተው ‹‹እኛ ከአንተ ጋ ፀብ የለንም፤ ፀባችን ከቀዩ በሬ ጋር ብቻ ነው ይሉታል››፤ ጠቁሩ በሬም ‹‹እኔን ካልነካችሁኝ እንደፈለጋችሁ›› ይላቸዋል፤ ጅቦቹም ወዲያውኑ ቀዩን በሬ ዘነጣጥለው በሉት፡፡ አሁንም ይህ ከሆነ ከጥቂት ቀናት በኃላ ጅቦቹ ወደእዛች መስክ ለመጨረሻ ጊዜ ይሄዱና ብቻውን ወደቀረው ጠቁሩ በሬ ይንደረደራሉ፤ ይህን ጊዜም በፍርሃት የተዋጠው ጥቁሩ በሬ ‹‹እኔን ላትነኩኝ ውል አለን እኮ›› ሲላቸው፣ ጅቦቹም እየሳቁ ‹‹አሁንማ ምን ውል ያስፈልጋል፣ያንግዜ እኮ የተዋዋልነው እንዳትተባበሩብን ነው›› አሉና ግራና ቀኝ አጣድፈው በሉት፡፡ ትብብር ለዘላለም ይኑር! ለዚህም ነው በቀዳዳ አጮልቀህ አትመልከት፡፡ መመልከት ያለብህ በርህን ከፍተህ ወጥተህ ነው የምልህ፡፡

…በፁሁፉ መጀመሪያ ላይ ያነሳነው ካርል ማርክስ ‹‹ወዛደሮች ተባበሩ›› የሚለውን ብሂሉን በዚህ ዘመን አይን ካየከው እመነኝ ‹ተጨቋኞች ተባበሩ›› ወደሚል መፈክር ተቀይሯል፡፡ አዎን ኢትዮጵያውያን ጭቁኖች ተባበሩ፡፡ በእናንተ ህብረት ፊት መቆም የሚቻለው ማንም የለምና፡፡

ሦስቱ የእስልምና ንቅናቄዎች እና ፖለቲካዊ እንድምታቸው

ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

በ1983ዓ.ም. ኢህአዴግ ወደ ስልጣን ሲመጣ ለእስልምና እምነት ተከታዮች ደርግ ከልክሏቸው የነበረውን የሀጂ ጉዞ ፈቀደ። እንደሌሎቹ ፓርቲው እንዳስተዋወቃቸው ፖለቲካዊ ማሻሻያዎች ሁሉ በክፉልም ቢሆን የተፈቀደው የሀይማኖት ነፃነት ሃይማኖቱ ላይ የሚያተኩሩ የስነ-ፅሁፍ ውጤቶች በብዛት ወደሀገር ውስጥ እንዲገቡ ማስቻሉን ፕ/ር ሁሴን ይናገራሉ። በሀገር ውስጥም ሀይማኖቱን በሚከላከሉ እና ዕሴቶቹን በማብራራት ላይ የሚያተኩሩ መጽሔቶች እና ጋዜጦች በብዛት ሲታተሙ፣ የመስኪዶችም ቁጥር በአንፃራዊነት እየጨመረ መምጣቱን ፕ/ር ሁሴን "Islamic discourse in Ethiopia (1973-1993)›› በሚለው ዕሁፋቸው ያነሳሉ። ከዚህ መሰል ለውጦች በተጨማሪ የተለያዩ የሃይማኖቱ ማህበራት ተቋቁመዋል። እድሜያቸው አጭር ቢሆንም ከኢትዮጵያ ሙስሊም አንድነት ማህበር ጀምሮ የኢትዮጵያ ሙስሊም ወጣቶች ማህበር ድረስ ያሉት ማህበራት የተቋቋሙት በዚህ ወቅት ነበር። ሃይማኖቱን ከፖለቲካ ጋር ያስተሳሰረ የመጀመሪያ ሊባል የሚችለው እንቅስቃሴ የተደረገው በ1987 ዓ.ም. የሼሪያ ህግ እየፀደቀ በነበረው ህገ-መንግስት ውስጥ መካተት አለበት በሚል የተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ እንደነበር እነ ፕ/ር ሁሴን ይጠቅሳሉ። ፀሐፊዎቹ እንደሚሉት ከ1980ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ የተደረጉት እስልምና ነክ እንቅስቃሴዎች በዋናነት የተመሩት መሰረታቸውን እያሰፉ መምጣት በጀመሩት ሶስቱ አሻሻይ የእስልምና ንቅናቄዎች አማካኝነት ነበር። በዚህ ፅሁፍ የእነዚህን ንቅናቄዎች ሀይማኖታዊ እና ፖለቲካዊ ትርክታ በጨረፍታ እንመለከታለን።

የሰለፊ መንገድ

ከሦስቱ የእስልምና አሻሻይ ንቅናቄዎች መሀከል በአንፃራዊነት የተሻለ የታሪክ እርዝማኔ ያለው በሳዑዲ ዓረቢያ የገንዘብ እና የሀሳብ ድጋፍ የቆመው የሰለፊ /selafi/ ንቅናቄ ነው። በ1940 ዎቹ መጀመሪያ እንደተጀመረ የሚነገርለት ይህ እንቅስቃሴ በመጀመሪያ በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍል ቀጥሎም ወደ አጎራባች የኦሮሚያ አካባቢዎች መስፋፋቱን ፕ/ር ጆን አቢቢኒክ ይናገራሉ። እስራኤላዊው የታሪክ ፀሐፊ ሃጋይ ኤርሊክ በበኩላቸው በጣሊያን ወረራ ዘመን የሀጂ ጉዞ ያደርጉ በነበሩ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ንቅናቄው ወደ ሀገር ውስጥ መግባት እንደጀመረ ያወሳሉ። እንቅስቃሴውም ቀስ በቀስ ከሀረር ወደ ባሌ እና አርሲ ለመስፋፋቱ እንደ ተማምሀጂ ያሉ ፀሐፊዎች በሳዑዲ የእስልምና ትምህርታቸውን ተከታትለው በተመለሱት የአካባቢው ሙስሊሞች ሚናን አጉልተው ያነሳሉ። ስለሰለፊ የፃፉ መምህራንን በሙሉ የሚያስማማው የንቅናቄው ሀሳብ ኢትዮጵያዊ ባይሆንም ቅሉ ወደ ሀገር ውስጥ የተሰራጨው እንደሌሎች ተመሳሳይ ክስተቶች በውጪ አማንያን ሳይሆን በኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች የመሆኑ ሁኔት ነው።

የተማሪዎቹን አብዮት በመጥለፍ ወደ ስልጣን የመጣው ደርግ ንቅናቄውን ለማፈን ሙከራ ቢያደርግም ከእንቅስቃሴው ህቡዕነት እና ተጨባጭ መዋቅር አልባነት አንፃር የአፈና እርምጃውን አስቸጋሪ አድርጎታል። የሀሳቡ አራማጆች መስኪዶችን ለሀሳቦቻቸው ማስፋፊያ መድረክነት መጠቀማቸው የደርግን የማፈን ሙከራ እንዲሻገሩ አስችሏቸዋል። የድህረ-ደርግን አንፃራዊ የሃይማኖት ነፃነት እወጃን ተከትሎ የእንቅስቃሴው መሪዎች ከሌሎች ሙስሊም ሀገራት ጋር ያላቸውን ግንኙነት በተሻለ ሁኔታ አዳበሩ። በተለይም በሳዑዲ በኩል የሚመጡት ሀሳቡን የሚያብራሩ ፅሁፎች ለእንቅስቃሴው መዳበር ዓይነተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል። ደርግ ከሱማሊያ ጋር ባደረገው ጦርነት ወደ ሱማሊያ የተሰደዱ የባሌ ሰዎች ከ1983 የመንግስት ለውጥ በኋላ ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ እንቅስቃሴውን በባሌ እና አጎራባች አካባቢዎች ሊያስፋፉት ሞክረዋል።

የገባርው ፓርቲ ልሂቃን እና የእንቅስቃሴው ተቺዎች ዋሀቢ እያሉ የሚጠሩት የሰለፊ ንቅናቄ ወደ አዲስ አበባ ለመስፋፋቱ ተርጂ አስቴቦ የተባሉ የጉዳዩ ቀዳሚ ተከታታይ የኢትዮጵያ ሙስሊም ወጣቶች ማህበርን በኃላፊነት ይጠቅሳሉ። "The question of becoming: Islamic reform movements in contemporary Ethiopia" በሚለው ጥናታዊ ስራቸው በሳዑዲ ከፍተኛ ድጋፍ ሪያድ ከሚገኘው ከአለም አቀፉ የሙስሊም ወጣቶች ማህበር ጋር ጥብቅ ቁርኝት የፈጠረው የሙስሊም ወጣቶች ማህበር የሰለፊን ሀሳቦች ወደ አዲስ አበባ ወጣቶች በማስፋፋት ከፍተኛ ስራ ሰርቷል። እንደ ዶ/ር ጀይላን ገለታ ያሉ የንቅናቄው ጉምቱ ተንታኞች በዋናነት በኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚራመደውን የሰለፊ እንቅስቃሴ በአዲስ አበባ የኦሮሞ ወጣቶች ዘንድ በማስረፅ አይተኬ ሚና ተጫውተዋል። በሳዑዲ እና በኢትዮጵያው የሰለፊ ንቅናቄ መሀከል ያለው ሀሳባዊ ትስስሮሽ ጫፍ በአወሊያ ትምህርት ቤት በኩል የተገለፀ ይመስላል። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስም ትምህርት ቤቱ በአለም የሙስሊሞች ሊግ እና በአለም አቀፍ የእስልምና ሪሊፍ ድርጅት ይመራ እንደ ነበር ባኡር ኡመር "The development of Islamic population in Addis Ababa and its surroundings" በሚለው የሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ ፅሁፋቸው ይጠቅሳሉ። ይህ የሰለፊ እንቅስቃሴ ከላይ እንደተጠቀሰው ከፍተኛ የሳዑዲ ድጋፍ ቢያገኝም በአለም አቀፍ የፖለቲካ ስርዓት ውስጥ የተከሰተው የፀረ-ሽብርተኝነት ትንቅንቅ በሳዑዲ የሚደረገለት ድጋፍ እየቀነሰ እንዲመጣ እንዳገደደ ፕ/ር ዴቪድ ሺን ይናገራሉ። የቀድሞው በኢትዮጵያ የአሜሪካን አምባሳደር እንደሚሉት ኢትዮጵያ ከአሜሪካ ጋር የገባችበት የፀረ-ሽብርተኝነት የፖሊሲ ስምምነት ከሳዑዲ ለንቅናቄው የሚደረገውን የፋይናንስ እና ገንዘብ-ነክ ያልሆኑ ድጋፎች በእጅጉ እንዲቀዘቅዝ አድርጎታል።

የእስልምና ድምጽ

በታሪክ ርዝማኔም ሆነ በስፋት ከሰለፊ ቀጥሎ የሚጠቀሰው እ.ኤ.አ. በ1929 ዓ.ም. በህንዱ ሼህ ሙሀመድ ኢልያስ የተመሰረተው ራሱን ተብሊግ /Tabligh/ ብሎ የሚጠራው የእስልምና ንቅናቄ ነው። ፕ/ር ተርጂ አስቴቦ እንደሚናገሩት ይሄ ንቅናቄ ወደ ኢትዮጵያ የገባው እ.ኤ.አ. በ1970ዎቹ መጀመሪያ በደቡብ አፍሪካውያን እና የኪኒያ ዜግነት ባላቸው ህንዳውያን ሚሽነሪዎች በኩል ሲሆን እንደነ ሼህ ሙሳ መሰል የእስልምና ሊቃውንት በኩል አዲስ አበባ በሚኖሩ የጉራጊኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች መስረፅ እንደጀመረ ፕ/ሩ ይጠቅሳሉ። እንደ ተቀናቃኙ የሰለፊ እንቅስቃሴ ሁሉ ይሽኛውም በቀደመው የደርግ ዘመን ይሄ ነው የሚባል እንቅስቃሴ ባያደርግም ባለፉት ሃያ ዓመታት በተጠቀሱት ቋንቋ ተናጋሪዎች መሀከል ሰፊ መሰረት አግኝቷል። የጉዳዩ ተከታታዮች እንደሚናገሩት ከሰለፊ በተሻራሪ ገንዘብ ነክ የሆኑ የውጭ ድጋፎች ባይኖሩትም በደቡብ አፍሪካ እና በኪኒያ ያሉ የንቅናቄው አራማጆችን ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው ሀሳቡን እንዲያፍታቱ ሁኔታዎችን ከማመቻቸት በዘለለ በፓኪስታን በሚካሄደው የተብሊግ አለም አቀፍ ኮንፈረንስ ላይ ተወካዮቹን ይልካል። ራሱን በአዲስ አበባ በሚገኙ የጉራጌ ብሄር አባላት ከመወሰን ውጪ ወደ ሌሎች አካባቢዎች በተለይም ወደ ኦሮሚያ ክልል ሊያደርጋቸው የሞከራቸው መስፋፋቶች በክልሉ ጠንካራ መሰረት ባለው የሰለፊ ንቅናቄ ተገትቷል። የተብሊግ አሻሻይ እንቅስቃሴ ራሱን እንደ ሰለፊው ብቸኛው የእስልምና ወካይ አድርጎ ከማቅረብ ይልቅ የእስልምና እሴቶችን በማብራራት እና ምዕመናኑ የሃይማኖቱን ግዴታዎች እንዲፈፅሙ በማሳሰብ ራሱን እንደ እስልምና ድምፅ ይቆጥራል።

የልሂቃን መንፈስ?

በሶስተኝነት የሚነሳው የእስልምና ንቅናቄ በ1980ዎቹ መጀመሪያ ላይ በዋናነት በአዲስ አበባ በሚገኙ ከተሜ የእስልምና ምሁራንን ያሰባሰበው አንዳንዶች ‹‹ሽክዋን›› ብለው የሚጠሩት ምሁራዊ መሰል እንቅስቃሴ ነው። የጉዳዩ ተከታታዮች እንደሚከራከሩት በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ እና ሌሎች ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት አካባቢ የተደራጀው ይህ ስብስብ እንደተቀሩት ሌሎች ንቅናቄዎች የእስልምና እሴቶችን ከማረም ይልቅ ሙስሊሞች ሁሉ ትናንሽ ልዩነቶቻቸውን ተሻግረው ለሃይማኖታቸው በአንድነት እንዲያድሩ ይሰብካል። ራሳቸውን ‹‹አሚር›› ብለው በሚጠሩ የእንቅስቃሴው ወካዮች አማካኝነት የጥናት ክበቦችን፣ አንዳንዴ ህቡዕ አልፎ አልፎ ደግሞ ግልፅ ህዝባዊ መሰል የማስተማሪያ መድረኮችን በማዘጋጀት ሀሳቦቹን ለማስረፅ ይሞክራል። ዋነኞቹ አባላቱ በአለማዊው ትምህርት የገፉ እንደመሆናቸው መፅሐፍትን በማሳተም እስከ 1987 ዓ.ም. ድረስ በገበያ ላይ በነበረው ቢላል መጽሔት ሀሳቦቻቸውን በመተረክ ከከተሜነታቸው ጋር በተያያዘ ከቀደሙት አባቶቻቸው የእስልምና ተግብሮት የተነጠሉ የተማሩ ከተሜ ወጣቶችን ወደ ራሱ ሰብስቧል።

ስለ ፖለቲካዊ ገፃቸው

ከላይ በተተረኩት ንቅናቄዎች መሀከል አንዳንድ ጊዜ መሰረታዊ የሚባሉ የግጭት መስመሮች ይታያሉ። የተብሊግ እንቅስቃሴ ራሱን ሃይማኖቱን ከሚመለከቱ የሥነ-መለኮት ንትርኮች ነፃ ማድረጉ ከሌሎቹ ሁለቱ እንቅስቃሴዎች ጋር ያለውን ተመሳሳሉም ሆነ ልዩነት እንዳንመለከት ያግዳል። በምሁራኑ ንቅናቄ እና በሰለፊ መሀከል ያለው መራራቅ አንዱ አንዱን እስከማውገዝም ይሻገራል። የ‹‹ሽክዋን›› አራማጆች ሰለፊዎችን ‹‹ያልሰለጠኑ›› ሲሉ ይተቿቸዋል። ሰለፊዎች በተቃራኒው ራሳቸውን በዘመናዊነት ያልተበከለው የቀደሙት አበው ሃይማኖት አራማጆች አድርገው ያቀርባሉ። የሰለፊ ሃይማኖታዊ ሙግት የሚያተኩረው የንቅናቄው ሀሳቦች ብቸኞቹ የእስልምና እውነቶች እንደሆኑ አድርጎ መከራከሩ ላይ ነው። ሌሎቹን ሀገር በቀል የእስልምና ሃይማኖታዊ አተገባበሮች ከሃይማኖቱ የተነጠሉ አድርጎ ይቆጥራቸዋል። ወደተለያዩ የሃይማኖቱ ቅዱስ ቦታዎች የሚደረጉትን ሃይማኖታዊ ጉዞዎች ከማውገዝ በዘለለ የመውሊድን መከበር አይቀበልም። ከዚህ ባለፈ ተከታዮቹ አለባበሳቸው ላይ ጥብቅ እንዲሆኑ ያሳስባል። ልሂቃኑ የእስልምና ሀዳሮች እስልምና የትኛውንም የብሔር አጥር መዝለል እንዳለበት ሲሰብኩ፤ የሰለፊ ተከታዮች ከኦሮሞ ፖለቲካ ጋር እስልምናን ለንቅጠው የፖለቲካ ልባስ ሊሰጡት ይሞክራሉ። የሰለፊ ንቅናቄ እንቅስቃሴውን ከተለምዶው ፅንፈኛ የኦሮሞ የፖለቲካ ተዋስኦ ጋር አዛምዶ ያስበዋል። በቀዳሚነት የንቅናቄው አባላትም ሆነ የአሻሻይ ሀሳቦቹ ወካዮች ከኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪ ውስጥ መሆናቸው ለዚህ መሰል የሃይማኖት እና የብሄር ፖለቲካ መለንቀጥ አስተዋፅኦ አድርጓል። በ1980ዎቹ መጀመሪያ አነግ ወደ ባሌ እና መሰል የኦሮሚያ አካባቢዎች ሲደርስ ከዚህ የንቅናቄው አባላት ከፍተኛ ድጋፍ አግኝቶ ነበር። እንደ ሞቴ ቢያ ያሉ ፀሐፊዎች የእስልምናን ወደ ኦሮሚያ መስፋፋት በአፄ ሚኒልክ ተካሂዷል ብለው የሚያምኑትን የቅኝ-ግዛት መስፋፋት ለመግታት እንደተሞከረ ሁነት አድርገው የሚከራከሩበትን ጭብጥ የሰለፊ ንቅናቄም አብዝቶ እንደሚሟገትለት ፕ/ር አቢቢኒክ "An Historical Anthropological approach to Islam in Ethiopia: Issues of identity And politics" በሚለው ጥናታዊ ፅሁፋቸው ይተነትናሉ። የኦሮሞን ጥያቄም በተመለከተ በኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስት ውስጥ ከቁጥራችን የሚቀራረብ ውክልና ሊኖረን ይገባል ይህ የማይሆን ከሆነም ኦሮሚያን ለመገንጠል እንሰራለን የሚለው ፖለቲካዊ አቋም እንዳላቸው በአጥኚዎቹ መጠቀሱ አደናጋሪ አቋም ያንፀባርቃል።

ራሱን ‹‹ሽክዋን›› ብሎ የሚጠራው የልሂቃኑ ስብስብ ፖለቲካዊ ገፅ እንደ ፕ/ር ሁሴን አህመድ ላሉ የጉዳዩ አጥኚዎች ግልፅ ነው። ፕ/ር ሁሴን "Islamic literature and religious revival in Ethiopia (1991-1994)›› በሚል ርዕስ ባሳተሙት ጥናት እንደሚሉት ይህ ከተማ ተኮር እንቅስቃሴ የርዕዮተ-ዓለሙን መሰረት የተዋሰው ከግብፅ የሙስሊም ወንድማማቾች ስብስብ ነው። የስብስቡ አባላት ሙስሊም ወንድማማቾች የሚታተሙ የስነ-ፅሁፍ ውጤቶችን ኢትዮጵያዊ ልባስ በመስጠት ብዙውን ጊዜ በብዕር ስም በቢላል መጽሔት ላይ ያሳትሙ እንደነበሩ ፕ/ሩ ያወሳሉ። የኢትዮጵያ ሙስሊሞች በሀገሪቱ ውስጥ በተከሰቱት ተከታታይ የፖለቲካ ስርዓቶች ደርሶባቸዋል የሚባሉትን በደሎች ደጋግሞ በማነሳሳት እኒህ የጎሉ ሃይማኖታዊ ኢ-እኩልነቶችን ለመፈወስ ሙስሊም ምሁራን ወደ ኢትዮጵያ የፖለቲካ አደባባይ እንዲመጡ አብዝቶ መሟገቱ ዋነኛ መለያው ነው።

እንደ መውጪያ

በዕሁፍ መግቢያ ላይ እንዳነሳነው የዚህ ፅሁፍ ግብ በእስልምና ተዋስኦው ውስጥ ጉልበት እያገኙ ስለመጡት ዋነኞቹ ሀይማኖታዊ አሻሻይ ንቅናቄዎች እጅግ ጥቂት ነጥቦችን ብቻ ማንሳት ነው። ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች እስከ 1983 ዓ.ም. ድረስ በነበሩት መንግስታት እና ገዢ መደቦች ወጥ ሃይማኖታዊ በደል አልደረሰባቸውም ብሎ መከራከር አግባብ አይመስለኝም። ጥቃቱ እና በደሉ ምንድረስ ነበር? ምንስ ለማሳካት ነበር? በሚሉት ጉዳዮች ላይ የማይሰማሙ የሚመስሉ ንትርኮችን ብንሰማም በዚህ ጭብጥ ላይ አብዝቶ ማተኮር ፋይዳው ብዙም ላይሆን ይችላል። የ‹‹ሽክዋን›› አራማጆች እንደሚሉት ሙስሊም ልሂቃን ወደ ኢትዮጵያ የፖለቲካ አደባባይ መምጣት ሀገራዊ ጥቅሙ ያመዝናል። ጃዋር መሀመድ አሁን የተነሳውን የፀረ-መጅሊስ እንቅስቃሴ ፖለቲካዊ ገፅን ለመፈለግ በመታተር የሙስሊሙ ጥያቄ በኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስት ውስጥም ሆነ በፌዴራል የፖሊሲ ክበቦች ውስጥ አለመወከል የፈጠረው ቅሬታ አድርጎ አቅርቦታል። ጃዋር "Growing Muslim activism and the Ethiopian state: Accommodation or repression?" በሚል ርዕስ ባስነበበው መጣጥፍ በተለምዷዊው የሃይማኖቱ ተገብሮት እና ከላይ ባየናቸው ሰለፊን መሰል እንቅስቃሴዎች መሀከል የተፈጠሩት ልዩነቶች ነው የሚለው ክርክሩ ጎዶሎ ሙግት ቢሆንም፤ በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳይ ላይ የሚፅፉ ምሁራን እጦትም ሆነ ሙስሊሙን እንደ አንድ የድጋፍ መሰረት አድርገው የሚቆጥሩ የፖለቲካ ስብስቦች የሉም የሚለውን ሙግት መቀበል አስቸጋሪ አይደለም።

አሁን የሙስሊም ማህበረሰብ መጅሊሱ አይወክለንም በሚል ብርቱ ተቋውሞ እያሰማ ነው። የተቃውሞ መሰረታቸውንም ሆነ በነሃ ሃይማኖታዊ ተቋም የመመራት ጥያቄያቸው እጅግ ትክክል ነው። ከዚህ ጥያቄ በተሻራሪ የኢህአዴግ አመራሮች እንቅስቃሴውን እስላማዊ መንግስት ለመመስረት ከመፈለግ ጋር አያይዘውታል። አቶ ሬድዋን ሁሴን ባለፈው ሳምንት ይህንን የፓርቲያቸውን አቋም በግልፅ አስረድተዋል። ለእኔ የዚህ የፓርቲው አቋም ሁለት ግቦችን ያዘለ ነው። የመጀመሪያው በዚህ ክስ መነሻነት እና ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በመከላከል ሰበብ እንቅስቃሴውን ማፈን ነው። ሁለተኛው የሌሎች ሃይማኖት ተከታዮችን በፍርሃት ውስጥ መክተት ነው። የፀረ-መጅሊሱ እንቅስቃሴ መሪዎች እኒህን የስርዓቱን ግልፅ ፖለቲካዊ ግቦች ለመግታት የመጀመሪያው ኃላፊነት ይወድቅባቸዋል። የሌሎች ሃይማኖት ተከታዮችም ይህን በስርዓቱ የሚተረከውን ፍርሃት አስራሚ መንፈስ ተሻግረው ንቅናቄውን መደገፍ ያለባቸው ይመስለኛል። እነዚህ ሁለት ሁነቶች ተሳስረው ከመጡ የስርዓቱን መሰረቶች መናድ ብዙም አስቸጋሪ አይሆንም። ሃይማኖታዊ ነፃነቶችን የማይቀበል አፋኝ ስርዓት ለመሰንበት ምንም ዓይነት የቅቡልነት መነሻ ሊኖረው አይገባምና።

ዶ/ር አድሬስ ለክቡር ፍ/ቤት ... ከገፅ 4 የዞረ

ሻዕቢያ ሊያቅድለት አይችልም።

ክቡር ፍ/ቤት፡- አሁን በአገዛዙ እየተወሰዱ ያሉት የአስር እርምጃዎች ዋነኛ ምክንያት ሽብር ስለተሞከረ፣ ወይም ስለታቀደ፣ ወይም ደግሞ የሻዕቢያ ተላላኪ ስለተገኘ ሳይሆን ዜጐች ህገ-መንግስታዊ መብታቸውን በመጠቀም የሚያቀርቧቸውን የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የሰብዓዊ መብት ጥያቄዎች ማዳፈን ነው። እስሩ ባለ ሁለት አሀዝ የኢኮኖሚ እድገት እያስመዘገበች ባለች ሀገራችን ለምን ራበን /ለምን ኑሮ ተወደደ/ ትላላችሁ ነው። ለምን የነፃነት ጥያቄ ታነሳላችሁ ነው። የእስሩ ምክንያት ለምን እኔ የምላችሁን ብቻ አትቀበሉም ነው። ለምን የለውጥ ጥያቄ ታነሳላችሁ ነው። የእሥሩ ምክንያት በአረብ አገራት የለውጥና የነፃነት ንፋስ ወደ አቶ መለስ አገዛዝም እንዳይመጣ የተወሰደ የመከላከል እርምጃ ነው።

ክቡር ፍ/ቤት፡- በሰላማዊ ፓርቲዎችና በህዝቡ የሚነሱ የዳቦ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ጥያቄዎችን በቀጥታ ከመመለስ ይልቅ የጥያቄውን ባለቤቶች የማንነታቸው መገለጫ ካልሆኑ የሽብር ድርጊቶች ጋር በማገናኘት በአባትም በእናትም ከማይገናኛቸው ሻዕቢያ ጋር በማገናኘት /በታሪክ፣ በዓላማና በስልት ከማይገናኛቸው ሻዕቢያ ጋር በማገናኘት በሻዕቢያ ተላላኪነት በመፈረጅ የህዝቡ ቀጥተኛ የለውጥና የነፃነት ጥያቄን ለማዳፈን መሞከር የትክክለኛ አዕምሮ ውጤት ነው የሚል እምነት የለኝም። እኔ አቶ ናትናኤል መኮንን የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ም/ቤት አባልና መስራች የወረዳ 2 እና 14 ሰብሳቢ /አደራጅ/፣ በሰላማዊ ትግል የማምን የኢትዮጵያ ህዝብ ሲራብ ተርቤ፣ ሲጠማ ተጠምቼ፣ ሲገረፍ ተገርፌ፣ እስሩንም መከራውንም ከህዝቤ ጋር እየተቀበልኩ ለዴሞክራሲና ለነፃነት የሚደረገውን ሰላማዊ ትግል ከሌሎች ሰላማዊ ታጋዮች ጋር በመሆን በፅናት እያካሄድኩ ያለሁ፣ ከችግሩ ባለቤት ከኢትዮጵያ ህዝብ ድጋፍና አጋርነት በስተቀር የማንንም ድጋፍ የማልፈልግና የማንንም ፍላጐት የማላስፈፅም፣ የሀገሬን ጥቅም በምንም ሁኔታ አሳልፌ የማልሰጥ፣ ኃላፊነት የሚሰማኝ፣ ኢትዮጵያዊና የአንድነት አባል ነኝ። አዎ እኔ የማንቦት ሰባት አባል ሳልሆን የአቶ መለስ ረጅም አገዛዝና ጭቆና በቃኝ ያልኩ የሻዕቢያ ተላላኪ ሳልሆን ለነፃነቴ መታገል የምችል፣ ነፃነቱን እስክ ሞት ድረስ የወደድኩ ኩሩ ኢትዮጵያዊና የአንድነት አባል እንጅ ሽብርተኛ፣ የሻዕቢያ ተላላኪና የግንቦት ሰባት አባል አይደለሁም። አያቶቹ እንዳስተማሩኝ ኢትዮጵያዊነት የርህራሔ፣ የኩራትና የነፃነት ምልክት እንጅ የጭካኔ፣ የባርነትና የውርደት ምልክት አይደለም። ስለዚህ የጭካኔ ምልክት የሆነው ሽብር ፈፃሚም አስፈፃሚም አይደለሁም። ወደፊትም አልሆንም። በሰላማዊ መንገድ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ የሚደረገውን ትግል ከድርጅቴ ከአንድነት ጋር በመሆን በፅናት የትም፣ መቼም፣ በምንም ሁኔታ ውስጥ ሆኜ እቀጥላለሁ። አዎ ያለነፃነት መኖር በቃኝ በቃኝ።

ፈጣሪ አገሬ ኢትዮጵያን ጠብቃት አሜን!!!

“አባይ ድክ ድክ እኛ ብርክርክ”



አቤ ቶኪቻው
abeto2007@yahoo.com

ወዳጄ እንዴት አሉልኝ ? እኔ ከእርሰዎ ሃሳብ እና ከፒያሳ ናፍቆት በሰተቀረ በጣም ደህና ነኝ። በዝች በምንወዳት እና በምትወደን፤ ፍትህ ጋዜጣ ላይ ባለፈው ሳምንት እከሰታለሁ ብዬ አስቤ ነበር። ግና እንዲሁ ስንደፋደፍ ሳይሳካልኝ ቀረ። ይህው እርሱ ባለው ቀን ተገናኘና!

እኔ የምልዎ ወዳጄ ሰሞኑን አባይ አንደኛ አመት ልደቱን ያከብራል ተብሎ ሽር ጉዱ ደርቶ የለ? እሰይ ይድራ እንጂ፤ ዋናው ነገር ሽር ጉድን ማድራት ነው። ሌላው ነገር ቀስ ብሎ ይመጣል። ካልመጣም ችግር የለም “እነሱ ተፍጨርጭረዋል!” የሚለው ስም ራሱ ግድቡ ከሚያመነጨው በላይ ሀይል ያመነጫል። እናም ሽር ጉድን የመሰለ ነገር የለም።

አንድ ወዳጄ ሰሞኑን በቴሌቪዥኮ “የታላቁ ህዳሴ ግድብ ከተጀመረ እነሆ አመት ሊሞላው ነው!” ሲባል ሰምቶ ጠላትዎ ድንግጥ ይበልና “ክው” ብሎ ሲደነግጥ አየሁት። ምን አስደነገጠህ? ብዬ ብጠይቀው “አባይ ገና አንድ አመቱ ነው እንዴ?” በማለት አናቱን ይዞ ጠየቀኝ። ምነው ያለ እድሜው አረጀብህ...? አልኩት ጥያቄው ቢያስገርመኝ። እሱም በንግግሬ በስጨት እያለ፤ “አይ እዳዬ እኔን አስረጀኝ እንጂ እርሱማ ምን አለበት?” አለኝ።

ይህ ወዳጄ እንደሚለው አባይ ገና አንድ አመቱ ከሆነ (በመንግስት ስሌት እንኳ) ለቀጣይ ስድስት አመት መዋጮ ማዋጣት ይጠበቅብናል ማለት ነው። እኛ ደግሞ ከወዲሁ ተዳክመናል። እናም አባይ ገና ድክ ድክ ሲል እኛን ብርክርክ እያደረገን ነው። እናም መጨረሻችንን እንዲያሳምረው መፀለይ አለብን ብሎኛል።

ለማንኛውም ጠቅላይ ሚኒስትራችን “አባይን የደፈረ መሪ!” ተብለው ከባንዲራችን እኩል ወደ ላይ ከተሰቀሉ... (ውይ የምን መሰቀል አመጣሁባቸው...? ከተውሰበሰቡ... ልበል ይሆን...? የባሰውን አመጣሁት... እኔ ልውሰብሰብሎ። አግዙኝ እንጂ ጎበዝ፤ በቃላት እጦት አኮ ጠቅላይ ሚኒስትሬን አጎሳቆልኳቸው ባንዲራ ከፍ ካለ በኋላ ምንድነው የሚሆነው...? አዎ... ጠቅላይ ሚኒስትራችን ከባንዲራው እኩል ከፍ ብለው ከደመቁልን... አንድ አመት ሞልቷቸዋል። ብዬ ልገላገል)

በነገራችን ላይ፤ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን ሰሞኑን ኬኒያ ውስጥ የላሙ ወደብ ግንባታ መጀመርን አስመልክቶ በተገኙበት ወቅት ባንዲራቸውን ዘቅዝቀው ይዘው የተነሱት ፎቶግራፍ በጣም አነጋጋሪ ሆኖ ሰንብቷል። አንድ ወዳጄ፤ “ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባንዲራችንን እንዴት ይገለብጣሉ...? ለዛውም ባለ ኮከቡን እኮ ነው። እኛ ብንሆን እንዲህ ያደረግነው “ባንዲራን የገለበጠ ይገለበጣል” የሚል አዋጅ ጠቅሰው ይገለብጡን ነበር። እሳቸው ባንዲራችንን ሲገለብጡ ማን ይገልብጣቸው...?” እያለ ያለቅጥ ሲያማርር ሰማሁት። ዝም ብለው ግዜም፤ እስከ ዛሬ የነበሩ መሪዎቻችን ለባንዲራቸው እንዴት ቀናኢ እንደነበሩ እያወሳ ወቀሳውን በጣም አበዛው።

በዚህ ግዜ እሳቸው ሲነኩብኝ የምታመመው እኔ፤ ተው እስቲ እሳቸው በስንት ስራ የተጠመዱ ሰው ናቸው እና ልብ ላይሉት ይችላሉ። አንዲት ባንዲራ ዘቀዘቁ ብሎ እንዲህ ማማረር ተገቢ አይደለም። ምንም ቢሆን አባይን የደፈሩ ባለውለታ ናቸው። ብዬ የወዳጅነቴን ላስረዳ ሞከርኩኝ። ይሄን ግዜ ወዳጄ የባሰውን ቱማ ብሎ “ይቅርታ አድርግልኝና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከዚህ በፊት ባንዲራ ጨርቅ ነው አሉ ሲባል አላመንም ብዬ ነበር። አሁን ግን በአይኔ በብረቱ ባንዲራችንን ዘቅዝቀው ሳያቸው፤ ሰውየው አባይን ሳይሆን የደፈሩት ኢትዮጵያን ነው። ብያለሁ!” አለኝ። እኔም በሆዴ ሌላ ተጨማሪ ምክንያት ቢኖረው ነው ብዬ የመማረር ነፃነቱን ሰጠሁት።

እኔ የምለው ወዳጄ ሰሞኑን ታድያ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአባይ ግድብ ዙሪያ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ ሊሰጡ እንደሆነ ሰምተናል። አብዛኛዎቹ ጥያቄዎች ግን ገና ግድቡ ሲጀመር በየ ጓዳው፣ በየ አደባባዩ ሲጠየቁ የነበሩ ናቸው ታድያ እነዚህን ግርታዎች ለማጥራት የተከበሩት ጠቅላይ ሚኒስትር፤ አንድ አመት ሙሉ ተጨነቅው የሚሰጡን መልስ አላጓጓችሁም?

ለማንኛውም አባይ መገደብ ከጀመረ አንድ አመት ሞላው። በዚች አንድ አመት ግዜ ውስጥ ስንቱን አሳለፈው? እስቲ የተወሰኑትን እንቁጠር

አንድ ፤

አባይ ላይ ሊገደብ የታቀደው ግድብ (ውይ ይቅርታ የታቀደው አልኩ እንዴ...? የምን ዕቅድ አመጣሁኝ... ዕቅድ ምናምን ለሚል ዝባዝንኬ የምናባክነው ግዜ የለንም ለካ...) ዝም ብለን አባይ ላይ የሚሰራው ግድብ... ብለን እንቀጥል። ስያሜው መጀመሪያ “ታላቁ የሚሊኒየም ግድብ ነበር” ከዛ በምን ምክንያት እንደሆን እንኳ ስሙ ተቀየረ።

ስለ ስም ቅያሬ እኔ የማውቀው አንድ ጨዋታ አለ። እንቃመሰው...

በሀገሬ በበርካታ ገጠራማ አካባቢዎች የመዞር እድሉ ገጥሞኛል። ታድያ ከዙሪት ብዛት አንዳንድ ሁነቶችን የት እንዳየዋቸው እዘነጋለሁ። ብቻ ከዞርኩባቸው አካባቢዎች በአንዱ፤ ገበሬዎች ስማቸውን ቶሎ ቶሎ ነበር የሚቀያይሩት። አምና እርገጣቸው የተባለ ሰው ዘንድሮ ታገሳቸው ሊባል ይችላል። የዚህ የስም መቃያየር ነገር ምስጢሩን በጠየቅሁበት ግዜ ምን ሆኖ ተገኘ መሰልዎ... “አዋቂ እያዘዘን ነው” አሉኝ። የምን አዋቂ...? አይባልም። የምድር አዋቂ ነው።

“ምርትህ እንዲሰምር ከብቶችህ ጤና እንዲያገኙ አትሻም?”

“አረ ጌታዬ ታድያ መባተሌ ለምን ሆነ...?”

“ስምህን ማን ነበር ያልከኝ...?”

“እልሁ... እሰኛልው ጌታዬ”

“እልሁ... እልሁ... ባዶ እልህ ምን ያደርጋል ማሽነፍ ያስፈልጋል... እልህ ብቻውን እህል አይሆንም... ትሰማኛለህ...?”

“አዎ ጌታዬ”

“እልሁ የሚለው ስም አይሆንህም። ጠላት ያበዛብሃል... ምርትህን ይቀንስብሃል... ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ አሸናፊ ብዬሀለሁ። አይዞህ ታሸንፋለህ...!”

ብለው ፊርደው የደንቡን ተቀብለው ይሸኙታል። እልሁም ዘንድሮ ስሙን አሸናፊ ብሎ ያማረ ምርት እንደሚገጥመው ተስፋ አድርጎ ይጠብቃል።

ትላንት አብዛኛውን ከገበሬው ማህበረሰብ የተውጣጡት ጀግና የኢህአዴግ ሰራዊት ታጋዮች፤ የዛሬ ባለስልጣኖች መጀመሪያ ሚሊኒየም ተብሎ ሲጠራ የነበረውን ግድብ “ህዳሴ ግድብ” ብለውታል። አዋቂ የሚለውን መስማት ጥሩ ነው። ብለን እኛም አልተጨቃጨቅንም እሺ ብለናል።

ሁለት፤

አባይ ግድብ ሲጀመር በአምስት አመት ግዜ ውስጥ ያልቃል ተብሎ ነበር። እያደር እያደር “በአምስት አመት ያልቃል የተባለው ለቀልድ ነው መቀለድ አይቻልም እንዴ?” ተባለና ወደ ስድስት አመት ተኩል ነው ወደ ሰባት አመት አደገ። ከዚህ ጋርም የተያያዘ ጨዋታ አናምጣ፤

ነብሱን ይማረውና ይህንን ጨዋታ ስብሀት ገብረ እግዚአብሄር ነበር የሆነ ቦታ የከተባት። ይችትልዎ፤

በአንድ ወቅት አንድ ሰውዬ ይኖር ነበር። ብቻውን ሳይሆን ከሚስቱ ጋር ነበር የሚኖሩት። እንዲሁ ቁጭ ብለው ሳይሆን ደግሞ አንሶላ እየተጋፈፉም ነበር። ሲኖሩ፣ ሲኖሩ፣ ሲጋፈፉ፣ ሲጋፈፉ በአንዱ ቀን ሚስት ፀነሰች። ባልም “አባት ደስ ይለዋል ልጅ ሲወለድለት” የሚለውን ሙዚቃ እያንጎራጎረ፤ ለልጁ አልጋ ሊያሰራ አንድ እውቅ አናጢ ቤት ሄደ። “ሚስቱ አርግዛልኝ ደስ ብሎኛል እስክትወልድ ድረስ ቀስ ብለህ በጥሩ ሁኔታ አንድ የህፃን አልጋ ታዘጋጅልኛለህ?” ብሎ ቢጠይቀው፤ አናጢውም “ሁሉ ሰው እንዳተ ብልህ ቢሆን ምንኛ መልካም ነበር? እንዲህ ቀደም ብለው ማዘዛቸውን ትተው ደረሰ አልደረሰ ብለው ይጨቃጨቃሉ!” ብሎ ቀድሞ ማዘዙን አመሰገነ።

ከወራት በኋላ ልጁ ሲወለድ አባት ሚስቱን “ሰርፕራይዝ” ሊያደርጋት አናጢው ዘንድ ሄደ። አልጋው አልደረሰም። “ትንሽ ቀናት ብትጨምርልኝ ይደርሳል” አለው። አባወራው እያጉተመተመ ተመለሰ። ከተጨማሪው ትንሽ ቀናት በኋላም ድጋሚ ሄዶ ጠየቀ አሁንም አናጢ ጢሙን እያሻሸ “ይቅርታ ጌታዬ ትንሽ ቀን ብንጨምርበት ጥሩ አልጋ አደርስልሃለሁ” አለው።

እያለ እያለ አልጋው ሳይደርስ የተወለደው ልጅ አደገ። ምን ማደግ ብቻ እርሱም አግብቶ አስረገዘ። ሚስቱ ማረገዟን ላባቱ ቢነግረው ግዜ አባቱም “ጎሽ እንዲህ ነው እንጂ...!” ብለው አስረጋዥነቱን ካደነቁት በኋላ፤ “አንተ ልትወለድ ስትል አንድ አናጢ ዘንድ አልጋ አዝገፎ ነበር ሂድና አመጣው ለልጅህ ይሆንሃል ሌላ አልጋ እንዳትገዛ” አሉት። ልጅም “ጎሽ ከወጪ ተገላገልኩ” እያለ በደስታ ሄደ።

አናጢውም የልጁን የወራሽነት መብት በተለያየ ማወጣጫ ካረጋገጡ በኋላ፤ ችግር የለም በጥሩ ሁኔታ ይደርስልሃል ብቻ ትንሽ ግዜ ስጠኝ አሉት ጢማቸውን እያሹ። ልጅም አንድም በአናጢው ሁኔታ፤ አንድም ይሄ ካልደረሰ የሚጠብቀውን ወጪ በማሰብ ብስጭቱ መጣ እና፤ “አባቴ እኔ ስወለድ ያዘዘው አልጋ እንዴት ለልጄ እንኳ አይደርስም? የምን ተጨማሪ ግዜ ነው የሚጠይቁኝ...?” ብሎ በቁጣ ተናገራቸው። አናጢ ሆዬ “ካፊርኩ አይመልሰኝ” ነውና፤ “አይ እንግዲህ... እኔ በስራዬ ላይ ሲያጣድፉኝ አልወድም” አሉት። ብሎ ስብሐት ነግሮናል። የጋሽ ስብሐትን ነብስ ጥሩ ቦታ ያስቀምጥልን!

በአምስት አመት ያልቃል የተባለው አባይ ግድብ እዛው አይናችን እያየ ወደ ሰባት አመት አደገ። “እንዴ ገና ሰባት አመት ሙሉ ደሞዛችን ሊቆረጥ” ብሎ ማጉረምረም አይገባም መልሱ “ይቅርታ ሲያጣድፉን አንወድም ነው!”

ሶስት

የመዋጮው ነገር፤ “አባይን በራሳችን አቅም እንገድባለን!” ብለን ከህፃን እስከ አዋቂ ሁላችንም ፎክረናል። አንዳንዶቻችንም “ፎግረናል” በነገራችን ላይ በቴሌቪዥን እና በመስሪያ ቤታቸው ስብሰባዎች ላይ፤ “እኔ ለአባይ ዘራፍ እላለሁ!” ብለው ፊታቸውን አስመትተው በአለቆቻቸው ዘንድ ሞገስ ያገኙ በርካቶች እንደሆኑ ባለፉት ግዜያት አይተናል። እነዚህ ወዳጆቻችን በመስሪያ ቤታቸው ሰዎች ዘንድ “አስተኳሽ” የሚል የማዕረግ ስምም ተሰጥቷቸዋል።

እኔ የምለው ወዳጄ አንዳንዶች የሚሰጡትን አስተያየት ልብ ብላችሁልኛል? “አባይን በራሳችን አቅም ገድበን ከአምስት አመት በኋላ ድህነትን ማጥፋት እና ካደጉት ሀገሮች ተርታ መቀላቀል አለብን!” እያሉ ነው።

ቆይ ቆይ እዝች ጋ ትንሽ ፍሬን ያዝ እናድርግ...

አባይ በራሳችን አቅም በእኛው መዋጮ ለማለቅ ስንት አመት እንደሚፈጅበት እናስላ፤ ባለፈው አመት ሰባት ቢሊዮን ብር ተገኝቷል። በመነሻው ሞራል እንቀጥላለን፤ “ምናባቱ የመጣው ይምጣ!” ብንል እንኳ፤ ሰማኒያ ቢሊዮን ለማግኘት... (ሰማኒያን ለሰባት ማካፈል ነው።) አስራ አንድ አመት ይፈጃል።

ታድያ “በአምስት እና በስድስት አመት ያልቃል” የሚሉን ወዳጆቻችን የሚያውቁት ሌላ ምስጢር ካለ ቢነግሩን ጥሩ ነው። የሚሉ ወገኖች በርካታ ናቸው። የምር ግን መንግስታችን ራሱ በሰባት አመትም ይሁን በስድስት አመት የሚያልቀው በምን ስሌት እንደሆነ፤ ድህነትንስ ሙልጭ አድርጎ የሚያጠፋው በምን መልኩ እንደሆነ የማስረዳት ኃላፊነት ያለበት አይመስልዎትም...?

አንድ ወዳጃችን አባይን ገድበን ድህነትን እናጠፋለን ተብሎ ቡቴሌቪዥን ሲነገር ሰምቶ ምን አለ መሰልዎ “እነዚህ ሰዎች ድህነት በኤሌክትሪክ ተንጨርጭሮ የሚጠፋ መሰላቸው እንዴ...?” ብሎ ጠየቀን። በዙሪያው ያለን ሰዎችም “ፖለቲካ አናወራም” ብለን ዝም ብንለው፤ “የኔ ጌታ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ድህነት ፕላስቲክ ለበስ ነው። ኤሌክትሪክ አይዘውም!” አለና ክት ብሎ መሳቅ፤ ከዛም ስቅስቅ ብሎ ማልቀስ ጀመረ።

የሆነ ሆኖ እያለቀስንም ሆነ እየሳቅን እናዋጣለን። “አናዋጣም” ብለን ከሚመጣው ጣጣ አዋጥተን የሚመጣውን ችጋር መቻል ይሻለናል።

አረስቼው ዋናው ከዚህ ከመዋጮ ጋር ተይዞ ልነገግርዎ የፈለግሁት፤ ልብ ብለው እንደሆነ መዋጮው መጀመሪያ በስጦታ ተብሎ ነበር ከዛ ደግሞ ወደ ቦንድ ግዢ ተለውጦላችኋል አታስቡ መንግስት ሰርቶ ይከፍላችኋል ብሏል። በርግጥ ለርሱም እስካሁን ማረጋገጫ ያገኘ የለም። (ካለ እጁን ያውጣ!)

እንግዲህ አባይ ይገደባል በተባለ አመት ባልሞላ ግዜ ውስጥ በርካታ ነገሮችን አይቷል። ጠዋት የተነገረለት ከሰአት ከበርጫ ሰዓት መልስ ይቀየራል። እስከ አሁን እንኳ ሶስት ዋና ዋና ለውጦቹን አየን። በአዲስ መስመር አንድ እንጨምር፤

አራት

አባይ ግድብ ሊጀመር ጠዋት አካባቢ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ሜጋ ዋት ኃይል ያመነጫል ተብሎ ነበር። ትንሽ ረፈድ ሲል በቃሚዎች ቋንቋ፤ “ኢጃባና” ከተቃመ በኋላ አባይ ስድስት ሺህ ሜጋ ዋት አመነጫለሁ ብሏል ተባለ።

ይሄ ነገር የደህናውን ግዜ የጉሊት ገበያ ያስታውሰኛል። በተለይ ክረምት አካባቢ የስሙኒ ተብሎ የሚታሰረው ጎመን በደንብ ከተከራከሩ ሌላ እሱኑ የሚያክል ይመረቅ ነበር። (በጥጋቡ ግዜ ነው) ታድያ አሁንም አባይ ጥሩ የጉሊት ኒጋዴ ነው የመሰለኝ። አምስት ሺህ ነው የማመነጨው ብሎ ሲያበቃ “አረ ባክህ አዋጥተን እኮ ነው ገንዘብ እንኳ የለንም እባክህን መርቅልን!” ብለው አስተዛዝነው ነግረውት ነው መሰለኝ፤ መረቅረቅ አድርጎ ስድስት ሺህ ገብቶልናል።

እኔ የምለው ግን “የሚያመነጨው ሃይል ስለጨመረልን “ቲፕ” እናድርገው” ተብሎ መዋጮው ላይ እንዳይጨመርብን አይሰጉም?

እናልዎ ወዳጄ አባይ ግድብ ከተጀመረ አንድ አመት ሞልቶታል። በአንድ አመት ውስጥ እኛም እርሱም ብዙ ነገር አሳልፈናል። እርሱም ከላይ እስከ አራት የገለዕናቸውን ለውጦች እና ከስር እስከ አርባ አራት ያልገለዕናቸው ድንገተኛ ለውጦች ተከናውነውበታል። (እንደውም በቅንፍ፤ ለውጪ ሃይሎች እና የሀገሪቱን መልካም ለማይሹ ሰዎች አይናገሩ እንጂ... ስሙያው ቅርበት ያላቸው ወዳጆቻችን እንደሚሉት ከሆነ፤ “አባይ ከስያሜው ጀምሮ ይሄን ሁሉ ለውጥ ያስተናገደበት ምክንያት ያለ ዕቅድ መሰራቱ ነው።”) ከቅንፍ ውጪ እኛን በእቅድ ኑሩ እያለ የሚመክረን መንግስት ራሱ ያለ ዕቅድ የሚሰራው የሚከተለውን ጦስ አያውቅምን? ብዬ እጠይቃለሁ።

የሆነው ሆኖ አባይ አንድ አመት ሞልቶታል። ልጅ ቢሆን ኖሮ ይሄኔ ድክ ድክ የሚልበት ግዜው ነበር። እርሱም ድክድክ እያለ እንደሆነ በቴሌቪዥን አይተናል! እኛም ለአባይ እናዋጣለን ብለን “በሞራል” ከተንቀሳቀስን አመት ሞላን። እኛም በዝች አንድ አመት ውስጥ ብዙ አሳልፈናል። ድጋሚ ኑሮ ውድነቱ ከፍቶ የዋጋ ተመኑም ቀርቶ መኖር ይሉት ጣጣ ብርክርክ አድርጎናል። እንዲህም ሆኖ ለቀጣይ ስንት አመት ለአባይ እናዋጣ ይሆን...? እስቲ እንበርታ... ባንበረታስ...? ብንበረታም እንበርታ!

በመጨረሻም
አማን ያሰንብተን!

ፅንቁ የቤተሰብም መፅሔት
ነገ በገበያ ላይ ውሳለች
ቆይታ ከልዩ ጀግና ሜዳልያ ተሸላሚ ጄኔራል ተስፋዬ ጋር
“በቲያትርም በፊልምም ማሸነፍ ብዙ የማይገኝ ዕድል ነውና አስደስቶኛል”
አርቲስት ፈለቀ አበበ
የ2ኛው የኢትዮጵያ ቲያትር ፌስቲቫል አሸናፊዎች!
- ዝግጅቱ በየሁለት ዓመቱ ይካሄዳል
- የሽልማት ገንዘቡ ወደ 10 ሺህ ብር አድጓል
በኩላሊት ሕመም የተሰቃየው ጋዜጠኛ ታደሰ ሙሉነህ
- የሕክምና ወጪውን ሞሃ ሸፍኗል


‹‹እኔም ይመለከተኛል›› የችግኝ ዓውደ-ርዕይ በመስቀል አደባባይ ሊካሄድ ነው

የተፈጥሮ ሀብት መመናመንንና የአየር ንብረት መዛባት ችግሮችን መቆጣጠር ‹‹እኔም ይመለከተኛል›› በማለት ኢሚነንስ ሶሻል ኢንተርፕረነርስ በአለም አቀፍ ደረጃ ግንቦት 27 ቀን 2004 ዓ.ም. የሚከበረውን የአለም አካባቢ ጥበቃ ቀን ምክንያት በማድረግ ከግንቦት 28-ሰኔ 13/2004 ለ15 ቀናት የሚቆይ የችግኝ ዓውደ-ርዕይ በመስቀል አደባባይ ለማካሄድ ማቀዱን ትላንትና ድርጅቱ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ አስታውቋል።

“Eminence Environment Initiative”በሚል ስያሜ የዓውደ-ርዕዩን ስራ ሲጀምር በተፈጥሮ ሀብት ልማት ፣ጥበቃና አጠቃቀም በህብረተሰቡ ውስጥ የአመለካከት መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣትና ለማስጨበጥ የሚሉ አላማዎችን አንግቦ ሲሆን በዝግጅቱ ላይም 120 ተሳታፊዎች እና ከ10 ሺ በላይ ጎብኚዎች እንደሚገኙበት አዘጋጆቹ በመግለጫው ላይ ተናግረዋል።



ከታዴዎስ ታንቱ

እንዳትወልድ የለ ሴት እንዳታምጥ፤ እንደ ውሻ ንፍር የሚያንቀጠቅጥ

ከአዝማሪ ግጥም የተወሰደ

ድም! ይህ ድምፅ በቀጥታ ከፈንጣጣ ዋሻ ያስተጋባል! አንድ የኢትዮጵያ አርበኛ መትረየሱን ደግኖ ፋሽስቶችን ይለቅማል! ጀግንነቱ በሰው ተፈጥሮ ከሚጠበቀው በላይ አሻቅቧል! በአራቱም ማዕዘናት ተከብቧል! ፊቱን በመትረየሱ ስር ቀብሯል። ጎፈሬው ይታያል! ግምባሩ ተደብቋል! ድም! ትንታግ ይበትናል! እሳት ይተፋል! በግራ በኩል የቀቡትን በቦምብ ይበትናቸዋል። በቀኝ አቅጣጫ የተጠጉትን ደግሞ በሽጉጥ ይዋላቸዋል፡ ፡ ሬሣ ያመርታል! ሬሣ ይከምራል! ካንዲት ጎጥ ሥር ሆኖ ታአምር ይሠራል! ድም! ይተኩሳል! በመትረየሱ ያጭዳል! ድም! ገድሏል! ቡም! ቦምብ ወርውሯል! ድም! ቡም! ድም! ቡም!

ከሌሊቱ አሥራ አንድ ሰዓት ላይ ስምንት ሆነው ተነሥተዋል። አምሥቱ የፋሽስቶችን ወቅታዊ የኃይል አሰላለፍ ሰልለው በተኩስ ምልክት እንዲያሰሙ በቀዳሚ ግዳጅ ጅረቱን ተሻግረዋል፡ ፡ ግን አልቀናቸውም። በፋሽስቶች ተቆርጠው ከወገን ተለያይተዋል። ሁለቱ ደግሞ ከጥቂት ሰዓታት በፊት ተሰውተዋል። በጀግንነት ወድቀዋል፡ ፡ በደማቸው ታሪክ ፅፈዋል። የወር ተራቸውን ተወጥተዋል። ግዴታቸውን ፈፅመዋል። በእለቱ ይህ ሆኗል። ታሪክ እውነትን ለትውልድ ቀርጿል። ድም! እስካሁን የሰማችሁት የአርበኛው የመትረየስ የቦምብና የሽጉጥ ድምፅ ነው! ፋሽስቶች ግን ብዙ አርበኞች የመሸጉ መስሏቸዋል። ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ ልጅ ከጣት አንሥቶ ፋሽስቶችን ብቻውን ሲያጭድ አርፍዷል። እውነት ላይመስል ይችላል፡ ፡ ግን ከወርቅ የጠራ፤ ከዐሐይ የበራና ከጨረቃ የወዛ እውነት ነው! ወራሪዎችን በጥይት ይባርካል፡ ፡ በፍፁም በማይታመን ተአምራዊ ኃይል ጀብዱ ደርድሯል። የዘመናችን ሳምሶን ወይም ዳዊት ለመሆኑ መረጃ አልታጠቅንም። እኔሱ ግን ከመለኮት የተቀቡ መሆናቸው ተመዝግቧል። መናፍቃንን ለአቋማቸው ትተናቸዋል! ከኢአማንያንም ጋር ክርክር አንገጥምም። ቃሉን በቃሉ አምነን ተቀብለናል! የፈንጣጣ ወቃሻው አርበኛ ታዲያ ምድቡ ከየት ሊሆን ይችላል? በሳምሶናዊ ፀጋ ከአንድዬ ተልኮ ይሆን እንዴ? አልታወቀም!

አሁን ከቀኑ ሰባት ሰዓት ሆኗል። አርበኛው በተከታታይ ቆስሏል። የውጊያው መንፈሱ ግን አልበረደም። የአንጎላላው አንበሳ የፈንጣጣ ዋሻው ነብር ብቻውን ከሺህ ጋር ይዋጋል። ድም! ተኩሰ! ገደለ! ከፋሽስቶች በኩል እንዲሁ የጥይት ዶፍ ይወርዳል። አርበኛው ግን እስካሁን አልተሰዋም፡ ፡ ጥይቱ ሊያልቅ ተቃርቧል። ሆኖም ከመተኮስ አልታቀበም። ከእጁና ከእግሩ ደም ይንቆረቆራል። አካሉ ዝሏል። ወኔው በባሩድ ሽታ ግሏል። አሁን ከቀኑ ስምንት ሰዓት ሆኗል። ፋሽስቶች ኃይላቸውን ሁሉ ለፈንጣጣ ዋሻ ከበባ አውለዋል። አርበኛው ግን የመጣለት አልነበረም። ስምንት ሰዓት ተኩል ሆኗል፡ ፡ የጀግናው አርበኛ ጥይት ተሟጠጠ። የመትረየሱ ልሳን ተዘጋ። ሽጉጡም ባዶ ሆኗል። ቦምቦቹ ሁሉ ሥራ ላይ ውለዋል። በየቦታው የፋሽስቶች ሬሣ ይስተዋላል። ጀግናው አርበኛ አሁንም በትኩስ ወኔ ላይ ይገኛል። ፋሽስቶች ሊማርኩት ተቃርበዋል፡ ፡ አርበኛው ግን ለማምለጥ ያሰላስላል። ፋሽስቶች በህይወት ይዘው ሊጫወቱበት አሰፍስፈዋል። አርበኛው መሣሪያ ቀምቶ ሊፈጃቸው ቋምጧል። ትንሽ አሰብ አደረገ! ወደ ቀኝ ተመለከተ! ወደ ግራ አየ! ወዲያው በመጠጋት ላይ ከነበሩት ባንዳዎች የአንዱን ግምባር በድንጋይ ባረከው። ባንዳው ወደቀ! አርበኛው ወደ ፊት ራመድ ብሎ ጠብመንጃውን አነሣ። ምን ያደርጋል ታዲያ? ጥይት አልባ ሆነ! ወደ መሬት ጣለው። የከበባውን ስስ ብልት ልብ ብሏል። ለማምለጥ ከጅሏል! በኋላ እርምጃ ወደ ኋላ ያፈገፍጋል። በህይወት ሳለ ላይማረክ ቆርጧል፡ ፡ ፋሽስቶች ተናደዱ። አንድ ግልፍተኛ ባንዳ ቦምብ ነቅሎ ወረወረበት። ጀግናው አርበኛ ቀልቦ መልሶ ለቀቀባቸው። በእርግጠኝነት ቀልቦ ወረወረባቸው፡ ፡ ሬሣ በሬሣ ተነባበረ። አርበኛው ከበባውን በጠሰ! አመለጠ! አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ተጓዘ! ሆኖም አልቀናውም! ከፊት መሸገው ይጠባበቁ ከነበሩ ፋሽስቶች በግምባሩ ላይ ጥይት ተርከፋከፈ! ታአምር ሠሪው ወደ ታሪክ ወረደ! አለፈ! ለሀገሩና ለወገኑ ተሠዋ! ፊታውራሪ ወንድምነህ ገብረኪዳን ወደቀ። መጋቢት 8 ቀን 1932 ዓ.ም.

ጀግናው የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጅ ወንድምነህ ገብረኪዳን በፈንጣጣ ዋሻ አካባቢ በታላቅ ጀግንነት እንደወደቀ ፋሽስቶች ወዲያው ተሰበሰቡ። ብዙም ሳይቆይ የሬሣውን አንገት ቆረጡ። እንዲሁም ቀኝ እጁን ጎምደው በተቆረጠው ራስ ግምባር ላይ በምስማር ችንክረዋል። ለገናናው የኢጣሊያ ፋሽስት ሰላምታ የሰጠ አስመስለዋል። እንዴት ሊሆን ይችላል? ሬሣ አምራቹ ጀግናው ወንድምነህ ለፋሽስቶች አንዴም ሰላምታ ሰጥቶ አያውቅም፡ ፡ ከተሰዋ በኋላ በሬሣ ላይ መጫወት ደግሞ ጀግንነቱን አይቀንስበትም። ለፋሽስቶች ሰላምታ መስጠት የባንዳ ባህል ነው። ወንድምነህ ገብረኪዳን አይነካውም። ኢትዮጵያን ለማሰልጠን መምጣቱን የለፈፈው የፋሽስት ወራሪ ኃይል ድንቁርናው ያሻቀበ እንደነበር ራሱ በተግባር አረጋግጧል። በሬሣ ላይ ተጫውቶበታል! አረመኔው ፋሽስት!

የአርበኛው የወንድምነህ ገብረኪዳን ራስ ከቀኝ እጁ ጋር በምሥማር እንደተቸነከረ በደብረ ብርሃን ከተማ ለሦስት ቀንና ሌሊት ተሰቅሏል፡ ፡ የተቀረው አካሉ ግን በፈንጣጣ ዋሻ አቦ ቤተ ክርስቲያን በዕለቱ እንደ ተቀበረ ተመልክቷል። የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከተመሰሰ በኋላ ደግሞ በህይወት የነበሩ አርበኞች የጀግናውን የወንድምነህን አፅም በየቦታው ከወደቀበት በማሰባሰብ አዲስ አበባ አምጥተው ለአርበኞች በተሰይ በተዘጋጀላቸው ሥፍራ ለማኖር ሐሳብ አቀረቡ። ሐሳቡ በበላይ አካል ተቀባይነት አገኘ። የአፅም ፍለጋው ሳይውል ሳያድር ቀጠለ። የጀግናውን ከአንገት በታች አካል ማግኘት ተችሏል። በባንዳዎች ጥቆማ የተቀበረበት ቦታ ታውቋል። አንድ ሐሳብ ወረደ።

የጀግናው ወንድምነህ ከአንገት በላይ አካሉ ከሦስት ቀን የህዝብ ዕይታ በኋላ የት እንደተጣለ ግን በቀላሉ አልተገኘም። የግድ ለቀናት መፈለግ ነበረበት። ባንዳ የነበሩ ግለሰቦችን መጠየቅና ማጠያየቅ የግድ ሆነ። ባንዳዎቹ ደግሞ ለመናገር ደስተኛ አልነበሩም። እነሱን ማግባባት ራሱን የቻለ ሥራ ሆነ። በዚህ ሂደት በደብረ ብርሃን ከተማ ውስጥ የተቀበረ መሆኑ ተጠቆመ። ሆኖም ትክክለኛ ቦታውን ለማወቅ አልተቻለም። ፍለጋው አሁንም ቀጥሏል። ከቀናት በኋላ ትክክለኛው የጀግናው ራስ የተቀበረበት ታወቀ። በሐምሌ ወር 1941 ዓ.ም. ተገኘ። በደማቅ ሥነ ሥርዓት ለመቅበር ታቅዷል፡ ፡ የዝግጅት እንቅስቃሴ ተጠናክሯል። ሐምሌ 10 ቀን 1941 ዓ.ም. ከፈንጣጣ ዋሻና ከደብረ ብርሃን የጀግናው አፅም ተሰበሰበ። ሐምሌ 11 ቀን 1941 ዓ.ም. አፅሙ ከመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክብር ተቀምጧል። በኃጋታው ከጧቱ 3 ሰዓት አንስቶ አፅሙ ወደ ዘለዓለማዊ ማረፊያው እንዲወሰድ እንቅስቃሴ ተደረገ። በዚህም መሰረት በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማና በአበባ ባጌጠ መኪና በግራና በቀኝ ባማረ ሰልፍ ወደ ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ጉዞ ሆነ። የቆራጡ ጀግና የጀግንነት ገድል በራስ አበበ አረጋይ ተነበበ። ጀግናው አርበኛ ወንድምነህ ከዘለዓለም ቤቱ ገባ። ነሐሴ 29 ቀን 1941 ዓ.ም. የሞሶሎኒ ምሥጢር የተባላ መጽሐፍ እንዳደራጀው።

ገና ሲፈጠር ለኢትዮጵያ ክብርና ሞገስ ሆኖ የተቀረፀው አርበኛው ወንድምነህ በወራሪ፤ በጫጫና በአብቹ ውስጥ ከፋሽስት ወራሪ ኃይል ጋር ከፍተኛ ጦርነቶችን አካሂዷል። እንዲሁም በሰላሌና በሙገር ውስጥ በተካሄዱት ጦርነቶች ተከታታይ ድሎችን አስመዝግቧል። ጦርነት! ድል! ጦርነት! ድል! ጦርነት! ድል! ቀጠለ! የወንድምነህ ስም ገነነ! ፋሽስት ተንቀጠቀጠ! 1929 ዓ.ም.

ልበ ሙሉ አርበኛ ወንድምነህ ብቻውን በፋሽስቶች ተከብቦ በተደጋጋሚ እንዳመለጠ የአርበኝነት ታሪኩ ይናገራል። በዚህ ችሎታው በተአምራዊ ኃይል የሚንቀሳቀስ ልዩ ፍጡር ተደርጎ እስከ መታሰብ ደርሷል።

በቦምብና በጥይት ቆስሎ ያመለጠበት ወቅትም እንደ ነበር ታውቋል። የፈለገውን የፋሽስት መኮንን ነጥሎ የመምታት ልዩ ችሎታም ነበረው። በዚህም መሰረት ኮሎኔሉን ወይም ማጀሩን ነጥሎ አነጣጥሮ ከትቢያ ጋር ያዋህዳል። አሊያም ደግሞ ከፍተኛ መኮንኖችን ትቶ ካፒቴኑን ያጋድማል።

ስመ ገናናው አርበኛ ወንድምነህ በልዩ ልዩ አውራጃዎችና ወረዳዎች ተዘዋውሮ ከፋሽስት ጋር ሲዋጋ ከቆየ በኋላ ወደ ትውልድ መንደሩ ለመመለስ ወሰነ። ተከታይ ለመመልመል አስቧል፡ ፡ በውጊያ ወረዳ የተሰውትን የግድ በሰው ኃይል መተካት አስፈልጓል። የሱ ወደ ትውልድ መንደሩ የመግባት ወሬ ሲሰማ በአቅራቢያው በነበሩ ፋሽስቶች ሰፈር ሽብር ሆነ። ወዲያው ደግሞ ጦርነት ተከፈተ፡ ፡ አርበኛው ወንድምነህ የሰው ኃይል ለማደራጀት እንደ መጣ ፋሽስቶች አውቀዋል። ስለዚህ ሳይደርቅ በቅጠሉ ብለዋል። ግን አልሆነላቸውም። ወንድምነህ የሰው ኃይል በብዛት ሰብስቧል። በነዋሪዎች መካከል ብሔራዊ ስሜትን አጎልምሷል። ለፀረ-ፋሽስት ትግል አነሣሥቷል። 1930 ዓ.ም.

ጀግናው ወንድምነህ ለምልምል አርበኞች ከወታደራዊ ትምህርት በተጓዳኝ የአስተዳደር ሥራ ግንዛቤም ያስጨብጥ እንደነበር ታውቋል። አርበኞች አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ህዝቡን እንዳይበድሉ ትምህርት ሰጥቷል። በምንም ዓይነት ህብረተሰቡ በፈቃደኝነት ለአርበኞች ከሚያዋጣው ውጭ ንብረቱ እንዳይነካ አስጨንቅቋል። ይህ የአርበኝነት ዲስፕሊን ነው። እንደ ሕግ ሰርቷል። ወንድምነህ ራሱ ለመልካም ተግባር ዘውትር ምሳሌ ነበር። ለአስተዳደር ችግሮች መፍትሔ ይሰጣል። ዳኝነት ያያል። ሌሎችም አርበኞች በተዋረድ መልካም ስም ገብይተዋል።

አርበኛው ወንድምነህ ወራና አንጎላላ ኪዳነምህረት አጠገብ በእነወደባ ቀበሌ በ1895 ዓ.ም. ተወለደ። አንጎላላ በሰሜን ሸዋ ውስጥ የሚገኝ ወረዳ ነው። ጀግናው ወንድምነህ በሕፃንነቱ አዲስ አበባ መጥቶ በቅዱስ ጊዮርጊስ ትምህርት ቤት ሲማር አድጓል። የዲቁና ማዕረግ ተቀብሏል። ካደገ በኋላ ወደ ተወለደበት መንደር ተመልሶ በጥብቅና ሥራ ተሰማርቷል። ወንድምነህ በጥብቅና ሥራው ለህብረተሰቡ በሰጠው አገልግሎት በጣም ተወዳጅ ሆነ። በክርክር ጭብጥ አቀራረብ ችሎታው ተደነቀ፡ ፡ እውቀትና ድፍረት አጣምሮ የሰጠው ጀግናው ወንድምነህ ተጠየቅን መነሻ በማድረግ ለሕግ እንዲሁም ለእውነት ሽንጡን ገትሮ የሚሟገት ጠበቃ እንደነበር በአርበኝነት ታሪኩ መግቢያ ላይ ተመልክቷል።

ጀግናው ወንድምነህ ፋሽስቶች ሰሜን ሸዋ እንደ ገቡ በየቦታው ተከማችቶ የነበረው የመንግስት እህል በህዝቡ እንዲዘረፍ በማድረጉም በታሪክ አድናቆትን አትርፏል። ወዲያው ደግሞ ለአርበኝነት ዝግጅት ያደርግ ገባ። በዚህን ጊዜ ሹክ ባዮች እንቅስቃሴውን በማስመልከት ለፋሽስቶች ተናገሩ። ፋሽስቶች ደግሞ ወዲያው ይዘው አሠሩት፡ ፡ ብዙም ሳይቆይ በሞት እንዲቀጣ ወሰኑበት። ጀግናው ወንድምነህ ግን ከእሥር ቤት ለማምለጥ ጊዜ አልፈጀበትም። በቀጥታ ቆርጦ ወደ አርበኝነት ገባ። ጀግናው አርበኛ ወንድምነህ በ23 ታላላቅ ጦርነቶች ጀብዱ ፈፅሟል። በብዙ መለስተኛ ጦርነቶች በአመራርና በተዋጊነት እንደተሳተፈ ለማወቅ ተችሏል።

የቆራጡ አርበኛ የወንድምነህ አፅም በታላቅ ሥነ ሥርዓት ነሐሴ 29 ቀን 1941 ዓ.ም. በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ቅጥር ግቢ ውስጥ ባረፈበት ዕለት የሱ ልጆች መሆናቸው የተነገረላቸው ሁለት ሴት ሕፃናት በለቀስተኛው ህዝብ መካከል እንደ ታዩ ተመልክቷል። ህፃናቱ አደጉ ይሆን? የንጉሰ ነገስቱ መንግስት አስተምሮአቸው ይሆን? ወይስ አስታዋሽ አጥተው የትም ወድቀው ቀሩ? በሕይወት ካሉ ዛሬም በልዩ አክብሮት ሊታዩ ይገባል እንላለን! የጀግና ልጆች ናቸውና!!

ነገርን ነገር ያነሳዋል ይባላል። እውነት ነው! ነገር በነገር ይመዘዛል። ገዥዎቻችን ሰሞኑን በፊልም አስታክከው ስለጀግንነታቸው ብዙ አነብንበዋል። ሲያስፈራሩን ሰንብተዋል። አንድ የህወሓት ታጋይ ከሃያ አምስት የቀድሞ ጦር አባላት ጋር ይዋጋ እንደነበር ይነግሩናል። ድል ነሺነታቸውን ደጋግመው ያወጉናል። የሞኝ ለቅሶ መልሶ ማልቀስ ነውና! አንድ ታጋይ ከ25 የቀድሞ ጦር አባላት ጋር ቢዋጋ ምን ያስደንቃል? የውጊያ ወረዳ ኪስ ሜዳ አይደለም! እንደ ኪስ ሜዳ በሁለቱም በኩል በአቻ የሰው ኃይል ጦርነት አይካሄድም። አንድ ታጣቂ ከመቶ ጠላት ጋር ሲዋጋ ይችላል። ከሞተ ሞተ! እያለቀሱ ለሚስቁ ገዥዎቻችን ይሄ እንዴት ብርቅ ሊሆንባቸው ቻለ? በታሪካችን የተለመደ ነው! ሁኔታው ሲያስገድድ አንድ ከብዙዎች ጋር ይዋጋል! ጀግናው አርበኛ ወንድምነህ በአራቱም አቅጣጫ በፋሽስቶች ተከብቦ እስከ ህይወቱ ፍጻሜ እንደተዋጋ ተመልክተናል። እንደ እናንተ ከሱዳን፤ ከሊቢያና ከሌሎችም የዐረብ ሀገሮች የጦር መሳሪያ፤ መድኃኒት እንዲሁም ምግብ እየቀረበለት አልነበረም፡ ፡ በራሱ ገንዘብ የራሱን ትጥቅ አሰናድቶ ተዋግቶ ተሰውቷል። ጀግና ማለት ይሄ ነው!

እርግጥ ነው! ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል! ሆኖም ቅል ከድንጋይ በጥንካሬ ሊበልጥ አይችልም። ይሄ መታወቅ አለበት! ትናንትና ድል ማድረግ የሁል ጊዜ አሸናፊነትን አያውጅም፡ ፡ አሸናፊ ተሸናፊ ይሆናል! ኮሎኔል በድንጋይ ማራኪዎች መሆናችሁን ስትነግሩን ጄኔራል ባርጩሜ የምንነዳበት ቀን እንደማይመጣ ምን ያህል እርግጠኞች ናችሁ? እብሪት ውድቀትን ያስከትላል! አትርሱ!

ገዥዎቻችን ሁልጊዜም የበላይነት ይሰማቸዋል። አንዳንድ ጊዜ እንኳን ህዝብን አያዳምጡም። ትንሽ ትልቅ ቦታ ላይ ተቀምጧል፡ ፡ የኢትዮጵያ ህዝብ እንዳይናገር ተለጉሟል። ተሰብስቦ ስለችግሩ እንዳይወያይ እንኳን ተከልክሏል፡ ፡ በእያንዳንዱ ዜጋ ላይ ጆሮ ጠቢ ተመድቦበታል፡ ፡ በየጉራንጉሩ ሁሉ ሳይቀር ታጣቂ ይርመሰመሳል፡ ፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ህይወት ተመሰቃቅሏል። የግርድና ፍልሰት እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ደርሷል። ገዢዎችና ሎሌዎቻቸው ህይወትን ይቀጫሉ። ባንዳ ጋዜጠኞች ደግሞ መለከት ይነፋሉ! ገዥዎቻችን ህዝብን ለማዳመጥ ፈፅሞ አይፈቅዱም! ይልቁንም የግፍ ቀንበርን እያጠበቁ ሄደዋል! ገዢዎቻችን በተላላኪነት ችሎታቸው ብዙ ባዕዳንን በወዳጅነት ይዘዋል። ለዚህ ህዝብ ግን አጋር የለውም። አንድነቱን አጠናክሮ ካልተናበበ የተገዥነት ዘመኑ በጣም ይረዝማል። አንድ ሁን! አንድ እንሁን!

እንዳትወልድ የለ ሴት እንዳታምጥ፤
እንደ ውሻ ንፍር የሚያንቀጠቅጥ።

የአርሶ አደሮቹ መፈናቀል ቀጥሏል

‹‹የዜጎች የመኖር መብት ይከበር ህልውናቸውም ይጠበቅ›› ሰመጉ መኢአድ በጽ/ቤቱ ጊቢ ውስጥ 114 ተፈናቃዮችን አስጠልሏል

ደቡብ ክልል ቤንጅ ማጂ ዞን ቡራፋርዳ ወረዳ በተለያዩ ጊዚያት በተለይም ከሰሜኑ ኢትዮጲያ ክፍል በመሄድ ኑሯቸውን በግብርና ላይ የመሰረቱ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በክልሉ አስተዳደር ከክልሉ እንዲወጡ በመደረጋቸው በርካታ አርሶ አደሮች በአዲስ አበባ እና በሌሎች ከተሞች የምግብና የመጠለያ ችግር እየገጠማቸው መሆኑን ገለፀው።

ተፈናቃይ አርሶ አደሮች ‹‹ወደ ክልሉ በ1997 ዓ.ም የገቡ ሲሆን ነሐሴ 1998ዓ.ም ላይ መሬት ተሰጥቷቸው መሬቱን ሲያለሙ እንደነበረ፤ለአራት ዓመትና ከዛ በላይ ግብር ስንገብርበት የነበረውንና ያለማነውን መሬት የካቲት 18 እና 19 2004ዓ.ም.በተደረገ ስብሰባ መሬቱን እንድንለቅ ተነግሮናል ፤ በግድ የመልቀቂያ ቅፅ ላይ እንድንፈርም በሀይል ተደርገናል፤ ቅፁን ለመፈረም ፍቃደኛ ያልሆኑት ለሁለት ሳምንት ያህል በእርስ እንድንቆይ ተደርገናል››ሲሉ በተለይ ለፍትህ ተናግረዋል።

የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ/ሰመጉ/ ‹‹በአሁኑ ሰአት ከቤንጅ ማጂ ዞን የተባረሩ በርካታ ቤተሰቦች፣ሴቶች፣ህፃናት እና በእድሚያቸው የገፉ ሰዎች በአዲስ አበባና በሌሎች ቦታዎች መጠለያና በቂ ምግብ በማጣት እየተንገላቱ ይገኛሉ ። በመሆኑም በእነዚህ ሰዎች በተለይም ችግሩን ለመቋቋም በማይችሉ ህፃናትና ሴቶች ላይ እየደረሰ ያለው ሰብአዊ ቀውስ አፋጣኝ መፍትሄ እንዲሰጠው እና ወደ ቀድሞ መኖሪያቸው እንዲመለሱ እንዲደረግ ››ሲል የዜጎች የመኖር መብት ይከበር ህልውናቸውም ይጠበቅ በሚል አስቸኳይ ጥሪ ለሚመለከተው ሁሉ የመንግስት አካላት አቅርቧል፡ ፡

ሰመጉ ዜጎቹ ወደ ቦታቸው እስኪመለሱ ድረስ ‹‹እነዚህ ዜጎች ከአካባቢው እንዲነሱ የተደረገበት አግባብ ጉዳዩ የበርካታ ዜጎችን ህይወት የሚነካ በመሆኑ በአገር አቀፍ ደረጃ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እንደገና እንዲጠና፤ እንዲሁም ከቦታቸው የተነሱት ሰዎች አስቀድሞ በባልተዘጋጀ እቅድ እና እንሱንም ባላሳተፈ ሁኔታ ያለፈቃዳቸው የሚደረግ ወደ ሌላ ቦታ የማዘዋወር ሂደት እንዲቆም እና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ፣ ዘላቂ የሆነ፣ህልውናቸውን አደጋ ላይ በማይጥል እና ሰብዓዊ ክብራቸውን በጠበቀ መልኩ እንዲከናወን››ሲል ገለጿል።

በተጨማሪም የመላው ኢትዮጲያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ ደቡብ ክልል ቤንጅ ማጂ ዞን ቡራፋርዳ ወረዳ የተፈናቀሉትን 114 አርሶ አደሮች መጋቢት19 2004 ዓ.ም ተቀብሎ በጽ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ መጠለያ ሰጥቷቸዋል።

በፓርቲው ግቢ ከተጠለሉት ተፈናቃይ አርሶ አደሩ ውስጥ ያነጋገርናቸው የ33 ዓመቱ አርሶ አደር ‹‹የመልቀቂያው ቅፅ ላይ አልፈርምም በማለቱ ለአስራ አምስት ቀን ታሰሩት፤ባስቸኳይ እንድሰቅ በመገደዱ የትራንስፖርት ገንዘብ ስልነበረብኝ ስድስት ልጆቼን እና ነፍሰጡር ሚስቴን ትቼ መጣሁ››ሲል ለፍትህ ተናግረዋል።

አርሶ አደሩ ‹‹ህገ-ወጥ ናችሁ ተብለን መፈናቀላችን እና ወደ ክልላችሁ ሂዱ መባላችን ቅሬታ አሳድሮብናል። ያለማነው ልማት ሳይገመትና መሸጥ ሳንችል በድንገት መፈናቀላችን አግባብ አይደለም፤ህገ-ወጥናችሁ ከተባልን ደግሞ ከዓመታት በፊት መሬቱን ስናለማ ለምን ዝም ተባልን የሚል ጥያቄ በማንሳት››ቅሬታቸውን ለፍትህ ገልፀዋል።

የመኢአድ ህዝብ ግንኙነት ምክትል ኃላፊ አቶ ጌታቸው አበበ ‹‹ቀደም ሲል ከክልሉ ተፈናቅለው የመጡት አርሶ አደሮች ከመንግስት አካላት ጋር በተደረገ ንግግር ቦታችሁ ላይ ትመለሳላችሁ ወይም ተለዋጭ ቦታ ይሰጣችኋል ተብለው ወደ አራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 ተዘዋውረዋል፤ ነገር ግን የተፈናቃዮቹ ቁጥር በርካታ ነው ዛሬ /ዕሮብ/ ዕለት ሰባት ያህል መኪናዎች ተፈናቃዮቹን ጭነው መነሳታቸው ታውቋል›› ሲሉ ገልፀዋል።

በመኢአድ ጽ/ቤት ቅጥር ጊቢ የተጠለሉት ተፈናቃይ አርሶ አደሮች ትላንት መጋቢት 20 ቀን 2004 ዓ.ም ለጠቅላይ ሚንስትር መለስ ዜናዊ አቤት እንላለን በማለት ወደ ጠ/ሚ ጽ/ቤት ሄደው አለመመለሳቸውንና የአርሶ አደሮች ንብረትም በፓርቲው ጽ/ቤት እንደሚገኝ የመኢአድ ህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ወ/ሪት መሰበወርቅ ቅጣው በተለይ ለፍትህ ተናግረዋል ።

በእነ አንዷለም አራጌ የክስ መዝገብ የመከላከያ ምስክሮች ተደመጡ

በሽብርተኝነት ወንጀል ተጠርጥረው በማረሚያ ቤት ሆነው ጉዳያቸውን በፍርድ ቤት እየተከታተሉ ባሉት ተከሳሾች ላይ በያዝነው ሳምንት ከሰኞ-ዕረቡ ባሉት ሦስት ቀናት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት የመከላከያ ምስክሮች የተደመጡ ሲሆን የ5ኛ ተከሳሽ አቶ ክንፈ ሚካኤል አበበ መከላከያ ምስክሮች የፊታችን ሰኞ በችሎቱ ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን ይሰጣሉ፡፡

1ኛ ተከሳሽ የነበሩት አቶ አንዷለም አራጌ የተከሳሽነት ቃላቸውን በሰጡበት ወቅት ሰላማዊ ታጋይ እንጂ አሸባሪ አለመሆናቸውንና ከግንቦት 7 ጋርም ምንም አይነት ግንኙነት እንደሌላቸው ዘርዝረው አስረድተዋል፡፡

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ፣ ዶ/ር ሀይሉ አርአያ፣ አቶ ግርማ ሰይፉና ሌሎች ስድስት ሰዎች መከላከያ ምስክር ሆነው በመቅረብ አቶ አንዷለም ጠንካራና ፅኑ፣ ማርቲን ሉተር ኪንግን አርአያ ያደረጉ ሰላማዊ ታጋይና ሰላማዊ ትግልን እምነታቸው ያደረጉ የፖለቲካ አመራር መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ተከሳሹ እንደተባለው በሽብር ተግባር ተሳታፊ እንደማይሆኑ ጠንካራ እምነት እንዳላቸው ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡ በአንዳንድ አቃቤ ሕግ በመስቀለኛ ጥያቄው፣ አቶ አንዷለም ከስራ ጊዜያቸው ውጪ በግል ስለሚያደርጉት እንቅስቃሴ ያውቁ እንደሆነ ለምስክሮች ደጋግመው ጥያቄ አቅርበው ነበር፡ ፡ ምክስሮችም አቶ አንዷለም ብዙ ጊዜያቸውን ለፓርቲ ስራ እንደሚያውሉ በመጥቀስ፣ ባላቸው ጥቂት የማህበራዊ ህይወታቸው ሰላማዊነት እንደሚታይባቸው መስክረዋል፡፡

2ኛ ተከሳሽም አቶ ናትኤል መኮንንም እንደ አቶ አንዷለም ሁሉ ለረዥም ዓመት በሰላማዊ ትግል ውስጥ ማሳለፋቸውን ጠቅሰው፣ ሽብርተኝነት ከእምነታቸው ጋር አብሮ እንደማይሄድ ደጋግመው አስረድተዋል፡፡ የመከላከያ ምስክሮች ተከሳሹ ሰላማዊ መርህ ያለው፣ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚገልፅና የፓርቲያቸው የአንድነትን ፖሊሲና እቅድ ተከትለው የሚሰሩ መሆናቸውን ገልፀው ነበር፡፡

3ኛ ተከሳሽ አቶ ዮሐንስ ተረፈና 4ኛ ተከሳሽ ሻምበል ይሁን አለም የመከላከያ ምስክር ሳያቀርቡ የተከሳሽነት ቃላቸውን እንባ እየተናነቃቸውና ጠንከር ባለ ስሜት ለፍርድ ቤቱ ሰጥተዋል፡፡ ሁለቱም ከኤርትራ መንግስትም ሆነ ከግንቦት 7 ጋር ግንኙነት እንደሌላቸው ጠቅሰው ‹‹ከደሙ ንፁህ ነን›› ብለዋል፡፡

በ1997 ዓ.ም. ቅንጅትን ወክለው ፓርላማ ገብተው የነበሩት 3ኛ ተከሳሽ አቶ አንዷለም አያሌው፣ የፓርላማ ዘመናቸውን ካጠናቀቁ በኋላ የተለያዩ ስራዎችን ለመስራት ጥረት ቢያደርጉም በመንግስት ምክንያት ሊሳካላቸው ባለመቻላቸው ከባለቤታቸው ጋር ተማክረው ለስራ ፍለጋ፣ ብሎም ወደ ሌላ ውጪ ሀገር አልፈው ለመሄድ ሱዳን ተሰድደው እንደነበር በምስክርነት ቃላቸው ገልፀዋል፡ ፡ በጎ ፈቃድ ላይም መንገድ ስተው ኤርትራ ድንበር በመግባት ከተያዙ በኋላ በኤርትራ ቴሌቪዥን ቃለ ምልልስ ካላደረጉ እንደማይለቀቁ በተነገራቸው መሰረት የሚያምኑበትን ተናግረው መለቀቃቸውንና ሱዳን መግባታቸውን ዘርዝረዋል፡፡ ሱዳንም ሆነው ከግንቦት ሰባት አስተባባሪ ከሆነው ወንድማቸው ጋር ተነጋግረው ወደ ስዊድን ለመሄድ በገፃቸው ላይ እንዳሉ መያዛቸውን ተከሳሹ ቢጠቅሱም ወንድማቸው በኢንተርኔት የአባልነት ፎርም ቢልኩላቸውም ፎርሙን አለመሙላታቸውንና ከግንቦት 7ም ሆነ ከኤርትራ መንግስት ጋር ንክኪ እንደሌላቸው ለችሎቱ አስረድተዋል፡፡ ባለቤታቸውና የባለቤታቸው እህትም የሚያውቁትን መስክረዋል፡፡

ረቡዕ በዋለው ችሎትም 7ኛ ተከሳሽ ጋዜጠኛና የፖለቲካ ተናታኝ እስክንድር ነጋ የተከሳሽነት ቃሉን ዘርዝሮ ለፍርድ ቤት በማስረዳት ከግንቦት 7 ጋር ግንኙነት እንደሌለውና በሽብርተኝነት ሊከሰስ እንደማይገባው መረጃዎችን በመጥቀስ በጥብቅ አስረድቷል፡፡ የአቶ እስክንድር የመጀመሪያ ምስክር የነበሩት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ነሐሴ 29/2003 ዓ.ም. ጋዜጠኛ እስክንድር፣ ‹‹ትግሉ ከቃላት ወደ ሰላማዊ ተግባር ይሸጋገር›› በሚል ርዕስ ያቀረበው ፅሁፍ የአንድነት ፓርቲ አመራሮች አይተውና ፈቅደው ማስታወቂያ በፍኖተ ነፃነትና በፍትሕ ጋዜጣ አስነግረው መሆኑን አስረድተዋል - ተከሳሹ በኢትዮጵያ የሚደረግ ትግል ሰላማዊና ህጋዊ መሆን ብቻ እንደሚገባው ተናግሯል በማለት፡፡

‹ስለኢሳት ቴሌቪዥን ምን ያውቃሉ?› ተብለው ለተጠየቁትም ዶ/ር ነጋሶ፣ ‹‹ተቋሙ በሆላንድ፣ በለንደንና በዋሽንግተን ዲሲ በህጋዊነት የተመዘገበ፣ ከየትኛውም የፖለቲካ ድርጅት ነጻ መሆኑንም ከሃላፊዎቹና ከዶክመንቶች አጣርቻለሁ፡ ፡ ...ታዋቂ የአሜሪካ ፖለቲከኞችና ምሁራኖችም በጣቢያው ይቀርባሉ›› በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ተስፋሚካኤል ደበበም እስክንድር ባቀረበው ስብስባ ላይ ‹‹ለ2004 እንገናኝ፣ እንሞታለን ማለት ምን ማለት ነው?›› ተብለው ከጠበቃዎች ለተጠየቁት፣ ‹‹ጥሪው የፍቅር ነው፡፡እንሞታለን ማለት እንገላለን ማለት አይደለም፡፡ ሰላማዊ ትግል መሞት እንጂ መግደል አይደለም›› ሲሉ መስክረዋል፡፡

የመኢዴፓ አመራር የነበሩት አቶ ዘመኑ ሞላ መስክረም 21/2003 ዓ.ም. ጠርተውት በነበረው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ እስክንድርን ካለው እውቀትና የፖለቲካ ተንታኝነት አኳያ አማክረውት እንደነበረ ገልፀው፣ እስክንድር ‹‹አሁን ባለው ሁኔታ ሰልፍ አታካሂዱ፣ ፓርቲዎች ህብረት የላቸውም፡፡ በተለይ ውጭ ካሉ ሀይሎች ጋር አትገናኙ፡፡ ብርም አትቀበሉ፡፡ ለወረቀት ማባዣና ለብሮሸር የገንዘብ ችግር ካለ እራሳችሁ በራሳችሁ ተቸግራችሁ አሚሉ፡ ፡ እኔም ረዳችኋለሁ›› እንዳላቸው መስክረዋል፡፡

የአዲስ ታይምስ ዋና አዘጋጅ ዳዊት ታደሰና የፍትሕ አዘጋጅ ሙሉነህ አያሌው ለእስክንድር የመከላከያ ምስክር ሆነው ቀርበዋል፡ ፡ ሁለቱም እስክንድርን በሚፅፋቸው ፅሁፎች እንደሚያደንቁትና ለሙያቸው አርአያቸው እንደሆነ ጠቅሰው ‹‹የነፃ ኢትዮጵያውያን ትውልድ ኮሚቴ›› የሚል ከሁሉም ነገር ነፃ የሆነ ሲቪክ ማህበር በማቋቋም በተቃዋሚዎችና በመንግስት መካከል ውይይት እንዲኖር ለማቋቋም ሲንቀሳቀሱ እንደነበረ መስክረዋል፡፡

5ኛ ተከሳሽ አቶ ተስፋሚካኤል ደበበም የምስክርነት ቃላቸውን ለችሎቱ አስረድተዋል፡፡ ‹‹ክሴ ከህግ ውጪ ነው፡፡ ህገ-መንግስቱን አክብሬ በሰላማዊ ፓርቲ ውስጥ የምንቀሳቀስ ፖለቲከኛ ነኝ፡፡ መሪዎች ሕገ መንግስቱን ባለማክበራቸውና ሃሳብን በነፃነት ለመግለፅ በወጣው ህግ መሰረት ባደረኩት እንቅስቃሴ ነው የተያዝኩት፡፡ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግም መብቴ ነው፡፡ ክሴም ፖለቲካዊ ጉዳይ እንጂ እኔ ሽብርተኛ አይደለሁም›› ብለዋል፡፡

ከአርበኞች ግንባር ጋር በተገናኘ በሽብርተኝነት ወንጀል የተከሰሱ በእስራት ተቀጡ

‹‹ከአርበኞች ግንባር ጋር በተገኘ የሽብርና የአመፅ ቡድን በመፍጠር የሽብር ጥቃት ለማድረስ ተንቀሳቅሰዋል›› በሚል ክስ በቀረበባቸው ስድስት ተከሳሾች ላይ በትናንትናው ዕለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት የፍርድ ውሳኔ አስተላለፈ፡፡

የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባቸው ግለሰቦች ሲሳይ ብርሌ፣ ቢራራ አለሙ፣ ማንደፍሮ አካልነው፣ ዘመድየ አገዘ፣ መሰለ ድንቁ እና ቴዎድሮስ አያሌው ናቸው፡፡ ሁሉም ተከሳሾች በ1ኛ ክስ በ1996 ዓ.ም. የወጣውን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1 (ሀ) (ለ)፣ 38 (1) (2) እና 240 (1) (ሀ) ስር የተመለከተውን መተላለፋቸው ተገልጿል፡፡

የወንጀል ዝርዝሩ እንደሚያስረዳው ከሆነ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ካልተያዙት የውጭና የሀገር ውስጥ አባሪዎች ጋር ተካፋይ በመሆንና ራሱን አርበኞች ግንባር ብሎ ከሚጠራው አሸባሪ ቡድን አባል ጋር በተለያዩ ጊዜያት ወደ ኤርትራ በመሄድ የሽብርና የአመፅ ቡድን በህቡዕ አደራጅተዋል፡፡

እንዲሁም ከሻዕቢያ የሽብር አሰልጣኞች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የጋራ የወንጀል አድማ ስምምነት ላይ በመድረስ፣ ህቡዕ ጉባኤ በማካሄድ፣ የሽብር ስትራቴጂና ዕቅድ ላይ በመወያየት፣ በማስፀደቅ፣ የሽብር ጥቃት የሚሰነዘርባቸው የመንግስትና የልማት ተቋማት ዝርዝር ላይ በመስማማት የስራ ክፍፍል አድርገው የሽብር ማከናወኛ ቁሳቁስና ድጋፍ የሻዕቢያ መንግስት እንዲያደርግ አስበው ነበር፡፡

በተጨማሪም የአሁኖቹ ተጠርጣሪዎች የሽብርና አመፅ ተግባሩን አጠናክረው እንዲቀጥሉ በመስማማት በተጨማሪ የተለያዩ ወታደራዊና ለሽብር ተግባር የሚረዷቸው ስልጠናዎች በመውሰድ የስራ ክፍፍል አድርገዋል፡፡ በዚህም መሰረት የወንጀል ድርጊቱን አላማ ውጤትና ፍሬ ሙሉ በሙሉ በመቀበል በአመራር ሰጪነት፣ ፈፃሚነትና አስፈፃሚነት በመሳተፍ በአማራ ክልል እና ሌሎች ቦታዎች ህቡዕ የሽብር ቡድን በመፍጠርና የሽብር ጥቃት ለማድረስ በመንቀሳቀሳቸው መከሰሳቸውን ክሱ ያስረዳል፡፡

በ2ኛ ክስም ሁሉም ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በ1ኛ ክስ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ በዝርዝር የተጠቀሰውን የሽብርተኝነት ወንጀል ለመፈፀም እና ለማስፈፀም በህቡዕ ከኤርትራ መንግስትና ራሱን አርበኞች ግንባር ብሎ ከሚጠራው አሸባሪ ቡድን የተሰጣቸውን/የሚላክ ገንዘብ ህገ-ወጥ አወጣጡን ሰውረው መጠቀማቸውን፣ በስራ ላይ ማዋላቸውንና ማስተላለፋቸው ተጠቅሷል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ካደመጠና መረጃዎችን ከመረመረ በኋላ 1ኛ ተከሳሽን በሁሉቱም ክሶች በ13 ዓመት ፅኑ እስራትና በ2000 ብር እንዲቀጣ ሲያደርግ፣ ከ2ኛ-6ኛ ያሉትን ተከሳሾች በ10 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኖባቸዋል፡ ፡ በተጨማሪም ሁሉም ተከሳሾች ከእስር ሲፈቱ ከህዝባዊ መብቶቻቸው ለአምስት ዓመት እንዲታገዱ ትእዛዝ አስተላልፏል - ይግባኝ የማለት መብታቸው እንደተጠበቀ መሆኑን በመግለፅ፡፡

መድረክ የአዳራሽ ኪራይ ውል ስለፈረሰብን የነገውን ህዝባዊ ስብሰባ ለመሰረዝ መገደዱን ገለፀ

መድረክ በሙገር ሲሚንቶ ማህበራዊ ኢንተርፕራይዝ ፒ ኤል ሲ የሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አዳራሽን በህጋዊ ውል ተከራይቶ ነገ ከቀኑ 7 ሰዓት ጀምሮ በሀገሪቷ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ሊያደርግ የነበረው ህዝባዊ ስብሰባ በድንገት ‹‹አይቻልም›› በመባሉ ምክንያት ስብሰባውን ለመሰረዝ መገደዱን ለፍትሕ ገለፀ፡፡

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ የሆኑት ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ለፍትህ እንደተናገሩት፣ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መዘጋጃ ቤት በ19/07/04 አ.አ/ ከፅ/10/30-4/138 በሚል የደብዳቤ ቁጥር ተገቢውን ፎርማሊቲ በሚሟላት ስብሰባውን ለማድረግ ፍቃድ አግኝተው ነበር፡፡

ሆኖም ከኢንተርፕራይዙ ጋር በህጋዊ የውል ደረሰኝ ቁጥር 22988 መሰረት በሁለት ሺህ ብር ኪራይ አዳራሹን ቀድመው ተከራይተው ለአዲስ አበባና በዙሪያዋ ለሚገኙ ነዋሪዎች በስብሰባው ላይ እንዲታደሙ በማስታወቂያ ከገለፁ በኋላ ከትናንት በስትያ የኢንተርፕራይዙ የሰው ሀብት ልማት ስራ አመራር ኃላፊ የሆኑት አቶ ከተማ ደምሴ ‹‹ ስብሰባውን ማድረግ አይቻልም፣ ገንዘባችሁን ውሰዱ›› እንዳሏቸው ዶ/ር ኃይሉ ይገልፃሉ፡፡

ፓርቲውም አዳራሹ የተከለከለበትን ምክንያት ለማወቅ የበላይ ኃላፊዎችን ለማነጋገር ጥረት ቢያደርግም ‹‹ወደ ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ ለስብሰባ ሄደዋል›› በሚል ሊሳካላቸው አለመቻሉን ለፍትሕ አስረድተዋል፡፡

ህዝብ በማስታወቂያ ከተጠራ በኋላ በተፈጠረው ነገር ፓርቲያቸውም ሆኑ አሳቸው ማዘናቸውን የገለፁት ዶ/ር ኃይሉ፣ ‹‹ጉዳዩ አሳሳቢ ነገር ነው፡፡ ስርዓቱ ሃቀኛና እውነተኛ ፓርቲዎች በተዘዋዋሪ መንገድ ከህዝቡ ጋር እንዳይገናኙ እንቅፋት እያደረገ ነው›› በማለት መንግስትን ተጠያቂ አድርገዋል፡፡

‹‹ከዚህም ቀደም ተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጥሮብን በፓርላማ ለጠ/ሚ/ሩ ጥያቄ አቅርበን ነበር፡፡›› የሚሉት የአንድነት የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ፣ ገንዘብ ከሌለን በስተቀር አዳራሽ ለስብሰባ የሚከለከልበት ነገር አለመኖሩን አቶ መለስ ያኔ ቢናገሩም ዛሬም ድረስ ይሄ አለመስተካከሉን አዝነው ይናገራሉ፡፡ መድረክ በዛሬው እለት አዳራሹ ሊፈቀድ ይችላል የሚል ተስፋ ቢኖረውም እሁድ በሚያደርገው የብሔራዊ ም/ቤት ስብሰባ ላይ ጉዳዩን እንደሚያነሳው ለፍትሕ ጨምሮ ገልጿል፡፡

የአይካ አዲስ ፋብሪካ ሠራተኞች ጉዳት ደረሰባቸው

በኢትዮጵያ የጨርቃ ጨርቅ ምርቶችን በማምረት ወደተለያዩ የውጭ ሀገራት የሚልከው አይካ አዲስ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ዓለም ገና ቅርንጫፍ ሰራተኞች ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰባቸው ተጎጂዎቹ በተለይ ለፍትህ ገለፁ፡፡

በጨርቃ ጨርቅ አምራች ሰራተኞቹ ላይ የደረሰው ጉዳት ‹‹ዕሮብ መጋቢት 19/2004 ዓ.ም. ከቀኑ 10፡00 ሰዓት ገደማ የፋብሪካ የእሳት አደጋ መድረሱን የሚያመለክት አላርም (ድምፅ) በመጮኹ፣ ሰራተኞቹ የእሳት አደጋውን ለመሸሽ በሩጫ ከፋብሪካው ጊቢ ለመውጣት ሲሞክሩ ‹‹እርስ በርስ ተገፋፍተው በመውደቃቸው ሳቢያ ሲሆን የጉዳቱ መጠን ከፍተኛ እንዲሆን ያደረገው ሰራተኞቹ ከጊቢው እንዳይወጡ በጥበቃ ሰራተኞች በመከልከላቸው እና ከፖሊስ በተኮሰ አስለቃሽ ጭስ ነው›› ሲሉ ጉዳት የደረሰባቸው ሰራተኞች ለፍትህ ተናግረዋል፡፡

ጉዳት የደረሰባቸው ሰራተኞች ዞዲያክ ጣቢያዎች የህክምና እርዳታ እየተደረገላቸው መሆኑን ምንጮቻችን ጠቅሰው 29 ያህሉ ወደ አዲስ አበባ ተዘንአ አጠቃላይ ሆስፒታል በሪፈር ተልከው ህክምና እየተደረገላቸው መሆኑን ከሆስፒታሉ አስተዳደርና በአካል በመገኘት የፍትህ ዝግጅት ክፍል ማረጋገጥ ችሏል፡፡

ስለሁኔታው የገለፀሉን የእሉቱ ተረኛ ሐኪም ተጐጂዎቹ ለህክምና ሲመጡ የመዝለፍለፍ ሁኔታ ይታይባቸው እንደነበርና ኦክስጅን ተሰጥቷቸው ማገገም እንደቻሉ ገልፀው፣ የተወሰኑት ተጐጂዎች ህክምና ተደርጐላቸው የሄዱ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ተኝተው ህክምና እየተደረገላቸው እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

በሰራተኞቹ ላይ አደጋ ይድረስ እንጂ በጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካው ላይ ግን ምንም አይነት የእሳት አደጋ አለመድረሱን ሰራተኞቹ አያይዘው ገልፀዋል፡፡

ከውጪ ተገዝቶ ከገባው ስንዴ ለህብረተሰቡ ማዳረስ የተቻለው 20 በመቶ ነው ተባለ

መንግስት የተከሰተውን የዋጋ ንረት ለማረጋጋትና በአነስተኛ ገቢ የሚተዳደረውን የህብረተሰብ ክፍልን ለመጥቀም ከውጪ በድጎማ ተገዝቶ ከገባው የስንዴ ምርት በስርጭትና በቁጥጥር ክፍተት የተነሳ መከፋፈል የቻለው 20 በመቶ መሆኑን የንግድ ሚኒስትሩ አቶ ከበደ ጫኔ ማክሰኞ ዕለት ለፓርላማ ባቀረቡት የመስሪያ ቤቱ የ6 ወር ሪፖርት ላይ ገልፀዋል፡፡ ቀሪው 80% በመጋዘን እንደሚገኝም ተገልጿል፡፡

እርሳቸው እንዳሉት ምንም አይነት የአቅርቦት ችግር ሳይኖር በአፈፃፀም ጉድለት ስንዴን ከግብይት መስመር ለማስወጣት ደብቆ በመያዝ /በማከማቸት፣ ፋብሪካዎች ከእህል ንግድ ድርጅት ገዝተውና ፈጭተው እንዲያስረክቡዋቸው ለተመረጡ ዳቦ ቤቶች በመሸጥ ፋንታ በከፍተኛ ዋጋ ለሌሎች በመሸጥ እንዲሁም ከጥቂት የክልል መስተዳድሮች በስተቀር በክልሎች ያለው ቁጥጥር ደካማ በመሆኑ ነው ብለዋል፡፡

የሚኒስቴሩ መስሪያ ቤቱ የስድስት ወር ሪፖርት፣ ‹‹ወደ አለም ገበያ በቀረቡት ምርቶች የዋጋ ንረት የተነሳ የ6 ወራት እቅዱን ለማሳካት አልተቻለም፡፡ በስድስት ወሩ ከውጪ ገበያ ይገኛል ተብሎ ከተገመተው 980.6 ሚሊዮን ዶላር ውስጥ ማግኘት የተቻለው ገቢ 674.1 ሚሊዮን ሲሆን ማሳካት የተቻለው የእቅዱን 79 በመቶውን ነው›› ተብሏል፡፡ ቡናን ወደ ውጪ በመላክ 398.8 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 314.13 ሚሊዮን ማግኘት የተቻለው ሲሆን ይህም የእቅዱ 79% ነው፡፡ የቡና ምርቱን በእቅዱ ላለመሳካቱ ምክንያት ናቸው ተብለው በሪፖርቱ የቀረቡት በምርት መዘግየት ሳቢያ በወቅቱ ወደ ገበያ አለመቅረብ፤ የዓለም ቡና ገበያ መቀዛቀዝና ያልተረጋጋ መሆን፣ ላኪዎች እርስ በርስ በነበራቸው አላስፈላጊ ሽኩቻ በውድ ዋጋ መግዛትና ሲሸጡ ደግሞ በአለም ገበያ ዋጋው በመቀነሱ ምክንያት ከአለም ገበያ ጋር መወዳደር አለመቻል ናቸው፡፡

የስርጭት ችግሩ በምን እንደተከሰተ ከፓርላማ አባላት ተጠይቀው ማብራሪያ የሰጡት ሚኒስትር አቶ ከበደ ጫኔ፣ ‹‹ምንም አይነት የአቅርቦት ችግር የለም፡፡ አንዳንድ ነጋዴዎች ምርቶቹን በመደበቅ አላግባብ በህገወጥ መንገድ በኮንትሮባድ ምርቶቹን ወደ ውጪ እየላኩ እጥረት እየፈጠሩ ናቸው፡፡ በህገ-ወጥ ንግዱ ላይ የተሳተፉትም ተገቢውን ቅጣት እያገኙ አይደለም፡ ፡ ፍርድ ቤቶችም ህገ ወጦቹን በዋስ እየለቀቋቸው ነው፡፡ የስርጭት ስርዓቱን ለማሳካት የተዋቀረው መዋቅር ስራውን በሚገባ እየሰራ ባለመሆኑ የስርጭት ችግሩ ተከስቷል፡፡›› ብለዋል፡፡

መምህራን ሕጋዊ ትግላቸው ... ከገፅ 1 የዞረ

ዘርዝረው ጠቅሰዋል፡፡

በተያያዘም፣ የኮከበ ፅባህ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት መምህር የሆኑት አቶ ታሪኩ መኮንን፣ ከትናንት በስትያ ከስራ የመሰናበቻ ደብዳቤ ከየካ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊ ከሆኑት አቶ ጥሩዓለም አያሌው ደርሷቸዋል፡፡ የስንብት ደብዳቤው እንደሚገልፀው ከሆነ መምህሩ በመንግስትና በህዝብ የተሰጣቸውን ኃላፊነት ወደ ጐን በመተው ከ13/07/2004ዓ.ም. ጀምሮ በት/ቤቱ ያሉ መምህራኖችን በማስተባበር የስራ ማቆም እንዲመታና የመማር ማስተማሩ ስራ እንዲቆም እና ተማሪዎች እንዲበተኑ በማድረግ ተማሪዎችን ለከፋ ጉዳት በመዳረጋቸው ነው፡፡

በተጨማሪም መምህር ታሪኩ የት/ቤቱን ሀብት ያለአግባብ በማባከን፣ ሁለት ጊዜ በተፃፈላቸው ደብዳቤ ከአድማ ተግባር ተቆጥበው ወደ ስራ ገበታ ለመመለስ አለመፈለግና አድማው እንዲቀጥል በማስተባበር ተግባር እንደቀጠሉበት በደብዳቤው ላይ ተጠቅሷል፡፡ በመሆኑም ይህ ተግባር በህግ የሚያስጠይቅ በመሆኑ ከትናንት በስትያ ጀምሮ ከስራቸው እንደተሰናበቱ ለመምህሩ ተገልፆ በእጃቸው የሚገኝ የመንግስት ንብረት ለሚመለከተው ክፍል እንዲያስረክቡ በጥብቅ ተጠይቀዋል፡፡

“እናንተም ኢትዮጵያውያን በሰይፌ ትገደላላችሁ”

ሶፎ ፪÷፲፪

እምነቶች ግን ተማሪዎችን ማስጠለልና ከለላ መሆን ችለው ነበር። ያ ታሪክ ተደገመ። ቤተ ክርስቲያን አይናችሁን አልይ ብላ ስታስወጣቸው መኢአድ ተቀበላቸው። የእንግዳ ተቀባይነት ባህል እንዳለረፀች የሚታመንላት ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዘመን ልጆቿን ስታባርር የፖለቲካ ተቋሙ ተቀበላቸው፣ አበላቸው፣ አጠጣቸው፣ መጠለያም አዘጋጀላቸው፣ በቋሚነት ለማቋቋምም ግብረ ሰናዮችን እየተማፀነ ነው።

ኢሳያስ በትንቢቱ “ምሩኮ ቸኮለ፣ ብዝበዛም ፈጠነ” ይላል። ሰይፍም ከሰገባዋ ተመዘዘች። መከራና ግፍም ኢትዮጵያውያንን ይገድሉ ዘንድ በታሪክ ባልታየ ግዘፈት ገነነ፣ ዘገነነም። ከሶስት አመት በፊት በዲግሪ የተመረቁ ልጆች በየሰፈሩ ተቀምጠዋል። ከአመት፣ ከሁለት ዓመት በፊት የተመረቁትም እንዲሁ። ዘንድሮም ምርቃት አለ። ከርሞም። እንዲህም ሆነ ዲግሪ በመያዝና ባለመያዝ መካከል ልዩነት ጠፋ። ከአስር እስከ ሰላሳ አመታት ድረስ ከኖሩበት፣ ሐረግ ከተማዘዙበት፣ በዝምድና ከተሳሰሩበት፣ ከተላመዱበት አንድ የኢትዮጵያ ግዛት ብሔራችሁ ሌላ ነው ተብለው ኢትዮጵያውያን ተባረሩ። አብያተ ክርስቲያናት እና ገዳማት በየሰበቡ ይፈርሳሉ። ህዝብ በኑሮ ውድነት ሰይፍ ይመተራል። በፍትህ እጦት ሰይፍም ይገድላል። እንዳይናገር ይታፈናል፤ እንዳይፅፍም ይኮደኮዳል። እንዳይንቀሳቀስ ይቀየዳል። መምህርን ያክል ግዙፍ የሀገር መሰረት ላይ “ሃምሳ ብር ጨመርንልህ እልል በል” ብለው ይሳለቁበታል። ብዝበዛም ይፈጥናል ግፍም ይቸኩላል። ቸኩሎ ቸኩሎም ጽዋውን ይሞላል።

ሰላም፣ ፍቅርና አንድነት ለአንዲት ኢትዮጵያ!!!

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!

ኤናግ ግርማ ክንፈ

ሰይፍ የሚለው ቃል በቅዱሱ መጽሐፍ በተደጋጋሚ ተዕፏል። ሰይፍ ቁጣን ይወክላል። መዐትን ይወክላል። መከራን ያመሰጥራል። ይህ ያለንበት ዘመን ደግሞ ከመቸውም ጊዜ በላቀ ረዥም የመከራ ሰይፍ የተመዘዘችበት። መዐትም ከሰገባዋ የወጣችበት ዘግናኝ ዘመን ነው። በትንቢተ ሶፎንያስ ላይ የሰፈረው አስፈሪ የሚመስል ቃልም ይህን ያስረግጣል።

ሰይፍ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ሊመዘዝ ይችላል። ገዢዎች በህዝባቸው ላይ ሰይፍን ከሰገባው ይመዛሉ። ህዝብ በህዝብ ላይ ሊማዘዝ ይችላል። እግዚአብሔርም በፍጡሩ ላይ (በተለይ በብሉይ ኪዳን ለተግሳጽ) መዐትን ያወርድ ነበር።

ምንጩ ከየትም ይሁን ከየት እኛ ኢትዮጵያውያን በመከራ እየተገረፍን፣ በሰይፍ እየተገደልን ነው። በስቃይ እየተፈተንን ነው። ደኖቻችን በእሳት ይጋያሉ። ሰዎች ይታሰራሉ፣ ያለፍትህ የሚሞቱም አሉ። ጥንታዊ የትምህርት እና የታሪክ መዘክሮች ይቃጠላሉ። ሀገሪቱ ውስጥ የመከራ ጩኸቶች አሉ። ተመርቆ ሥራ መያዝ የለም ። አንድ ኢትዮጵያዊ የኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ መኖር አይችሉም። ሀገሪቱ ውስጥ የመከራ ጩኸቶች አሉ።

ሰይፍ ፩

በ፳፻ ዓ.ም ገዳማትን ማፅከል ባደረገ ሁኔታ ጥንታዊና ለመተካት የሚያዳግቱ ሀገር በቀል ዛፎች በቃጠሎ ወደሙ። በሺዎች በሚቆጠር ሄክታር ላይ ጥቅጥቅ ደኖች ነደዱ። ሰሞኑንም ከሶስትና አራት ዓመት በፊት እንደነበረው ደኖች ተቃጠሉ። ይህም ክፍል ሁለት መሆኑ ነው። የሚገርመው መገጣጠም ደግሞ ቃጠሎው የሚካሄደው ባለፈው ተቃጥለው ከነበሩ ተመሳሳይ ቦታዎች ላይ መሆኑ ነው። እናም በዚህ ሰሞን በአሰቦትና ዝቋላ ገዳማት ደኖች ላይ ከፍተኛ የሆነ ሰደድ እሳት ነበር። በተለይ የዝቋላው የሚከፋና ብዙ ድረገፆች አብዛኛው የዘገባዎቻቸው ጭብጥ አድርገውት የነበረ ጉዳይ ነው። እኔ እሳቱ ለምን ተነሳ እያልኩ አይደለም። ከእሳቱ መነሳት በኋላ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የሰጡት ምላሽ አንዳንድ ጥርጣሬዎች እንድናጭር ስለሚያደርጉን ነው። እኚህን አካላት ከእነ ጥርጣሬያችን በወፍ በረር አንይ

ቤተ ክህነት፦ በገዳማቱ ዙሪያ ለተነሱ ቃጠሎዎች ቤተ ክህነቱ የሰጠው ምላሽ ከዝምታ ብዙም ያልራቀ ነው። ከአራት ቀናት በላይ በዘለቀው እና ከፍተኛ አካባቢያዊ ውድመት ስላስከተለው የእሳት ሰደድ ቤተ ክህነቱ የሰማው ዘግይቶ ነበር። በእርግጥ ‘ዘግይቶ ሰማ’ ማለት ከሞኝነት ያስፈርጃል። ከደብረ ዘይት፣ ናዝሬት እና አዲስ አበባ እንዲሁም ሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች እሳቱን ለማጥፋት አያሌ ህዝብ ተምመጿል። ከአካባቢው መልክዐ ምድራዊ አቀማመጥ አኳያ በሰው ኃይል ለማጥፋት አዳጋች እንደሆነ የተረዱ የደብረዘይት ወጣቶች ወደ ጠቅላይ ቤተ ክህነት በመምጣት ቤተ ክህነቱ መንግስትን ሄሊኮፕተር /እሳት ለማጥፋት/ ይመድብ ዘንድ እንዲጠይቅ ተማፀኑ። ፓትርያርኩ ለአቡነ ሺኖዳ ቀብር (እግዚአብሔር ከቀደሙት ደጋግ አባቶች ወንድሞቻቸው ጋር በሰላም ያሳርፋቸውና) ግብፅ ሄደዋል በሚል ምክንያት ወጣቶቹ ተሸኙ። ፓትርያርኩ ሳይኖሩ እርሳቸውን ተክቶ በጊዜያዊነት ስራ የሚያስኬድ ተወካይ ይኖራል። በተወካይ አማካይነት፣ ወይ በጠቅላይ ቤተክህነት ሥራ አስኪያጅ፣ ወይ ቋሚ ሲኖዶሱ ወይ ሊቃነ ጳጳሳቱ በግላቸው በቀጥታ ለመንግስት ባይቻል እንኳ በሚዲያ /የግል ጋዜጦችና መጽሔቶች/ ወዘተ መንግስትን ስለ ጉዳዩ ማሳሰብ አይቻልም? ሌላ እኮ አይደለም በቃ ማሳሰብ፣ ማስገንዘብ። ግን ቤተ ክህነት ሆየ ፀጥ ። “ቁሱም ዝም መዕሐፉም ዝም”። ከሁሉም በላይ የሚያበሽቀው የምላሻቸው ዘየ የመንግስት ባለስልጣናት ግልባጭ መሆኑ ነው “እየታየ ነው” “ተነጋግረን የምንወስነው ይሆናል” “ከሚመለከተው አካል ጋር ለመነጋገር ጥረት እያረግን ነው” “ በሂደት ላይ ነው” እና ሌሎች አሰልቺ ሃረገ ንግግሮች። እና ከዚህ የተመዘዘ ሰይፍ ጀርባ የሆኑ አካላት እጃቸውን ከተው እያማሰሉ ይሆናል ብለን ብንጠረጥርስ። መናንያን የሚጠለሉበት አፀድ ሲቃጠል የአገሪቱን አየር ንብረት ሊያዛባ የሚችል ኢትዮጵያዊ ደን ወደ አመድነት ሲቀየር የአባ ጳውሎስ ቤተክርስቲያን ዝምታን መረጠች። እሳቱን ለማጥፋት ከተመመው ሰው ውስጥ እሰቱን ለማጥፋት እንገባለን አትገቡም ከፖሊስ ጋር ‘አለመስማማት’ ተፈጥሮ ነበር። በዚህ አለመግባባት ውስጥ በተለይ የተሳሳተ መረጃ ሲሰጥ የነበረን አንድ ጋዜጠኛ የተቃወሙ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሶስት ያክሉ በፖሊስ ጥይት ተመትተው ቆሰሉ። የአባ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንም ስለቆሰሉ ልጆቿ ዝምታን መረጠች።

ቤተ መንግስት፦ በእርግጥ የአቶ መለስን ወንበር የሚወዘውዝ፣ ለሥልጣናቸው ተግዳደሮች ወይም ስጋት ነው ተብሎ የሚጠረጠር እስካልሆነ ድረስ ለሀገራዊና ቤተ ክርስቲያናዊ ጉዳዮች ተገቢውን ትኩረት ወይም አፋጣኝ ምላሽ ባለመስጠት የኛ መንግስት የካበተ ልምድ አለው። ይህንንም ልምዱን ተጠቅሞ የዝቋላን እና አሰቦት ገዳማትን የደን ቃጠሎ በተመለከተ አድበስብሶ ማለፍን መረጠ።

በከሰል አክሳዮች፣ በዛፎች ፍትጊያ (friction)፣ ከጎሳ ታጣቃዎች በሚተኩሱ ጥይቶች እና መሰል ነገሮች እሳቱ እንደተቀሰቀሰ መላምት። ከዚያም ብዙዎችን ባሳዘነ ሁኔታ ይህ ነው የሚባል ተሳትፎ ባልነበራቸው አካላት እሳቱ በቁጥጥር ስር እንደዋለ እሱ በቁጥጥር ስር ባዋላቸው ሚዲያዎች ከመግለፅ ባሻገር እዚህ ግባ የሚባል ነገር ሲፈይድ አላየንም። በስፍራው /ዝቋላ/ እሳት ለማጥፋት የነበሩ ሰዎች እንደሚሉት የማጥፋት ዘመቻው በሄሊኮፕተር የታገዘ ቢሆን ኖሮ በሰላሳ ደቂቃዎች ይጠናቀቅ ነበር። እና ይህች አገር እሳት ለማጥፋት የሚሆን አንድ ሄሊኮፕተር የላትም? ነው ወይስ አገልግሎታቸው ጦርነት ሲቀሰቀስ ብቻ ነው?። የሚቃጠለው ደን የሀገሪቱ አይደለም? በጉዳቱስ የሚጎዳው ያው ኢትዮጵያዊው አይደለም?። በመጨረሻም ከላይ ለመጠቆም እንደሞከርኩት እሳቱ ሳይጠፋ እንደጠፋ በማስመሰል መረጃ ሲሰጥ ከነበረ ጋዜጠኛ ጋር ከተጋጨ ተማሪዎች ሶስቱ በፖሊስ ጥይት ተመቱ። ይህ ሁሉ ሲደረግ መንግስት በሀገሪቱ አለ። የገዳማቱ ባለቤት ቤተ ክህነትም ከነ ሙሉ ባለስልጣናቷ በሀገሪቱ ህልው ናት። እናም ልቡናየ እንዲህ አለኝ “አንተ ሆይ ትጠረጥር ዘንድ የተገባህ ነህና ጠርጥር” እኔም ፈራ ተባ እያልኩ ጠረጠርኩ። ወዲያውም የጨኸት ድምፅ በረከተ። ሰይፍም በኢትዮጵያውያን ላይ ተመዘዘ!

ሰይፍ ፪

ስለ አሰቦት ደን ቃጠሎ እንደመንስኤ ከተቀመጡት ትንበያዎች ባለፈ ጥርጣሬ እንዳለው ቤተ ክህነቱ የዘገየ ቢሆንም መግለጫ ሰጠ (ይበል የሚያሰኝ ነው)። ግን ተዕዕኖ ከመፍጠር አንፃር ከዝምታ ብዙም የራቀ አይደለም። አቡነ ሺኖዳ በአንድ አማኝ ላይ ተዕዕኖ (ግፍ) ከደረሰ መንበራቸውን ለቀው ገዳም እስከመግባት ከመንግስት ጋር ይተናነቁ ነበር። እስከ መጋዘም (ግዞት) የደረሱበት ጊዜ ነበር። ያውም ከግብፅ ህዝብ አስር በመቶ ብቻ ክርስቲያች በሚኖሩበት ሁኔታ። የእኛዎቹ እንዲህ እንደሚደረግ እንኳ የሚያውቁ አይመስለኝም። ግን እኛ አገር ቤተ ክህነት አለች፤ በውስጧም አለቆች አሏት። መንግስትም አለ። ሰይፍ ከሰገባው ወጣ፤ መከራና መዐትም በዚያ ተደገኑ።

ባሳለፍነው ወር ጎንደር ከተማ። አንድ ብቸኛ የመፅሐፈ መነኮሳት ማስመስከርያን ጨምሮ ሁለት ጥንታውያን የአብነት ትምህርት ቤቶች በእሳት ተቃጠሉ። በዋልድባ ገዳም ዙሪያ እየደረሰ ስላለው ነገር ቤተ ክህነቱ “ገዳሙ ከስጋቶች ነፃ” ስለመሆኑ መንግስት ማረጋገጫ ሰጠኝ ብሎ መግለጫ ሰጠ። ያም ሆኖ በአስራ አንድ ቀበሌ ገበሬ ማኅበራት ውስጥ ያሉ አስራ አንድ የሚሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ይፈርሳሉ። ይህን በተመለከተ ቤተ ክህነቱ መረጃው አለው። ረዣዥም የስኳር ሰልፎችን ለማስወገድ እየተወሰደ ያለው ርምጃ ይበል የሚያሰኝ ነው። ግን ለስኳር የሚሆን ቦታ ከዚያ አካባቢ ውጭ በሌላ ክፍላተ ሀገር ጠፋ? ልቡናየም አለኝ፦ “ጠርጥር በገንፎ ውስጥ ይገኛል ስንጥር”።

ሰይፍ ፫

ኢትዮጵያውያን ነበሩ። ኢትዮጵያ ውስጥ ሄደው ኖሩ። ወለዱ ከበዱ። ከዚያም ከኢትዮጵያ ውጡ ተብለው ወደ ኢትዮጵያ ተባረሩ። ተረት አይደለም። የቅርብ ጊዜ እውነት እንጂ። ትርጉም፦ በቤንቺ ማጂ የሚኖሩ የአማራ ተወላጅ (ኢትዮጵያውያን) ከኖሩበት፣ ሀብት ካፈሩበት፣ ከወለዱበት፣ ከከበዱበት ቀየ ማቄን ጨርቄን ሳይሉ እንዲወጡ (ከኢትዮጵያ) ተደረጉ።

ቤተክህነት፦ ሀንዳውያን፣ ቻይናውያን፣ ቱርካውያን በኢንቨስትመንት ስም እልፍ ጋሻ መሬት ይዘው በሰፈሩባት ሀገር ኢትዮጵያውያን መፃተኛ ሆኑ፤ በአባቶቻቸው አገርም መኖር እንዳይችሉ ሆኑ። ወደ ቀደመ ታሪካችን እንመለስ። እነኚህ ‘የአማራ’ ተወላጅ (እንዲህ አይነት ስሞችን ስጠራም ይሁን ስዕፍ ምኞት አይሰማኝም) ኢትዮጵያውያን (ይህን ስም ደግሞ ስጠራውም ይሁን ስዕፈው ብውል አይሰለቸኝም) በፌስታል ልብሶቻቸውን ብቻ አንጠልጥለው ሲወጡ የመጡት ወደ አዲስ አበባ ነበር። እንደደረሱም ቤተክርስቲያንን በድሮው ትርጓሜዋ አይተው መውደቂያ ሲያጡ ሊጠለሉባት ሄዱ። ወደ ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል። ጠባቂዎችም እንዲወጡ አስገደዷቸው በመኢአድ ጽ/ቤትም ድንኳን ተሰርቶላቸው ለጊዜው ተጠለሉ። ቤተክርስቲያን ስሟ እንደሚያመለክተው የክርስቲያን ቤት ማለት ናት። አምባ፣ መጠለያ፣ መጠጊያ ብለውም አባቶች ይጨምሩላታል። እውነታው ግን ተገልብጧል። ቤተክርስቲያን የክርስቲያኖች ቤት አልሆነችም፣ አምባም፣ መጠጊያም፣ መጠለያም እንዲሁ። በአርግጥ የአባ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ልጆቿን አላስጠልል በማለት የካበተ ልምድ አላት። በ፲፱፻፹፰ የአ/አ/ዮ ተማሪዎች አመፅ ጊዜም በመ/ፓ/ቅ/ቅ/ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተጠለሉ ተማሪዎች በፌደራል ፖሊስ ርምጃ ሲወሰድባቸውና በግፍ ከቤታቸው (መጠለያችን ካሏት ቤተ ክርስቲያን) እንዲወጡ ሲደረግ የአባ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ከሙሉ ፈቃደኝነቷ ጋር መልካም ይሁንታዋን አሳይታ ነበር። ምስጋና ይግባቸውና ሌሎች ቤተ

